# የደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር የ2018 በጀት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ለማት ዕቅድ




# (የትውልድ ቁጭትን ለትውልድ ልዕልና የማነጽ ትልም)

መስከረም/2018

ደሴ

# Contents


መግቢያ ..... 1

ክፍል አንድ፡- የእቅዱ መነሻ ..... 3

1.1. የዞናዊ አቅሞች እንደመነሻ ..... 3

1.1.1. አምራች ሰብዓዊ ሀብት ..... 3

1.1.2. በግብርና የመልማት አቅም ..... 4

1.1.3. የእንስሳት ሀብት እንደ መልማት አቅም ..... 6

1.1.4. የአየር ንብረት ..... 7

1.1.5. የማዕድን ሀብት ..... 8

1.1.6. የቱሪዝም ሃብት ..... 9

1.1.7. የዉሃ ሃብት ..... 10

1.2. የክልሉ ጥቅል ኢኮኖሚ አፈጻጸም እንደመነሻ ..... 11

1.3. ዞናዊ የዘርፎች ልማት አፈጻጸም እንደመነሻ ..... 17

1.3.1. አምራች ኢንደስትሪ ..... 17

1.3.2. ዘመናዊ ግብርና ..... 20

1.3.3. እንስሳትና አሳ ሀብት ልማት ..... 22

1.3.4. ህብረት ስራ ማህበራት ..... 23

1.3.5. ማዕድን ሀብት ..... 25

1.3.6. ትምህርት ..... 25

1.3.7. ጤና ..... 28

1.3.8. ቱሪዝም ..... 30

1.3.9. ንግድና ገበያ ልማት ..... 31

1.3.10. ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ..... 32

1.4. ማህበራዊ ፍትህ አፈጻጸም ..... 34

1.5. የገጠርና የከተማ ልማት አፈጻጸም ..... 37

1.5.1. ገጠር ልማት ..... 37

1.5.2. ከተማ ልማት ........ 38

1.6. የአካባቢ ጥበቃ ልማት አፈጻጸም ........ 40

1.7. የልማት አቅሞች አፈጻጸም ........ 42

1.7.1. የሰው ኃይል ልማት ........ 42

1.7.2. ቴክኖሎጅ ........ 44

1.7.3. መሰረተ ልማት ........ 44

1.7.4. የመንግስት ፋይናንስ ........ 49

1.8. የስርአታትና ልማት አፈጻጸም ........ 50

1.8.1. የዳኝነትና ፍትህ ዘርፍ ........ 50

1.8.2. የባህልና እሴት ልማት ........ 56

1.8.3. የመንግስት ተቋማትና የአመራር ሚና ........ 56

1.9. የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ተግባራት አፈጻጸም ........ 57

1.10. የመልካም አስተዳደር ስራዎች አፈጻጸም ........ 58

1.11. ክትትልና ግምገማ ስርአት አፈጻጸም ........ 59

ክፍል ሁለት፡- የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ ........ 61

2.1. ርዕይ እና ተልዕኮ ........ 61

ርዕይ ........ 61

ተልዕኮ ........ 61

2.2. የዕቅዱ መነሻዎች፣ ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች፣ የትኩረት መስኮች እና የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 61

2.2.1. የዕቅዱ መነሻዎች ........ 61

2.2.2. ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች ........ 62

2.2.3. የትኩረት መስኮች ........ 63

2.2.4. የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 64

2.3. የዕቅደ ዓላማ እና ዋና ዋና ግቦች ........ 64

2.3.1. የዕቅደ ዓላማ ........ 64

2.3.2. የዕቅደ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 64

2.3.3. ዋና ዋና ግቦች ........ 65

2.4. ጥቅል ኢኮኖሚ ........ 65

2.4.1. የስራ ዕድል ማስፋት ........ 65

2.4.2. የዋጋ ግሽበትን መቀነስ ........ 66

2.5. የዘርፎች ልማት ........ 66

2.5.1. አምራች ኢንዱስትሪ ........ 66

2.5.2. ዘመናዊ ግብርና ........ 73

የማስፈጸሚያ ስልቶች ........ 87

2.5.3. የማዕድን ሀብት ........ 87

2.5.4. ትምህርት ........ 92

2.5.5. ጤና ........ 102

2.5.6. ቱሪዝም ........ 112

2.5.7. ንግድና ገበያ ልማት ........ 115

2.5.8. ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ........ 122

2.5.9. ኮንስትራክሽን ........ 127

2.6. ማሕበራዊ ፍትህ ........ 132

2.7. የከተማና ገጠር ልማት ........ 136

2.7.1. የከተማ ልማት ........ 136

**2.7.2. የገጠር ልማት** ........ 143

2.8. የአካባቢ ጥበቃ ልማት ........ 147

ክፍል ሶስት የልማት አቅሞች ........ 153

3.1. ተፈጥሮ ሀብት (መሬት) ........ 153

3.2. የሰዉ ኃይል ልማት ........ 157

3.3. ቴክኖሎጅ ........ 162

3.4. መሰረተ ልማት ........ 162

ክፍል አራት፡- ስርዓታትና ልማት ........ 178

4.1. የዳኝነትና የፍትህ ዘርፍ ........ 178

4.2. የባህል እና እሴት ልማት ........ 187

4.3. የመንግስት ተቋማትና የአመራር ሚና ........ 192
ክፍል አምስት፡- የልማት ፋይናንስ ........ 195
5.1 መዋዕለ ንዋይ ........ 195
5.2. የመንግስት ፋይናንስ ........ 197
ክፍል ስድስት፡- የማስፈጸሚያ ስልት ........ 207
6.1. የቀጠና ልማት ........ 207
6.2. ልዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ........ 207
6.3. የተቋማት አደረጃጀትና ሚና ........ 209
6.4. ክትትልና ግምገማ ........ 211
**6.4.1. የመረጃ ስርዓት** ........ 211
**6.4.2. ክትትልና ድጋፍ** ........ 212

## መግቢያ

ደቡብ ወሎ ዞን በክልሉ ከሚገኙ ዞኖች በህዝብ ብዛቱም ሆነ በቆዳ ስፋቱ ከፍተኛው ሲሆን በተለያዩ የመሬት አቀማመጥ፣ በበለጸገ ባህሉ እና በግብርና አቅሙ ይታወቃል። ከደጋማ አካባቢዎች ከቀዝቃዛ ለም አፈር ጋር እስከ ቆላማው ሜዳማ አካባቢዎች ድረስ የአየር ንብረት ያለበት ዞን ነው። ይህ የከፍታ እና የአየር ንብረት ልዩነት የተለያዩ የግብርና እና የእንስሳት እርባታ ስራዎችን ሞቺ ያደርገዋል። ይህም ለአካባቢው ኢኮኖሚ እድገት የተሻለ አቅም የሚሆን እድል ያለበት ዞን ያደርገዋል። እንደ ደሴ እና ኮምቦልቻ ያሉ ዋና ዋና ከተሞች ለዞኑ የንግድ እና የአስተዳደር ማዕከል ሆነው ያገለግላሉ። በዞኑ ወርቅ፣ ኦፓል እና ሌሎች የኢንዱስትሪ ማዕድናትን ጨምሮ የማዕድን ሃብቶቹ ለኢኮኖሚ እድገት እድሎች ናቸው። ይሁን እንጅ እነዚህ አቅሞች ቢኖሩትም የአየር ንብረት መለዋወጥ፣ ተደጋጋሚ ድርቅ እና የመሠረተ ልማት ክፍተቶች ተግዳሮቶቹ በመሆናቸው በግብርና፣ በኑሮ እና በአጠቃላይ ልማት ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ። በአጠቃላይ ደቡብ ወሎ ዞን ለግብርና ልማት፣ ለእንስሳት እርባታ እና ለማዕድን ልማት ትልቅ እድሎች ያሉበት እንድሁም የተፈጥሮ ብዝሃነት እና የባህል ባለፀጋ ዞን በመሆኑ ሁለንተናዊ ልማት ለማረጋገጥ መልካም እድል ያለበት ዞን ያደርገዋል።

ይህን እንደ መነሻ በመውሰድ እንደ ዞንም ሆነ እንደ ክልል ሰላምን ማስፈን፣ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትንና ልማትን ማረጋገጥ እንዱሁም ድህነትን መቀነስ ቀዲሚ አጀንዲዎች በመሆናቸው ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። በዚህም አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል። እነዚህ እየተመዘገቡ ያሉ ሁለንተናዊ የልማት ውጤቶች በመንግስትና በህዝብ የተቀናጀ ጥረት በመሆኑ ይህንን ጥረት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በየበጀት ዓመቱ ያሉ መልካም ውጤቶችን ይበልጥ ለማስፋፋትና መሰረት ለማስያዝ እንድሁም እጥረቶችን በመቅረፍና ወደ ታለመለት ግብ በመድረስ የተያዘውን የእድገትና የብልጽግና ጉዞ ለማረጋገጥ ሰፋፊ ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። በመሆኑም በ2018 በጀት ዓመትም እስካሁን ሲደረጉ የነበሩ ጥረቶችን በማጠናከር የተጀመረውን የእድገትና የብልጽግና ጉዞ ማስቀጠል በየደረጃው ከሚገኝ የሚመለከተው አካል ሁሉ የሚጠበቅ ይሆናል።

በዞኑ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዕድገትን የሚፈታተኑ አዝማሚያዎችን ለማስወገድ በማስፈጸም አቅም፣ በድሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ እንዱሁም የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ ላይ መላ የዞኑን ህዝብ በማሳተፍ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ተገቢ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪም የዞኑን ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብት በስፋት በማንቀሳቀስ ህዝባችንን ከድህነት ለማውጣት እንዲቻል ከዚህ በፊት ይታይ የነበሩትን አደናቃፊ አመለካከቶችና ጎታች አስተሳሰቦች በማስወገድ አበረታች ጥረቶችን አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ ይሆናል። በአሁኑ ወቅት ካሉ አበይት ችግሮች መካከል ስራ አጥነት፣ የዋጋ ንረት፣ ዝቀተኛ ምርታማነት እና ቅልጥፍና አሳሳቢ ችግሮች ሲሆኑ በተለይም በዋጋ ንረት ምክንያት

የግንባታ ወጪ በመጨመሩ በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል በተከሰተው በሰላም እጦት ምክንያት በገቢ አሰባሰብ ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የፈጠረ በመሆኑ ለልማት የሚውለውን የፋይናንስ አቅም በሚፈለገዉ ልክ እንዲያድግ አድርጓል፡፡ ስለሆነም የዋጋ ንረትን በመቀነስና ሠላምን በማረጋገጥ ረገድ የተጠናከረ ስራና የጋራ ርብርብ ይጠይቃል፡፡

ይህ ዓመታዊ ዕቅድ የዞናችን ችግሮች ፈርጀ-ብዘ እንደመሆናቸው መጠን ዕቅዱ የማሕበራዊ እና ኢኮኖሚ ልማት፣ የሰላም እና ፍትህ፣ የእሴቶች፣ ባህል እና ወጎች፣ እንዲሁም የተቋማት አቅም ግንባታ እንዲያካትት መደረጉ እንዲሁም እንደት እንደሚፈጸም የሚያመላክቱ የአቅም ፍላጎቶች እና የማስፈጸሚያ ስልት ያመላክታል፡፡ ዕቅዱ በዋናነት በውጤታማነት ተፈጻሚ እንዲሆን ሁሉም በየደረጃው የሚገኝ የፖለቲካና የሲቪል ሰርቪስ አመራር አካላት፣ ሰራተኞች፣ ህብረተሰቡና ሌሎች አጋር አካላት ጋር የጋራ ተደርጎ የሚገባ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ይህ ዓመታዊ የልማት ዕቅድ በውስጡ የዞኑን አቅም፣ የ2017 ዓም አፈጻጸም፣ የዞኑን ርዕይ ተልዕኮ እና እሴቶች፣ የትኩረት መስኮች፣ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ዓላማዎች ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት፣ የዘርፎችን ዕቅድ፣ የማስፈጸሚያ ስልቶች፣ መልካም አጋጣሚዎች ስጋቶችና የስጋት መከላከያ ስልቶች እንድሁም የክትትልና ድጋፍ ስርዓት እንዲያካትት ተደርጎ ጠቅለል ባለ መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ፡- የእቅዱ መነሻ

## 1.1. የዞናዊ አቅሞች እንደመነሻ

ለአንድ አካባቢ ልማት የተፈጥሮ ሃብት በስፋትም ሆነ በጥራት መኖር ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ ዞናችንን ወስደን ስንመለከት ደግሞ ከሞላ ጎደል ሁሉም አይነት መሠረታዊ የተፈጥሮ ሀብት አቅሞች ያሉት ዞን ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በብልጽግና ዘርፈ ብዙ የኢኮኖሚ ልማት አቅጣጫ መሰረት ጤናማ የኢኮኖሚ እድገት ሊያስገኝ የሚችል ሁኔታ አለን ማለት ነው፡፡ በመሆኑም በዞኑ ያሉትን እምቅ የልማት አቅሞች ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ አጥንቶ በመለየትና በማልማት የዞኑን ኢኮኖሚ ማሳደግና ህዝቡን ተጠቃሚ ማድረግ ያስችላል፡፡ ስለሆነም የዞኑን ዕቅድ ስናቅድና ስንተገብር ያለንን አቅም አውቀንና ከግምት ውስጥ አስገብተን መሆን ስለሚኖርበት ተነጻጻሪ ተጠቃሚነታችንን የሚያሳዩ የመልማት አቅሞቻችንን በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 1.1.1. አምራች ሰብዓዊ ሀብት

የህዝብ ቁጥር በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ድርብ ሚና ይጫወታል። በአዎንታዊ ጎኑ ሰፊ የሰው ሃይል ያቀርባል፣ ለሸቀጦች እና አገልግሎቶች ገበያን ያሰፋል፣ ፈጠራን ያበረታታል፣ ኢንቨስትመንት ይስባል፣ በተለይም የስራ እድሜ ቡድኑ የበላይ ሆኖ ሲገኝ (የዲሞግራፊ ክፍፍል) ጠቀሜታው ከፍ ይላል። ይሁን እንጂ ፈጣን የህዝብ ቁጥር መጨመር እንደ ሥራ አጥነት፣ የሀብት ጫና፣ ከፍተኛ ጥገኝነት ጥምርታ፣ የከተማ መጨናነቅ እና ድህነት መጨመር የመሳሰሉ ፈተናዎችን ይፈጥራል። ስለዚህ የህዝብ ብዛት በትምህርት፣ በስራ እድል ፈጠራ እና በዘላቂ ልማት ፖሊሲዎች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ በመወሰን ሀብትም ሸክም ሊሆን ይችላል።

የህዝብ ቁጥር በኢኮኖሚ ልማት ውስጥ ያለውን አወንታዊ ሚና ለማጉላት ሀገራት ጥራት ያለው የትምህርት እና የክህሎት ስልጠና ላይ ኢንቨስት ማድረግ፣ ተጨማሪ የስራ እድሎችን መፍጠር እና ውጤታማ የሰው ሃይል ለመገንባት የጤና እንክብካቤን ማሻሻል አለባቸው። ወጣቶችን እና ሴቶችን ማብቃት፣ ስራ ፈጠራን ማበረታታት እና ሀብትን በዘላቂነት ማስተዳደር የሰውን አቅም ከፍ ለማድረግ ይረዳል። በተጨማሪም የመልካም አስተዳደርና የመሰረተ ልማት ዝርጋታ እያደገ የመጣውን የህዝብ ቁጥር ከሸክም ይልቅ የእድገት ሞተር እንዲሆን ያደርጋል።

የዞናችን ህዝብ ከ1999 ህዝብና ቤት ቆጠራ ወደዚህ 22 በመቶ ጨምሮ አሁን ላይ 3,078,587 የደረሰ ሲሆን ከክልሉ ህዝብ ቁጥር 12.7 በመቶ ድርሻ አለው፡፡ ከዚህ ውስጥ ደግሞ 52 በመቶ የሚሆነው ህዝባችን ሰሪ ሃይል የሚባለው የህብረተሰብ ክፍል የሚሸፍን ሲሆን ከላይ ለማመላከት የተሞከሩትን የህዝብን ቁጥርን እንደ መልካም አጋጣሚ መጠቀም የሚያስችሉንን ተግባራት መስራት ከቻልን እድለኛ ያደርገናል ማለት ነው፡፡

እንደሚታወቀው የዞናችን ግብርና 90% ህዝባችንን የተሸከመ በመሆኑ የህዝብ ቁጥራችንን እንደመልካም አጋጣሚ መጠቀም ከቻልን ለግብርናው ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገቱ ላይ የሚኖረው አወንታዊ ሚና ተገማች ነው፡፡ በተለይም ሰሪ ሃይሉ አብላጫውን ድርሻ የሚወስድ መሆኑ ደግሞ ያሰብነውን ዘመናዊ ግብርና ተግባራዊ ለማድረግና ተክኖሎግ ለመጠቀም እንደመልካም አጋጣሚ የሚታይ ነው፡፡ በተመሳሳይ በኢንደስትሪው መስክ የሚፈለገውን አምረች የሰው ሃይል ማቅረብ የሚያስችል አቅም በመሆንም በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

ዲጅታል ቴክኖሎጅ ላይ የተሻለ ስራ ለመስራት ትኩስ የሰው ሃይል ያለበት ህዝብ በመሆኑ ወጣቱን በቴክኖሎጅ እውቀት አንጾ የስራ እድል ለመፍጠር እና ኢኮኖሚውን በዕውቀት ለማገዝ የሚያስችል አቅም አድርገን የምንጠቀመው ህዝብ ያለበት ዞን ነው፡፡

በአጠቃላይ የትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ላይ ስራ በመስራት፣ የክህሎት ስልጠና ላይ ኢንቨስት በማድረግ፣ ተጨማሪ የስራ እድሎችን በመፍጠር እና ውጤታማ የሰው ሃይል በመገንባት የጤና እንክብካቤን በማሻሻል፣ ወጣቶችን እና ሴቶችን በማብቃት፣ ስራ ፈጠራን በማበረታታት እና ሀብትን በዘላቂነት ማስተዳደር የሰውን አቅም ከፍ ማድረግ ከቻልን የዞናችንን ህዝብ ለኢኮኖሚ እድገቱ ትልቅ አቅም አድርገን መጠቀም መጠቀም እንችላለን፡፡

## 1.1.2. በግብርና የመልማት አቅም

መሬት ለሁሉም ነገር መሰረት የሆነ ውድ ሀብት ነው፡፡ ይሄን ውድ ሀብት ለዛሬው ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩ ትውልድ ሊጠቅም በሚችል መንገድ ማስተዳደርና አጠቃቀሙን መወሰን ግድ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዘመናዊ የመሬት አስተዳደር ስርአት መገንባት አስፈላጊ ነው፡፡ እንደ ደቡብ ወሎ ዞን ከ4.2 ሚሊየን ማሳ በላይ መሬት አለን፡፡ የካዳስተር ስርአቱን እየገነባን ስንሄድ ከዚህ በላይ የመሬት መጠን ሊኖረን እንደሚችል ግልፅ ነው፡፡ የዞናችንን መሬት በአግባቡ ማስተዳደርና መምራት ለሌሎች ሴክተሮች ዋነኛ  የልማት አቅም ሁኖ ያገለግላል፡፡ አ/አደሩን የመጠቀም መብትና ባለቤትነት፣ በመጨመር የግብርና ምርታማነታችንን ይጨምራል በተመሳሳይ የመሬት አቅርቦት ለኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መስፋፋት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

በኢትዮጵያ ያለው ግብርና ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አንድ ሶስተኛውን (35%) ያዋጣል፣ ከህዝቡ ሁለት ሶስተኛው በግብርና ስራ የተሰማራ ሲሆን ከ70% በላይ የወጪ ንግድ ይሸፍናል፡፡ በአማራ ክልል ያለውን ስንመለከት ደግሞ ከጠቅላላ የክልሉ ምርት አንድ ሁለተኛውን (51.9%) ያዋጣል፣ ከህዝቡ 90% የሚሆነው በግብርና ስራ የተሰማራ ሲሆን 41.5% የአገሪቱን ምርት ይሸፍናል፡፡ እንደ አገር ግብርና በኢኮኖሚ ልዩነት ምክንያት የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻው ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሲሆን የአማራ ክልል ግብርና የኢኮኖሚው የጀርባ አጥንት ሆኖ እንደቀጠለ መሆኑ መረጃወች ያስረዳሉ፡፡

የግብርና ልማት የሰብል እና የእንስሳት ምርትን በማስፋፋት የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ለረሃብ ተጋላጭነትን እና የዕርዳታ ጥገኝነትን ይቀንሳል፡፡ የስራ እድል በመፍጠር፣ የቤተሰብ ገቢ በመጨመርና የአገር ውስጥ ንግድን በማሳደግ በኢኮኖሚው ላይ ትርጉም ያለው እድገት ማምጣት የሚያስችለን ሲሆን በገጠር የሚኖረውንና አብዛኛውን ህዝብ ኑሮውን ማሻሻል ስለሚያስችለን በድህነት ቅነሳው ላይ የሚኖረው ትርጉም ከፍ ያለ ነው የሚሆነው፡፡ ለአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች (ዱቄት፣ የወተት፣ ማር፣ ወዘተ) ግብአቶችን ማቅረብ እና ገበያ ተኮር ምርትን በማሳደግ የኤክስፖርት አቅምን ከፍ ማድረግ ስለሚያስችል የውጭ ምንዛሬ ገቢን ይጨምራል፡፡ እንድሁም በማህበራዊ ልማት፡ ትምህርትን፣ ጤናን እና መሠረተ ልማትን በተሻለ ገቢ ይደግፋል፡፡ በአጠቃላይ የግብርና ልማት የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ ድህነትን በመቀነስና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን በማስፈን ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

ደቡብ ወሎ ዞን የተለያዩ አግሮ-ኢኮሎጂካል ዞኖች ስላሉት የተለያዩ ሰብሎችን (ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ጥራጥሬ፣ አትክልት እና ፍራፍሬ) ለማልማት ያስችላል፡፡ በብዙ አካባቢዎች ለም አፈር ያለው ሲሆን ለእህል እና ለጥራጥሬ ተስማሚ በመሆኑ የተሸለ ምርታማ ነው፡፡ እንደ ቦርከና፣ ሚሌ፣ በቶ፣ ወለቃ፣ በሽሎ እና ሌሎች መሰልና ገባር ወንዞች ያሉ በመሆኑ የተሻለ የመስኖ አቅምም ያለው ዞን ነው፡፡ ይህም ግብርናውን በዝናብ ላይ ያለውን ጥገኝነት ሊቀንስ ይችላል፡፡ አርሶ አደሮች የሰብል እርሻን ከከብት እርባታ ጋር በማዋሃድ ጥምር ግብርና የመጠቀም ልምድ ያላቸው በመሆኑ ፍግ እንደ ማዳበሪያ እና የሰብል ተረፈ ምርቶችን እንደ የእንስሳት መኖ ይጠቀማሉ፡፡ ይህ ዘላቂነትን እና ምርታማነትን በእጅጉ ይጨምራል፡፡ በዞናችን ያለው የሚሰራ ጉልበት የግብርና ስራውን በማገዝ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ ለደሴ እና ኮምቦልቻ ከተሞች ቅርበት እና ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ኮሪደር ጋር ያለው ትስስር የተሸለ የገበያ እድል ይፈጥርልናል፡፡

በ2016/17 ምርት ዘመን አማካኝ ምርታማነት 31 ኩ/ል በሄ/ር ሲሆን 13398827 ኩንታል አጠቃላይ ምርት አምርተናል፡፡ የተመረተው ጥቅል ምርት ከክልል አጠቃላይ ምርት 170378749 ኩ/ል ያለው ድርሻ ተወስዶ ሲታይ 7.9 በመቶ ነው፡፡ ያለን የሚታረስ መሬት ደግሞ 432168 ሄ/ር ሲሆን አጠቃላይ ከክልሉ 5398392 ሄ/ር እርሻ መሬት የዞኑ ድርሻ 8 በመቶ ድርሻ የምንይዝ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ እንድሁም የዞኑ ህዝብ ብዛት 3078587 ሲሆን ከክልሉ 24,206,997 ህዝብ ተወስዶ ሲታይ 12.7 በመቶ ድርሻ እንወስዳለን፡፡ ይህ መረጃ የሚያሳየን ከክልሉ የሚታረስ መሬት በሚኖረን ድርሻ ልክ የተመረተው ምርታችን በትይዩ ቢሆን ወይም ክልሉ የደረሰበት ምርታማነት ላይ ብንደርስ ጥቅል ምርታችን 16004154 ኩንታል ማድረስ የምንችል ሲሆን አሁን ካመረትነው 2605327 ኩንታል በብልጫ ማምረት የምንችል ሲሆን ይሄም ህዝብ 1157923 ወይም የዞኑን አንድ ሶስተኛ ህዝብ አመታዊ ፍጆታ መሸፈን ይችላል ማለት ነው፡፡ ህዝባችን በቁጥሩ ልክ ከክልሉ ምርት ማገኘት

የሚችለውን የምርት ድረሻ ማምረትን ከግምት አስገብተን ማየት ከቻልን ደግሞ 23,634,042 ኩንታል ወይም 10,235,215 ኩ/ል በብልጫ ማምረት እንደነበረብን ያሳየናል፡፡

በአጠቃላይ ዞኑ በግብርናው ዘርፍ የተሻለ ከፍታ የሚያደርስ ገና ያልተጠቀምንበት እምቅ አቅም ያለው ሲሆን ከ1,855,890 ሄ/ር የቆዳ ስፋት ውስጥ ለእርሻ አገልግሎት የሚሆን 543,728 ሄ/ር ሲሆን አሆን ያለውን አመካኝ 31 ሄ/ር በሄክታር ምርታማነት ወደተሻለ ደረጃ በመሳደግ የዞኑን ህዝብ ከመመገብ ባለፈ ትርፍ አምርቶ ለኢንዱስትሪ ግብአትና ለውጭ ገበያ የሚሆን ምርት ማምረት የሚያስችል አቅም አለን፡፡ በተመሳሳይ ለእርሻ ስራ የማይሆኑ አካባቢዎች ደግሞ በእንስሳት እርባታ፣ በደን ልማት እና በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተሻሉ አመራጮች በመሆናቸው በዞናችን ዘርፈ ብዙ ግብርና በማስኬድ በተለይም በሌማት ትሩፋት ውጤታማ የመሆን ምርጥ አማራጭ ያለው ዞን ነው፡

በአጠቃላይ ደቡብ ወሎ ዞን የተለያዩ አግሮ-ሥነ-ምህዳር፣ ለም አፈር፣ የመስኖ እድሎች፣ ሰፊ የሚሰራ የሰው ሃይል እና ሰፊ የገበያ ተደራሽነት በመኖሩ የሰብል ምርት ለማምረት የሚያስችል አቅም ምቹ ሁኔታ ያለው ዞን ነው፡፡ ዞናችን የተሸለ የተፈጥሮ ሃብት ልማት በመስራት እንደ ድርቅንና የመሬት መራቆት አይነት ያሉ ተግዳሮቶችን መቀነስ ከተቻለ በኢትዮጵያ ውስጥ በሰብል ምርታማነት ግንባር ቀደም ከሆኑት ዞኖች አንዱ ሲሆን እንደሚችል የአየርንብረት ብዝሃነቱና የመሬት አቀማመጡ ማሳያወች ናቸው፡፡

### 1.1.3. የእንስሳት ሀብት እንደ መልማት አቅም

የእንስሳት ሀብት ልማት በእንስሳትና በእንስሳት ተዋጽዖ ምርት የገቢና የሥራ ዕድል ምንጭ በመሆን ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅዖ በማድረግ፣ በተፈጥሮ ማዳበሪያ፣ በእርሻና በትራንስፖርት አገልግሎት ግብርናውን በመደገፍ፣ የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ በተጨማሪ በፕሮቲን የበለፀጉ ምግቦች አመጋገብን በማሻሻል የተመጣጠነ ምግብ ምንጭ በመሆን፣ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን በማሳደግ፣ የቆዳ፣ የወተት፣ የስጋ ወዘተ ኢንዱስትሪዎችን በግብአት በመደገፍ እና በገጠር በሚሊዮን ለሚቆጠሩ አባወራዎች እንደ “የቀጥታ ባንክ” በማገልገል በአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በአጠቃላይ የእንስሳት ሀብት የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ ስራ እድል በመፍጠር፣ ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ ገጠርም ሆነ በከተማ ውጤታማ ስራ መስራት ስለሚያስችል የሀገራዊ ኢኮኖሚ እድገትን በማፋጠን ትልቅ ድርሻ አለው፡፡

እንደ አለም ባንክ መረጃ ከሆነ በሀገራችን ኢትዩጲያ 252 ሚ እንስሳት ሃብት ያላት ሲሆን በብዛት ከአለም 10ኛ ከአፍሪካ ደግሞ 1ኛ ደረጃን እንደምትይዝ ይነገራል፡፡ የእንስሳት ሀብት ከኢትዮጵያ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት የእንስሳት እርባታ ከ19-20% የሚሆነውን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርት የሚሸፍን ሲሆን ከግብርና ምርት ውስጥ ደግሞ 45 በመቶውን ይይዛል፡፡

አማራ ክልል ከፍተኛ የእንስሳት ሃብት ካላቸዉ ክልሎች ዉስጥ አንዱ ሲሆን በክልሉ ዉስጥ በጥቀሉ 53,514,348 የሚሆኑ እንስሳት ይገኛሉ፡፡ የእንስሳት ሀብት ከአማራ ክልል አጠቃላይ ክልላዊ ምርት የእንስሳት እርባታ ከ17% የሚሆነውን የአማራ ክልላዊ ምርት የሚሸፍን ሲሆን ከግብርና ምርት ውስጥ ደግሞ 33 በመቶውን ይይዛል:: ከዚህ ዉስጥ በደቡብ ወሎ የሚገኙት ጠቅላላ የእንስሳት ብዛት 7,740,186 ሲሆኑ የክልሉን (14.5%) የሚሸፍን ሃብት ነዉ፡፡ የክልላችን የእንስሳት ሃብት ከአጠቃላይ ምርትም ሆነ ከግብርናው የሚኖረው ድርሻ አገራዊ ድርሻው ጋር ሲነጻጸር ዝቅተና እንደሆነ ያሳያል፡ ፡ የዞናችንም በክልሉ ትይዩ የሚታይ ሲሆን በዘርፉ ዞኑ ካለዉ ሰፊ ሃብት አንጻር ገና ያልተነካ እና ብዙ መስራት እንደሚጠበቅ እንደሆነ ያሳያል፡፡

ስለሆነም በእንስሳት አስተዳደርና እንክብካቤ፣ በዝርያ ማሻሻል፣ በመኖ ልማት እና በህክምናው ዘርፍ ያለንን የእንስሳት ቁጥርና አጠቃላይ የመልማት አማራጭ ከግምት ውስጥ ያስገባ ስራ በመስራት ከእንስሳት ሃብት የሚጠበቀውን ዘርፈ ብዙ ውጤት እውን ማድረግ ትኩረትን የሚጠይቅ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

## 1.1.4.የአየር ንብረት

የአየር ንብረት በግብርና፣ በውሃ ሃብት፣ በኢነርጂ፣ በጤና እና በመሠረተ ልማት ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ ስላለው በኢኮኖሚ ልማት ውስጥ መሠረታዊ ሚና ይጫወታል:: ምቹ የአየር ጠባይ (መካከለኛ የሙቀት መጠን፣ አስተማማኝ የዝናብ መጠን) ሲኖር የእርሻ፣ የንግድ፣ የቱሪዝም ወዘተ ስራን የሚያበረታታ ሲሆን በተጨማሪም የተረጋጋ የኑሮ ሁኔታ እንድኖር ያደርጋል፡፡ በተቃራኒው አስቸጋሪ የአየር ንብረት (ድርቅ፣ ጎርፍ፣ ከፍተኛ ሙቀት) ሲኖር አደጋን ይፈጥራል፣ ወጪን ይጨምራል እና ምርታማነትን ይገድባል:: ባጭሩ ጥሩ የአየር ንብረት እድገትን እና ኢንቨስትመንትን ያስገኛል፣ ፈታኝ የአየር ንብረት ደግሞ ለዘላቂ ልማት መላመድ እና መቻልን ይጠይቃል::

ደቡብ ወሎ ዞን ከ500 ሚሜ እስከ 1500 ሚሜ አመታዊ የዝናብ መጠን የሚያገኝ እና የሙቀት መጠኑም ከ12.2-22.2$^{oc}$ የሚደርስ ነው ሲሆን ደጋ፣ ወይና ደጋ እና ቆላማ አካባቢዎችን በመያዝ የተለያየ የአየር ንብረት ያለው ዞን ነው:: ደጋ የሚባለው የአየር ንብረት ያለበት አካባቢ፡ አሪፍ የሚባል ዝናብ (1000-1500 ሚሚ) ያለው እንደ ገብስ፣ ስንዴ እና ድንች ላሉ እህሎች ተስማሚ አካባቢ የዞናችንን 35.2 በመቶ የሚሸፍን ሲሆን በስፋት መሃል ሳይንት፣ አማራ ሳይንት፣ ለጋምቦ፣ መቅደላ፣ ተንታ፣ ደሴ ዙሪያ፣ ኩታበር እና ደላንታ ወረዳዎችን የሚያካልል ነው::  ወይና ደጋ የአየር ንብረት ያለበት አካባቢ፡ መጠነኛ ዝናብ (800-1200 ሚሚ) የሚያገኝ የአየር ንብረት ያለበት ሲሆን ለጤፍ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ጥራጥሬ እና አትክልት ልማት ተስማሚ ነው:: ይህ አይነት የአየር ንብረት የዞናችንን 54.4 በመቶ የሚሸፍን ሲሆን በመጠን የሚለያይ ቢሆንም በዞናችን በሁሉም ወረዳዎች ሽፋን ያለው የአየር ንብረት ነው፡፡ ቆላ የሚባል የአየር ንብረት ያለበት አካባቢ፡ ዝቅተኛ የሚባል የዝናብ (500-

800 ሚሚ) መጠን ያለበት፣ ሙቅ እና ለድርቅ የተጋለጠ አካባቢ ሲሆን ለእርሻ ስራ ፈታኝነት ያለው ቢሆንም ለእንስሳት ሃብት ልማት እና ድርቅን መቋቋም ለሚችሉ ሰብሎች ምርታማ ሊያደርግ የሚችል ምቹ አካባቢ ነው። ይህ የአየር ንብረት የዞናችንን 9.2 በመቶ የሚሸፍን ሲሆን ወረባቦ፣ ቃሉ፣ አርጎባ፣ ከላላ፣ ወግድ እና ተሁለደሬ ሰፋ ያለውን ሽፋን ይይዛሉ። የዝናብ ሁኔታው ወቅታዊ እና ተለዋዋጭ ሲሆን አንዳንድ አካባቢዎች አልፎ አልፎ ለድርቅና ጎርፍ ተጋላጭነት የሚሆኑበት ሁኔታ ይፈጠራል።

በአጠቃላይ ዞኑ ለተለያዩ የሰብል አይነቶች፣ ለፍራፍሬ ልማት እና ለእንስሳት ሃብት ልማት ምቹ የአየር ንብረቶች የያዘ መሆኑ ለምግብ፣ ለኢንዱስትሪ ግብአት እና ለኤክስፖርት የሚሆን ምርት ማምረት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ያለበት አካባቢ እንደሁነ እና እርጥበት አጠር በሆኑት አካባቢ የአጭርና የረጅም ጊዜ ውጤት ያለቸውን የተፈጥሮ ሃብት ልማት ስራ በእቅድ አካቶ መስራትን የሚጠይቅ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

### 1.1.5. የማዕድን ሀብት

የማዕድን ሃብቶች ለኢንዱስትሪያላይዜሽን፣ ለኤክስፖርት እና ለመሰረተ ልማት መሰረት በመሆን ያገለግላል። ዘርፉ ማዕድንን ወደ ውጭ በመላክ እድሁም በሮያሊቲ እና በታክስ የገቢ ምንጭ በመሆን፣ ለምርት፣ ለግንባታ እና ለኢነርጂ የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎችን (ወርቅ፣ የኖራ ድንጋይ፣ ፖታሽ፣ የድንጋይ ከሰል ወዘተ) በማቅረብ የኢንዱስትሪ እድገትን በማፋጠን፣ ማዕድን በማውጣት፣ በማቀነባበር እና ተዛማጅ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሥራ እድሎችን በመፍጠር፣ በመሠረተ ልማት ዝርጋታ የመንገድ፣ የሀይል እና የውሃ መሠረተ ልማቶችን በማንቀሳቀስ ለሌሎች ዘርፎችም ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት እን ቴክኖሎጂ እና ቴክኒካል እውቀትን ወደ ኢኮኖሚ በማስተዋወቅ በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ትልቅ ሚና የሚጫወት ሲሆን ይህም ለሀገራዊ ጂዲፒ በቀጥታ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

የአማራ ክልል የተለያዩ ማዕድን ሃብቶች የተጎናፀፉ ሲሆን ይህም ለክልሉ ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በክልሉ ከ40 በላይ የማዕድን ሃብቶች እንደሉ የሚነገር ሲሆን ከነዚህም መካከል፡ - ወርቅ፣ የከበሩ ድንጋዮች፣ ኦፓል፣ አምበር፣ ጃስጲድ፣ ኦኒክስ፣ ቱርማሊን፣ በሃ ድንጋይ፣ ካኦሊን፣ ጂፕሰም እና ኢኒምብሪት፣ ብረት፣ ማንጋኒዝ፣ መዳብ፣ ኒኬል እና ድኝ፣ ግራናይት፣ ባሳልት፣ ፓም እና የአሸዋ ድንጋይ፣ የድንጋይ ከሰል እና ኳርትዝ የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ሲሆን ብዙዎቹ ዞናችን እንደሚገኙም ይነገራሉ።

በዞናችን የማዕድን ሀብት በተለይም ኦፓል ለአካባቢው ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ይገኛል። ከ30 የሚበልጡ ማዕድናት የሚገኙበት ዞንም እንደሆነ ይነገራል። ከነዚህም መካከል

የሚጠቀሱት፦ ኦፓል፣ አምበር፣ ጃስፐር፣ ኦኒክስ፣ ቱርማሊን፣ ላይምስቶን፣ ድንጋይ ከሰል፣ ሲልካ ሳንድ፣ ክሌይ፣ ነዳጅ፣ ኳርትዝ እና ጂፕሰም ወዘተ ሲሆኑ በተለይም የድንጋይ ከሠል በውጫሌ 3.3 ሚሊየን ቶን እና በላይ የክምችት መጠን እንዳለ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ እነዚህ ማዕድናት በዞኑ የተለያዩ ወረዳዎች ይገኛሉ፡፡

በዞናችን ውስጥ ያለው የማእድን ስራ በዋናነት የእጅ ጥበብ ስራ ሲሆን በባህላዊ ዘዴ እና ውስን ሜካናይዜሽን የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ አካሄድ ብዙውን ጊዜ ለደህንነት አደጋዎች፣ ለአካባቢ መራቆት እና በዘርፉ ለተሰማሩት አካላት ውጤታማ አለመሆንን ያስከትላል፡፡ ለምሳሌ በ2016 በደላንታ የሚገኘው የማዕድን ጉድጓድ መደርመስ የማዕድን አውጪዎች ታፍነው እንድቀሩ አድርጓል፡፡ ይህም ሰራተኞች የሚያጋጥሟቸውን አደገኛ ሁኔታዎች አጉልቶ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም የማዕድን ዘርፉ እንደ ህገወጥ ንግድ፣ እሴት መጨመር እና በቂ የመሰረተ ልማት አለመሟላት በመሳሰሉት ጉድለቶች ይተዩበታል፡፡

በአጠቃላይ በዞኑ ያለው የማዕድን ሀብት በተለይም ኦፓል ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድሎችን የፈጠረ ቢሆንም በዘርፉ ያለውን ጸጋ አሟጦ ለመጠቀም የማዕድን አሰራርን ማዘመን፣ የደህንነት ደረጃዎችን ማሻሻል እና የተሻለ የገበያ ተደራሽነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን ተግዳሮቶች መፍታት ዘላቂ ልማትን እና በማዕድን ቁፋሮ ላይ ለሚሳተፉ ማህበረሰቦች የተሻሻለ የኑሮ ደረጃን ስለሚፈጥር ኢኮኖሚውን የሚያሣድግ እንድሁም ሰፊውን ስራ ፈላጊ ወጣት በከፍተኛ ደረጃ ችግሩን ሊቀርፍ የሚችል ወሳኝ ዘርፍ ነው፡፡

### 1.1.6. የቱሪዝም ሃብት

ቱሪዝም የውጭ ምንዛሬ ገቢን በማስገኘት፣ የስራ እድል በመፍጠር እና ለሀገር ውስጥ ልማት ድጋፍ በማድረግ የኢኮኖሚ እድገትን ስለሚያበረታታ ቁልፍ የልማት አቅም ነው፡፡ በሌላ መልኩ ቱሪዝምን ተከትሎ እንደ መንገድ፣ ሆቴሎች እና የመገናኛ ተቋማት ስለሚስፋፉ ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚጠቅሙ የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎችን የማንቀሳቀስ አቅም አለው፡፡ ከዚህም በላይ ቱሪዝም የባህል ጥበቃን፣ የአካባቢ ጥበቃን እና ዓለም አቀፍ ግንኙነቶችን በማስፋፋት ኢንቨስትመንትን ወደ ገጠርና ብዙም ወዳለሙ አካባቢዎች ይስባል፡፡ በአጠቃላይ ቱሪዝም በብቃትና በዘላቂነት ሲመራ ለኢኮኖሚ፣ ለማህበራዊ እና ለባህል ልማት ወሳኝ ሞተር ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ቱሪዝም የኢኮኖሚ እድገትን የሚያበረታታ፣ስራ እድል የሚፈጥር፣ ባህልን የሚጠብቅ፣ መሰረተ ልማትን የሚያሻሽል እና ዘላቂነትን የሚያጎለብት በመሆኑ የልማት አቅም ነው፡፡

ቱሪዝም ቁልፍ የልማት አቅም ነው ምክንያቱም የውጭ ምንዛሪ ገቢን በማስገኘት፣ የስራ እድል በመፍጠር እና ለሀገር ውስጥ ቢዝነሶች ድጋፍ በማድረግ የኢኮኖሚ እድገትን ስለሚያበረታታ ነው፡፡

እንደ መንገድ፣ ሆቴሎች እና የመገናኛ ተቋማት ለቱሪስቶች እና ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚጠቅሙ የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎችን ያንቀሳቅሳል፡፡ ከዚህም በላይ ቱሪዝም የባህል ጥበቃን፣ የአካባቢ ጥበቃን እና ዓለም አቀፍ ግንኙነቶችን በማስፋፋት ኢንቨስትመንትን ወደ ገጠር እና ብዙም ያልበለጸጉ አካባቢዎችን ይስባል፡፡ ቱሪዝም በዘላቂነት ሲመራ ለኢኮኖሚ፣ ለማህበራዊ እና ለባህል ልማት ኃይለኛ ሞተር ይሆናል፡፡

በደቡብ ወሎ ዞን በባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች የቱሪዝም እምቅ ሀብት ያላት ሲሆን ለማሳያም ያክል ሎጎ፣ አርድቦ፣ ጎልቦና ማይባር የሚባሉ 3 ሃይቆች መኖራቸው፣ በርካታ መንፈሳዊ ተቋማትና ቅርሶች ያሉበት ሲሆን በክርስትና እምነት ሃይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ አንድነት ገዳም፣ አምባሰል የዳግማዊት ኢየሩሳሌም ግሸን ደብረ ከርቤ፣ አምሃራ ሳይንት ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም፣ ከላላ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገዳም፣ በእስልምና እምነት የአልብኮ ጀማ ንጉስ፣ የወረባቦ ሽህ ጫሌ መስጂድ፣ የደሴ ዙሪያ የአርባ ጫማ ጥንታዊ መስጂድ፣ የአርጎባ ጥንታዊ መስጂድ፣ የቃሉ ገታ ሃጂ ቡሽራ ሰይድ መስጂድና የሸህ ሁሴን ጅብሪል መቃብር በቅርስነት ተመዝግበው ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ የበቶ ወለቃ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክና የቦረና ወረሂመኖ ብሄራዊ ፓርክ ብርቅየ አዕዋፎችን ይዘው ከሚስብ መልክአምድር ጋር ቱሪስትን ቀልብ የመሳብ አቅም ያላቸው ሌሎቹ የቱሪስት መዳረሻ ሃብቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የህዝብ ወጎች፣ በዓላት፣ ሙዚቃዎች፣ ውዝዋዜዎች እና የሀገር ውስጥ ጥበቦች ለባህል ቱሪዝም ጠንካራ እድሎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በዞናችን በብዙ ዘርፍ ያልተሰራባቸው ብዙ አቅሞች ያሉት ዞን ሲሆን እነዚህን ማልማትና ማስተዋወቅ ከተቻለ ከዘርፉ የሚጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ የሚያስችል እምቅ አቅም እንዳለን ማሳያ ናቸው፡፡

## 1.1.7.የዉሃ ሃብት

በደቡብ ወሎ ዞን በከርሰ ምድር ውሃ ከፍተኛ እምቅ አቅም ያለው በመሆኑ የግብርና ምርታማነትን በማሳደግ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ የገጸ ምድር ውሃ ሀብትም ቢሆን በዞኑ የተለያዩ ወንዞች ተዘዋውረው የሚያልፍ ሲሆን በመስኖ የተሻለ የማልማት አቅም አላቸው፡፡ እነዚህን የገጸ ምድር ውሃዎች ተከትሎ የተሰሩ 476 አነስተኛ የመስኖ አውታሮች በዞኑ የሚገኙ ሲሆን 19172.55 ሄ/ር መሬት በማልማት 58616 ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡ በተጨማሪም ሌሎች የተጠኑ እና ያልተጠኑ በተለያየ ደረጃ ለመስኖ አውታር ግንባታ እና ለንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን ማስፋፊያ የሚውሉ የገጸ ምድርና ከርሰ ምድር የውኃ አማራጮች በስፋት የሚገኙበት ዞን ነው፡ ፡ ይሁን እንጅ የከርሰ ምድር ውሃ ቢኖርም በበጀትና በቴክኖሎጂ እጥረት እንድሁም በቂ መሠረተ ልማት አለመሟላት በዞኑ የከርሰ ምድር ውሃን መሰረት ያደረጉ የመስኖ ልማት ተጠቃሚነት ማሳደግ አልተቻለም፡፡ እነዚህን አማራጮች በመጠቀም በመስኖ የሚያለማውን አርሶ አደር በአመት በርካታ

የሰብል ዑደቶችን እንዲያመርት ስለሚያስችለው የምግብ ዋስትናውን እንዳረጋግጥ እና ኢኮኖሚያዊ መረጋጋትን እንድጨምር ያደርገዋል፡፡ በሌላ መልኩ እነዚህ የውሃ ሃብት አቅሞች በዞኑ ለሚደረገው የንጹህ መጠት ውሃ ግንባታ ግብአት በመሆን የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋንን በማሳደግ አይነተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ከወንዞችና ከርሰ ምድር ውሃ በተጨማሪ በዞኑ 3 ሰፋፊ ሃይቆች የሚገኙ ሲሆን እነርሱም ሎጎ ሃይቅ፣አርርዲቦ ሃይቅና ማይባር ሃይቅ ናቸዉ፡፡ እነዚህ ሃይቆች ለቱሪዝም፣ የአሳ ሃብት ልማት፣ ለመስኖ እና ለመዝናኛ በመሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ሲሆን የስራ እድል በመፍጠር እና የእኮኖሚ እድገቱን በመገዝ የሚኖራቸው ድርሻ የተሻለ ነው፡፡

በአጠቃላይ ደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ የውሃ ሃብት ባለቤት ሲሆን ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ከዋለ የግብርና መልክዓ ምድሩን ሊለውጥ ይችላል፡፡ ይህንን እምቅ አቅም ሙሉ በሙሉ እውን ለማድረግ ደግሞ ከመሠረተ ልማት፣ ከቴክኖሎጂ እና ከግንዛቤ ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶችን መፍታት ወሳኝ ነው፡፡

## 1.2. የክልሉ ጥቅል ኢኮኖሚ አፈጻጸም እንደመነሻ

ባለፉት ዓመታት የታዩ እጥረቶችን በመቅረፍ እና የተገኘውን አወንታዊ ለውጥ በማጠናከር አጠቃላይ በክልሉ አሻጋሪ እድገት እና ዘላቂ ልማት ለማምጣት በአምራች ዘርፎች በተለይም በዘመናዊ ግብርና እና በአምራች ኢንደስትሪው ምርታማነትን እና ቅልጥፍና የማሳደግ፣ የኢንደስትሪና ኢንቨስትመንትን በተለይም የአምራች ኢንደስትሪዎች ኢንቨስትመንትን የማስፋፋትት፣ ኢንቨስትመንትና ቁጠባን የማጎልበት፣ የሳይንስና ቴክኖልጅ፣ የቱሪዝም ልማት፣ በማዕድን ልማት፣ በክትመት፣ የተጀመሩ ስራዎችን በተጠናከረ መልኩ የማስቀጠል እንዲሁም ከመሰረተ ልማት አኳያ ግንባታዎች የማጠናቀቅና አድሶችን የመገንባት፣ በሁሉም የልማት ዘርፎች የሥራ እድል በመፍጠር በክልሉ የሚታየውን የሥራ አጥነት ችግር የመቅረፍ፣ በሰው ሃይል ልማትና በኑሮ ደህንነት በዘላቂ ልማት ግቦች የተቀመጡትን መስፈርቶች የማሳካት፣ የትምህርት፣ የጤና እንዱሁም የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን የማጎልበት፣ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ አላማን የማሳካት ተግባራትን በማስቀጠል ህልም ብሌጽግናን እውን የማድረግ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት በማክሮ ኢኮኖሚና በየዘርፎች የነበረው ዘፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የክልል የኢኮኖሚ እድገት በ2016 በጀት ዓመት በተወሰደ መረጃ ላይ በመመርኮዝ በነበረው የቋሚ ዓመት የገበያ ዋጋ እና በወቅታዊ የገበያ ዋጋ መሰረት (Trends of Real and Nominal GDP) በቋሚ ዓመት ዋጋ የተሰላው የ2016 በጀት ዓመት አጠቃላይ ክልላዊ ጥቅል ምርት ብር 370.64 ቢሊዮን መድረሱን ያሳያል፡፡ ይህም በ2015 በጀት ዓመት ከነበረው ግምት በብር 20.9 ቢሉዮን ብር

ብልጫ አለው፡፡ በሌላ በኩል በዚሁ ዓመት በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሰረት የተሰላው ጥቅል ክልላዊ ምርት (GDP) ብር 1,329.25 ቢሉየን ደርሷል፡፡ ይህም ከባለፈው 2015 ጋር ሲነጻጸር ከብር 260.56 ቢሉየን በላይ ብልጫ እንዳለው ያሳያል፡፡ የ2017 በጀት ዓመት ዓመታዊ የክልል አጠቃላይ ምርት እድገት ትንበያ 6.8 በመቶ የነበረ ሲሆን ይህም በ2015 በጀት ዓመት ከተመዘገበው 5.6 በመቶ ዕድገት ብልጫ ያለው መሆኑን ያመላክታል፡፡ በ2017 የዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች ማለትም የግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች 4.9 በመቶ፣ የኢንደስትሪ ዘርፍ 9.4 በመቶ እንዱሁም የአገልግሎቱ ዘርፍ 5.8 በመቶ እድገት በማስመዝገብ የአጠቃላይ ክልላዊ የኢኮኖሚ እድገቱ አስተዋጽኦ አበርክተዋሌ፡፡ ክልሉ በበርካታ ችግሮች ውስጥ ሆኖ የተሻለ የሚባል ዕድገት ማስመዝገቡ የሚበረታታ ቢሆንም አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት የማምጣት ከሚጠበቀው አኳያ ገና ብዙ የሚቀረው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

የክልሉ የነፍስወከፍ ገቢ በ2015 በጀት ዓመት ከነበረበት 874 የአሜሪካ ዶላር በ2016 በጀት ዓመት ወደ 1,021 የአሜሪካ ዶላር ከፍ ማለቱን መረጃው ያሳያል፡፡ ይህም ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ ገና ብዙ የሚቀረው በመሆኑ በቀጣይ የተጠናከረ ስራ መስራትን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን በሚመለከት በ2017 በጀት ዓመት የዋና ዋና ኢኮኖሚ የዘርፎች እሴት ጭማሪ ከጥቅል ክልላዊ ምርት (GDP) ያሊቸው ዴርሻ ሲታይ ግብርና 51.4 በመቶ፣ የኢንደስትሪ 16.7 በመቶ እና የአምራች ኢንደስትሪው 9.8 በመቶ  እንዱሁም የአገልግሎት 33.3 በመቶ ድርሻ ነበራቸው፡፡ ይህም የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ከክልል ጥቅል ምርት ያለው ድርሻ ከፍተኛ ሲሆን በአንጻሩ የኢንደስትሪው ድርሻ ዝቅተኛ መሆኑ የክልሉ ኢኮኖሚ አሁንም በግብርናው ላይ ጥገኛ እንደሆነና የሚታሰበው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ አዝጋሚ እና ብዙ እንደሚቀረው መረጃው ያሳያል፡፡ ስለሆነም የኢኮኖሚ ዕድገቱ እመርታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ከማድረግ አንጻር ለግብናው ዘርፍም የሚገባውን ያህል ትኩረት በመስጠት መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጡ አሠራሮችን መከተል፣ በኢንደስትሪው ዘርፍና በተለይም በአምራች እንደስትሪው ንዑስ ዘርፍ የሚታዩ ማነቆዎችን በመፍታትና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ዘርፉን በማስፋፋት ለአጠቃላል ኢኮኖሚው የሚኖረውን አስተዋጽኦ ማሳደግ ተገቢ ይሆናል፡፡ በተለይም የግብርና የ2018 በጀት ዓመት የአሻጋሪ እድገት እና የዘላቂ ልማት ዕቅድ ምርቶችን የማቀነባበርና እሴት/Value Addition/ የተጨመረባቸውን ምርቶች ወደ ውጪ መላክ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል፡፡

**የድህነት ምጣኔ፡-** የክሌለ አጠቃሊይ የዴህነት ምጣኔ በ2003 ከነበረበት 30.5 በመቶ በ2008 ወደ 26.1 በመቶ የቀነሰ ሲሆን የከተማና የገጠር የድህነት ምጣኔ እንደ ቅደም ተከተላቸው ከ29.2 በመቶ እና ከ30.7 በመቶ ወደ 11.6 በመቶ እና 28.8 በመቶ የደረሰ መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግ በከተማ የ17.6 በመቶ እና በገጠር የ1.9 በመቶ ቅናሽ የሚያሳይ ሲሆን

ይህም ድህነት በከተማ ትርጉም ባለው ደረጃ የቀነሰ እንደሆነና በገጠር ግን ብዙም እንዳልቀነሰ ያመላክታል፡፡ በአጠቃላይ የክልል የድህነት ሁኔታ ከአገር አቀፍ አማካይ 23.5 በመቶ በላይ እና አሁንም ከፍተኛ እንድሆን ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩል በዘርፈ ብዙ ድህነት (Multidiametional poverty) አመልካችም በክልሉ ሰፊ ችግር እንዳለ መረጃዎች ያሳየሉ፡፡ በመሆኑም ድህነትን ከመቀነስ አኳያ ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት የተጠናከረ ስራ መስራት ይገባል፡፡ እንደ ድህነት እና የኢኮኖሚ እድገት በኢትዮጵያ (1995/96-2015/16 እኤአ) ሰነድ በክልሉ ያለው የሀብት ልዩነት (Gini-coefficient) በአገር አቀፍ ደረጃ በ2003 ከነበረበት በከተማ 0.371፣ በገጠር 0.274 በአጠቃሊይ 0.298 በ2008 እንደ ቅደም ተከተላቸው ወደ 0.380፣ 0.284 እና 0.328 መሆኑን ያመላክታል፡፡ በክልል ደረጃ ደግሞ በ2003 ከነበረበት በከተማ 0.416፣ በገጠር 0.270 በአጠቃላይ 0.296 በ2008 እንደቅደም ተከተላቸው ወደ 0.400፣ 0.283 እና 0.343 እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን በተጋነነ ሁኔታ ባይሆንም በደሃና በሀብታሞ መካከል ያለው የሀብት ልዩነት እየሰፋ መምጣቱን መረጃው ያሳያል፡፡ ስለሆነም የዜጎችን የነፍስወከፍ ገቢ ለማሳደግ ከሚደረገው ጥረት ባሻገር ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንድኖር ማድረግ የሚያስችል ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡

**የስራ አጥነት ሁኔታ፡-** ከ2014 በጀት ዓመት በኂላ የወጣ መረጃ ባለመኖሩ ምክንያት መረጃውን ማሻሻል አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በ2014 በጀት ዓመት በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በወጣው መረጃ በክልል የከተማ ስራ አጥነት ምጣኔ በ2009 ከነበረበት 15.5 በመቶ በ2014 ወደ 20.0 በመቶ ከፍ ማለቱን ያሳያል፡፡ ከጾታ አኳያ በ2009 የወንዶች ስራ አጥነት ከነበረበት 8.0 በመቶ እና የሴቶች 23.4 በመቶ በ2014 በጀት ዓመት እንደቅደም ተከተላቸው ወደ 10.8 በመቶ እና 29.5 በመቶ ከፍ ማለቱን መረጃው ያመላክታል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት በገጠርና በከተማ 68,175 ኢንተርፕራዞችን በማቋቋም 1,233,744 የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ባለፉት 11 ወራት ውስጥ 46,393 ኢንተርፕራይዞች የተቋቋሙ ሲሆን በቋሚ 817,041 እንዲሁም በጊዜያዊ 298,002 በድምሩ 1,115,043 የስራ እድል በፍጠር እንደተቻለ እና አፈፃፀሙም ከዓመቱ ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር በኢንተርፕርይዝ ምስረታ 68.05 በመቶ እና በስራ ዕድል ፈጠራ 90.38 በመቶ ማከናወን መቻሉን ያመላክታል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ በክሌለ ሰፉ የስራ ዕዴሌ ከመፌጠር አኳያ የተጠናከረ ስራ መስራት የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ በክልሉ የስራ አጥነት ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እየመጣ እንደሆነ እና ከአገር አቀፈ አማካይ ከ19.2 በመቶ በላይ እንደሆነ እና አሳሳቢ ደረጃ ላይ መደረሱን ያሳያል፡፡ ይህም ኢኮኖሚው በክልሉ ያለውን አምራች የሰው ኃይል በሚጠበቀው ልክ ወደ ስራ ማስገባት አለመቻሉን እንዱሁም የሚሰለጥነው አምራች የሰው ኃይልም ገበያው በሚፈልገው መልኩ አለመሆኑን እና ከፍተኛ የሀብት ብክነት እንዳለ የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም ሰፉ የስራ እድል የሚፈጥሩ የኢኮኖሚ

ዘርፎችን ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት እና የሰው ኃይል ስልጠናውም የስራ ገበያዉን መሰረት ያደረገ መሆን ይገባዋሌ፡፡

ሠንጠረዥ 1፡- የስራ አጥነት ምጣኔ ከ2009-2014 ዓ.ም

| የስራ አጥነት ምጣኔ በሀገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **በሀገር አቀፍ ደረጃ** | 20.4 | 18.9 | 18.0 | 17.5 | 25.4 | 19.2 |
| **ወንድ** | 12.2 | 11.0 | 11.ር4 | 11.4 | 11.2 | 10.8 |
| **ሴት** | 29.6 | 27.4 | 25.3 | 24.2 | 17.9 | 28.6 |
| **በክልል ደረጃ** | 15.5 | 15.7 | 19.3 | 16.5 | 17.0 | 20.0 |
| **ወንድ** | 8.0 | 8.9 | 12.6 | 10.8 | 11.3 | 10.8 |
| **ሴት** | 23.4 | 22.8 | 26.1 | 22.0 | 24.9 | 29.5 |

ምንጭ፡- CSA (THE 2020 & 2022 URBAN EMPLOYMENT UNEMPLOYMENT SURVEY)

**የዋጋ ግሽበት፡-** ከኢኮኖሚ ዕድገት በተጓዳኝ በመንግስት በትኩረት መሰራት ያለበት ጉዳይ የዋጋ ግሽበት ሲሆን ይህም በዋናነት በፍላጎት እና በአቅርቦት አለመጣጣም እንዱሁም በማምረቻ ወጪ መጨመር ምክንያት ሊከሰት ይችላል፡፡ በዚህም መሰረት በአገር ደረጃ የ2010 በጀት ዓመት የነበረው የዋጋ ንረት ምጣኔ 20.5 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ማለትም 33.3 በመቶ ደርሶ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ በ2016 በጀት ዓመት እና በ2017 ጥር ወር የተመዘገበ ተንከባላይ አማካይ የዋጋ ግሽበት እንደቅደም ተከተላቸው ወደ 26.6 በመቶ እና 15.5 በመቶ የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቷል፡፡ በ2017 ጥር ወር ላይ የተመዘገበው አገራዊ የዋጋ ግሽበት ሲታይ ምግብ ነክ ያልሆኑ 15.0 በመቶ እና ምግብ ነክ የሆኑ ሸቀጦች ደግሞ 15.8 በመቶ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡- ከ2010 - 2017 በጀት ዓመት የተመዘገበ አገራዊ ተንከባላይ ዓመታዊ አማካይ የዋጋ ግሽበት

| የበጀት ዓመት | የዋጋ ግሽበት ሁኔታ |
|---|---|

| | አጠቃላይ | ምግብ ነክ | ምግብ ነክ ያልሆኑ |
|---|---|---|---|
| **2010** | 10.6 | 11.7 | 11.0 |
| **2011** | 13.7 | 12.8 | 14.9 |
| **2012** | 16.2 | 19.2 | 12.8 |
| **2013** | 20.3 | 23.1 | 16.9 |
| **2014** | 27.3 | 32.4 | 20.7 |
| **2015** | 33.3 | 36.3 | 30.2 |
| **2016** | 26.6 | 28.1 | 24.3 |
| **2017** | 15.5 | 15.8 | 15.0 |

* እስከ ጥር ወር የ6 ወር አማካይ

*ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የተለያዩ ዓመታት መረጃዎች*

በተመሳሳይ በክልሉ የ2010 በጀት ዓመት የነበረው የዋጋ ንረት ምጣኔ 10.3 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ማለትም 33.1 በመቶ ደርሶ ነበር፡፡ ነገር ግን በ2016 እና በ2017 ጥር ወር እንደቅደም ተከተላቸው ወደ 31.9 በመቶ እና 18.6 በመቶ የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቷል፡፡ በ2017 ጥር ወር ላይ የተመዘገበው ክልላዊ የዋጋ ግሽበት ሲታይ ምግብ ነክ ያልሆኑ 15.7 በመቶ እና ምግብ ነክ የሆኑ ሸቀጦች ደግሞ 20.7 በመቶ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመላታል፡ ፡

ሠንጠረዥ 3፡- ከ2010 - 2017 በጀት ዓመት የተመዘገበ ክልላዊ ተንከባላይ ዓመታዊ አማካይ የዋጋ ግሽበት

| **የበጀት ዓመት** | **የዋጋ ግሽበት ሁኔታ** | | |
|---|---|---|---|
| | አጠቃላይ | ምግብ ነክ | ምግብ ነክ ያልሆኑ |
| **2010** | 20.5 | 16.4 | 25.2 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **2011** | 11.9 | 13.3 | 10.4 |
| **2012** | 19.9 | 23.7 | 15.6 |
| **2013** | 15.3 | 18.6 | 11.4 |
| **2014** | 32.9 | 35.9 | 29.2 |
| **2015** | 33.1 | 26.1 | 49.5 |
| **2016** | 31.9 | 34.4 | 28.7 |
| **2017** | 18.6 | 20.7 | 15.7 |

* እስከ ጥር ወር የ6 ወር አማካይ

ምነጭ:- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተለያዩ ዓመታት ዓመታዊ ሪፖርቶች

የዋጋ ግሽበት አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ከማክሮ ኢኮኖሚ አመላካቾች ውስጥ የሸቀጦች የዋጋ ንረት የገንዘብ የመግዛት አቅምን በማዳከም፣ ኢንቨስትመንትን በማቀጨጭ፣ ስጋቶችን በመጨመር፣ የምርት አቅርቦት ውድድርን በመቀነስ የሀገሪቱንም ሆነ የክልሉን ኢኮኖሚ በመፈታተን ላይ ይገኛል: : ተፈጥሯዊ የሆነው የዋጋ ግሽበት ሰው ሰራሽ በሆኑ ምክንያቶች ሊባባስ ይችላል። የእርስ በርስ ግጭቶችና የሰላም መደፍረስ፣ በምርት ግብዓት አቅርቦትና በምርት ስርጭቶች ላይ ከፍተኛ ችግርን ስለሚያስከትል ለዋጋ ግሽበት ትልቅ አስተዋጽዖ ነበራቸው። በሌላ በኩል የኮቪድ 19 መከሰት፣ አለም አቀፋዊ ሁኔታዎች እንድሁም ምርትን ሆን ብለው ያለአግባብ በመከዘን የአቅርቦት እጥረቱ እንድባባስ የሚሰሩ ነጋደዎችንና ህገ-ወጥ ደላሎችን መቆጣጠር ያለመቻልም የኑሮ ውድነቱ መባባስ ተጠቃሽ ምክንያቶች ነበሩ። በመሆኑም የኑሮ ውድነት በፍጥነት እያደገ በመምጣቱ ዝቅተኛ እና ቋሚ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች በመፈታተን ላይ ይገኛል።

በአንጻሩ ከቅርብ ጊዜ ወድህ የዋጋ ግሽበቱ እየቀነሰ የመምጣት አዝማሚያ እያሳየ የመጣ ሲሆን ለዚህም ከሚጠቀሱ ምክንያቶች መካከል በዋናነት ጥብቅ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች መተግበር፣ የግብርና ምርት ማሻሻል እና በአስተዳደራዊ ወጪዎች (ድጎማዎች) ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ናቸው።

በአጠቃላይ የዋጋ ንረትን ከመቀነስ አንጻር በአገር አቀፍ ደረጃ የተጀመሩ የተለያዩ ማሻሻያዎች ማለትም የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን በቀጣይ በተጠናከረ መልኩ ማስቀጠል የሚጠበቅ ሆኖ እንደ

ሀገርም ሆነ እንደ ክልል ግብርናውን ጨምሮ የአምራች ዘርፎችን ምርታማነት በማሳደግ የምርት አቅርቦትን ችግር መፍታት ተገቢ ይሆናሉ፡፡

## 1.3. ዞናዊ የዘርፎች ልማት አፈጻጸም እንደመነሻ

### 1.3.1.አምራች ኢንደስትሪ

የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት፣ የአካባቢ ጸጋን የለየ በራሪ ወረቀት በማዘጋጀት፣ የኤሌክተሮኒክስ ሚዲያዎች በመጠቀም ኢንቨስትመንቱን የማስተዋወቅ ስራ መስራት ተችሏል፡፡ የዞኑን ጸጋዎች በማስተዋዎቅ የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለማሳደግ በተመረጡና አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ኢንቨስት የሚያደርጉ 191 አቅምና ፍላጎት ያላቸዉን ባለሀባቶች ለመመልመል በእቅድ ተይዞ 454 (ከ100% በላይ) መመልመል የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ 191 ባለሃብቶች በተለያዩ ዘርፎች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ለማድረግ ታቅዶ 201 ባለሃብቶች ፈቃድ ማውጣት ችለዋል፡፡ ፈቃድ ባወጡ ባለሃብቶች የተመዘገበ ካፒታል 25ቢ ታቅዶ 14.8ቢ (59.2%) ተመዝግቧል፡፡

ለአምራች ኢንዱስትሪዎችና ለሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በሳይት ፕላንና በካርታ የተመላከተ 200 ሄ/ር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 363.015 ሄ/ር መፈጸም ተችላል፡፡ ከተዘጋጀው መሬት ለሁሉም ኢንዱስትሪ ቀጠና የሚሆን 100 ሄ/ር፣ ለሁለገብ ኢንዱስትሪ መንደር /ኢንዱስትሪ ፓርክ/ አገልግሎት የሚውል 90 ሄ/ር እና ከኢንዱስትሪ መንደርና ፓርክ ውጭ ለሚቀርቡ ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል 7.5 ሄ/ር መሬት ከሶስተኛ ወገን ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 112.1043 ሄ/ር፣ 59.368 ሄ/ር እና 52.7363 ሄ/ር እንደ ቅደም ተከተላቸው ነጻ ተደርጓል፡፡

ከማኑፋክቸሪንግ ውጭ ለሆኑ ፕሮጀክቶች 920 ሄ/ር መሬት በሳይት ፕላን ማዘጋጀት ታቅዶ 1507.8 ሄ/ር የተዘጋጀ ሲሆን በተመሳሳይ 789 ሄ/ር ከሶስተኛ ወገን ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 967.844 ነጻ ማድረግ ተችሏል፡፡ በግብርናው ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት የሚቀርቡ ፕሮጀክት በሳይት ፕላን የተመላከተ 224 ሄ/ር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 993.02 የተዘጋጀ ሲሆን 191 ሄ/ር መሬት ከሶስተኛ ወገን ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 565.084 ነጻ ማድረግ ተችሏል፡፡ በአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ዕፀ-ጣዕም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት የሚቀርቡ ፕሮጀክት በሳይት ፕላን የተመላከተ 718 ሄ/ር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 388.26 የተዘጋጀ ሲሆን 582 ሄ/ር መሬት ከሶስተኛ ወገን ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 388.26 ነጻ ማድረግ ተችሏል፡፡ በአገልግሎት ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት የሚቀርቡ ፕሮጀክት በሳይት ፕላን የተመላከተ 28 ሄ/ር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 126.54 የተዘጋጀ ሲሆን 16 ሄ/ር መሬት ከሶስተኛ ወገን ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 14.5 ነጻ ማድረግ ተችሏል፡፡

አምራች ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚቀርቡ 60 ፕሮጀክቶችን ለመገምገም ታቅዶ 63 የተገመገሙ ሲሆን ተገምግመው የሚያልፉ 35 ፕሮጀክቶች ታቅደው 40

ግምገማውን ማለፍ ችለዋል፡፡ ተገምግመው ካለፉት ውስጥ ለ15 ፕሮጀክቶች መሬት ለማስተላለፍ ታቅዶ ለ17 ፕሮጀክቶች 40.74 ሄ/ር መሬት ማስተላለፍ ተችሏል፡፡ ከአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ዉጭ ያሉ በሌሎች ኢንቨስትመንት የሚቀርቡ 27 ፕሮጀክቶችን ለመገምገም ታቅዶ 54 የተገመገሙ ሲሆን ተገምግመው የሚያልፉ 23 ፕሮጀክቶች ታቅደው 50 ግምገማውን ማለፍ ችለዋል፡፡ ተገምግመው ካለፉት ውስጥ ለ23 ፕሮጀክቶች መሬት ለማስተላለፍ ታቅዶ ለ18 ፕሮጀክቶች 16.5 ሄ/ር መሬት ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

22 የአምራች ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ እንክብካቤ ስርዓት የሚጠይቀውን ቅድመ ሁኔታ(EIA) እንዲያሟሉ ለማድረግ ታቅዶ 17 ያሟሉ ሲሆን የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ አፈፃፀም ማስገባትን በተመለከተ 22 መሬት የተሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ ለማስገባት ታቅዶ 19 (86.36%)፣ 10 ግንባታ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች ግንባታቸዉን እንዲያጠናቅቁ ታቅዶ 2 (20%) እና 5 ግንባታ ያጠናቀቁትን ወደ ማምረት እንዲገቡ ማድረግ ታቅዶ 2 (40%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከታለመለት አላማ ውጭ ለረጅም ጊዜ መሬት አጥረው የተቀመጡ 41 ፕሮጀክቶች ርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡

90 የመሰረተ ልማት ችግር ያለባቸውን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ጥያቄ ለመመለስ ታቅዶ 126 መመለስ ተችሏል፡፡ 77 የአምራች ኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 24 ኢንዱስትሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በዚህም 88.01 ሚሊዮን ብር ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 132.01 ሚሊዮን ብር ማስጠቀም ተችሏል፡፡

በአምራች ኢንዱስትሪዎች እና በግብርና ኢንቨስትመንት ከሚገኙ ምርቶች የሚገኝ የኤክስፖርት ገቢን ለማሳደግ በግብነት የተጣለ ሲሆን ምርታቸውን ወደ ውጭ ገበያ የሚልኩ ነባር አምራች ኢንዱስትሪ 3 በእቅድ የተያዙ ሲሆን 5 ኢንዱስትሪዎች ምርታቸውን እንድልኩ ተደርጓል፡፡ 9 ተኪ ምርቶችን ለመለየት ታቅዶ 8 የተለዩ ሲሆን ተኪ ምርት የሚያመርቱ 65 ኢንዱስትሪ ለመለየት ታቅዶ 169 በመለየት 7838 ቶን ምርት በእቅድ ተይዞ 1626 ቶን ማምረት ተችሏል፡፡ በዚህም ያዳኑት የውጭ ምንዛሬ መጠን 19.54 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማዳን ታቅዶ 43.83 ሚሊዮን ዶላር ማዳን ተችሏል፡፡

እንደ ዞን የስራ እድል ፈጠራውን ውጤታማ ለማድረግ የተሰራ ሲሆን የስራ ፈላጊወች ልየታ በተመለከተ ጠቅላላ 133,403 ታቅዶ 142,451 (106%) ስራ ፈላጊ ወጣቶች ተለይተዋል፡፡ በተመሳሳይ 133,403 ስራ ፈላጊዎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 147,297 (110.4%) ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ ስራ እድል ፈጠራ በተመለከተ እንደ ዞን ለ133,403 ስራ ፋላጊዎች ስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ

ለ142,378 (106.72%) ስራ ፈላጊዎች ስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡ የኢ/ዝ ምስረታን በተመለከተ 7574 ኢ/ዝ ለመመስረት ታቀዶ 7804 (103%) ተመስርቷል፡፡

አበዳሪ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ለ2297 አዳዲስ እና ነባር ኢንተርፕራይዞች የብር 310,346,561 የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ለ6120 ኢንተርፕራይዝ ብር 414790551 ማበደር ተችሏል፡፡ መደበኛ ብድር ማስመለስ 97,339,448 ታቅዶ 134,994,314.1 ብር (138.68%) እና ከተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር 85,135,730 ለመመለስ ታቅዶ 72,889,760.79 ብር (85.62%) እንድመለስ ተደርጓል፡፡

የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል እና ግንዛቤ በማሳደግ ብር 337,004,244 ለማስቆጠብ ታቅዶ 839071480.2 ብር ማስቆጠብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪ የዋልያ ማሽነሪ ሊዝ ፋይናንስ 37 ማሽን በማስጠቀም ለ15 ኢንተርኘራይዞችና ለ34 አንቀሳቃሾች የብር 1,917,118 የሚፈጅ ተሰራጭቷል፡፡

ለሸድ ግንባታ የሚሆን ገንዘብ ብር 160,077,743 ለመሰብሰብ ታቅዶ 63,722,647 (39.80%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ከመያድ በብር 56,695 ታቅዶ 14,133,675 (38.55%) ማገኘት ተችሏል፡፡ አዲስ የሚገነባ ሸድ 252 ታቅዶ 95 (37.69%) የተገነባ ሲሆን 1599 ኢንተርፕራይዝ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 641 (40.08%) ተጠቃሚ የተደረገ ሲሆን 7997 አንቀሳቃሽ ተቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 2203 (27.74%) ተጠቃሚ ተደርጓል፡፡

ለኢንተርፕራይዞች የማምረቻና መሸጫ ቦታ የለማ መሬት ከማዘጋጀት አንጻር 2,965 ሄ/ር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 2976.8757 ሄ/ር በመለየት 2167.1897 ሄ/ር (72.82[illegible]) ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል፡፡ በዚህም 2965 ኢንተርፕራይዝ እና 20061 አንቀሳቃሾች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 2341 (78.95%) ኢንተርፕርይዝና 31536 (ከ100% በላይ) አንቀሳቃሽ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ያለአግባብ የተያዙ 376 ሸድ ከሶስተኛ ወገን ለመንጠቅ ታቅዶ 425 ተለይቶ 405 (ከ100% በላይ) ማስመለስ የተቻለ ሲሆን በተለቀቁ ሸዶች 1860 ኢንተርፕራይዝ እና 9300 አንቀሳቃሽ ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ በእቅድ ተይዞ 296 (15.91%) እንተርፕራይዝና 1076 (11.56%) አንቀሳቃሽ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ያለአግባብ የተያዙ 488 ኮንቴኔር ከሶስተኛ ወገን ለመንጠቅ ታቅዶ 302 ተለይቶ 284 (58.19% በላይ) ማስመለስ የተቻለ ሲሆን በተለቀቁ ኮንቴነሮች 482 ኢንተርፕራይዝ እና 964 አንቀሳቃሽ ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ በእቅድ ተይዞ 232 (48.13%) እንተርፕራይዝና 347 (35.99%) አንቀሳቃሽ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በመንግስትና በግል ኮሌጆች የስልጠና ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ለማሳደግ በእቅድ ተይዞ የተሰራ ሲሆን በመደበኛ መርሃ ግብር ብቻ በመንግስት 1693 እና በግል 1162 ሰልጣኝ ለመቀበል ታቅዶ

በመንግስት 1140 (67.3%) እና በግል 1100 (94.6%) በድምሩ 2240 (78.5%) ሰልጣኝ በመቀበል ማሰልጠን ተችሏል፡፡

### 1.3.2. ዘመናዊ ግብርና

ግብርና በማክሮ ኢኮኖሚውም ሆነ በማይክሮ ኢኮኖሚው አይነተኛ ሚና የሚጫወት ዘርፍ በመሆኑ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እድገቱም ሆነ በዞናችን ለምንመራው ህዝብ የምግብ ዋስትና መረጋገጥ የአንበሳውን ድርሻ ይጫወታል፡፡ በመሆኑም በበጀት አመቱ እቅዳችን ትልቅ ድርሻ የነበረው ሲሆን ሰፊና የተቀናጀ ርብርብ በማድረግ በርካታ ተግባሮችን ያከናወንን ሲሆን ብዙ አበረታታች ውጤቶችም ተመዝግበዋል፡፡

**ኤክስቴሽን ኮሙንኬሽን፡-** በአድሱ የግብርና ልማት ቡድን አደራጅቶና አሰልጥኖ ወደ ስራ ለማስገባት ይቻል ዘንድ 14637 ልማት ቡድን ለማደራጀት ታቅዶ 16314 በማከናወን አፈጻጸሙን 111.5% ማድረስ የተቻለ ሲሆን በዚህ አደረጃጀት ውስጥ 439118 አባዋራና እማዋራ ለማካተት ታቅዶ 489044 በማካተት አፈጻጸሙን 114.4% ማድረስ ተችሏል፡፡ አ/አደሩን በሰርቶ ማሳያ ከማስተማር አኳያ በተለያዩ አመማራጮች 13240 ሰርቶ ማሳያ ለማዘጋጀት አቅደን 13725 ሰርቶ ማሳያዎችን ወይም የዕቅዳችንን 103.7% መስራት የተቻለ ሲሆን 35250 የአርሶ አደር በአል በማዘጋጀት በድግግሞሽ 1740840 አርሶ አደሮች እንድማሩበት ማድረግ ተችሏል፡፡ 2546176 አ/አደሮችን የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ 252302 አ/አደሮችን ወይም 99.3% መፈጸም ተችሏል፡፡ እንድሁም 11 የአ/አደር ማሰልጠኛዎችን ደረጃ ማሻሻል አቅደን 13 (118%) መፈጸም ተችሏል፡፡

**ሰብል ልማት፡-** እንደ ዞን 432168 ሄ/ር መሬት እርሻ በማረስ 14224614 ሚሊዮን ኩ/ል ምርት ለማምረት አቅደን 432168 ሄ/ር በዘር በመሸፈን 101% ማገናወን የተቻለ ሲሆን 13398827 ኩ/ል ወይም የእቅዳችንን 94% ማምረት ተችሏል፡፡ ይህንን ተግባር ውጤታማ ለማድረግ 194427 በመስመር መዝራትና 96833 ጥቁር አፈር ማጠንፈፍ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸማቸውም እንደ ቅደም ተከተላቸው 80%ና 121% ነው፡፡ በተመሳሳይ የሰብል ጥበቃና እንክብካቤ ተግባር 432168 ሄ/ር የተባይ አሰሳ (100%)፣ 25521 ሄ/ር ተባይ መከላከል (86%)ና 432124 ሄ/ር መደበኛ አረም ማረም 432346 ሄ/ር (100%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ የ2016/17 ምርት ዘመን አፈጻጸም ከ2015/16 ምርት ዘመን አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር 2948827 ኩ/ል (28%) የምርት ጭማሬ መኖሩን ያሳያል፡፡

መደበኛ ኮምፖስት 100279942 ሜ3፣ ቨርሚ ኮምፖስት 56022 ኩ/ል እና ባዮሳላሪ ኮምፖስት 43432 ሜ3 የተዘጋጀ ሲሆን አፈጻጸማቸውም እንደ ቅደም ተከተላቸው 116%፣ 82% እና 113% ነው፡፡ 25410 ኩ/ል ኖራ በማቅረብ 847 ሄ/ር በአሲዳማነት የተጎዳውን የእርሻ መሬት በኖራ ለማከም

ዕቅድ ተይዞ 7904 ኩ/ል ኖራ የቀረበ ሲሆን 7448 ኩ/ል ኖራ ጥቅም ላይ በማዋል ተችሏል። እንድሁም 221784 ሄ/ር መሬት በኮሞዲቲ ሰብሎች ለማደራጀት ታቅዶ 217784 ሄ/ር ወይም የዕቅዳችንን 98% በመፈጸም 358071 አ/አደሮች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል። ለዚሁ ተግባር አርሶ አደሮቹ 227375 ኩ/ል ምርጥ ዘር እንዳዘጋጁ ታቅዶ 256282 ኩ/ል ወይም የዕቅዳችንን 112% ተፈጻሚ ሆኗል።

**መስኖ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፡-** ጥቅል መስኖ ልማት 31895 ሄ/ር ታቅዶ 30486 ሄ/ር ወይም 95.6% መፈጸም የተቻለ ሲሆን የአድስ መስኖ 4149 ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ 3023 ሄ/ር ወይም ከእቅድ 72%፣ ነባር በስኖ ደግሞ 27746 ሄ/ር ለማልማት አቅደን 27463 ወይም 99% መፈጸም ተችሏል፡ ፡ በዚህም ከ1ኛ ዙር 2401307 ኩ/ል ምርት ለማገኘት ታቅዶ 1994333 ኩ/ል ምርት ተመርቷል። በ2ኛ ዙር መስኖ 8484 ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ 8538.52 ሄ/ር ወይም 100.6% የለማ ሲሆን ከዚህም 844921 ኩ/ል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ 965419 ኩንታል ወይም 114% ተሰብስቧል። በጥቅል በ1ኛና በ2ኛ ዙር 3246288 ኩ/ል ምርት ለማግኘት ታቅዶ 2959752 ኩ/ል ምርት ወይም 91.2% ማሳካት ተችላል። በተመሳሳይ ለፍራፍሬ ልማት 2258935 ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ 2049468 ወይም 90% መፈጸም ተችሏል። የበጋ ስንዴ ልማት ስንመለከት በመስኖ 21500 ሄ/ር፣ በበልግ 15000 ሄ/ር በድምሩ 36500 ሄ/ር መሬት ለማልማት አቅደን በመስኖ 20318 ሄ/ር ወይም 95% ያሳካን ሲሆን የበልጉን በዝናብ እጥረት ምክንያት ማሳካት አልተቻለም። ከዘራነው የበጋ ሰንደ 860000 ኩ/ል ምርት ለማገኘት ታቅዶ 718950 ኩ/ል ወይም የዕቅዳችንን 83.5% ማምረት ተችሏል።

**ተፈጥሮ ሃብት፡-** የተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ ተግባርን በተመለከተ 233.4 ሚ/ን ችግኝ ለማረምና ለመኮትኮት ታቅዶ 229.1 ሚ/ን ወይም 98.3% በማከናወን 53082.8 ሄ/ር የተከላ ቦታ መሸፈን የተቻለ ሲሆን በ2016/2017 ክረምት ከተተከሉ 233.4 ሚ/ን ችግኞች ውስጥ 168.5 ሚ/ን ወይም 72.2% በጽድቀት መመዘኛ መስፈርቱ መሰረት የጸደቀ ነው። የተከላ ቦታ ልየታ ለደንና አግሮፎረስትሪ 29675 ሄ/ር ለመለየት ተቅዶ 29527 ሄ/ር ወይም 99.5% እና ለደን የX-Y ኮኦርዲኔት መረጃ ተሰብስቦለት ካርታ የሚዘጋጅለት 7378 ሄ/ር መሬት ለመለየት ታቅዶ 9070.3 ሄ/ር ወይም 122.9% ተፈጻሚ ሆኗል። የችግኝ ጣቢያ እንቅስቃሴ በተመለከተ 24980 ችግኝ ጣቢያ ወደ ስራ ለማስገባት ታቅዶ 25339 ወይም 101.4% የተፈጸመ ሲሆን 180.1 ኩ/ል የደንና የመኖ፣ 228 ኩ/ል የፖሊቲን ትዩብ እና 11959.5ሜ/ኩ ኮምፖስት ማቅረብ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸማቸውም እንደቅደም ተከተላቸው 130%፣ 135% እና 91% ነው። በዚሁ መሰረት ለደን 156 ሚ/ን፣ ሁለገብ የመኖ ችግኝ 55 ሚ/ን በድምሩ 211 ሚ/ን ለማፍላት ታቅዶ ለደን 152 ሚ/ን (97.2%)፣ ሁለገብ የመኖ ችግኝ 53 ሚ/ን (95.3%) በድምሩ 204.81 ሚ/ን ወይም 97% ማፍላት ተችሏል። ከዚህ ውስጥ በፕላስቲክ ችግኝ

ማፍላት 15.8 ሚ/ን ታቅዶ 19.78 ሚ/ን ወይም 125.6% ማሳካት ተችሏል፡፡ ለ2017/18 ተከላ 211 ሚ የችግኝ ጉድጓድ ለማዘጋጀት ታቅዶ 187.1 ሚ ወይም 88.7% ማሳካት ተችሏል፡፡

የተፋሰስ ልማት በተመለከተ በነባር በ1426 ተፋሰሶች 846367 ሄ/ር፣ በአዲስ በ7 ተፋሰሶች 3494 ሄ/ር በድምሩ በ1433 ተፋሰሶች 849861 ሄ/ር ወደ ልማት የሚገቡ ለመለየት ታቅዶ ነባር በ1437 ተፋሰሶች 852928.6 ሄ/ር፣ አዲስ በ9 ተፋሰሶች 4220.3 ሄ/ር በድምሩ በ1446 ተፋሰሶች 857148.9 ሄ/ር ወይም 100.9% ልየታ የተካሄደ ሲሆን በ1283 ተፋሰሶች ወደ ልማት በማስገባት 587579 ህዝብ በ25 ቀናት በማሳተፍ በድግግሞሽ 14689475 ጉልበት ስራ ላይ ለማዋል ከታቀደው 14426662 (98%)ቱን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ በዚህም ከተለየው 51627ሄ/ር መሬት ውስጥ 53031ሄ/ር ወይም 102.7%ቱን በፊዚካል ስራ የተሸፈነ ሲሆን 51627ሄ/ር መሬት በተለያዩ የስነ-አካላዊ ስራዎች ለመሸፈን በእቅድ ተይዞ 53031 ሄ/ር (102.7%) ማከናወን ተችሏል፡፡ የተፋሰስ ተቋማት ግንባታ በተመለከተ 132 ተፋሰሶችን ህጋዊ ሰውነት ለመስጠት አቅደን 152 ተፋሰሶች ወይም 115.2% መፈጸም ችለናል፡፡

**ግብዓት አቅርቦት፡-** ከግብአት ስርጭት አንጻር 631476 ኩ/ል ማዳበሪያ ለአርሶ አደሮች ለማቅረብ ታቅዶ 504461 ኩ/ል ማቅረብ የተቻለ ሲሆን 423951 ኩንታል በማሰራጨት አፈጻጸሙ ከእቅዱ 67% ከአቅርቦቱ 89% ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 27596 ኩ/ል ማዳበሪያ ለመስኖ ማሰራቸት ተችሏል፡፡ 13200 ኩ/ል ስንዴ ምርጥ ዘር ለማቅረብና ለማሰራጨት ታቅዶ 12224 በማቅረብ 5097 ኩንታል ተሰራጭቷል፡፡ በተመሳሳይ 24500 ኩንታል ኖራ ለማቅረብ ታቅዶ 8273 ኩንታል የቀረበ ሲሆን 7838 ኩ/ል ወይም 95% እና ህያው ማዳበሪያ 21153 ሳቼት ለማቅረብና ለማሰራጨት ታቅዶ 21150 የቀረበ ሲሆን 4043 ማሰራጨት ተችሏል፡፡ የቴክኖሎጅ ስርጭትን ስንመለከት ሞተርፓምፕ 882 ታቅዶ 516፣ ትራክተር 18 ታቅዶ 13፣ ጸረ ተባይ መድሃኒት 16120 ሊትር ታቅዶ 16120 ሊ/ር ማሰራጨት ተችሏል፡፡

### 1.3.3. እንስሳትና አሳ ሀብት ልማት

**የእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ምርት፡-** የእንስሳት ተዋጽኦን ለማሳደግ በአነስተኛ ስፔሻላይዜሽን የወተት ከብት እርባታ 53 አርቢዎችን ለማሳተፍ ታቅዶ 58 አርቢዎችን፣ በተሻሻለ የቤተሰብ የወተት ከብት እርባታ 33,776 አርቢዎች ለማሳተፍ ታቅዶ 13,909 አርቢዎችን ማሳተፍ የተቻለ ሲሆን 249544.7 ቶን ወተት ለማገኘት ታቅዶ 211945 ቶን ወይም 85% መፈጸም ተችሏል፡፡ 1,716,540 እንስሳት ለማድለብ ታቅዶ 1739610 (101%) ማድለብ የተቻለ ሲሆን ከታቀደው 58,889 ቶን ስጋ 60071 ቶን ወይም 102% ማሳካት ተችሏል፡፡ በሞዳሊቲ እና ስፔሻላይዜሽን 704998 ዶሮ ለማሰራጨት ታቅዶ 602955 (86%) እና ከ12 እስከ 25 የተሻሻሉ ዶሮዎች 129102 ለማሰራጨት ታቅዶ 208410 (161%) በማሰራጨት በአመቱ ከታቀደው 81 ሚ እንቁላል 86 ሚ በማምረት

የእቅዱን 106% መፈፀም ተችሏል፡፡ ወደ ተሻሻሉ ቀፎዎች 7151 (87.9%) ህብረ ንብን ማዛወር እና 16735 (100%) ህብረ ንብ ማባዛት የተቻለ ሲሆን በአመቱ ይገኛል ተብሎ ከታቀደው 3145 ቶን ማር 3015 ቶን (95.9%) ማገኘት ተችሏል፡፡ 20 የአሳ ኩሬ (22.7%) በማዘጋጀትና በግድቦችና በአሳ ኩሬዎች 95,000 (119%) የአሳ ጫጩት በመጨመር በአመቱ ለማመረት ከታቀደው 1622 ቶን አሳ 1156.61 ቶን ወይም 71.3% ማምረት ተችሏል፡፡ ከዚህም 567.7 ቶን ስጋ ለማምረት ታቅዶ 404.81 ቶን (71.31%) ተመርቷል፡፡ ቆዳና ሌጦ ምርት 1,389 470 ታቅዶ 1,421,638 (102%) መፈጸም ጸችለዋል፡፡

**መኖ ልማት፡-** ከመኖ ልማት አንጻር ልቅ ግጦሽን ማስቀረት 439,218 ሄ/ር ታቅዶ 377,689 ሄ/ር (85%)፣ የመኖ ችግኝና ቁርጥራጭ ማዘጋጀት 164.2ሚ ታቅዶ 96.71ሚ (71%)፣ የተቀነባበረ መኖ ማቅረብ 9133.25 ቶን ታቅዶ 9480.15 (103%)፣ ገፈራ ማዘጋጀት 138.6 ቶን ታቅዶ 149 ቶን (124%)፣ 1647 ሄ/ር በመስኖ መኖ ለማልማት ታቅዶ 3067.9 ሄ/ር (186%)፣ 6583.879562 በቶን የሰብል ተረፈ ምርትን በዩርያ ለማከም ታቅዶ 3209.78 (48.7%) እንድሁም 136.147305 ሚ የመኖ ችግኝና ቁርጥራጭ ለማዘጋጀት ታቅዶ 96.7153 ሚ (71.03%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን በአጠቃላይ ከሁሉም የመኖ ምንጮች 3.96 ሚ/ቶን ደረቅ መኖ ለማምረት ታቅዶ 3.97 ሚ/ቶን በማምረት የእቅዱን 100.2% በመፈፀም ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

**ዝርያ ለማሻሻል፡-** የእንስሳት ዝርያ ለማሻሻል 59453 ላሞች ለማዳቀል ታቅዶ 32355 (54%) በማዳቀል ይወለዳሉ ተብሎ ከታቀደው 23199 ጥጆች 18154 ወይም 78%፣ በአዋሲ አውራ በግ 62900 ለማዳቀል ታቅዶ 68688 (109%) እንድሁም 929709 የአንድ ቀን ጫጩት ለማቅረብ ታቅዶ 564212 (60.7%) ማሳካት ተችሏል፡፡

**የእንስሳት ጤና፡-** ከእንስሳት ጤና አንጻር ክትባትን በተመለከተ የአመቱ እቅድ 7,176,198 ሲሆን ክንዉን 6,952,460፣ ቅድመ መከላከል ህክምናን በተመለከተ እቅድ 3,262,699 ሲሆን ክንዉን 4,125,554 እንድሁም የፈዉስ ህክምናን እቅድ 1,233,071 ሲሆን ክንዉን 717,442 ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ኦዲት አግልግሎት 175 ታቅዶ 182 (104%)፣ ከአገልግሎት ክፍያ 2,400,000 ታቅዶ 1,983,166 (96%) እንድሁም የላብራቶሪ አገልግሎትን በተመለከተ 127,048 ታቅዶ 59,126 (47%) ተፈጻሚ ሆኗል፡፡

### 1.3.4. ህብረት ስራ ማህበራት

**ሪፎርም ትግበራን በተመለከተ፡-** የተቋሙን የሪፎርም ስራዎችን ከመፈጸም አንጻር ሪፎርሙ የሚያተኩረው ደረጃ ፍረጃ፣ ሰራተኛ ግምገማ፣ የሰራተኛ ድልድል፣ የማዋሀድና ማፍረስ ስራዎችን ማከናወን ሲሆን በመ/ማኀበራት የደረጃ ፍረጃ 217 ታቅዶ 249 (114%)፣ ሰራተኞች አመራራቸውን

እንድገመግሙ ማድረግ 321 ታቅዶ 433 (134%) መፈጸም የተቻለ ሲሆን በዩኑዬን ደረጃ ደግሞ የአመራርና ቅጥር ሠራተኛ 100% መገምገም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ተጠናክረው ሊቀጥሉ የማይችሉ 163 ማኅበራትን ህጉን ጠብቆ ለማፍረስ በአመቱ ታቅዶ 174 (106%) ማከናወን መቻሉ እና ሰራተኛ ድልድል በአመቱ 242 ዕቅድ ተይዞ 278 (114%) መፈፀሙ የሚሉትን ማከናወን ተችሏል፡፡

**ማደራጀት፡-** 201 አዲስ ኅብረት ስራ ማኅበራቶችን ለማቋቋም በዕቅድ ተይዞ 312 (100%) በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡ 464 መሰረታዊ ማኀበራት በየወሩ ሂሣባቸው እንዲሰራላቸው በእቅድ ተይዞ 397 (86%) እና 9860 አባላት ማፍራት በዕቅድ ተይዞ 29501 (100%) በላይ መፈፀም የተቻለ ሲሆን ካፒታል ማሣደግ 13344573 ብር በዕቅዱ ተይዞ 48894672 (100%) በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡ በዩኒዬንና በመሰረታዊ ማህበራት ደረጃ 100% ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ መቻሉ እና 118 ቅጥር ሰራተኛ ለመቅጠር ታስቦ 130 ከ100% በላይ መፈፀም መቻሉ የሚሉት የህብረት ስራ ማህበራትን ከማቋቋምና ከማደራጀት አኳይ የተከናመኑ ተግባሮች ናቸው፡፡ በዩኒዬንና በመሰረታዊ ማህበራት ደረጃ ካፒታል ማሳደግ 17230889 ብር በእቅድ ተይዞ 24,003,010.40 ብር ወይም ከ100% በላይ መፈጸሙ፣ መደበኛ ቁጠባ ማሰባሰብ 15704328 ብር በእቅድ ተይዞ 15,703,183.58 ብር (100%) መፈጸሙ፣ መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ ማሰባሰብ 414659613 ብር በእቅድ ተይዞ 616,386,751.48 ብር በማስቀጠብ ከ100% በላይ መፈጸሙ እና የዘመኑ ብድር ማስመለስ ብር 237535123 በእቅድ ተይዞ 214,121,342.67 ብር (90%) መፈጸሙ የሚሉት ካፒታል ለማሳደግ የተከናወኑ ተግባራት ናቸው፡

**ግብይት፡-** ገባያ ማረጋጋት በተመለከተ 9,244 ኩ/ል የተለያዬ የግብርና ምርት በማቅረብ ገበያ ለማረጋጋት ታቅዶ 30425 ኩ/ል በማቅረብ ከ100% በላይ መፈጸሙ፣ 129,882,520 ብር የሚያወጣ የኢንዱስትሪ ምርት ለማቅረብ ዕቅድ ተይዞ የ130,205,215 ብር የሚያወጣ የኢንዱስትሪ ምርት ማቅረብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ መሆኑ እና ለተማሪ ምገባ የሚውል 112712 ኩ/ል እህል በዩኔኖች በኩል እድቀርብ መደረጉ የሚሉት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዩኒየን ደረጃ የግብይት ፋይናንስ ትስስር መፍጠር 32 ሚሊየን ብር በእቅድ ተይዞ 26 ሚሊየን ብር 81.25% መፈጸሙ፣ በአመልድ ኢትዮጵያ /መያ/ ፕሮጀክት አስተባባሪነት ከአባይ ባንክ የተገኘ ብድር ብር 41 ሚ በማገኘት ለወጣት ስራ እድል ፈጠራ መዋሉ እና የሂሳብ ምርመራ የኦድት አገልግሎት እንድሰራላቸው እቅድ ከተያዘላቸው 557 መሰረታ ማህበር 588 (106%) የኦድት አገልግሎት መስጠት መቻሉ የሚሉት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

**የገንዘብ ብድርና ቁጠባ፡-** በገንዘብ ቁጠባ የአባላትን ሽፋን ማሳደግ እቅድ 11784 ተይዞ 12493 (106%) መፈጸም የተቻለ ሲሆን 305020738 ብር ብድር ለማሰራጨት ታቅዶ 356,907,164 ብር (103%) መፈጸሙ፣ ከዘመኑ ብድር 204655363.23 ብር ለማስመለስ ታቅዶ 269,261,933.73 ብር በማስመለስ አፈጻጸሙን ከ100% በላይ ማድረስ መቻሉ፣ የብድር የህይወት መድህን ሽፋን አገልግሎት

መስጠት የመአቱ እቅድ 114393336.58 ብር ተይዞ በክንውን ደረጃ 262,357,043 ብር በማከናወን አፈጻጸሙን 229% በማድረስ 5226 ግለሰብ አባላት የብድር መድህን ሽፋን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ የሚሉት የገንዘብና ቁጠባ የአባላት ሽፋን ከማሳደግ አንጻር የተከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡ የገንዘብ እና ቁጠባ የግብይት ትስስር መፍጠርን በተመለከተ በመሰረታዊ ህብረት ስራ የግብይት ፋይናንስ ትስስር መፍጠር 16250000 ብር እቅድ ተይዞ 35,398,250.00 ብር ብድር በማቅረብ ከ100% በላይ መደረሱ እና የዩኒየን አባል ማድረግ የአመቱ እቅድ 9 ተይዞ 102 በመፈጸም ከ100% በላይ መከናወኑ የሚሉትን መፈጸም ተችሏል፡፡

## 1.3.5.ማዕድን ሀብት

ፈቃድ አሰጣጥን በሚመለከት በአነስተኛ ኮንስትራክሽን ማዕድናትና በባህላዊ ማዕድን ስራ 400 ፈቃዶችን ለመስጠት ታቅዶ 325 (81.25%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን ከማዕድን ስራ ፈቃድና ሌሎች ክፍያዎች 7,781,199 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 11,944,342.07 ብር (153.5%) መሰብሰብ ተችሏል፡ እሴት ያልተጨመረበት 12,798 ኪ.ግ፣ እሴት የተጨመረበት 2380 ኪ.ግ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ዕቅድ ተይዞ እሴት ያልተጨመረበት 30674.2 ኪ.ግ (100%) እሴት የተጨመረበት ደግሞ 1743.8 ኪ.ግ (73.27%) ተከናውኗል፡፡ ከውጭ አገር ይገባ የነበረ 56.32 ቶን የድንጋይ ከሰል በአገር ውስጥ በማምረት እና በመተካት 8,222.72 USD የውጭ ምንዛሬን ማዳን ተችሏል፡፡ እንዲሁም ለውጭ ገበያ የሚቀርብ የኦፓል ሽያጭን በተመለከተ እሴት ያልተጨመረበት ኦፓል ሽያጭ በብር 12,797,640፣ እሴት የተጨመረበት ኦፓል ሽያጭ በብር 11,900,040 ለመሰብሰብ ዕቅድ ተይዞ እሴት ያልተጨመረበት ኦፓል ሽያጭ በብር 14,922,150 (›100%)፣ እሴት የተጨመረበት ኦፓል ሽያጭ በብር 4,061,850 (34.13%) ማገኘት ተችሏል፡፡

በባለፈቃዶች በቁርጥ ዋጋና በነፃ የመጠቀም መብት ባላቸው የተመረቱ የኮንስትርክሽን ማዕድን ምርት መጠን በሜትር ኩብ ዕቅድ 648,994 ሲሆን ክንውን 801,048.07 (123.43%) ተፈፀሟል፡፡ በማዕድን ልማት ስራ የተጎዱ የፈቃድ ቦታዎችን ወደ ነበረው ይዞታቸው 100% እንዲመለሱ ከማድረግ አንፃር 288 ሄ/ር ታቅዶ 81.95 ሄ/ር (28.45%) የተፈጸመ ሲሆን በችግኝ መሸፈን ሥራ ማከናወን 160 ታቅዶ 65.54 ሄ/ር (40.96%) ማከናወን ተችሏል፡፡

## 1.3.6.ትምህርት

በሀገራችን የተጀመረው ለውጥ ዘላቂነቱ አስተማማኝ እንዲሆን ለሁሉም የልማት ሴክተሮች መሰረት የሆነውን የተማረ የሰው ኃይል ከማፍራትና ጥሩ የአገር ተረካቢትውልድ ከማፍራት አንፃር ትልቅ ሚና ያለውን የትምህርት ሴክተር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ይገኛል፡፡

ፋይናንሻል ግብዓት ማሟላትን በተመለከተ 8,938,164.00 ብር የተማሪዎች ነፍስ ወከፍ በጀት እንድመድቡ የተደረገ ሲሆን የተመደበውን በጀት ለሁሉም ት/ቤቶች ከማስራጨት አንጻር ወረዳዎች የጥሬ ገንዘብ እጥረት አለብን በሚል ምክኒያት ምንም ሳያሰራጩ መክረም እንዳለም ተገምግሟ፡፡ የህብረተሰብ ተሳትፎን በማሳደግ የትምህርት ተቋማትን ከመደገፍ አንጻርም በጉልበት ብር 207,506,251.39፣ በቁሳቁስ ብር 125,184,298.41፣ በጥሬ ገንዘብ ብር 149,450,041.04 በድምሩ ብር 482,140,590.84 የሚገመት አስተዋጽኦ ህብረተሰቡ እንድያበረክት ታቅዶ በጉልበት ብር 185,392,512.90 (89.34%) በቁሳቁስ ብር 98,369,556.00 (78.57%) በጥሬ ገንዘብ ብር 130,856,789.47 (87.5%) በድምሩ ብር 414,618,858.37 (85.99%) መፈጸም ተችሏል፡፡ በዚህ ተግባር የወረዳዎች አፈጻጸም በ2.1% እና 143.1% መካከል የአፈጻጸም ልዩነት የታየበት ነው፡፡

ከትምህርት መሣሪያዎች አቅርቦት አንጻር በአዲስ የቀረቡ ጥቁር ሰሌዳዎች እቅድ 953 ሲሆን ከንውን 524 (55%)፣የተጠገኑ ጥቁር ሰሌዳዎች ዕቅድ 2,936 ሲሆን ክንውን 3,028 (103%) ነው፡፡ በአዲስ የቀረበ ኮምባይንድ ደስክ እቅድ 3791 ሲሆን ክንውን 2,242 (59.1%)፣ የተጠገነ ኮ/ደስክ እቅድ 11571 ሲሆን ክንውን 9,007 (77.8%) ነው፡፡ አዲስ የተገዙ ማጣቀሻ መጽሃፍት እቅድ 13,547 ሲሆን ክንውን 6,985 (51.6%)፣ አዲስ የተገዙ ሳይንስ ኪት እቅድ 147 ሲሆን ክንውን 7 (4.8%) ነው፡፡ በአጠቃላይ ከመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች የቁሳቁስ አቅርቦት አፈጻጸም ከጥቁር ጥቁር ሰሌዳ ውጩ ያሉ አፈጻጸሞች ዝቅተኛ ናቸው፡፡ የቤተ ሙከራ የተሟላላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሁለገብ ቤተሙከራ ክፍል ያላቸው ት/ቤቶች ብዛት 862 (71.2%)፣ ሳይንስ ኪት ያላቸው ብዛት 872 (72%)፣ የሳይንስ ትምህርት በቤተ-ሙከራ አስደግፌው የሚሰጡ ብዛት 521 (68.6%) ናቸው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሶስቱም ሳይንሶች የተለያዩ ክፍሎች ያላቸው ብዛት 46 (67.6%)፣ ሁለት ቤተሙከራ ክፍሎች ያላቸው 17 (25%) አንድ ቤተ ሙከራ ክፍል ያላቸው 5 (7.4%) ሲሆኑ በትክክክል የተደራጀ አፓራተስ እና ኬሚካል ያላቸው ብዛት 41 (60.3%) ያህሉ ብቻ ናቸው፡፡

**የትምህርት ተሳትፎና ውስጣዊ ብቃት አፈጻጸም፡-** በ2017 ዓ.ም 117,730 የቅድመ-አንደኛ ተማሪዎችን ለመመዝገብ ታቅዶ 95,481 ማለትም የእቅዱን 81.1 በመቶ መፈጸም ተችሏል ከተመዘገቡት ውስጥም 56043 ማለትም 58.7 በመቶ ያህሉ ብቻ የትምህርት ዘመኑን ያጠናቀቁ ናቸው፡፡ በቅድመ አንደኛ ጥቅል ተሳትፎ እድገት በመቶኛ 2016 ዓ.ም 37.88 በመቶ የነበረው በ2017 በጀት ዓመት 38.24 በመቶ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ በዚህም 0.36 በመቶ ጭማሪ ያሳየ ቢሆንም በአመቱ ሊደረስበት ከታቀደው አንፃር ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡

502,775 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ተማሪዎችን ለመመዝገብ ታቅዶ 315,601 ወይም 62.77 በመቶ የእቅዱን መመዝገብ ተችሏል፡፡ ከተመዘገቡት የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች ውስጥ በአመቱ

መጨረሻ በመማር ላይ የነበሩት 204326 ማለትም 64.7 በመቶ ያህሉ ናቸው፡፡ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ጥቅል ተሳትፎ እድገት በመቶኛ 2016 ዓ.ም 51.1 በመቶ የነበረው በ2017 በጀት ዓመት 44.83 በመቶ ነው፡፡ በዚህም 6.27 በመቶ መቀነስ ያሳየ ሲሆን በአመቱ ሊደረስበት ከታቀደው 71.42 በመቶ አንፃር በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት 148,082 የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎችን ለመመዝገብ ታቅደ መፈጸም የተቻለው 41,028 ወይም የእቅዱን 27.7 በመቶ ብቻ ነው፡፡ ከተመዘገቡት የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ውስጥ 32111 (78.27 በመቶ) የሚሆኑት የትምህርት ዘመኑን ያጠናቀቁ ናቸው፡፡ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ጥቅል ተሳትፎ በመቶኛ 2016 ዓ.ም 18.45 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2017 ዓ.ም ከተቀመጠለት ግብ በከፍተኛ ሁኔታ የራቀና ከባለፈው ዓመት 5.59 በመቶ ቀንሶ 12.86 በመቶ ነው፡፡

ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ከዞኑ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በተግባር ከሚገኝ ልምድ እና በመንግስትና በሕዝብ ትብብር በየደረጃው ይበልጥ የተደራጀና የተቀናጀ እንዲሆን ለማድረግ መልካም ጅምሮች የታዩ ሲሆን በ 2017 በጀት አመት የተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ተሳትፎ ቁጥር ወደ 88,929 ለማድረስ በእቅድ ተይዞ ከተመዘገቡት 50,628 ጎልማሶች ውስጥ 5,431 የሚሆኑ ጎልማሶች (6.1 በመቶ) የትምህርት እድሉን አግኝተዋል፡፡

ከ1ኛ -12ኛ ክፍል ከተመዘገቡት 356,629 ተማሪዎች መካከል 236,437 ተማሪዎች 66.3 በመቶ የሚሆኑት ተማሪዎች ብቻ እስከ በጀት አመቱ ማጠናቀቂያ ድረስ በመማር ላይ ያሳለፉ ሲሆን ከተመዘገቡት ተማሪዎች መካከል 120,192 ተማሪዎች የትምህርት ዘመኑን ሳያጠናቅቁ አቋርጠዋል፡ ፡ በመሆኑም የማቋረጥ ምጣኔው 33.7% አሻቅቧል፡፡ ይህ መረጃ የሚያሳየዉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የተመዘገበ ተማሪ በመማር ላይ እንዳልሆነ የሚያሳይ ሲሆን አቋራጭን ለመቀነስ ከተያዘው እቅድ አንጻር አፈጻጸሙ እጅግ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

**የትምህርት ጥራትና ፍትሀዊነት አፈጻጸም፡-** የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፓኬጅ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በመምህራን ልማት ፕሮግራም፣ በአመራርና አስተዳደር ፕረግራም እና በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ያካተተ ከጥራት ጋር የተያያዙ ግብአቶችን፣ ሂደቶችንና ውጤቶችን የማሻሻል ስራ ታሳቢ አድርገው እየተተገበሩ የሚገኙ ናቸው፡፡ ከመምህራን ልማት አንጻር በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ተከታታይ የሙያ ማሻሻል ኮርስ የሚወስዱ መምህራን ድርሻ 2016 ዓ.ም ከነበረበት 95.5% በ2017 የትምህርት ዘመን መጨረሻ ወደ 100% እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተከታታይ የሙያ ማሻሻል ኮርስ የሚወስዱ መምህራን 2016 ዓ.ም ከነበረበት 96.4% ወደ 100% ለማድረስ ታቅዶ በቅደም ተከተል 76.5% እና 92.3% ለማድረስ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከትምህርት አመራር ልማት አንጻር በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ተከታታይ የሙያ ማሻሻል ኮርስ የሚወስዱ ር/መምህራን ድርሻ 2016 ዓ.ም ከነበረበት 95.2% በ2017 መጨረሻ ወደ

100% ለማድረስ፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተከታታይ የሙያ ማሻሻል ኮርስ የሚወስዱ ር/መምህራን 2016 ዓ.ም ከነበረበት 97% ወደ 100% ለማድረስ ታቅዶ በቅደምተከተል 69.4% እና 85.4% ለማድረስ ጥረት ተደርጓል፡፡

የትምህርት ጥራትና ተገቢነት በተመለከተ በ2017 በጀት አመት የ8ኛና 6ኛ ክፍል ፈተና ተፈታኝ ተማሪዎችን በበይነ መረብ እንድመዘገቡ ተደርጓል፡፡ የ6ኛ ክፍል መፈተን ከነበረባቸው 596 ት/ቤቶች እና 23,026 ተማሪዎች ውስጥ በ596 ት/ቤቶች 20,821 (90.4%) ተማሪዎችን ያስፈተን ሲሆን የ8ኛ ክፍል መፈተን ከነበረባቸው 426 ት/ቤቶች እና 23,675 ተማሪዎች ውስጥ በ426 ት/ቤቶች 21,865 (92.4%) ተማሪዎችን አስፈትነናል፡፡ ከተማሪ ውጤት አንጻርም ፈተና ላይ ከተቀመጡት የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ 16804 (65.67%) የሚሆኑት ተማሪዎች 50% በላይ ውጤት የስመዘገቡ ናቸው፡ ፡ አጠቃላይ የማሳለፍ ምጣኔውም 74.5% መሆኑን ያሳያል፡፡ የ8ኛ ክፍል ፈተና ላይ ከተቀመጡ ተማሪዎች ውስጥ 14311 ማለትም 40.45% የሚሆኑ ተማሪዎች 50% በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ናቸው፡፡ አጠቃላይ የማሳለፍ ምጣኔም 65.8% ነው፡፡

ከትምህርት ፍትሀዊነት አንጻር የጾታ ምጥጥን አንዱ የትምህርት ፍትሀዊነት ማረጋገጫ መንገድ ነው፡፡ የትምህርት ማህበራዊ ደህንነቱና ፍትሃዊነቱ የተረጋገጠ መልካም መስተጋብር ያለዉ ዜጋ እንዲኖር ለማስቻል በትምህርት ላይ እኩል የጾታ ተሳትፎ እንዲኖር በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ነው፡ ፡ ከ9-12ኛ ክፍል ጥቅል ቅበላን መሰረት ያደረገ ጾታዊ ምጥጥን በ2016 ዓ.ም ከነበረበት 1.3 ጾታዊ ምጥጥን ወደ 1.58 ከፍ ያለ ነዉ፡፡ ከ1-8ኛ ክፍል ንጥር ቅበላን መሰረት ያደረገ ጾታዊ ምጥጥን በ2016 ዓ.ም 1.1 የነበረው ጾታዊ ምጥጥን በ2017 በጀት ዓመት 1.05 መድረስ ችሏል፡፡

### 1.3.7. ጤና

**የእናቶች ጤና፡-** የእናቶችን ጤና ለማሻሻል ግብኣት ማሟላት፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናወች በመንግስትና በአጋር አካላት በሰፊው እንድሰጥ ማድረግ፣ በየቀበሌው የነፍሰጡር እናቶች በመለየት ኮንፈረንስ ማካሄድ፣ በ7 ጤና ጣቢያ የቀዶ ህክምናና በ31 ጤና ጣቢያወች የአልትራሳውንድ ምርመራ በጤና ጣቢያወች ማስጀመር፣ የአልትራሳውንድ ምርመራ out reach ጤና ኬላዎች መስራት፣ 98 የሚሆኑ የእናቶች ማቆያዎችን ከተንከባካቢ ጋር ወደ ተግባር በማስገባት 12,486 እናቶች የመውለጃ ጊዜያቸው ሲደርስ ቀድመው መጥተው አርፈው እንድወልዱ ማድረግ የሚሉትን ተግባራት በትኩረት ይዞ ማከናወን የተቻለ ሲሆን በተጨማሪም በማህበረሰብ ተሳትፎ ከ7,412,348 ሚልዮን ብር በላይ እና 144 ኩንታል እህል ለእናቶች ማቆያ ምግብነክ እና ምግብ ነክ ላልሆኑ ግብአቶች እንድሁም ለአምቡላንስ ነዳጅና ጥገና የሚውል 29,071,148 ብር መሰበሰብና ችግሩን ለመፍታት ማህበረሰቡን ማሳተፍ ተችሎል፡፡

የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት አንጻር 616,102 እናቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 604,093 (98.1%) እናቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ 94,254 ነፍሰጡር እናቶችን በቅድመ ወሊድ አንድ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ 83,285 (88.4%)፣ 89,019 ነፍሰጡር እናቶች የቅድመ ወሊድ ክትትል 4 ጊዜ እንዲያገኙ ለመስራት ታቅዶ 75,749 (85.1%) እንድሁም በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት 87,970 ነፍሰጡሮች ለማዋለድ በእቅድ ተይዞ 66,566 (75.7%) መፈጸም ተችሏል፡፡ በህይወት የሚወለዱትን 100% የልደት ማሳወቂያ ለመስጠት የታቀደ ሲሆን በህይወት ከተዋለዱት 66,365 ህጻናት 65,895 ማሳወቂ የተሰጣቸው ሲሆን አፈጻጸሙ ደግሞ 99.3% ነው፡፡ ከወሊድ በኂላ በ7 ቀን ውስጥ የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት 94,255 ወላዶች አገልግሎቱን ለመስጠት ታቅዶ 76,624 (81.3%) መፈጸም ተችሏል፡፡

**የህጻናት ጤና አገልግሎትን ማሻሻል፡-**ከአንድ አመት በታች ኀጻናት 96,648 ሶስተኛውን የፔንታቫለንት ክትባት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 99,199 (102.6%)፣ የመጀመሪያ ዙር የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት ለ96,648 ህጻናት ለመስጠት በእቅድ ተይዞ 96,921 (100.3%) እና ሙሉ በሙሉ ክትባት ያገኙ ህጻናት 95,681 ለመፈጸም ታቅዶ 96,429 (100.7%) መፈጸም የተቻለ ሲሆን የክትባት አቋራጭን በተመለከተ የፔንታቫለንት አቋራጭ መጠን ከ3% በታች ለማድረስ ታቅዶ 0.9%፣የኩፍኝ አቋራጭ ከ5% በታች ለማድረስ ታቅዶ 3.2% ማድረስ ተችሏል፡፡

**የሥርዓተ-ምግብ አገልግሎትን ማስፋፋትና ማሻሻል፡-** ተግባሩን ውጤታማ ለማድረግ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ጤና ተቋሞች በጸጥታው ምክንያት እንዳይዘጉና የግብአት አቅርቦት ስራው እንዳይስተጓጎል ተደርጓል፡፡ በ1987 በሚሆኑ የደርሶ መልስ የክትባት መስጫ ጣቢያዎች እና 496 የሚሆኑ ቋሚ የክትባት መስጫ ጣቢያወች በተንቀሳቃሽ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ተችሎል፡፡ የክትባት ተደራሽነትና ተጠቃሚነትን ለማሻሻል ካሉን 132 ጤና ጣቢያወች መከከል 103 (79%) በሚሆኑት ጤና ተቋማት የክትባት ክፍልን የማዘመን ስራ ተሰርቶል፣ በየወረዳው የክትባትና የስርተ-ምግብ ልየታ ዘመቻዎችን በማመቻቸት የመፈጸም አቅማችንን ከፍ የማድረግ ስራ በሰፊው ተከናውኗል፡፡ በዚህም ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት 395,528 በየወሩ የምግብ እጥረት ልየታ ስራ ለመስራ ታቅዶ በአማካይ 362,688 (91.7%) በየወሩ በመለየት የምግብ እጥረት ያለባቸው በሙሉ ወደ የምግብ ህክምና አገልግሎት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከሁለት አመት በታች የዕድገት ክትትል የሚደረግላቸው እቅድ 140,962 ሲሆን 138,974 (98.6%) መፈጸም ተችሏል፡፡

**የበሽታ መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት ጥራትን፣ አቅርቦትንና ሽፋንን ማሻሻል፡-** ኤችአይቪ መከላከል፣ መቆጣጠርና ህክምናን ከማሻሻል አንጻር የመጀመሪያው 95 ምርመራ ከተደረገላቸው ውስጥ ፖዘቲቭ የሚሆኑ 1,138 ታሳቢ የተደረገ ሲሆን 764 (67.1%) ፖዘቲቭ ናቸው፡፡ ሁለተኛውን

95 ለማሳካት ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው አዋቂዎችና ህጻናት የፀረ ኤች አይቪ ህክምና አገልግሎትን ከ94% ወደ 100% ለማሳደግ የታቀደ ሲሆን ፖዘቲቭ ከሆኑት 764 ሰዎች ውስጥ መድሃኒት እንድጀመሩ የተደረጉት 693 (91%) ያህሉ ናቸው፡፡ የ3ኛው 95 እቅድ 18,668 ሰዎች የቫይረስ መጠን ምርመራ እንዲያካሂዱ ታቅዶ ክንውን 15,483 (82.9%) ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የቫይረስ መጠን ከ1,000 ኮፒ በታች የሆኑት 15,216 (98.3%) ናቸው፡፡ የቲቪ በሽታ ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንጻር የሁሉም አይነት የቲቢ በሽታ ልየታ መጠን እቅድ 3629 ሲሆን 2752 (75.8%) በመፈጸም ህክምናውን ማስጀመር ተችሏል፡፡ የወባ በሽታን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንጻር በበጀት አመቱ 196,928 ለሚሆኑ ህሙማን የወባ ምርመራ እቅድ ተይዞ 152,173 (77.2%) ምርመራ የተደረገ ሲሆን ከእነዚህ ዉስጥ ወባ የተገኘባቸዉ 26,816 ሲሆኑ የወባ በሽታ ስርጭቱን ለመቀነስና ለመግታት የግንዛቤ ፈጠራ፣ ግብአት የማሟላት፣ የማፋሰስና የማዳፈን፣ የኬሚካል ርጭት እና የአካባቢ ቁጥጥር ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በአካባቢ ቁጥጥር ስራው ላይ 117,016 ህዝብ ማሳተፍ የተቻለ ሲሆን 1,433,383 ህዝብ ደግሞ የጤና ትምህርት እንዳገኙ ተደርጓል፡፡

## 1.3.8.ቱሪዝም

ቅርሶችን ከመጠበቅና መንከባከብና በተመለከተ፡- ለ30 ቋሚ ቅርሶች የጉዳት መጠን ልየታ ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ37፣ ለ23 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ21፣ ለ154 ቋሚ ቅርሶች የጽዳትና እንክብካቤ ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ148፣ ለ 3437 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጽዳትና እንክብካቤ ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ2973፣ ለ40 ቋሚ ቅርሶች የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰራላቸው ታቅዶ ለ130፣ 6 ቋሚ ቅርሶች ለመመዝገብ ታቅዶ 5፣ ለ160 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ምዝገባ ለማድረግ ታቅዶ 109፣ 24 የማይዳሰሱ ቅርሶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 25፣ ለ136 ቋሚ ቅርሶች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ስራ ለመስራት ታቅዶ 125 እንድሁም ለ4000 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ስራ መስራት ታቅዶ 3446 በመፈጸም የቅርስ ምዝገባና ጥበቃ ስራው ላይ ውጤታማ መሆን ተችሏል፡፡ የቱሪስት መዳረሻዎችን ከማልማት አንጻር ለ20 መስህቦች 245 ኪ.ሜ መንገድ ለመስራት ታቅዶ ለ22 መስህቦች 129 ኪ.ሜ መንገድ፣ 4 መጠጥ ውሃ ለመስራት ታቅዶ 8 የመጠጥ ውሃ ግንባታ እና 3 ቋሚ መጸዳጃ ቤቶችንና 3 መታጠቢያ ለመስራት ታቅዶ 11 መፀዳጃ ቤትና 7 መታጠቢያ መስራት ተችሏል፡፡ ቱሪዝሙን ከማስተዋወቅ አንጻር በቴቪ፣ ሬዲዮ፣በርዕስና በቅጅ በማሰራጨት እና የዞኑን የቱሪዝም ሀብት መረጃዎች በማህበራዊ ሚዲያ በማጋራት እና በፎቶ ኤግዚቢሽን እና የአገርህን እወቅ ክበብና ጉዞና ጉብኝት ማህበር በመጠቀም የማስተዋወቅና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡

የቱሪስት ፍሰት እና ገቢ ማስገኘትን በተመለከተ 80 የውጭ ሀገር ቱሪስቶች በዞኑ ይጎበኛሉ ተብሎ ታቅዶ 71 የውጭ አገር ቱሪስቶች መጎብኘታቸው እንድሁም የአገር ውስጥ ቱሪስቶችን 2,260,377 ለማድረስ ታቅዶ 2,224,830 ቱሪስቶች ማስተናገድ የተቻለ ሲሆን ከውጭ ቱሪስቶች 202,560 ብር

ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 179,772 ብር እና ከሀገር ውስጥ ቱሪስት 1,018,298,766 ብር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 1,004,026,609 ብር ገቢ የተገኘ ተችሏል።

### 1.3.9.ንግድና ገበያ ልማት

ለጅምላ ንግድ ፈቃድ ትኩረት በመስጠት የንግድ መሰረቱን ወደ 48803 ማሳደግ በግብ ተይዞ በኦንላይን የተሰጠ አገልግሎት 49800 ሲሆን ነባር ፈቃድ እድሳት 40810 ለማድረስ ታቅዶ 27556 (67.5%) እና አደስ ንግድ ፈቃድ 8000 ታቅዶ 10256 (128%) ተፈፅሟል። አደስ ንግድ ምዝገባ እቅድ 8000 ታቅዶ 7922 (99%) ተፈፅሟል። ህጋዊ የንግድ ሽፋኑን አሁን ካለበት 44.85% ወደ 60% ለማሳዳግ ግብ ተጥሎ የበር ከበር ጉምኝት 131420 ታቅዶ 125,103 (95%)፣ የመለኪያ መሳሪዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኢንስፔክሽን 136,236 ታቅዶ 137,959 (100%)፣የቬሪፊኬሽን 40316 ታቅዶ 40576 (100.2%)፣ የ32,268 ነጋደ መረጃ ወደ ኮምፒዩተር ለማስገባት ታቅዶ 32,268 (100%)፣ የነጋደ ፍረጃ 131,420 ታቅዶ 125,103 (95%) ማከናወን ተችሏል።

በተመሳሳይ የተለያዩ የንግድ ድርጅቶችንና መጋዘኖችን ለ125,103 ጊዜ በድግግሞሽ ለመጎምኘት ተሞክሮ የተገኘ ውጤት የሪፎርም ጉድልት 12024 ሲሆን ዋና ዋናዎቹ ያለንግድ ፈቃድ መነገድ 7015፣ ያለ አድራሻ መነገድ፣ጊዜ ያለፈበት ምርት ይዞ መገኘት 537፣ ደረጃውን ባልጠበቀ የመለኪያ መሳሪያ ሲጠቀሙ የተገኙ 911፣ በወቅታዊ የመሸጫ ዋጋ መሰረት አድርጎ ግብይትን በደረሰኝ የማይፈጽሙ 1646፣ የንግድ ምርቶችን በወቅቱ ለገበያ አለማቅረብ 176፣ ዘርፍ ቀላቅሎ መነገድ 626 የሚሉት ናቸው። በተገኘው ጉድለት ላይ የተወሰደ እርምጃ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ 8128፣ እሽጋ 3862፣ እገዳ 6 እና ስረዛ 9 ሲሆኑ በድምሩ 120005 ተወስዷል። ቀሪ 19 ወደ ፍትህ ተመርቶ ክስ ተመስርቶባቸው ውሳኔ ያገኙ 9 ( በገንዘብ የተቀጡ 5፣ በእስራት የተቀጡ 2፣ ገንዘብና እሰራት 1፣ በነጻ የተለቀቀ 1)፣ በሂደት ላይ ያሉ 10 ናቸው።

በተወሰደው እርምጃ የተገኘ ውጤት አዲስ የንግድ ስራ ፈቃድ ያወጡ 7220፣ አድራሻቸውን ያስተካከሉ 213፣ ደረጃውን በጠበቀ የመለኪየ መሳሪያ የተጠቀሙ 911፣ በወቅታዊ የመሸጫ ዋጋ መሰረት ግብይቱን የፈጸሙ 1635፣ ጥራት የጎደለው ምርት ከማቅረብ የታቀቡ 537፣ ምራታቸውን በወቅቱ እንዲያቀርቡ የተደረጉ 176፣ ዘርፍ ከመቀላቀል የታቀቡ 626 እና እራሳቸውን ከንግድ መረቡ ያወጡ 686 በድምሩ 12004 እንዲስተካከል ተደርጓል።

በህግ ወጥ ሲዘዋወር የተያዘ መሰረታዊ ምርት ስኳር 427.97 ኩ/ል፣ ዘይት 29552 ለትር፣ ነዳጅ 58006 ሊትር፣ የግብርና ምርት በኩ/ል 3651.8፣ በሊትር 3500፣ በቁጥር 16227 እንድሁም የኢንዱስትሪ ምርት በኪ/ግ 58006.88፣ በሊትር 11388.2 እና በቁጥር 127437 ተይዞ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማህበረሰቡ እንዲሸጥ የማድረግ እና በአጥፊዎች ላይ ተመጣጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ተደርጓል፡

፡ በሌላ መልኩ ህጋዊ ደረሰኝ ማሳተም 26169 ታቅዶ 284064 (108.8%)፣ የዋጋ ዝርዝር መለጠፍ 43066 ታቅዶ 55939 (129.9%) እና የንግድ እቃ መገለጫ ስለመኖሩ መከታተል 56651 ታቅዶ 71576 (126.3%) ማከናወን ተችሏል፡፡

የገበያ መሰረተ ልማትን ለማዘመን ሳምንታዊ መረጃ 52 ለማስተላለፍ ታቅዶ 52፣ ዳታ ቤዚ በ23 ወረዳ ለመስራት ታቅዶ በ23 ወረዳ በመስራት እና የምርት ዋጋ አዝማሚያ ጥናት 12 ጊዜ በመስራት የገበያ መረጃ ማስተላለፍ ተችሏል፡፡ አድስ ቦርድ ማቋቋም እቅድ 18 ታቅዶ 18 የተፈጸመ ሲሆን ነባር ቦርድ ማጠናከር እቅድ 92 ታቅዶ 92 በመፈጸም የመረጃ ቦርድ ማልማት ተችሏል፡፡ አደስ መደበኛ ገበያ ማቋቋም 11 ታቅዶ 11፣ ነባር ገበያ ማሻሻል 120 ታቅዶ 120 እና አምራችና ሸማች በቀጥታ የሚያገናኝ ማዕክል መገንባት 9 ታቅዶ 7 በማከናወን የገበያ መሰረተ ልማት መስራት ተችሏል፡፡ እሁድ ገበያ ልማት በተመለከተ አደስ ማቋቋም እቅድ 3 ታቅዶ 3 እና ነባር ማጠናከር 12 ታቅዶ 12 መፈጸም ተችሏል፡፡

ወቅታዊ የገበያ ማረጋጋት ስራ በተመለከተ 46.3 ሚሊየን ብር በጀት በመያዝ የቀረበ ምርት ግብርና 60000 ኩ/ል ታቅዶ 70134 ኩ/ል (9117%)፣ የኢንዱስትሪ ምርት በጠጣር እቅድ 12000 ኩ/ል ታቅዶ 25989 ኩ/ል (217%) ማቅደብ የተቻለ ስሆን 133310 ማህበረሰብ ተጠቃሚ ተደርጓል፡፡ የእንስሳት ተዋፅኦ ግብይት በትስስር ወተት በሊትር 3500000 ታቅዶ 3502664፣ ማር በቶን 1550 ታቅዶ 1566.5፣ ዶሮ በቁጥር 240000 ታቅዶ 333990፣ እንቁላል በቁጥር 3300000 ታቅዶ 4452864፣ ስጋ በቶን 8 ታቅዶ 12.37 እንድሁም አሳ በቶን 246 ታቅዶ 278 ማከናወን ተችሏል፡፡ የድጎማ ምርት አቅርቦት ስኳር የቀረበ 16674 ኩ/ል የተሰራጨ 100%፣ ዘይት የቀረበ 256796 ሊተር የተሰራጨ 100% እንድሁም ነዳጅ የቀረበ (ናፍታ፣ቤንዚን፣ኬሮሲን) 9,692,861 ሊትር ሲሆን የተሰራጨ 100% ነው፡፡

አጠቃላይ በቁጥጥር ስራችን (በተቋም እና በግብረ ሀይል) የተገኘ የተለያዩ ሪፎርም ጉድለቶች 12,024፣ በህገ ወጥ ሲዘዋወር የተያዘ እንስሳት 4507፣ በህገ ወጥ ሲዘዋወር የተያዘ ምርት የግብርና 9321 ኩ/ልና የኢንዲስትሪ ምርት 129657 ሊትር ሲሆን የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውንና የምርት ጥራት ችግር ያለባቸውን ምርቶች መከታተልና ማስወገድ በጠጣር 5084.58 ኪ/ግ በሊትር ደግሞ 4924.98 መፈጸም ተችሏል፡፡

### 1.3.10. ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ

የትራንስፖርት መሠረት ልማት ለማስፋፋት 5 መናኸሪያ ለመጠገን ዕቅድ ትይዞ ከህዝብ ተሳትፎ 55,000 ብር፣ ከመንገስት /ካፒታል በጀት 651,984 ብር እና ከመናኸሪያ የውስጥ ገቢ 2,056,705.04 በድምሩ ብር 2,763,689.04 ብር ወጭ በማድረግ 9 መነሃሪያዎች ላይ የጥገና ሥራ ተከናውኗል፡፡

በዘህ ዘርፍ  በአመቱ ውስጥ 1,009,799 የህዛብ ትራንስፖርት ተሽከርከሪዎች በድግግሞሽ ስምሪት በመስጠት 18,631,226 ህዝብ በማጓጓዛ 59,120,950 ኪ/ል ሜትር የመሸፈን ስራ የተሰራ ሲሆን የመናኸሪያዎችን ስታንዳርድ ማስከበር 87% ለማድረስ ታቅዶ 75% ማድረስ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 86% ነው፡፡ 32,328 እጩ አሽከርካሪዎች የንድፈ ሃሳብ ፈተና እና የተግባር ፈተና ለመስጠት ታቅድ ክንውን 39,530 አፈጻጸሙ (122%) መፈጸም ተችሏል፡፡ 12,444 ብቁ ለሆኑ እጩ አሽከርካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ /መንጃ ፈቃድ/ ለመስጠት ታቅድ ለ18,235 አሽከርካሪዎች የተሰጠ ሲሆን አፈፃጸሙ 146% ነው፡፡ ለ18,800 አድስ እና ነባር አሽከርሪወች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማደስ ታቅዶ የ22,598 አሽከርካሪዎች ፈቃድ የታደሰ ሲሆን አፈፃጸሙ(120%) ነው፡፡ አድስ የተሽከርካሪ ምዝገባ ለማድረግና ሰሌዳ ለመስጠት 4,888 ታቅዶ 2,174 የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ 44% ነው፡፡ የተሽከርካሪ ምርመራ ቦሎ ማድረግ 13,440 ታቅዶ ክንውን 13,135 ሲሆን አፈጻጸሙ 98% ነው፡፡ የተሽከርካሪ የባለቤትነት ስመ ንብረት ዝውውር ለማድረግ 1,750 ታቅዶ ክንውን 924 አፈጻጸሙ 53 ሲሆን የፋይል ዝውውር 1356 ታቅዶ ክንውን 747 አፈጻጸሙ 55% ነው፡፡

ለ2,361,357 የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር በእቅድ የተያዘ ሲሆን ለ2,518,844 (107%) ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የመንገድ ትራፉክ አደጋ ከ2016 በጀት አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር በማነፃፀር በ10,000 ተሽከርካሪ 34% ለመቀነስን ታቅዶ የደረሰ አደጋ 54 ሲሆን 31 በመጨመር፣ የሞት አደጋ 47 ሲሆን 8 በመጨመር እንድሁም በንብረት ውድመት 7,335,000 ብር የሚገመት ንብረት የወደመ ሲሆን በ954,500 ብር ከባለፈው አመት በመጨመር የተመዘገበ መሆኑን ያሳያል፡፡ አጠቃሊይ አፈጻጸሙ ከእቅደ አንጻር ሲወሰድ የሰው ሞት እና ጉዳት ከታሰበው በላይ መጨመሩን ያመላክታሌ፡፡

ድንገተኛ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራን ለማድረግ 3,527 ታቅዶ 3,547 (100.5%)  የተፈጸመ ሲሆን ምርመራ ከተደረገላቸው 3,547 ተሽከርካሪዎች ውስጥ ከባድ ችግር የተገኘባቸዉ 509 (14.4%)፣ ቀላል ችግር የተገኘባቸው 606 (17.1%) እና ምንም ችግር የሌለባቸው 2,432 (68.5%) መሆኑን ያሳያል፡፡ የኦፕሬተር ፈቃድ ደረጃ ሲሰጣቸው በትክክል ደረጃ መሰጠቱን በውስጥ ኢንስፔክሽን ማረጋገጥ በአመቱ 160 ታቅዶ ክንውን 161 ሲሆን አፈጻጸም 100.6% ነው፡፡

ኢ-ቲኬቲንግ አገልግሎት በዞን መናኸሪያ ከተጀመረ ከጥቅምት 1/2017 ጀምሮ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ የተሰጠ ስምሪት አገር አቋራጭ ተሽከርካሪ ብዛት 3,654፣ የተጓጓዘ መንገደኛ 167,052 ሲሆን የተሰጠ ስምሪት መለስተኛ ተሽከርካሪ ብዛት 11,129፣ የተጓጓዘ መንገደኛ 385,121 እና አነስተኛ ተሽከርካሪ ብዛት 32,002፣ የተጓጓዘ መንገደኛ 450,969 ነው፡፡ በተመሳሳይ ኢ-ቲኬቲንግ አገልግሎትም በወረዳ ደረጃ ኩታበር፣ሀርቡ እና ሀይቅ  መናኸሪያ አገልግሎት መስጠት ማስጀመር ተችሏል፡፡

የህግ ማስከበር ስራዎች አንጻር በመናሃሪያ ዉስጥ፣ በመንገድ ደህንነት የመደበኛ ቁጥጥር፣ የራዳር ቁጥጥር እና በኢንስፔክሽን ቡድን የውጭ ቁጥጥር በድግግሞሽ 1,397,255 ተሽከርካሪዎች ላይ ቁጥጥር በማድረግ 12,390 ተሽከርካሪዎች ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው 11,918,015 ብር የቅጣት እርምጃ በመውሰድ ህግ የማስከበር ስራ ተሰርቷል፡፡

## 1.4. ማህበራዊ ፍትህ አፈጻጸም

ለአደጋ ተጋላጭ ህዝብ ቁጥር ለመቀነስ የጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አምባሰል፣ ተሁለደሬ፣ ቃሉ ወረዳዎችና ሀርቡ ከተማ አስተዳደር በ25,702,839 ብር የጎርፍ መከላከልና ወንዝ መግራት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ የሰብልና ገበያ ወርሃዊ ሪፖርት በተመለከተ ከ20 የገጠር ወረዳዎች በዓመቱ 240 ጥራዝ ለማሰባሰብ ታቅዶ 240 (100%) የተከናወነ ሲሆን በተመሳሳይ ሣምንታዊ ሪፖርት ከ20 የገጠር ወረዳዎች በዓመቱ 52 ሳምንታዊ ሪፖርት ለማጠናቀር የታቀደ ሲሆን 52 (100 %) ተከናውኗል፡፡ የተለያዩ ጥናቶችን በማከናወን የአደጋ ስጋት ቅነሳ ተግባራት በተመለከተ የመኸር ዝናብ አጀማመር፣ የ2016/17 መኸር ምርት የምርት ግምገማና የተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሄ ጥናት የተካሄደ ሲሆን የህብረተሰቡን የአደጋ ተጋላጭነት በዘላቂነት ለመቀነስ የሚያስችሉ የአደጋ ተጋላጭነት ጥናቶችን በማካሄድ የወረዳ ፕሮፋይሎችንና ዕቅድ ከማዘጋጀት አንጻርም 5 ወረዳዎች (ቃሉ፣ ተሁለደሬ፣ደሴ ዙሪያ፣አርጎባ እና ወረባቦ) የወረዳ ፕሮፋይል ጥናት ተካሂዷል፡፡ በተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ለሚጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ማቅረብ በተመለከተ ለተፈናቃዮች በመንግስት ለ7 ዙር 40914 ኩ/ል የምግብ እህል የቀረበ ሲሆን መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች 145,461,276 ብር እና 16755000 ብር የሚገመት ምግብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ለሴፍትኔት ተጠቃሚዎች ክፍያ 2,420,180,700 የተለቀቀ ሲሆን 2,419,297,820 ብር (99.99%) ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡ በተመሳሳይ አደጋ ምላሽ ሴፍቲኔት /Shock Responsive Safety net/ ክፍያ የተፈቀደ 185208660 ብር ሲሆን የተከፈለውም 185208660 ብር /100%/ ነው፡፡ የኑሮ መሰረት ማሻሻል መደበኛ ብድር ለማሰራጨት 8188 ተጠቃሚ ተለይቶ 6589 ቢዝነስ ፕላን ተዘጋጅቶ 4581 (97.6%) የብድር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ የተሰጠ ብደር ስንመለከት 135,671,079 ብር (151%) ነው፡፡ በጠቅላላ የተሰራጨ የነጻ ትራንስፈር ገንዘብ መጠን ብር 1,507,703,120 አፈፃፀም 100% የነጻ ትራንስፈር ክፍያ በሁሉም ወረዳዎች ተጠናቋል፡፡

በሴቶች መብትና ጥበቃ/ ጉጂ-ልማዳዊ ድርጊቶችና ያታዊ ጥቃቶች/ ዙሪያ ለ404,952 የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያዩ ዘዴዎች ግንዛቤ ለማስጨበጥ እቅድ ተይዞ 550,428 ማከናወን ተችሏል፡፡ 78 ቀበሌዎችን ከሴት ልጅ ግርዛት ነፃ ለማውጣት፣ 16 ቀበሌዎችን ከህጻናት ጋብቻ ነጻ ለማድረግ እና 21 የተጠናከሩና እውቅና የተሰጣቸው ሞዴል የስርዓተ ጾታ ቀበሌዎችን ለመፍጠር ታቅዶ እንቅደም ተከተላቸው 79፣ 42 እና 39 ቀበሌዎች በማድረስ በሁሉም ከ100 % በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

ህፃናትን በህግ አባትነትን የማወቅ መብታቸው እንድረጋገጥላቸው ማድረግ እቅድ 10 ሲሆን 19 (ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ ሴቶች ሁለተናዊ መብታቸውን እንዲያስከብሩ በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ዙሪያ ለ340,943 ሴቶች ግንዛቤ ለማስጨበጥ ታቅዶ 357,540 (100%) መፈጸም ተችሏል፡፡ በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊት ዙሪያ ለህፃናት ግንዛቤ በመፍጠር 28,915 ህፃናትን በአድስ በህጻናት ፓርላማ እና በትምህር ቤቶች በሚቋቋሙ ክበባት እንዲደራጁ ታቅዶ 104,270 ህፃናትን ማደራጀት ተችሏል፡፡

የሴቶች፣ የህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን ተሳትፎና ውክልና ከማረጋገጥ አንጻር በየደረጃው በሚገኙ አመራር ቦታዎች የሴቶችን ተሳትፎ 25% ለማድረስ በእቅድ ተይዞ በዞን-አመራር 19%፣ በወረዳ- አመራር 16%፣ በቀበሌ- አመራር 8.5%፣ በህግ ተርጓሚ 32 %፣ በቀበሌ- ማህበራዊ ፍ/ቤት 14%፣ በወረዳ- ም/ቤት 51.7% እንድሁም በቀበሌ- ም/ቤት 48.29% ላይ ይገኛል፡፡ በየደረጃው ባሉ የሕዝብ ምክርቤቶች የሕጻናት ፖርላማ አባላትን በመወከል በሚካሄዱ የምክር ቤት ጉባኤዎች 1078 ሕጻናት በቋሚነት እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 488 (45%) ህፃናት ተሳታፊ ሁነዋል፡፡

የሴቶች፣ ህፃናት አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንጻር ለሴቶች 380 እና ለአካል ጉዳተኛ 30 የስራ ትስስር መፍጠር ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ 53,450 ሴቶች በተለያየ የገቢ ማስገኛ ተግባራት ተሠማርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ 49626 ሴቶች 34,477,139 ብር እንድቆጥቡ ለማድረግ 49,626 ሴቶች (93%) 26,698,237 ብር (77%) መቆጠብ ችለዋል፡፡ በተመሳሳይ 209,687 ሴቶች በገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር በማሳተፍ 65,994,504 ብር እንድቆጥቡ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ 37,723 ሴቶችን በማሳተፍ 25,638,409 ብር እንድቆጥቡ ተደርጓል፡፡ ሴቶች ከቆጠቡ በኂላ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ በኩል 14,773 ሴቶች 65,994,504 ብር እንድበደሩ ለማድረግ ታቅዶ ክንውን 22,005 ሴቶች 78,821,453 ብር እንድበደሩ ተደርጓል፡፡

የአካባቢውን ፀጋ በማስተባበር ለአረጋዊያን ልዩ ልዩ ድጋፍ በማድረግ በቋሚ የገቢ ማስገኛ ሥራ እንዲሠማሩ ማድረግ እቅድ 375 ሲሆን 60 (16%) እንድሁም የአካል ጉዳተኞች እቅድ 550 ሲሆን 146 (26.5%) ማከናወን ተችሏል፡፡

ከድኀነት ወለል በታች የሚኖሩ አረጋዊያን ነፃ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ 20,000 በእቅድ ተይዞ 33078 ተከናውኗል፡፡ በተፈጥሮና ሰውሰራሽ አደጋ እና ሌሎች የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጮችን ለመደገፍ በእቅድ 23,853 ተይዞ 73,120 ሰዎች 2,631,466.00 ብር የሚገመት በጥሬና በአይነት ድጋፍ የተደረገ ሲሆን አረጋውያን 17,076፣ አካል ጉዳተኞች 6,191፣ ወላጆቻቸውን ያጡና ህፃናት 17,167፣ አጥቢና ነፍሰጡር እናቶች 4,058ና ሌሎች ተጋላጮች 28,628 ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም ከጉምሩክ በተገኘ የቦንዳ ልብስ በ11 ወረዳና በ3 ከተማ አስ/ር ለተፈናቃይና

ለአካባቢው ነዋሪዎች ከ7 ሚሊየን ብር በላይ የሚገመት ሃብት ለድጋፍ አገልግሎት እንዲውል ተሰራጭቷል፡፡

በተለያዩ የህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ አማራጭ ፕሮግራሞች 31,507 ህጻናት እና ማህበረሰብን መሰረት ባደረጉ ምድቦች 31,419 ህጻናት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ እንደቀደም ተከተላቸው 69,683 እና 69,593 ህፃናት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

የወጣቶች የመደራጀት መብትን ከማስጠበቅ አንጻር በወጣቶች ብሄራዊ ፖሊሲ፣ የእድገት ፓኬጅ፣ ስትራቴጅ ግንዛቤ መፍጠር 170,268 እድሁም በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ግንዛቤ መፍጠር 170,268 በእቅድ ተይዞ እንደቀደም ተከተላቸው 125,823 (73.9%) እና 124,947 (73.4%) መፈጸም ተችሏል፡፡ ከነዚህም 107,693 ወጣቶችን በተለያዩ አደረጃቶች ለማደራጀት ታቅዶ 142,253 (100%) መፈጸም ተችሏል፡፡ 22,500 ወጣቶችን በ1938 ልማት ቡድን ለማደረ ታቅዶ 48,874 (100%) ወጣቶችን በ3524 ልማት ቡድን ማደራጀት ተችሏል፡፡ ለ62,787 ወጣቶች አመራር ጥበብ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ 9,134 (14.5%) ማሰልጠን ተችሏል። የወጣቶችን ተሳትፎና ውክልና ከማረጋገጥ አንጻር በመልካም አስተዳደር ዙሪያ 115,000 እና በሰላም ግንባታና ግጭትን በመከላከል ዙሪያ ለ295,550 ወጣቶች ግንዛቤ ለመፍጠር በእቅድ ተይዞ እንደቀደም ተከተላቸው 109,302 ( 95%) እና 307,899 (100+%) መፈጸም ተችሏል፡፡ በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች ወጣቶች ያለ ድምጽ ተሳታፊ ማድረግ እቅድ 1,809 ሲሆን ክንዉን 1,695 (93.7%) ማከናወን ተችሏል፡፡ ወጣቶችን በተለያዩ ንቅናቄ መድረኮች ተሳታፊ ለማድረግ 175,056 በእቅድ ተይዞ 163,052 (93%) ማሳተፍ ተችሏል፡፡

የወጣቶችን ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ስራን በሚመለከት በበጋና ክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት 1,213,579 በጎ ፈቃደኞችን ተሳታፊ በማድረግ፣ 822,545,230 ብር የሚገመት ድጋፍ ለማሰባሰብ እና 3,094,521 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 1,296,944 በጎ ፈቃደኞችን (106.9%) በማሳተፍ፣ 699,457,874 ብር (85%) የሚገመት ድጋፍ በማድረግ 2,933,789 የህብረተሰብ ክፍሎችን ማለትም የእቅዱን 94.8% ያህሉን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ የወጣቶች የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭነት ከመቀነስ አኳያ በማህበራዊ ጠንቅ ተጋላጭነት ዙሪያ ለ143,750 ወጣቶች እና ለ 86,250 ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለማስጨበጥ ታቅዶ 127,765 ወጣቶች እና ለ92,441 ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ አፈፃፀሙም በቅደም ተከተል 83% እና 100% ነዉ፡፡ በተመሳሳይ በህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ዙሪያ ለ143,750 ወጣቶች እና ለ86,250 ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለማስጨበጥ ታቅዶ ለ133,011 ወጣቶች እና ለ69,125 የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ አፈፃም 92.5% እና 80% ነዉ፡፡ የወጣት ስብእና ግምባታ ማዕከላትን አንጻር 4 ለመገምባት በእቅድ ተይዞ የተገነባ 2

(50%)፣ 28 የወጣት ማዕከላት ለማጠናከር በእቅድ ተይዞ 9 (32%)፣ ስታንዳርድ ያሟሉና ርክክብ የተፈፀመባቸው የወጣት ማዕከላት 20 በእቅድ ተይዞ 5 (17%)፣ ለ29 የወጣት መአከላት የይዞታ ማረጋገጫ እንድኖራቸው ለማድረግ ታቅዶ 5 (17%) የተፈጸመ ሲሆን በነዚህ በማዕከላት 71,382 ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 59,435 (83.3%) ወጣቶች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በሴቶችና ህፃናት በሚፈፀሙ የልዩ ልዩ ወንጀሎች አፈጻጸምን በተመለከተ፦ የወንጀል ምርመራ መዛግብትን የማጥራት ምጣኔ 161 መዛግብት ምርመራቸው ተጠናቀ ለዐ/ሕግ ከደረሱት 154 ዉሳኔ የተሰጣቸዉ ሲሆን አፈጻጸሙ 95.65% ነው፡፡ በሴቶችና ህፃናት የወንጀል ቀጥታ ክርክር የማስቀጣት ምጣኔን 95.8% ለማድረስ ታቅዶ 172 መዛግብት ውስጥ 61 መዘገብ ላይ በፍ/ቤት ውሳኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡ ውሳኔ ከተሰጠባቸው መዛግብት ውስጥ 52 መዛግብት ላይ የቅጣት ውሳኔ ሲሰጥባቸው 11 በነፃ የተሰናበቱ ናቸው፡፡ የማስቀጣት ምጣኔ አፈፃፀማችን 100% ነው፡፡ የኃይል ጥቃትቱሪዝም ደርሶባቸው ለህክምናና ምክር አገልግሎት ፈልገው ወደ ፈለገ ህይወት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ አካላትን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በማዕከሉ የመስክ ምልከታ በማድረግ የተስተዋሉ አካባቢያዊ፣ የአሰራር ስርዓትን፣ የሰው ኃይል እና የበጀት አለመኖር ችግሮች እንዲፈቱ ከሚመለከታቸው አካለት ጋር ውይይት በማድረግ ማዕከሉ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ምክረ ሀሳቦች ተሰጥቷል፡፡

## 1.5. የገጠርና የከተማ ልማት አፈጻጸም

### 1.5.1.ገጠር ልማት

የመሬት አስተዳደር ስርአት ዘመናዊና ዘላቂ ማድረግ በተመለከተ በበጀት ዓመቱ በዚህ ተግባር ስኬታማ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ አኳያ የ2ተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ማሰራጨትን በተመለከተ በአመቱ ለ61048 ባለይዞታ ለ324,173 ማሳ ካርታ በማሰራጨት ከዞኑ አልፎ ለክልሉ አፈፃፀም ውጤታ ስራ ለመስራት ተቿሏል፡፡ በዚህም በዞኑ ከፋተኛ የህዝብ ንቅናቄ ስራና ለሌሎች የመንግስት ስራወች ባለይዞታውን በማሳተፋ ስኬታማ ስራ ተሰርቷል፡፡ በሌላ በኩል ካርታውን ከማሰራጨት በዘለለ ባለይዞታዎች ካርታቸውን በማስያዝ 54,697,475 ብር የብድር ዋስትና ተጠቃሚ እንድሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ካዳስተር በተሰራባቸው ወረዳወች በከፋተኛ ሁኔታ ከእርሻ መሬት የሚገኘው ገቢ እንድጨምር አስተዋፆ አበርክቷል፡፡ የምናስበውን ዘመናዊ የመሬት አስተዳደር ስርአት ዘላቂና ውጤታማ የምናደርገው በሲስተም የመሬት ግብይትን ስናከናውን ስለሆነ በአመቱ 80152 ማሳ በNRLAIS (በብሄራዊ የገጠር መሬት መረጃ ስርአት) የመሬት ግብይት በመፈፅም ከአመቱ እቅድ በላይ ማከናወን የተቻለ ሲሆን በዚህ አፈፃፀም ወረዳወች እንደየ አፈፃፀማቸው ሀብት እንዳገኙ አድርጓል፡፡

ከመሬት አጠቃቀም አኳያ የተከናወኑ ተግባራት በተመለከተ መሬትን በዘላቂነትና በላቀ ደረጃ ለመጠቀም አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም እቅድ ማቀድ ቁልፋ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በአመቱ 11 አድስ ቀበሌዎች አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም እቅድ ማቀድ ተችሏል፡፡

ከመሰረተ ልማትና ዲዛይን ዝግጅት ተግባርን በተመለከተ በዚህ ዘርፍ ዞናችን ከራሱ አልፎ ለክልሉ ሞደል የሆኑ የቀበሌ ማዕከል ማስፋፋት ስራወችን አከናውኗል፡፡ በመሆኑም የተሰሩት የቀበሌ ማዕከላት ለፖርቲያችን ኢኒሽቲቭ ለሆነው ለገጠር ኮሊደር ልማት መሰረት መሆን ችለዋል፡፡ ከዚህ አኳያ በአመቱ ለ22 አድስ የቀበሌ ማዕከላት ፕላን እንሰራለን ብለን አቅደን ለ32 አድስ የቀበሌ ማዕከላት ፕላን በማዘጋጀት ከዞኑ እቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ በዚህ ዘርፋ አ/ደሩን ወደ አንድ በማሰባሰብ የመሰረተ ልማት ተጠቃሚ እንድሆን ከማድረጉም በላይ በከፍተኛ ሁኔታ በእርሻ መሬት ላይ የሚሰራ ህገወጥ የቤት ግንባታን በመቀነስ በኩል የተሻለ አስተዋፆ አበርክቷል፡፡ በቀበሌ ማዕከል ቤት ለገነቡ አ/አደሮች የይዞታቸው ማረጋገጫ  የሚሆን 1124 ተጠቃሚዎች ካርታ የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህ ዘርፋ ብቻ በተሰጠ አገልግሎት 3,520,317 ብር ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

ከካሳና ሀብት ዋጋ ትመና መልሶ ማቋቋም አኳያ እንደሚታወቀው መሬት ለላቀ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ሲባል ለልማት ሲፈለግ ካሳ እየተከፈለ አ/አደሩ እንድለቅ ይደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት 578.76 ሄ/ር መሬት ለልማት እንድውል  በማስለቀቅ 1,882,252,230.93 ብር ካሳ የተሰራ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1,424,998,409.47 ብር (75%)ቱ ካሳ ለልማት ተነሽዎች እንድከፈል ተደርጓል፡፡ ቀሪ ያልተከፈለው ገንዘብ የፌደራል ፕሮጀክቶች ክፋያ ሲሆን መረጃውን በተገቢው መንገድ ለክልሉ መንግስት እንድደርስ ተደርጓል፡፡ በዚህ ዘርፋ ዋና ተግባር በልማት ምክንያት የተፈናቀለውን አ/አደር በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም ተግባር ሲሆን ከዚህ አኳያ ከባለድርሻዎች ጋር ምክክር መድረክ ያካሄድን ሲሆን በልማት ምክንያት ለተፈናቀሉ 968 ባለይዞታዎች ትክ የመኖሪያ ቦታ እንዳገኙ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ለ2099 የባለይዞታ ልጆች የመኖሪያ ቤት እንዳገኙ ተደርጓል፡፡ ከመኖሪያ ቤት በዘለለ ለ385 የልማት ተነሽወች የስራ መስሪያ ቦታ በመስጠት በዘላቂነት እንድቋቋሙ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

ለገጠር ኢንቨስትመንት የሚሆን መሬትን መለየት አንዱ የተቋማችን የአመቱ ቁልፋ ስራ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከ517 ሄ/ር መሬት መለየት ተችሏል፡፡ መሬት የወሰዱ ባለሀብቶችን ድጋፋና ክትትል የማድረግ ስራና የልማት አፈፃፀም የመሙላት ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም መሰረት መሬት ወስደው ያላለሙ 6 ባለሀብቶችን ማስጠንቀቂያ 1 ባለሀብት ላይ በውለታው መሰረት እንድነጠቅ ተወስኗል፡፡

## 1.5.2. ከተማ ልማት

በከተሞች በህብረተሰቡና በመንግስት በጋራ በሚከናወኑ የአካባቢ ልማት ፕሮጄክቶች ላይ የማህበረሰብ አቀፍ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ህብረተሰቡ በጥሬ ገንዘብ፣ በአይነትና በጉልበቱ 311,270,962

ብር የሚገመት ተሳትፎ እንድኖረው ታቅዶ 385,780,813 ብር (ከ100% በላይ) የተፈጸመ ሲሆን በዚህም 1,509,192 የህብረተሰብ ክፍል ለማሳተፍ ታቅደ 1,679,532 (ከ100% በላይ) ማሳተፍ ተችሏል፡፡

በዞኑ የሚገኙ 25 ከተሞች 3450 ሄ/ር የመሬት ሀብታቸውን በመቆጠር በመሬት መረጃ መመዝገቢያ ቋት በተደራጀ መልኩ በመመዝገብ ከብክነት እና ከወረራ እንዲጠብቁ ለማድረግ ተቅዶ 4,291 ሄ/ር (100%) እንድሁም በከተሞች የይዞታ ፋይሎችን ወይም ሰነዶችን በሀርድና በሶፍት መረጃ 51000 ይዞታ ፋይል ታቅዶ 65,472 (100% በላይ) ማከናወን ተችሏል፡፡ በከተሞች ማስፋፊያና በመሃል ከተማ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 594 ሄ/ር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 768 ሄ/ር (ከ100% በላይ) በፈጸም የተቻለ ሲሆን 475 ሄ/ር መሬት ለተጠቃሚ እንድተላለፍ ታቅዶ 506 ሄ/ር (ከ100% በላይ) እንድተላለፍ ተደርገኋል፡፡

በከተሞች በጨረታ እና በምደባ ለተጠቃሚዎች የተላለፉ ቦታዎች 100% ለታለመላቸው ጥቅም እንዲውሉ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ሲሆን በባለሃብት ተይዘው ባለመልማታቸው የተነጠቁ ቦታዎች በቁጥር 298 ሲሆኑ 7.758 ሄ/ር በሬት ወደ መሬት ባንክ ማስገባት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 1 የመሬት ኦድት ማድረግ ታቅዶ 1፣ ህገወጥ ይዞታወች በመረጃ አደራጅቶ መያዝ 21,900 ታቅዶ 22,230፣ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በማዘጋጀት መስጠት 15,257 ታቅዶ 18,795፣ በህገ-ወጥ የተገነባ ግንባታ መረጃ መለየት 10,950 ታቅዶ 11,871 እንድሁም ከተለየው 2,570 የፈረሰ ሲሆን 11.04 ሄ/ር መሬት ወደ መሬት ባንክ ማስገባት ተችሏል፡፡

በተለያዩ የመኖሪያ ቤት ልማት አማራጮች ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅደ የተሰራ ሲሆን በመንግስት ቁጠባ ቤቶች 154 ታቅዶ 155፣ በማህበራት 2716 ታቅዶ 3498፣ በግለሰብ 1422 ታቅዶ 3675 በድምሩ 4292 ታቅዶ 7328 የመኖሪያ ቤቶች ተገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ለቀበሌ ቤቶች ጥገና ማድረግ 162 ታቅዶ 159፣ የቀበሌ ቤቶችን መረጃ በማሰባሰብ ወደ ሶፍትዌር ማስገባትና ከዘረፋ መጠበቅ 3866 ታቅዶ 3469 እንድሁም በመንግስት ባለቤትነት የሚከራዩ የቀበሌ ቤቶች የዉል እድሳት ማድረግ 3866 ታቅዶ 3009 መፈጸም ተችሏል

በከተሞች የሚገነቡ ሁሉም ፕሮጅክቶች የማህራዊና አካባቢያዊ ደህንነት ማሟላታቸው እየተረጋገጠ እንዲገነቡ እንድሁም አዲስ የሚገነቡ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች በተያዘላቸው በጀትና በተቀመጠላቸው ጊዜ ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ ሲሆን የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅእኖ ግምገማ ጥናት ማዘጋጀት 100 ታቅዶ 102 (100%)፣ የግንባታ ይሁንታ ፈቃድ መስጠት 100 ታቅዶ 97 (97%)፣ ኮብል ግንባታ 8.7 ኪሜ ታቅዶ 1.812 ኪሜ ኪ/ሜ (20.8%)፣ አድስ ጠጠር መንገድ ግንባታ 80 ኪ/ሜ ታቅዶ 85.748 ኪ/ሜ (100% በላይ)፣ አዲስ መንገድ ከፈታና ማስፋት ግንባታ 90 ታቅዶ 139.3 ኪ/ሜ (100%)፣ ዘመናዊ የጎርፍ

ማስወገጃ ቦይና መከላከያ ግንብ ግንባታ 12.57 ኪ/ሜ ታቅዶ 11.431 ኪ/ሜ (91%)፣ መለስተኛ ድልድይ ግንባታ 1 ታቅዶ 2 (ከ100% በላይ)፣ ካልቨርት ግንባታ 50 ታቅዶ 55 (100%)፣ ጌጠኛ መንገድ ጥገና 1 ኪ.ሜትር ታቅዶ 0.284 ኪ/ሜ (28%)፣ ጠጠር መንገድ ጥገና 60 ኪ.ሜትር ታቅዶ 85 ኪ/ሜ (100%)፣ የመንገድ መብራት መስመር ዝርጋታ 54 ኪ.ሜትር ታቅዶ 65.56 ኪ/ሜ (100% በላይ) እና በከተማው ፕላን መሰረት የውሃ መስመር ዝርጋታ 60 ኪ.ሜትር ታቅዶ 158 ኪ/ሜ (ከ100% በላይ) ማከናወን ተችሏል።

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት  በማዘመን የአረንጓደ ልማት ግንባታን በማስፋፋት ፅዱና ውብ ከተማ ለመፍጠር እቅድ ተይዞ የተሰራ ሲሆን ከተሞች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ ስራ ላይ 184,492 የከተማ ነዋሪ ህብረተሰብ ግንዛቤ በመፍጠር198,382 የከተማ ነዋሪ በፅዳት ስራ እንድሳተፍ ተደርጓል፣ 50,000 ግለሰቦች በ20 ሜትር ርቀት ግቢና አካባቢያቸውን እንዳጸዱ ታቅዶ 50,736 (100% በላይ)፣ 2400 ተቋማት በ50 ሜትር ርቀት ግቢና አካባቢያቸውን እንዳጸዱ ታቅዶ 2831 (100% በላይ)፣ 16 ነባር ማህበራት ለማጠናከር ታቅዶ13 (75%)፣ አዲስ ማህበራትን በከተሞች ማደራጀት 10 ታቅዶ 7 (70%)፣ 125,000 ሜትር ኪዩብ ደረቅ ቆሻሻ በከተሞች ለመሰብሰብ ታቅዶ 126,755 ሜ/ኩ (100%)፣ የመንገድ ላይ ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ቅርጫት ማዘጋጀት 60 ታቅዶ 65 (100%)፣ በአጠቃላይ 348 የደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ቅርጫት አገልግሎት እንድሰጡ ታቅዶ 343 (98%) እንድሁም ጊዚያዊ  የቆሻሻ ማስወገጃ ማዘጋጀት 41 ታቅዶ 40 (98.6%) መፈጸም ተችሏል። የከተሞች ውበትና አረንጓደ ልማት ስራዎችን በተመለከተ የተለዩ አረንጓደ ቦታዎች 150 ታቅዶ 104 (69%)፣ የይዞታ ማረጋገጫ የሚሰራላቸው የአረንጓዴ ቦታዎች 150 ታቅዶ 104 (69%)፣እንክብካቤ የሚደረገላቸው ነባር አረንጓዴ ቦታዎች 503 ሄ/ር ታቅዶ 466 ሄ/ር (94%) እንድሁም በአዲስ የለሙ ፓርኮች ማልማት 6 ታቅዶ 6 (100%) ማከናወን ተችሏል።

## 1.6. የአካባቢ ጥበቃ ልማት አፈጻጸም

በአካባቢ ነክ ጽሁፍ በማዘጋጀት ለ400000 ህዝብ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ405533 (101.4%) የተለያዩ የህ/ሰብ ክፍል ተደራሽ ማድረግ ተችሏል። በዞናችን በሚከሰቱ ዋና ዋና አካባቢያዊ ችግሮች መሰረት ተደርጎ 5350 ኮፒ ብሮሸር በማዘጋጀትና በማሰራጨት ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 7626 (142.5%) ማሳካት ተችሏል። በደን ጥበቃና ቁጥጥር፣ በደን ምርት ውጤት ዝውውር እና በሮያሊቲ አሰባሰብ አንድ መልካም ተሞክሮ ለመቀመር ታቅዶ አንድ ሰነድ ማዘጋጀት ተችሏል።

የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ስርዓትን ማጎልበት ለ600 አዳዲስ ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድ ሰርቲፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ785 ፕሮጀክቶች የተሟላ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ በማቅረባቸው የይሁንታ ፈቃድ ሰርቲኬት የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ በመቶኛ ከ100 በላይ ነው። 215 ነባር ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ምርመራ በማካሄድ የይሁንታ ፈቃድ ሰርቲፊኬት ለማደስ ታቅዶ 427

ፕሮጅክቶች በገቡት ግዴታ መሰረት በመፈፀማቸው ሰርቲፊኬታቸው ታድሷል፡፡ አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሳያልፉ ወደ ተግባር ለገቡ 25 ፕሮጀክቶች የአካባቢ ምርመራ በማካሄድ የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ በማድረግና ሰነዱን በማጽደቅ ብር 35000 ቅጣት በማስከፈል ለ7 ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድ ሰርቲፊኬት ተሰጥቷቸዋል፡፡

የአካባቢ ህግ ተከባሪነትና ተፈፃሚነትን ማሳደግን በተመለከተ በ325 ፕሮጀክቶች የአካባቢ ክትትል በማድረግ በአካባቢ የሚደርሰውን ብክለትና ብክነት ለመቀስ ታቅዶ በ421 ፕሮጀክቶች ክትትል የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙ በመቶኛ ከ100 በላይ ነው፡፡ በ275 ፕሮጀክቶች የአካባቢ ምርመራ በአካባቢና በማህበረሰብ የሚደርሰውን ብክለት ለመቀነስ ታቅዶ በ294 ፕሮጀክቶች በማከናወን እጥረቶቻቸውን እንዲያርሙ ግብረ መልስ በመስጠት እንዲያስተካክሉ በመደረጉ አፈፃፀም በመቶኛ 105 ነው፡፡ በአካባቢ ክትትልና ምርመራ በተሰጣቸው ግብረ-መልስና በገቡት ግዴታ መሰረት መተግበር ያልቻሉ 200 ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ቁጥጥር በማካሄድ እርምጃ ለመውሰድ ታቅዶ በ130 ፕሮጀክቶች ላይ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤና የይሁንታ ፈቃድ የመሰረዝ ስራ በመከናወኑ አፈፃፀሙ 65% ነው፡፡ 245 ለቀረቡ ብክለት ይወገድልኝ አቤቱታዎችና ቅሬታዎች ክትትል በማድረግ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ ለቀረቡ 246 አቤቱታዎች ምለሽ የተሰጠ በመሆኑ አፈፃፀም በመቶኛ 100.4 ነው፡፡

ወራሪ መጤ አረም ዝርያዎች ሽፋን መጠን ለመቀነስ በ22000 ሄ/ር 110000 ሰው በማሳተፍ የሚገኘውን መጤ አረም በህ/ሰብ ተሳትፎ ለማስወገድ ታቅዶ በ35595.675 ሄ/ር በ113552 ተሳታፊ የህ/ሰብ ተሳትፎ ተጠቅመን ማስወገድ በመቻሉ አፈፃፀሙም በመቶኛ ከ100 በላይ ነው፡፡ የህብረተሰቡ ተሳትፎ በገንዘብ ሲተመን 11,014,544 ብር እንደሚሆን ይገመታል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ አካተው እንድሰሩ ከሚመለከታቸው ባለድርሳ አካላትን ክትትል የተደረገ ሲሆን ለ60 ባለሙያዎች ለማሰልጠን ታቅዶ 66 በማሰልጠን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

በመንግስት ደኖች ውስጥ በ650 ሄ/ር የማበልፀጊያ የተከላ ቦታ ለመለየት ታቅዶ 518.8 ሄ/ር (79.8%) የተፈጸመ መሆኑ፣ በሬድ ኢንቨስትመንት ፕሮግራምና በኬይ.ኤፍ.ዳብልዩ ፕሮጀክቶች በ5181.84 ሄ/ር መሬት ላይ የተከላ ቦታ ልየታ በማካሄድና 25,657319 ችግኝ አፍልቶ ለመትከል ታቅዶ የተከናወነው 5,160.612 ሄ/ር የተከላ ቦታ ልየታና ካርታ ስራ የተሰራ ሲሆን 23,300,210 ችግኝ ማፍላት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙን ከቦታ ልየታና ካርታ ስራ 99.6% እና ከችግኝ ዝግጅት 90.8% ማድረስ ተችሏል፡፡

በ8 የማህበረሰብ ደንና በ2 የማህበራት ደን በድምሩ በ10 ደኖች የማኔጅመንት ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ በ10 የማህበረሰብ ደንና በ1 የማህበራት ደን በድምሩ በ11 ደኖች የማናጅመንት ፕላን በመሰራቱ አፈፃፀም በመቶኛ 110 ማድረስ ተችሏል፡፡ በ29 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች የደን ቁጥጥርና አጠቃቀም ግበረ-ኃይል ለማጠናከር ታቅዶ በ20 የገጠር ወረዳዎችና በ4 ከተማ አስተዳደሮች/በድምሩ በ23/ማጠናከር በመቻሉ አፈፃፀሙም 82.8% ነው፡፡ በ94348 ሄ/ር መሬት ላይ የሚገኘው የተፈጥሮ

ደን በህ/ሰቡና በደን ጥበቃ ሰረተኞች ትብብር እየተጠበቀ ይገኛል፡፡ እንደዚሁም በ374 የሐይማኖት ተቋማት የሚገኙ ደኖች ተገቢ የሆነ ጥበቃ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡ በ16000 ሄ/ር መሬት ላይ የሚገኘውን የተራቆተ መሬት በመከለል እንዲያገግም ለማድረግ ታቅዶ ከሬድ ፕላስ ፕሮጀክት ጋር በመተባበር በ16,645ሄ/ር የተራቆተ መሬት በመከለልና በመጠበቅ እንዲያገግም እየተደረገ ይገኛል፡፡ የደን ሀብት ለኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ ማሳደግ በበጀት ዓመቱ 18 ሚልዮን የደን የሮያሊቲ ክፊያ ለመሰብሰብ ታቅዶ እስከግንቦት ወር 24,279,766.8 ብር መሰብሰብ በመቻሉ አፈፃፀም በመቶኛ ከ134 በላይ ነው፡፡ 122163.4 ሜ$^3$ የደን ምርት ውጤት  በህጋዊ መንገድ ለማምረትና እንዲዘዋወር ለማድረግ ታቅዶ 125128.67 ሜ3 የደን ምርት ውጤት በህጋዊ መንገድ ወደ ገበያ እንዲቀርብ በመደረጉ አፈፃፀሙም 102% ነው፡፡

## 1.7. የልማት አቅሞች አፈጻጸም

### 1.7.1.የሰው ኃይል ልማት

የሰው ሃብት ልማት ስረዓቱን ማሻሻልን በሚመለከት ለመንግስት ሰራተኞ የተሰጠ የረጅም ጊዜ አመታዊ የስልጠና እቅድ ወ 50 ሴ 50 ድ 100 ሲሆን ክንውን ወ 107 ሴ 199 ድ 306 አፈጻጸም 100% ተከናውኗል፡፡ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ 5 ባለሙያወች ወደ ዩኒቨር ሲቲው እንድገቡ፥ የቀበሌ ግብርና ጣቢያ ባለሙያወች  179 ለሚሆኑ ባለሙያዎች፥ ጤና አክስትንሽን ከደረጃ 3 ወደ ደረጃ 4 የገቡ 111፥ ድንገተኛ ጤና ተክንሽያን ከደረጃ 3 ወደ ደረጃ 4 የገቡ 11 በማሳተፍ የረጅም ጊዜ ስልጠና ዞናችን ከኮታው በላይ ማስጠቀም ተችሏል፡፡ በተቸማሪ ለሰራተኞች የተሰጠ የአጭር ጊዜ ስልጠና እቅድ 3,000 ይዘን ክንውኑ 3611 የሚያመላክት ሲሆን አፈጻጸም 100% ቢሆንም የጥራት ችግር ያለበት እንደሆነ ተገምግሟል፡፡

የተቋማትን ውጤታማነት በአደረጃጀት ከማጎልበት አንጻር ምላሽ ያገኙ የተናጠል ስራ መደቦች ጥያቄወች ብዛት እቅድ 26 ክንው 18 አፈጻጸም 69.2 ሲሆን በመምሪያችን ተጠይቀዉ ምላሽ ያላገኙ በመኖራቸው አፈጻጸሙ ዝቅ እንድል ሁኗል፡፡ ለስራ መደቦች የደረጃ ማሻሻያና የስያሜ ለውጥ የተደረገባቸው ተቋማት እቅዳችን 1 ሲሆን ይህንኑ ማከናወን ተችሏል፡፡ በአዲስ ለተቋማት የተፈቀዱ የስራ መደቦች ስንመለከት 205  የስራ መደቦች በአድስ መልክ ተፈቅደው ስራ ላይ እንድውሉ በመደረጉ የዞናችንን የተቋሞችን ችግር ከመፍታታቸውም በተጨማሪ የስራ አጥ ቁጥር እንድቀንስ ማድረግ ተችሏል፡፡

የሰራተኞች የስራ አፈፃፀም ምዘና ስርዓቱን ማሻሻል በሚመለከት በዞናችን የ6 ወር የስራ አፈጻጸም ምዘና ውል የያዙ  እና መለካት ያለባቸው ሰራተኞች በተመለከተ ውል መያዝ ያለባቸው ሰራተኞች ብዛት ወ 15,069 ሴ 9,390  ድ 24,459 ሲሆኑ ውል የያዙ ሰራተኖች ሁሉም 24,459 አፈጻጸም

100% ኣመላከታል። የ6ወር የስራ አፈጻጸም የተሞላላቸው ሰራተኖች የስራ አፈጻጸም ሊሞላላቸው የሚገባ ወ 15,069 ሴ 9,390 ድ 24,459 ሲሆኑ የተሞላላቸው ወ 14,657 ሴ 8,976 ድ 23,583 አፈጻጸም 96.41% በጥቅል ከምዘና አኳያ የግቡ አፈጻጸም 98.21% ያመላክታል። ከምዘና አኳያ ከጊዜ ወደ ጊዜ በቁጥርም ሆነ በጥራት እየተሻሻለ የመጣ አፈጠጻጸም መኖሩን ያሳያል።

የለውጥ አመራርና አደረጃጀት ስራዎች አተገባበርን ከማሻሻል አንጻር የ2017 ዓ.ም የሪፎርም ስራውን አጠቃላይ አመራሩና ሁሉም ሰራተኞች በተገኙበት ገምግመው በአፈጻጸማቸው ከፍተኛ ውጤት ላመጡ ተቋማትና ሰራተኞች እውቅናና ሽልማት የሰጡ ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች በ29 ወረዳ/ከተሞች እና በዞን ደረጃ አቅደን 26 ወረዳና ከተሞች እውቅና የሰጠን ሲሆን አፈጻጸሙ 90% ያመላክታል። በአፈጻጸማቸው ከፍተኛ ውጤት ላመጡ የመንግስት ሰራተኞች ከወረዳ/ከተማ እስከ ዞን ድረስ ከፍ ያለ እውቅናና ሽልማት ተሰጥቷል። የለውጥ መሳሪያወችን አሟልተው የሚተገብሩ ተቋማት እቅድ 725 ክንውን 669 አፈጻጸም 92.27% ነው። ሞደል ተቋማት መፍጠር እቅድ 109 ክንውን 146 አፈጻጸም 100%። የተቀመሩና የሰፉ ተሞክሮወች ብዛት እቅድ 51 ክንውን 67 አፈጻጸም 100% በማከናወን በጥቅል የለውጥ አሰራርና አደረጃጀት ስራወችን ከመተግበር አኳያ የግቡ አፈጻጸ 95.5% እንደሆነ ያመላከታል። በሂደቱ በርካታ ትምህርት የሚወሰድባቸው ስራወች የተጀመሩ ሲሆን ጥራት እና ጥቅም ላይ ማዋል ላይ ኣሉ ክፍተቶችን መሙላት እንደሚያስፈልግ ግምገማችን ያሳያል።

የተቋማት ድጋፍና ክትትል ስራን ከማጎልበት አንጻር በበጀት አመቱ ክትትልና ድጋፍ የሚደረግላቸው ተቋማት እቅድ 725 ክንውን 697 ከአንድ እስከ 4 ጊዜ በድግግሞሽ የደገፍናቸው ሲሆን አፈጻጸም 96% ያመላክታል። ከድጋፍ የምናገኘውን ግብረ መልስለሁሉም እንድደርሳቸው ማድረግ ተሞክሯል። በተጨማሪም በምስለ ተገልጋይ በዞን የተዋቀረ ቡድን እና በወረዳና ከተሞች በራሳቸው ፍተሻና ድጋፍ ተደርጓል።

ዲጂታል ሲቪል ሰርቪስ ግንባታ አፈጻጸም አንጻር የተቋሙን አገልግሎቶች ድጅታላይዝ ማድረግ የበጀት አመቱ እቅድ 73% ሲሆን ይህንኑ 73 በማከናወን እቅዳችንን 100% መፈጸም ተችሏል። የመረጃ ቋት በማልማት መረጃ አየያዝና አጠቃቀምን ማሳደግ እቅድ 29 ክንውን 24 (82.7%) መፈጸም ተችሏል። የተቀናጀ ሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ስርአትን አጠናክሮ መተግበር እቅድ 30 ሲሆን ክንውን 30 (100%) መፈጸም ተችሏል። የግቡ አፈጸፀም 87.3% ሲሆን በበጀት አመቱ ድጅታላይዜሽን መሰረት ከመጣል አኳያ ከዞን እስከ ወረዳ/ከተሞች/ ድረስ አመርቂ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ቀሪ ወረዳዎችን በቀጣይ አመት ማጠናቀቅ እንደሚያስፈልግ ግምገማችን ያሳያል።

## 1.7.2.ቴክኖሎጅ

ኢትዮ-ቴሌኮም በዞናችን ያለውን የሞባይል ኔትወርክ ጥራት እና ተደራሽነት ለማስፋፋት እስከ 2016 ድረስ በ226 የሞባይል ጣቢያዎች አገልግሎት እየሰጠ ሲሆን የዞኑ  የሞባይል ኔትወርክ ሽፋንን 68 በመቶ በላይ እንደደረሰ የተቋሙ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ በተለይም ከለውጡ በኋላ የሞባይል ጣቢያዎችን በመገንባት፣ በማስፋፋት እና ደረጃቸውን በማሳደግ የሞባይል ኔትወርክ ተደራሽነት እና የአገልግሎት ጥራቱን ለማሻሻል ተችሏል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት በ29 ወረዳ እና ከተሞች 47 አቅደን 45  አዲስ የሞባይል ጣቢያ ግንባታዎች የተጠናቀቁ እና ስራ የጀመሩ ሲሆን ቀሪዎቹ 2 በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ በበጀት ዓመቱ በድምሩ 271 በላይ የሞባይል ጣቢያዎችን የማስፋፊያ እና የማይክሮዌቭ አቅም የማሳደግ ስራ በመስራት የሞባይል ኔትወርክ አገልገሎት የማሻሻል ስራ ተሰርቷል፡፡

የቴክኖሎጅ መሰረተ ልማት ተደራሽነትንና የአሰራር ስርዓት ለማሳደግ በተከናወነ ስራ እስከ 2016 በጀት ዓመት የነበረውን 22 የወረዳ ኔትወርክ ማዕከላት በ2017 በጀት ዓመት ማስቀጠል የተቻለ ሲሆን የቴክኖሎጂ ማሻሻያ የተሰራላቸው 3 ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ የችሎት አገልግሎት መስጠት የጀመሩ የሉም፡፡ እስከ 2017 ባለው ጊዜ ውስጥ 2 የማህበረሰብ የመረጃ ማዕከላት አገልገሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም እስከ 2017 በጀት ዓመት ሚኒ ዳታ ማዕከል ባይኖርም 2 ሲስተሞችና 7 ዌብሳይቶች ተሰርተዋል፡፡ እነዚህ እንደተጠበቁ ሆነው በሳይንስና ቴክኖሎጅ ዘርፍ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ወጣቶች የፈጠራ አቅም ለማጎልበት ከተሞች ላይ የወጣቶች ሳይንስ ካፌ ተደራጅተው አገልግሎት ከመስጠጥ አንፃር፣ በከተሞች የስማርት ሲቲ የደህንነት ካሜራ መሰረተ ልማት ዝርጋታና ቴክ እስታርታፕ ማዕከላት መፍጠር ገና ያልተሰሩ ስራዎች ናቸው፡፡

## 1.7.3.መሰረተ ልማት

መንገድ ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፓለቲካዊ መስተጋብር ለማሳለጥ የሚያስችል ግንባር ቀደም የመሰረተ ልማት ዘርፍ ሲሆን ግብርናውን ከቴክኖሎጅና ግብአት ጋር በማስተሳሰር ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር፣ የማምረት ባህሉ እንዲለወጥ፣ የትራንስፖርት ወጪ እንዲቀንስ፣ አዳዲስ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች እንድቋቋሙ እና በግብርናው መስክ ኢንቨስትመንትን እንዲስፋፋ በማድረግ ኢኮኖሚያዊ እድገቱን በማሳደግ ቀጥተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ በ2017 በጀት ዓመት በዞናችን በፌደራል በጀት፣ በክልል በጀት፣ በወረዳ በጀት እና በህብረተሰብ ተሳትፎ የተገነቡ የደረጃ ማሳደግ፣ የጥገናና የአዲስ መንገድ ግንባታ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን በቅድ ለያዝናቸው አዲስ መንገድ፣ ቀረጣና የአፈር ድልዳሎ እንደሁም ለመንገድ ጥገና ከወረዳ አስተዳደር ም/ቤት 50 ሚሊዮን ብር ለማስመደብ አቅደን 90,683,000 ብር ማስመደብ ተችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ከማህበረተሰብ ተሳትፎና ከአጋር አካላት 65 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅደን 144,543,740 ብር መሰብሰብ ችለናል፡፡

በህብረተሰብ ተሳትፎ በጀት በርካታ አዳዲስና ነባር የመንገድ ጥገና ስራዎች የተሰሩ ሲሁን በተጨማሪ ወረዳዎች ያለባቸውን የበጀት እጥረት ተቋቁመውና ለመንገድ መሰረተ ልማት ቅድሚያ በመስጠት በወረዳ አሰተዳደር ም/ቤተ በጀት 273 ኪ/ሜ የመንገድ ጥገና፣ 19 እስትራክቸር፣ 24.2 ኪ/ሜ አዲስ መንገድ የቆረጣ ስራ፣ 4 ኪ.ሜ የጠጠር ማልበስ ስራ 130 ሜ$^3$ በጋቢዮን ጥገና እና 6.43 ኪ.ሜ የመንገድ ዲዛይን ስራ መስራት ተችሏል፡፡

በዚህ ቀውስ ውስጥ ሆነን የተሰራው ስራ አበረታች ቢሆንም የተወሰኑ ወረዳዎች ለመንገድ ግንባታ የሚሆን በጀት በወረዳ ምክር ቤት ካጸደቁ በኋላ ለገጠመን የጸጥታ ችግር ተጠቀምነው በሚል ሰበብ ከዛሬ ነገ ይሰራልናል እያለ ይጠብቅ የነበረውን ህዝብ ተስፋ ከማስቆረጥም በላይ በመንግስት ላይ አመኔታ እንዲያጣና እንዲጠራጠር አድርገውታል፡፡

የዞናችን ህዝብ ከገጠመው የመንገድ ተደራሽነት ችገር የተነሳ ለመንገድ መሰረተ ልማት የሚጠየቀውን ሁሉ ለመስጠት የወሰነ በመሆኑ ያለምንም ክፍያ የግል መሬቱን፣ የተከለውን ባህርዛፍና አትክልት ከመስጠቱም በተጫማሪ ከእለት ጉርሱ ቀንሶ ብር በማውጣት፣ የወልም ይሁን የግል ሃብቱን በጋራ ወስኖ በመስጠት እና በሀገር ውስጥ እና በውጭ አገር የሚኖሩ ልጆቹ ብር አሰባስቦ 110.7 ኪ/ሜ የመንገድ ጥገና፣ 2 ስትራክቸር፣ 14 ኪ/ሜ የመንገድ ድዛይን እና 101.9 ኪ/ሜ የመንገድ የቆረጣና 30.2 ኪ.ሜ የአድስ መንገድ ጠጠር ማልበስ ስራ መስራት ተችሏል፡፡ በመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታ ላይ የማህበረሰቡ ተሳትፎ እያደገና እየጨመረ የመጣ ቢሆንም በዞናችን ያለውን ስር አንገብጋቢ የመንገድ ጥያቄ የሚፈታ አይደለም፡፡ ይህ በሆነበት ከወረዳ በጀታቸው ሳይመድቡና በወረዳቸው ላይ ሰፊ የማህበረሰብ ደን እያለ ያንን መጠቀም ሳይችሉ ወደ ላይ የይሰራልን ጥያቄ የሚያቀረቡ ወረዳዎችም አሉ፡

በሌላ በኩል በያዝነው በጀት አመት የክልሉ የመንገድ ቢሮ አንድ ኮንክሬት ድልድይ እና ሁለት ተጠልጣይ ድልድይ እንድንሰራ የሰጠን ሲሆን የጸጥታውና የነዳጅ ችግር የፈተነንም ቢሆንም ሁሉንም 100% ማጠናቀቅ ችለናል፡፡

ምንም እንኳን በክልሉ መንግስት አዳዲስ መንገዶች ባይሰሩልንም የዞናችንን ህዝብ እያስተነፈሰልን ያለው የወሎ ጥገና ጽ/ቤት ሲሆን በጀት ዓመቱ በሰው ሃይል፣ በመደበኛ እና በወቅታዊ የጥገና ፕሮግራም 870 ኪ/ሜ መንገድ ለመጠገን በእቅድ የተያዘ ሲሆን በብዙ ርብርብ 100% መጠገን ተችሏል፡፡ ለዚህም አፈጻጸም የበቃው ከባለፈው ዓመት ልምድ በመውሰድ የመንገድ ጥገናው ከመጀመሩ በፊት የከፋ የጽጥታ ችግር የሌለባቸውን ፣ በክረምቱ ዝናብ ምክንያት ለመስራት

የማያስቸግሩን እና  ቀድመው መሰራት ያለባቸውን ወረዳዎች ተለይተው ወደስራ በመገባቱ፣ በቅድ ተይዘው በወቅታዊ የጸጥታ ሁኔታ አስቸጋሪ የሆኑትን መስመሮች በወረዳው አስተዳደር ጥያቄ መሰረት ወደሌላ መስመር ተቀይሮ መሰራት መቻሉ፣  የጥገና ፅ/ቤቱ ከራሱ ማሽን በተጨማሪ የዞንና የኪራይ ማሽን በመጠቀሙ፣ የመንገድ ጥገናው በሚሰራባቸው አብዛኛው ወረዳ ከሶስተኛ ወገን ነፃ የሆነ ኳሪሳይት ማቅረባቸው፣ በስራ ላይ ያሉ የተቋሙም ይሁን የኪራይ ማሽኖች በማንኛውም ግዳጅ እንዳይያዙ የዞኑ ከፍተኛ አመራር አቅጣጫ በማስቀመጡ እና የመንገድ መምሪያውና የጥገና ፅቤ/ቱ የተሻለ ቁርኝትና ክትትል በመኖሩ ነው፡፡

ዞኑን ከሌላ ከዞን እና ከሌሎች ክልሎች ማገናኘት የሚችለው የፌደራል የአስፓልት መንገድ ሲሆን በብዙ ችግር ውስጥ ቢሆኑም አሁን በስራ ላይ ያሉት ሀይቅ - ብሰቲማ - ጭፍራ እና ግሸን መገንጠያ - ግሸን ያለው አስፓልት መንገዶች በስራ ላይ ሲሆኑ ለብዙ አመት ተቋርጦ የነበረው የመካነ ሰላም ከተማ የአስፋልት መንገድ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ ቢሆንም ግን የዞኑ የአስፓፋልት ሽፋን ደሴና ኮምቦልቻ ከተማን ጨምሮ 278.7 ኪ/ሜትር ብቻ ነው፡፡ ይህም ካለን የህዝብ ብዛት ሲነጻጸር 0.08 ኪ/ሜ ለ1000 ህዝብ ማለት ነው፡፡ ከቆዳ ስፋቱም ቢሆን 15.02 ኪ/ሜ ለ1000 ኪ/ሜ እስኩየር ማለት ነው፡፡ በዞናችን ካለንም አጠቃላይ 3,912.548 ኪ/ሜ የመንገድ ሺፋን ሲነጻጸር ደግሞ የአስፋልት ድርሻው 7.1 % ብቻ ነው፡፡

የደቡብ ወሎ ዞን ህዝብ ከብዙ ጥያቄዎቹ መካከል አንዱ የኢ-ፍታሃዊነት ጉዳይ ሲሆን በለውጡ ማግስት የለውጡ መንግስት ከኢ-ፍታሃዊነት ጥያቄዎቹ መካከል አንዱ የሆነውን የአስፓልት መንገድ 462.45 ኪ/ሜ  መንገድ እንዲሰራ በጀት ተመድቦ እና ውል ተወስዶ ወደስራ በመገባቱ የዞናችን ህዝቡ ለተሰጠው ምላሽም ከልብ ያመሰገነ ቢሆንም አንዳንዶቹ ከጦርነት በፊት ቀሪዎች ደግሞ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት የተቋረጡ ሲሆን አሁን ላይ የዞኑ ህዝብ በለውጡ ያገኘው የመልማት ጭላጭል ተመልሶ በመደፈን ላይ ስለሆነ የዞኑንም ሆነ የክልሉን ርብርብ የሚጠይ ጉዳይ ነው፡፡

የውሃና ኢነርጂ ዘርፍ ዋና አስተባባሪና ፈጻሚ ሃይሉን፣ እንዲሁም ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ለቀጣይ ስምሪት ዝግጁ ማድረግ የሚያስችል ዞናዊ የንቅናቄ መድረክ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና ከተሞች ከፍተኛ የመንግስት አመራሮች፣ በየደረጃው የሚገኝ የውሃና ኢነርጂ መዋቅር ማኔጅመንት አባላት እና የዞን መምሪያ ጠቅላላ ሰራተኞች የተሳተፉበት “አመርታዊ የውሃና ኢነርጂ መሠረተ ልማት ንቅናቄ” በዞን ደረጃ የተመራ ሲሆን መድረኩ እስከ ውሃ ጣቢያ ድረስ በድምቀት ተካሂዷል፡፡ በንቅናቄ መድረኮቹ ለመጠጥ ውሃ ግንባታ 3,878,367 ብር፣ ጥገና ብር 716,344 ብር የተሰበሰበ ሲሆን 1,122,464 ብር ደግሞ መቆጠብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶች የውሃ ታሪፍ ለማስጠናትና ለመወሰን የነበረውን ተግዳሮት በማለፍ ታሪፍ ከ65.15% እስከ 100% ማስወሰን ተችሏል፡፡ በሌላ

መልኩ ከዞን እስከ ወረዳ በተቀናጀ አሰራር፣ ክትትልና ድጋፍ ከወረዳ መደበኛ ካፒታል ብር 39,211,358 ማስመደብ ተችሏል፡፡

በመሪ ዕቅድ ዘመን ስታንዳርድ መሠረት በገጠር በ1.0 ኪ/ሜ ርቀት 25 ሊትር በቀን በሰው ለአነስተኛ ተቋማትና በ0.5 ኪ/ሜ ርቀት 25 ሊትር በቀን በሰው በባለመስመር ተቋም በ2016 ከደረስበት ከ68.4% የንጹህ መጠጥ ዉሃ ሽፋን በመነሳት ወደ 68.9% ማድረስና የተጠቃሚውን ቁጥር በ2016 ከተደረሰበት 1,617,591 ወደ 1,720,096 ማሳደግ ዕቅድ ተይዞ የተፈጸመው በገጠር አዲስ ተጠቃሚ 132,392 በማከናወን የተጠቃሚውን ቁጥር በ2016 ከተደረሰበት 1,617,591 ወደ 1,749,983 ማሳደግ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በከተማ በ0.25 ኪ.ሜ ርቀት ከ30-80 ሊትር በቀን በሰው እንደ የከተማ ምድባቸው በ2016 ከደረስበት ከ69.07% የንጹህ መጠጥ ዉሃ ሽፋን በመነሳት ወደ 70.07% ማድረስና የተጠቃሚውን ቁጥር በ2016 ከተደረሰበት 234,196 ወደ 248,196 ማሳደግ ታቅዶ የተከናወነው በከተማ አዲስ ተጠቃሚ 49,272 በማከናወን የተጠቃሚዉን ቁጥር በ2016 ከተደረሰበት 234,196 ወደ 283,468 ማሳደግ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በዞኑ 116,505 ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ የ0.75% ሽፋን በማሳደግ፣ በ2016 ከተደረሰበት 1,851,787 ህዝብ ወደ 1,968,292 በማድረስ ሽፋኑም ከ68.35% ወደ 69.1% ማድረስ ታቅዶ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን መፈጸም የተቻለውና አሁን የደረስንበት አፈጻጸም፡- በዞን ደረጃ አዲስ ተጠቃሚ ወ 181,664 በማከናወን የተጠቃሚዉን ቁጥር በ2016 ከተደረሰበት 1,851,787 ወደ 2,033,451፣ የንጹህ መጠጥ ውኃ ሽፋን በገጠር የ1.75% ጭማሪ በማድረግ ከ68.4% ወደ 70.15%፣ የንጹህ መጠጥ ውኃ ሽፋን በከተማ የ3.52% ጭማሪ በማድረግ ከ69.07% ወደ 72.59% እንድሁም የንጹህ መጠጥ ውኃ ሽፋን በዞኑ 2.15% ጭማሪ በማድረግ ከ 68.35 % ወደ 70.5% ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

የአነስተኛ ገጠር መጠጥ ውሃ ጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ በተመለከተ በወረዳ አቅም የማህበረሰብ የአነስተኛ የመጠጥ ውኃ መገኛ ጥናት 406 ታቅዶ 723 (178.1%)፣ በወረዳ አቅም የማህበረሰብ የአነስተኛ የመጠጥ ውኃ ዲዛይን 406 ታቅዶ 639 (157.4%) እና በዞን መምሪያ ደረጃ የጥናትና ዲዛይን ዶክመንት ሠርቶ ለትግበራ ዝግጁ ማድረግ 16 ታቅዶ 13 (81.25%) መፈጸም ተችሏል፡፡ አነስተኛ የገጠር መጠጥ ውሃ ግንባታ ማጠናቀቅ 406 ታቅዶ 533 (131.28%) የተፈጸመ ሲሆን በግለሰቦች 50፣ በማህበረሰብ 38፣ በወረዳ መደበኛ ካፒታል በጀት 151፣ የማህበረሰብ መር ፕሮጀክት (CMP) ፕሮግራም 176፣ ሰቆጣ ቃል ኪዳን በውሃ ግንባታ ዘርፍ 17፣ ካልም 11 እንድሁም በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች 90 ተቋማት ተገንብተዋል፡፡

በከተማና ገጠር የትልልቅ የመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ አፈጻጸም በተመለከተ በ2016 በስራ ላይ ከነበሩት 15 ፕሮጀክቶች 8 ፕሮጀክቶችን (አፈጻጸማቸው ከ83%-99.5% የነበሩ) ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን 7 ፕሮጀክቶች (አፈጻጸማቸው 12.5%-80.92% የነበሩ) በዚህ አመት አፈጻጸማቸውን

41.56%-85.03% ባለው ማድረስ ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ በዚህ አመት የተጀመሩ 5 ፕሮጀክቶች 59%-75.3% አፈጻጸም እንድኖራቸው ተደርጓል፡፡

የውሃ ተቋማትን የብልሽት መጠን ከ16.28% ወደ 13.51% ለመቀነስ ቀላል ጥገና 1106 ታቅዶ 1746 (157.87%) መካከለኛ ጥገና 833 ታቅዶ 1441 (160.98%)፣ ከባድ ጥገና 356 ታቅዶ 672 (176.97%) ጠቅላላ 2295 ጥገና ታቅዶ 3859 (168.15%) መፈጸም ተችሏል፡፡ በዚህም 655,925 የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ተደርገዋል፡፡

የውሃ ኮሚቴን ማቋቋምና ማጠናከር በተመለከተ የአዲስ ውሃ ኮሚቴን 406 ታቅዶ 413(101.7%) እና ነባር የውሃ ኮሚቴን ማጠናከር 8506 ታቅዶ 10,655 (125.3%)፣ ዋሽኮ ሌጋላይዜሽን 406 ታቅዶ 699(172.2%)፣ አዲስ የገጠር መጠጥ ውሃ ማህበራት ማደራጀት 4 ታቅዶ 8 (200%) እንድሁም አዲስ የገጠር ውሃ አገልግሎት ማደራጀት 5 ታቅዶ 5 (100%) ማከናዎን ተችሏል፡፡

በከተማ ያለዉን የውሃ ብክነት ከ17.19% ወደ 16.51% በመቀነስ ንጽህናውን የጠበቀ የመጠጥ ውሃ ለህብረተሰቡ ለማዳረስ የውሃ ብክነትን በ0.96% በመቀነስ ከ17.19 ወደ 16.9% መቀነስ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 141.12% ነው፡፡

የዉሀ ጥራት ቁጥጥር ስራዎችን በማከናወን ንጽህናውን የጠበቀ የመጠጥ ውሃ ለህብረተሰቡ ለማዳረስ፡ -_የፊዚካል ጥራት ቁጥጥር 12,600 ታቅዶ በድግግሞሽ 70,032 (>100%)፣ የባክቶሮሎጂካል ጥራት ቁጥጥር 1,949 ታቅዶ 3,281 (>100%)፣ የሳኒቴሽን ቅኝት ስራ 12,600 ታቅዶ በድግግሞሽ 70,032(>100%) እንድሁም ኬሚካል ቴስት የዓመቱ ዕቅድ 406 ታቅዶ 46 (11.33%) ማከናወን ተችሏል፡፡

የዞኑን የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር ውሃ ሃብት ክምችት በማጥናት ለልማት አገልግሎት እንዲውሉ ማድረግ በተመለከተ ልዩ ልዩ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር የዉሃ ሀብት ክምችት ጥናት፣ መረጃ ማሰባሰብና በዳታ ቤዝ ማደራጀት የዓመት እቅድ 1253፣ ክንውን 1665 ወይም 132.88% ሲሆን የዉሀ ብክለትንና ብክነትን ለመከላከል የዉሀ ምንጮችን ማስከለልና የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ስራ ማሰራት የዓመት እቅድ 1000፣ ክንውን 973 ወይም 97.3% ነው፡፡

የተሻሻሉ ኃይል ቆጣቢ ምድጃዎችን ስርጭት ሽፋን ከ61.3% ወደ 65.3% ለማድረስ የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን በሰለጠኑ አምራቾች ማስመረትና ማሰራጨት 49,00 ታቅዶ 48,777(99.5%) በማከናወን የተሻሻሉ ማ/ቆ/ምድጃ ሽፋን በ3.98% በማሳደግ 65.28% ማድረስ ተችሏል፡፡ በገጠር መንደሮችና ከተሞች የኤሌክትሪክ ምጣድና ምድጃዎች ምርትና ስርጭት በማቅረብ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ኤሌክትሪክ ምጣድ 2120 ታቅዶ 3930(185.4%) እና ኤሌክትሪክ ምድጃ/Stove/ 3500 ታቅዶ 7555(215.9%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በገጠር መንደሮችና ከተሞች ከተለያዩ አማራጭ ኢነርጂ ሀይል በማቅረብ (ከፀሃይሃይል) አባዉራ/ እማዉራ ተጠቃሚ ማድረግ 11250 ታቅዶ 6896 (61.3%) መፈጸም ተችሏል፡፡ የባዮጋዝ ማመንጫ ፕላንቶችን በቤተሰብ ደረጃና በተቋማት ተጠቃሚነት

ለማሳደግ የባዮ ጋዝ ግንባታ 564 ታቅዶ 627 (111.2%) በማከናወን 2740 ሕዝብ የቴክኖሎጅ ተጠቃሚ ማድረግ እና ለመኽር እርሻ አገልግሎት የሚውል ባዮሳለሪ ኮምፖስት የመለየት ሰራ ተሰርቷል።

## 1.7.4.የመንግስት ፋይናንስ

የመንግስት ገቢ ከመሰብሰብ አንጻር፡- የቀረቡ የታክስ በዛብኝ ቅሬታዎችን 100% ፈጣን ምላሽ በመስጠት የማጽናት አቅምን ወደ 85% ማሳደግ በግብ ተይዞ የተሰራ ሲሆን 2,084 ቅሬታ አቅራቢ በብር 61,385,795.04 አቤቱታ ይዘው ቀርበው 13 /0.62%/ በመጨመር፣ 1613 (77.93%) በማጽናት እና 458 (21.97%) ወይም (78.03%) በመቀነስ በድምሩ ለ2,084 (100%) ግብር ከፋዮች ምላሽ ውሳኔ መስጠት ተችሏል። ይግባኝ የሚጠየቅባቸዉ የታክስ ዉሳኔዎችን ፈጣን ምላሽ በመስጠት ተከራክሮ የማሸነፍ አቅም ወደ 80% ለማሳደግ በእቅድ ተይዞ የተሰራ ሲሆን ለግብር ይግባኝ ጉባኤ 552 አቤቱታዎች ብር 15,749,287.7 ቀርበው መልስ የተሰጣቸው በማጽናት 336 (62.92%) እና በመቀነስ 198 (37.08%) ወይም (62.92%) በድምሩ ለ534 (96.73%) ውሳኔ እንዲያገኙ ተደርጓል፡ ፡

ከሦስተኛ ወገን የሚሰበሰበውን የግብይት መረጃ በ2016 ከተሰበሰበው 1,365,514,433.75 ብር ወደ 2.4 ቢሊዮን ብር የግብይት መረጃ በመሰብሰብና ለግብር አወሳሰን 100% ጥቅም ላይ በማዋል የሚሰበሰበውን ገቢ ለማሳደግ በእቅድ ተይዞ ብር 1,283,236,430.30 (53.54%) የግብይት መረጃ ተሰብስቦ 100% በማሰራጨት ሁሉንም ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል። በተመረጡ ወረዳዎች ከተሞች በተደጋጋሚ ተመላሽ እና ዜሮ ሪፖርት የሚያቀርቡ የሚጠይቁ የመጋዘን ቆጠራ ስራን በ2016 ከነበረው 0 በ2017 በጀት አመት ወደ 20 ለማሳደግ ግብ ተጥሎ 6 በማድረስ በቆጠራ 1,319,631.55 የሽያጭ ብር እና 184,623.04 ታክስ ብር ማገኘት ተችሏል።

የንግድ ግብር ከፋዮችን ቁጥር 38,354 ወደ 45,145 ለማሳደግ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን 5211 ግብር ከፋዮችን ወደ ንግድ መረቡ በማስገባት የንግድ ግብር ከፋዮችን ቁጥር ወደ 40,256 (89.2%) ማሳደግ ተችሏል። በተመሳሳይ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮችን ቁጥር ወደ 734 ለማድረስ ዕቅድ ተይዞ 598/81.47%/፣ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮችን ቁጥር ወደ 967 ለማሳደግ በዕቅድ ተይዞ 783 /80.97%/፣ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮችን ቁጥር ወደ 38,634 ለማሳደግ በዕቅድ ተይዞ 38,884 (100%) ማስከፈል ተችሏል። እንድሁም 6,513 የኪራይ ገቢ ግብር ከፋዮችን ለማስከፈል ታቅዶ 5,567 (97.3%) ማስከፈል የተቻለ ሲሆን በአጠቃላይ ከመደበኛና ከከተማ አገልግሎት ገቢ 3.010 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ በእቅድ ተይዞ 2,588,082,454.74 ብር (85.98%) መሰብሰብ ተችሏል።

የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር በተመለከተ፡- የተደለደለ መደበኛና ካፒታል በጀት በምክር ቤቶች ማፀደቅና ለታለመለት ዓማ መዋሉን የማረጋገጥ ስራ በእቅድ የተያዘ ሲሆን ሁሉም ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ክልሉ የመደበውን በጀት ክልሉ በሰጠው የጊዜ ገደብ በምክር ቤቶቻቸው አፀድቀው ወደ ስራ እንዲገቡ ተገቢውን ክትትል ተደርጓል፡፡ የተመደበውን በጀት በጠንካራ ክትትልና ድጋፍ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን እየተረጋገጠ የተመራ ሲሆን አጠቃላይ የበጀት አፈፃፀሙን በእስትሪንግና ቴክኒክ ኮሚቴ በየሩብ አመቱ እየተገመገመ እየተመራ ተደርጓል፡፡

ከብድርና እርዳታ የበጀት ምንጮች የሚገኘውን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ለማድረግ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን የተገኘውን 5,033,027,388.71 ብር ለታለመለት አላማ ማዋል ተችሏል፡፡ ውስን ሀብትን ከብክነት ለመከላከል የግዥ ስርአቱን ግልጽ በማድረግና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በእቅድ የተያዘ ሲሆን ከዞን እስከ ወረዳ ድረስ የሴክተር መስሪያ ቤቶች የግዥ ፍላጎት መሰረት ያደረገ እቅድ በማቀድ በማኔጅመንትና በሚመለከታቸው የግዥ አካላት እቅዱ ተገምግሞ እንዲፀድቅና ግዥ በጸደቀው አወቅድ መሰረት እንዲመራ ጥረት ተደርጓል፡፡ በእርዳታና ብደር የሚመጡ ሃብቶችን የግዥ እቅዱ አካል በማድረግ ለአጋር አካላት እቅድን የማስተዋወቅ ስራ የተሰራ ሲሆን በአጠቃላይ በግልፅ ጨረታ የተጠቃለለ ግዥ ተፈፅሞል፡፡ ፍትሃዊነትን፣ ጥራትንና ጊዜን ታሳቢ ያደረገ ግዥ ከመፈጸም አኳያ በፕሮጀክት የሚመጡ ሃብቶች የሚሰሩ ፕሮጀክት ላይ ብልሹ አሰራር የተፈጠራባችና ሃብቱን በጊዜ የመጠቀም ችግር የታየባቸውን ወረዳዎች የማስተካከልና ወደ ትክክለኛ መስመር እንዲሄዱ ተደርጎል፡፡

የውስጥ ኦዲትና ቁጥጥር ስራን በማጠናከር የተጠያቂነት አሰራርን ለማጎልብት በእቅድ ተይዞ የተሰራ ሲሆን 121,230,279.40 ብር ውዝፍ የኦዲት ግኝት ለማስመለስ ታቅዶ ብር 80,127.005.66 (66.09%) እንድሁም 13831929.13 ብር የዘመኑ የኦዲት ግኝት ለማስመለስ ታቅዶ ብር 4269244.57 (31%) ማስመለስ ተችሏል፡፡

## 1.8. የስርአታትና ልማት አፈጻጸም

### 1.8.1.የዳኝነትና ፍትህ ዘርፍ

**በፍትህ ተቋማት የተከናወኑ ተግባራት በተመለከተ፡-** የመንግስትንና የህዝብን ፍትሐብሔራዊ ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር፡- በህግ ምክር በ650,000 ብር የገንዘብ ግምት ያላቸው 188 ጉዳዮች፣ በውል ሰነድ ዝግጅትን 11,261,537.03 ብር የገንዘብ ግምት ያላቸው 9 ጉዳዮች እና ረቂቅ ውል ምርመራ 5,685,098,346.40 የገንዘብ ግመት የያዙ 1,461 ጉዳዮች ጥያቄዎች ቀርበው ለሁሉም ተገቢው ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

የድርድር ስራዎችን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ ከቀረቡት 27,561,186 ብር 445 መዛግብት ውስጥ 13,458,389.06 ብር የገንዘብ መጠን የያዘ 338 መዝገብ በድርድርመቋጨት ተችሏል፡፡ በፍትሐብሄር ጉዳዮች በይግባኝ መልስና ሰበር መልስ ክርክሮች የዐቃቤ ህግ መዛግብት ማጥራት በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 83,284,326 የገንዘብ መጠን 199 መዛግብት ለዐቃቤ ህግ ቀርበው 100% ውሳኔ ያገኙ ሲሆን ወንድ 96 ሴት 294 ድምር 490 የህብረተሰብ ክፍሎችን ነፃ የህግ ድጋፍ ማገኘት ችለዋል፡፡

የአቤቱታ አቀባበል ውሳኔ አሰጣጥ እና የአቤቱታ ተፈጻሚነት ምጣኔ አንጻር በበጀት ዓመቱ ውስጥ 3,782,021.96 የገንዘብ መጠን 437 መዝገብ አቤቱታ ቀርቦ ሁሉም ውሳኔ አግኝቷል፡፡ በፍትሐብሄር ጉዳዮች የቀጥታ ክስና መልስ የዐቃቤ ህግ በ36,494,109.52 ብር በ225 መዛግብት ላይ ክርክር በማድረግ 17,824,589.97 ብር 574 መዛግብት በአሸናፊነት እነድሁም 749,779.70 ብር በ11 መዝገብ በተሸናፊ ሲጠናቀቅ የማሸነፍ አቅም 92% ሲሆን ከዕቅድ አንፃር በገንዘብ 95.53% በመዝገብ ደግሞ 95.96% መፈጸም ተችሏል፡፡ ዐ/ህግ ጉዳያቸውን ይዞ በፍ/ቤት ክርክር የተደረገላቸው ነፃ የህግ ድጋፍ ያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በሚመለከት ጠቅላላ ወንድ 86 ሴት 313 ድምር 399 ባለመብት ሆነዋል፡፡

የዐቃቤ ህግ ከባለፈው ዓመት የዞሩና አዲስ የተከፈቱ 129 መዛግብት እና 15,623,206.55 ብር ላይ የይግባኝ ክርክር የተደረገባቸው ሲሆን 31 መዛግብት 1,194,750 የገንዘብ መጠን ዐቃቤ ህግ አሸናፊነት እና በ29 መዝገብ 1,960,180 ብር በተሸናፊነት የተጠናቀቀ በመሆኑ በበጀት ዓመቱ መዛግብትን የማጥራት ምጣኔ 76% ከዕቅድ አንፃር ደግሞ በመዝገብ 51.66% በገንዘብ 70.68% መፈጸም ተችሏል፡፡

የፍርደኛ ወይም ተከሳሾች ከባለፈው ዓመት የዞሩና አዲስ በተከፈቱ 180 መዛግብት እና 239,054,009.16 ብር ላይ የይግባኝ ክርክር የተደረገባቸው ሲሆን 69 መዛግብት 98,090,733.68 የገንዘብ መጠን ዐቃቤ ህግ አሸናፊነት በ24 መዝገብ 2,140,000 ደግሞ ተሸናፊነት የተጠናቀቀ በመሆኑ መዛግብትን የማጥራት ምጣኔ 87% ሲሆን ከዕቅድ አንፃር በመዝገብ 85.27% በገንዘብ 97.86% መፈጸም ተችሏል፡፡ በሴቶች፣ በህጻናት፣ በወጣቶች፣ በአረጋውያንና በአካል ጉዳተኞች በፍትሐብሄር የቀጥታ ክስና መልስ የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅም አንጻር በነፃ የህግ ድጋፍ ለቀረቡ 217 መዝገብ 32,138,467.90 የገንዘብ መጠን ቀርቦ 97 መዝገብ 11,112,597 ብር በፍርድ ቤት በማሸነፍ ውሳኔ አግኝቷል፡፡ አፈፃፀም በመዝገብ 99.46 በገንዘብ 95.74% ነው፡፡

የፍትህ ተቋሙ ክስ ባቀረበባቸው ጉዳዮች አስቀድሞ ንብረት ፈልጎ ማሳገድን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 15 መዝገብ 2,347,299 ገንዘብ መታገድ ከነበረበት ሀብት ውስጥ በ7 መዝገብ 1,791,860 የገንዘብ መጠን ንብረት ታግዷል፡፡ ለበጀት ዓመቱ የተያዘው ዕቅድ 64% የነበረ ሲሆን አፈፃፀሙ በመዝገብ 46% በገንዘብ 76.33% ነው፡፡ የአፈጻጸም ክስ ከቀረበባቸው ጉዳዮች ውስጥ የማስፈጸም

አቅም አንጻር የፍርድ አፈጻጸም መዛግብትን በበጀት ዓመት ውስጥ ጠቅላላ መዛግብት 392 ሲሆኑ የያዙት የገንዘብ መጠን በድምሩ 65,635,570.48 ብር የያዙ ጉዳዮች ተፈላጊ የነበረ ሲሆን 259 መዝገብ 14,829,198.68 የገንዘብ መጠን የያዙ ገቢ በማድረግ በበጀት ዓመቱ ምጣኔ 98% ዕቅድ አንፃር በመዝገብ 100% በገንዘብ 100% መፈጸም ተችሏል፡፡ በነፃ የህግ ድጋፍ ለተደረገላቸው ዜጎች በ200 መዝገብ 23,716,905.50 የገንዘብ መጠን የያዙ ተፈላጊ ዕዳ የነበረ ሲሆን በ157 መዝገብ 20,092,647.10 ብር ገቢ እንዲፈጸምላቸው የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙ በመዝገብም በገንዘብም 100% ነው፡፡

የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ተደራሽነትና የወንጀል ህግ አፈጻጸም ውጤታማነትን ከማሳደግ አንጻር ምርመራቸው ተጠናቅቀው ለዐቃቤ ህግ ቀርበው ውሳኔ ያገኙ መዝገቦችን 100% ለማጥራት ታቅዶ ለዐ/ህግ ከደረሱት 3,335 የምርመራ መዝገቦች ውስጥ ብዛታቸው 3,329 መዝገቦች ላይ ዐቃቤ ህግ የተለያዩ ውሳኔዎችን የሰጠ ሲሆን 6 በዐ/ህግ ናቸው፡፡ በመሆኑም መዝገቦችን የማጥራት ምጣኔ አፈፃፀሙ 99.82% ነው፡፡ የክስ አይቀርብም የውሳኔ የመጽናት ምጣኔን በተመለከተ እቅዳች 98% ለማድረስ ታቅዶ 88 የሚሆኑ መዝገቦች ቀርበው 69 የፀኑ ሲሆን 2 የተሻሩ በመሆናቸዉ አፈጻጸሙ 97.18% ነዉ፡፡

የወንጀል መዛግብት የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅምን ከማሳደግ አንጻር የክርክር መዝገቦች የመርታት ምጣኔ 95.8 በመቶ ለማድረስ በዕቅድ ተይዞ ክርክር ከተደረገባቸው 2,898 የክስ መዝገቦች ውስጥ 1,489 መዝገቦች በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠባቸው ሲሆን 1,392 መዝገቦች ላይ የቅጣት ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም 97 መዝገቦች ላይ ደግሞ በነጻ እንደሰናበቱ ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የማስቀጣት ምጣኔ አፈጻፀም 97.58% ነው፡፡ በዚህም በሁሉም ወንጀል ጉዳይ ከቅጣት 264,000 በሙስና ወንጀል ጉዳይ ከክስ በፊት እና በኂላ 991,341.12 ብር ገቢ ሆኗል፡፡ በሁሉም የወንጀል ጉዳዮች 2,264,744.22 ብር በኤግዚቢት ገቢ ተደርጓል፡፡

የዐቃቤ ህግ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነትን በተመለከተ ተከራክሮ የማሸነፍ ምጣኔን 86% ለማድረስ ታቅዶ 48 የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦ ክርክር የተደረገ ሲሆን አጠቃላይ 33 መዛግብት ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ውሳኔ ካገኙት ዉስጥ 30 የይግባኝ መዛግብት ላይ ለዓ/ህግ የተወሰነ ሲሆን 3 የይግባኝ መዛግብት ለተከሳሽ የተወሰነ በመሆኑ የዐ/ህግ ተከራክሮ የመርታት ምጣኔ 90.90% ነው፡፡

የፍርደኛ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነትን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 90% ለማድረስ በእቅድ ተይዞ 155 የይግባኝ እና ሰበር አቤቱታ ቀርቦ ክርክር የተደረገ ሲሆን አጠቃላይ 99 መዛግብት ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ዉሳኔ ካገኙት ዉስጥ 93 የይግባኝ መዛግብት ላይ ለዓ/ህግ

የተወሰነ ሲሆን 6 የይግባኝ መዛግብት ለተከሳሽ የተወሰነ በመሆኑ የዐ/ህግ ተከራክሮ የመርታት ምጣኔ 93.93% ነው፡፡

ህገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከል አቅምን ማሳደግ በተመለከተ በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የፈፀሙ ሰዎችን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 95.8% ማሸነፍ ዕቅድ የነበረ ሲሆን በ11 ወራት የቀረበ የለም ለፍርድ ቤት የቀረቡ መዛግብትን በተመለከተ 4 መዛግብት የቀረቡ ሲሆን እነዚህም ውሳኔ አላገኙም፡፡ በሰው የመነገድ የቀረበ መዝገብ 51 ሲሆን ሁሉም መዛግብት ላይ ዐቃቤ ህግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ለፍርድ ቤት የቀረቡ መዛግብትን በተመለከተ 33 መዛግብት የቀረቡ ሲሆን እነዚህም ውሳኔ አላገኙም፡፡ በቀረቡ የዋስትና ጥያቄዎች በወቅቱ እና በአግባቡ ያለው የዋስትና አስተያየት መስጠት ውጤታማነትን በተመለከተ፡፡ በበጀት ዓመቱ 98% የዋስትና ጥየቄዎችን አስቴየት ለመስተተት ታቅዶ በ12 ወራት ከቀረቡት 888 የዋስትና ጉዳዮች ውስጥ 693 ዐ/ህግ በሰጠው አስተያየት መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ አፈጻፀሙ 79.63% ነው፡፡

የሀብት ምርመራ መዛግብተን በተመለከተ 17,522,457.99 የሚሆን የገንዘብ መጠን ታቅዶ የሚገኝ ሲሆን፣ 10 ጉዳዮች የገንዘብ መጠናቸው ብር 27,666,972.18 የሀብት ምርመራ ስራ እንዲከናወንባቸው ጥቆማዎች ቀርበዋል ከዚህም ውስጥ 1 መዝገብ 8,439,726.85 ብር ገንዘብ በፍትሐብሄር ክርክር ተደርጎባቸው መመለሱ ተረጋግጧል፡፡ 4 መዝገብ 11,357,372.18 ብር ስልጣን ላላው የተላከ 2 መዝገብ 22,000 ካሬ ሜትር ቦታ ውርስ ሊሆን አይገባም የተባለ፣ 3 መዝገብ 9,059,600.00 በዐቃቤ ህግ በምርመራ ላይ ያሉ ናቸው፡፡ የውርስ ጥያቄ ከ 2016 በጀት ዓመት የዞረ 2 መዝገቦች ገንዘብ እና 24,982 ካ/ሜ የከተማ ቦታ በድምሩ የገንዘብ ግምታቸው ብር 22,836,895.80 የያዘ ጉዳይ ለፍርድ ቤት ቀረበው በቀጠሮ ላይ ይገኛል፡፡

የፍትሕ አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነትን ከማሳደግ አንጻር ንቃተ ህግ ትምህርት የተሰጣቸው ዜጎች በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 75% (573,579) ለሚሆነው የክልሉ ህዝብ ንቃተ ህግ ትምህርት ለመስጠት ታቅዶ በፍትህ ስርኣቱ ውስጥ የህብረተሰቡ ሚና ለማሳደግ እና ወንጀልን ለመከላከል ይቻል ዘንድ ለወንድ 37,300 ሴት 30,452 ድምር 67,752 ለሚሆኑ ብረተሰብ ክፍሎች የንቃተ ህግ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ አፈፃፀሙም 11.81% ብቻ ነዉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ህፃናት ወንድ 18,286 ሴት 20,189 ድምር 38,475፣ ወጣቶች ወንድ 7,952 ሴት 4,283 ድምር 12,235፣ ጎልማሶች ወንድ 9,672 ሴት 5,737 ድምር 15,409፣ አረጋውያን ወንድ 1,588 ሴት 45 ድምር 1,633 ናቸው፡፡ የወንጀል አቤቱታ የውሳኔ አሰጣጥ ቅልጥፍና፣ ፍትሃዊነትና ተፈጻሚነት ማሳደግ በበጀት ዓመቱ 513 አቤቱታዎች ቀርበው 438 ውሳኔ ያገኙ ሲሆን አፈፃፀሙ 97.12% ነው፡፡

ለወንጀል ጠቋሚዎችና ምስክሮች የተደረገ ጥበቃን በተመለከተ የአሰራር መመሪያ ለማዘጋጀት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱ ለቀረቡ የጠቋሚዎች እና ምስሮች ጥበቃ ከለላ 100% በዕቅድ

ተይዞ ለ35 ለቀረበ የወንጀል ምስክሮች ጥበቃ ከለላ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡ በተከሳሽና ምስክር አለመቅረብ የመዛግብት መቋረጥ ምጣኔን መቀነስን በተመለከተ የመዛግብት መቋረጥ ምታኔን 3% ለማድረስ ታቅዶ ለፍርድቤት ከቀረቡ 2,898 መዛግብት ውስጥ 328 መዛግብት ተከሳሽና ምስክር በለመቅረብ ስለተቋረጡ አፈፃፀሙ 11.31% ነው፡፡

**የሰላምና ጸጥታ ስራዎች አፈጻጸም፡-** በበጀት ዓመቱ በተሰራው የተናበበ የፖለቲካና የህግ ማስከበር ዘመቻ ሂደት የጠላት ሃይልን ከህዝቡ ለመነጠልና የጠላትን መዋቅር ለማፍረስ የፖለቲካና የጸጥታ ሃይለ በጋራ በመቀናጀትና በጋራ ካውንስል የተሰጠውን ተልዕኮ ወስደዉ ወደ ተግባር መግባት በመቻሉ በርካታ ውጤቶች ተመዝግባዋል፡፡ በኦፕሬሽን ስራችን በአዳንድ የዞናችን አካባቢዎች ሰፊ ቁጥር ያለው የጠላት ተዋጊ ሃይል ተደምስሷል፡፡ በከተማ የተደራጀውን የጠላት የመረጃና የሎጂስቲክስ አቅም የሆነውን ህቡዕ አደረጃጀት (ሴል) በመለየት፣ በማፈራረስና በቁጥጥር ስር በማዋል በተሃድሶ ስልጠና እንዲያልፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚህ ሂደትም ጠላት ይጠቀምበት የነበረውን ሀብት የማምከን፣ በጠላት መዋቅር ውስጥ የሚገኙትን ተዋጊ ሀይልና መሪዎችን በህዝብ ግንኙነት ስራ በሠላም እንዲገቡና እጃቸውን እንዲሰጡ እየተደረገ መሆኑ፣ የጠላት የትጥቅ አቅም እንዲከስም እየተደረገ መሆኑና የቡድን መሳሪያ የመማረክ ሁኔታዎች የተመዘገቡ ውጤቶች ናቸዉ፡፡ በተጨማሪም ደጀን የመፍጠር፣ ተጨማሪ ሀይል የማሰባሰብ፣ የፖለቲካ አመራሩ፣ የፀጥታ አመራሩ እና የመከላከያ ሰራዊታችን ቅንጅትና በመናበብ፣ በሰዉ ሃይል እና በኦፕሬሽን የተሻለ ዉጤት በመምጣቱ የጠላት ሃይልን በብዙ የዞናችን አካባቢዎች ከዋና ዋና መንገዶች ማስወጣት መቻል እና እራስን ችሎ መምራትና የማስተዳደር ተነሳሽነት መፈጠር መጀመሩ መልካም የሚባሉ ስኬቶች ናቸው፡፡

ያለንን የጸጥታ ሀይል በግምገማ ማጥራትና በግንባታ የማጠናከር በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ 3461 በስምሪት የሚተሳተፍ የሠላም አስከባሪ ሀይል (89%) ከዚህ ውስጥ 2762 (80%) የሚሆነው የታጠቀ ሀይል የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ የ TOP 70 ሚሊሻ ሃይል የማደራጀት፣ማሰልጠንና ለተልዕኮ ዝግጁ የማድረግ ስራ በስፋት ለመስራት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ በዚህም በምናስተዳድራቸውና ነፃ በሆኑ 440 ቀበሌዎች ውስጥ 25,690 TOP70 ሚሊሻ ለማሰልጠን ታቅዶ በድምሩ 25,082 ሚሊሻ ማለትም 98% ያህል የሰለጠነ መሆኑ የጸጥታ መዋቅሩን በአዲስ ሀይል በማጠናከር ጉልህ ሚና ተጫውቷል፡፡ የመጀመሪ ዙር መከላከያ ምልመላ 207 ወጣቶችን፣ በሁለተኛ ዙር የመከላከያ ምልመላ 624 በድምሩ በበጀት ዓመቱ 831 ወጣቶችን በመመልመል ወደ ስልጠና እንዲገቡ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ የክልላችንን የጸጥታ ሀይል በሰው ሀይል ከማጠናከር አንጻር 33ኛና 34ኛ ዙር የአድማ መከላከልና መደበኛ ፖሊስ ምዝገባ 461 ወጣቶች የአድማ መከላከል ፖሊስ፣ 137 ወጣቶች መደበኛ ፖሊስ እና 15 ወጣቶች የማረሚያ ቤት ፖሊስ ተቋማትን እንዲቀላቀሉ አመራር ተሰጥቷል፡፡ በ34ኛ ዙር ከዕቅድ በላይ ከ820 በላይ ወጣቶችን መልምለናል፡፡

የተዋጊውን ሀይል የውጊያ ስነልቦና እና የውጊያ አቅምን የሚያሰድጉ የስልጠና ሰነዶችን በማዛጋጀት ለተዋጊ እና አዋጊዎች በተከታታይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ‹‹ጠንካራ ተቋማዊ አቅም ለዘሊቂ ሠላም›› በሚል መሪ መልእክት እና ‹‹በመስዕዋትነት ኢትዮጲያን የሚያጸና አማራዊ አንድነትን እናረጋግጣለን›› በሚል መሪ ሃሳብ የፖለቲካ ሰነዶች ተዘጋጅተው የ TOP 70 ሚሊሻን ጨምሮ ተዋጊ ሀይሉን እና መሪዎችን ለማሰልጠን ጥረት ተደርጓል፡፡ በመጀመሪያ ዙር 2640 ተዋጊ ሀይል እና በሁለተኛ ዙር 710 ተዋጊ ሀይልና መሪዎችን ለማሰልጠን ጥረት ተደርጓል፡፡ በሂደቱም የስነምግባር ጉድለት የታየባቸው የተባረረ 123፣ ከሀላፊነት የወረዳ 1፣ ትጥቅ አዉርደዉ በጀሌ እንዲሰሩ የተደረገ 1፣ የታሰረ 41፣ ማስጠንቀቂያ 4፣ በህግ እንዲጠየይቁ የተደረጉ 2፣ በአጠቃላይ 172 የፀጥታ ሃይልች ላይ ልዩ ልዩ ዕርምጃ በመውሰድ የማጥራት ስራ ተሰርቷል፡፡ እነዚህ ስልጠናዎች የተዋጊው ሀይል ቁርጠኝነትና ሞራል እንዲያድግ፣ መሪዎቹ በኃላፊነት እንዲሰሩ፣ ተነሳሽነቱ እንዲጨምርና ግጭቱን ቀረብ ብሎ እንዲመሩ አቅም ፈጥሯል፡፡ የሎጀስቲክስ አቅም የሚሆን ጠንካራ ደጀን ህዝብ መፍጠር በመጀመራችን 35,185,755 ብር ሀብት ተሰብስቦ ለጸጥታ ሀይል የሎጀስቲክስ አቅም እንዲሆን እየተደረገ ነው፡፡

የኦፐሬሽንና የህግ ማስገበር ስራ አፈጻጸም፡- ከተማ ላይ ተቀምጦ ለጠላት ሀይል የመረጃና ሎጀስቲክስ አቅም ሆኖ ሲያገለግል የነበረን 548 የጠላት ሴል በመያዝ 377 ቱ ተሀድሶ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በድምሩ ከ1265 በላይ የሚሆን የታጠቀና ያልታጠቀ የጠላት ሀይል የሠላም አማራጭን መርጦ ለመንግስት እጅ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

አወንታዊ ሠላም ለመገምባት እየተደረገ ባለው ርብርብ በርካታ ውጤቶችና ተሞክሮዎች ተገኝተዋል፡፡ ከምንም በላይ 19 የዞናችን ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች በራስ አቅም ጸጥታን የመምራት ተነሳሽነትና አቅም መፈጠር መጀመሩ ትልቅ ውጤት ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ 440 የዞናችን ቀበሌዎችም የመንግስትነት ሚናን መወጣት የሚያስችል አቅም መፍጠር መጀመራቸው አወንታዊ ሠላም ግንባታ ሂደታችን ውጤታማነት ማሳያ ተደርጎ የሚታይ ነው፡፡ በሌላ መንገድ ቀበሌዎች ቤት ለቤት በተደረገ ፍተሻም የነፍስ ወከፍ መሳሪያ 86፣ የቡድን መሳሪ (ብሬን) 1፣ ሽጉጥ 34፣ ቦምብ 7፣ ካዝና 17 እና ልዩ ልዩ ጥይቶች 3943 ተይዟል፡፡ የኬላ ፍተሻ፣ ጥበቃና ፓትሮል ስራዎች በማጠናከር የተገኙ ውጤቶች፡- ክላሽ 13፣ የቡድን መሳሪያ 4 (3 ብሬንና 1 ዲሽቃ) እና ልዩ ልዩ ጥይቶች 6172 ተይዟል፡፡ በህግ ማስከበር ስምሪቶች የተገኘ ውጤት አንጻር በጠላት ላይ የደረሰ ጉዳት ፡- የተደመሰሰ ጠላት 860 (17-አመርራ ናቸው)፣ የቆሰለ ጠላት - 791፣ የተማረከ ጠላት - 401፣ በምህረት የገባ 1597 የጠላት ሃይል በምህረት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በሌላ መንገድ እርስበርስ በመታኮስ የሞተ ጠላት 41 የቆሰለ 39 በድምሩ 80 ጠላት ነው፡፡ ከጠላት የተገኘ ጦር መሳሪያ ዲሽቃ 2፣ ብሬን 1፣ ክሊሽ 106፣ ግማሽ አውቶማቲክ 27፣ ቃታ 56፣ ሽጉጥ 17 እና ሌሎች ጨምሮ በድምር 208

የተለያዩ መሳሪያዎች ከጠላት ተማርኳል። ተተኳሽን በሚመለከት የዲሽቃ 80፣ የብሬን 204፣ የክሊሽ 5685፣ የሽጉጥ 1071፣ ሳልች 365 በድምሩ 7405 ጥይቶች ተይዟል።

**አስተዳደራዊ ፍትህ ማረጋገጥን በተመለከተ፡-** የቀረቡ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን ተቀብሎ ፍትሃዊ ውሳኔ በመስጠት የተገልጋዮችን እርካታ ከማሻሻል አንጻር አጠቃላይ የቀረበ አቤቱታ በፆታ ወ 3,800 ሴ 1,779 ድ 5,579 ደረጃውን ጠብቀው የቀረቡ አቤቱታዎች ወ 25 ሴ 11 ድ 36 ናቸው። ደረጃውን ጠብቀው ከቀረቡት ውስጥ የጽሁፍ ውሳኔ የተሰጣቸው ወ 25 ሴ 11 ድ 36 (100%) በመወሰን ሁሉም ውሳኔ ያገኙ አቤቱታዎች ተፈጻሚ እንድሆኑ ማድረግ ተችሏል። በዚህም ተጠቃሚ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ወ 5,977 ሴ 2,521 ድምር 8,498 ናቸው።

## 1.8.2.የባህልና እሴት ልማት

ከባህል እሴቶችና ኢንዱስትሪ ልማት አንጻር መጤ ባህሎችን፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ አመለካከቶችንና አሰራሮችን ለመቀነስ በ172 የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ለ100,000 የህብረተሰበብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ በ183 መድረክ ለ111,319 የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፈጠር ተችሏል። 110 ነባርና 4 አድስ ክብረ በዓላትን ለማልማትና ለማክበር እቅድ ተይዞ 131 ነባርና 4 አድስ ክብረ በዓል ማክበር መቻሉ። የሰላም፣ የመከባበር፣ የመደጋገፍ፣ የመቻቻል እና ሌሎች ጠቃሚ ባህሎች እንዲስፋፉ እና በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲሰርጹ 20 የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት 10000 የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፍጠር ታቅዶ 79 መድረክ 28040 ህብረተሰብ መሳተፉ ተችሏል። 20 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ቀንን ለማክበር ታቅዶ 14 እንድሁም 20 የዞኑን ባህላዊ ተምሣሌቶች /icons/ በመለየት እንዲታወቁ ማድረግና ዕውቅና መስጠት ታቅዶ 14 መፈጸም ተችሏል።

በዞን ደረጃ ዓመታዊ የባህል ፌስቲቫሎችን ማካሄድ 1 ታቅዶ 1፣ ከዞን እስከ ወረዳ የሚካሄዱ ዓመታዊ የኪነ-ጥበብ ውድድሮችን በ6 አይነት የፈጠራ ስራዎችን 110 ማድረስ ታቅዶ 6 አይነት 111 ስራዎች፣ የሥነጽሑፍ እና ቅኔ ምሽቶች 80 በመድረክ እና የሚታደሙ የህብረተሰብ ክፍሎች ብዛት 50000 ታቅዶ 121 መድረክና 41257 ህብረተሰብ፣ ልማታዊ ቲያትሮችን ለህብረተሰቡ ማቅረብ 27 ታቅዶ 31 እና ለ270 በአማተር ኪነ-ጥበብ ከያኒያን በስነ-ጽሑፍ፣ በቲያትር፣ በሙዚቃ፣ በባህል ሙዚቃ መሣሪያ አጨዋወት፣ በስዕልና ቅርጻቅርጽ ሙያ ዙሪያ ስልጠና መስጠት ታቅዶ 204 አማተር ስልጠና መሰጠቱ የሚሉትን ማከናወን ተችሏል።

## 1.8.3.የመንግስት ተቋማትና የአመራር ሚና

ጠንካራና መልካም የመንግስት አስተዳደር ለመፍጠር የተቋማት ግንባታ የሪፎርም ስራዎች እጅግ አስፈላጊ ናቸው። ሪፎርሙ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያልነበሩ አዎንታዊ ውጤቶችን ለማግኘት የመንግስት ስራዎች የሚሰሩባቸው የቆዩ አመለካከቶች፣ አሰራሮች፣ አደረጃጀቶችና ሂደቶች በታቀደና

በተቀናጀ ሁኔታ በአዳዲስ የሚለወጡበት መሳሪያ ነው፡፡ ጠንካራ የማስፈጸም አቅም ያለው ተቋምና መንግስት ሲፈጠር፣ ብቁና ሥነ-ምግባር ያለው እንዲሁም በሚወስዳቸው እርምጃዎች ተጠያቂ ሲሆን የሚችል ባለሙያ ይኖራል፡፡ በመንግስታዊ ጉዳዮች በንቃት የሚሳተፍ ህብረተሰብ ይፈጠራል፡፡ ሁሉም አካላት በህግ የበላይነት አምነው የሚንቀሳቀሱበትና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርዓት ይገነባል፡፡ ሀገራዊ ቅርጽ ከያዘ የሪፎርም አድስ ፓኬጅ ይልቅ ያልተማከለና ለዘርፍ ልዩ ባህርይ ትኩረት የሚሰጥ፣ በእውቀት የሚመራና የሴክተሩን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ሪፍርም የበለጠ ውጤታማ ይሆናል ፡፡ እንድህ አይነት ዘርፍና ተልዕኮ ተኮር የተቋማት ግንባታ ሪፍርም ታክቲክ ስኬታማነት በዋናነት የሚወሰነው በየተቋማቱ የበቁ የለውጥ ሐዋርያት ካለ ነው፡፡ ይህን ለመፍጠር ደግሞ የአመራር ብቃት እጅግ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም የአመራር የፖለቲካ ቁርጠኝነት መረጋገጥ ከለለ በቀጣይ ዓመታት እደርስበታለሁ ያለውን ርዕይ ለማሳካት ከፍተኛ ዕድል የሚሰጥ ይሆናል፡፡ አመራሩ የዞኑን ህዝብ ከድህነት ለማላቀቅና ወደተሟላ ሰላም ለመመለስ የዞኑን መሰረታዊ ችግሮች በየጊዜው እየለየና መፍትሄ እያስቀመጠ መሄድ ይጠበቅበታል፡፡ በሌላ በኩል እንደ ክልል የዕድገት ጉዞ ሲታይ ትምህርት የተወሰደባቸዉ ተግዳራቶች መኖራቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡ እነዚህ ተግዳራቶች በዋነኛነት በሁለት ተከፍለው የሚታዩ ናቸው፡ ፡ አንደኛው የግጭት አዙሪት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የድህነት አዘሪት ነው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ደግሞ ቁልፉ መሳሪያ ፖለቲካ ነው፡፡ ፖለቲካ የግጭትና የድህነት አዙሪትንለመፍታት አይነተኛ ሚና አለው ከተባለ የፖለቲካ በንግስት ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥንና አመራር ሰጭነት ማሻሻል ይኖርበታል፡፡

## 1.9. የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ተግባራት አፈጻጸም

ህዝባዊ ተሳትፎን የሚያጎለብት የመረጃ አቅርቦትና እርካታን ከማሳደግ አንጻር የደንበኞች የመረጃ ፍላጎት ጥናት ማድረግ አንዱ ተግባር ነው፡፡ በመረጃ ማዕከል ውስጥ ደንበኞቻችን ምን አይነት መረጃዎች ቢኖሩ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ለማሳየትና የመረጃ ማእከላትን አፈጻጸም የበለጠለ ማጠናከር የሚያስችል ተግባር የአመቱ እቅድ 19 ሲሆን ክንውን 16 ማለትም 84% ተፈጽሟል፡፡

የመንግስት ኮሙኒኬሽንና የሚዲያ አሰራሮችን ብቃት ማጎልበት የሚችሉ ተግባራት ታቅደው ተፈጽመዋል፡፡ አድስ የማስታወቂያ ሰሌዳ ማቋቋም የአመቱ እቅድ 4 ሲሆን ክንውን 5 (125%) ተፈጽሟል፡፡ ለነባር ማስታወቂያ ሰሌዳ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ የአመቱ እቅድ 304 ክንውን 304 (100%) ተፈጽሟል፡፡ አዳዲስ የመረጃ ማዕከላትን ማቋቋም የአመቱ እቅድ 3 ሲሆን ክንውን 3 (100%) ተፈጽሟል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ነባር የመረጃ ማዕከላት ክትትልና ድጋፍ ከማድረግ አንጻር የአመቱ እቅድ 193 ሲሆን ክንውን 193 (100%) ተፈጽሟል፡፡ አዳዲስ የቲቪ ፓርክ ማቋቋም የአመቱ እቅድ 1 ክንውን 3 (300%) ተፈጽሟል፡፡ ለነባር ቲቪ ፓርኮች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ የአመቱ

እቅድ 35 ክንውን 35 (100%) ተፈጽሟል፡፡ አዳዲስ የሚኒሚዲያ ማቋቋም የአመቱ እቅድ 3 ክንውን 6 (200%) ተፈጽሟል፡፡ ነባር ሚኒሚዲያ ድጋፍ እና ክትትል የአመቱ እቅድ 200 ክንውን 200 (100%) ተፈጽሟል፡፡

የኀብረተሰቡን ልማታዊ አስተሳሰብ ማጎልበት የሚያስችሉ የሚዲያና ኮሚኒኬስን ተግባራት ተፈጽመዋል፡፡ በወሳኝ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይየአቋም መግለጫ ከማዘጋጀት አንጻር የዞኑን መንግስት አቋም የሚያንጸባርቁ አቋም መግለጫ ማዘጋጀትና ማስተጋባት የአመቱ እቅድ 4 ክንውን 6 (150%) ተፈጽሟል፡፡ የፓናል መድረክ ዝግጅትና አፈጻጸም አንጻር በመንግስት ፖሊሲዎች ስትራቴጅዎች ፕሮግራሞችና ወቅታዊ አጀንዳዎች ዙሪያ 4160 የሰው ኃይል የተሳተፈባቸው የተለያዩ የፓናል መድረኮችን ማዘጋጀት ተችሏል፡የአመት እቅድ 96 ሲሆን ክንውን 100 (104%) ተፈጽሟል፡፡ የሚዲያ መግለጫ ከማሰጠት አንጻር በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ መግለጫዎች በዞንና በወረዳ መዋቅራችን አመቻችነት ማሰጠት ተችሏል፡፡መግለጫዎቹ በአካባቢያችን በሚገኙ ሚዲያዎች፣ በተለያዩ የማኅበራዊ ሚዲያ አማራጮች ሽፋን እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ የአመቱ እቅድ 288 ክንውን 341 (118%) ተፈጽሟል፡፡ ምርጥ ተሞክሮ መቀመርና ማስፋፋትን በተመለከተ በመቀመሪያ መስፈርቶቹ መሰረት |የአመቱ እቅድ 96 ሲሆን ክንውን 87 (90.62 %) መቀመርና ማስፋት ተችሏል፡፡

የመረጃ አቅርቦትና ጥራትን ከማሳደግ አንጻር የመረጃ ማሰራጨት ተግባር አንዱ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የተለያዩ የልማት ፎቶዎችን፣ አዋጆችንና ደንቦችን፣ የሴክተር መ/ቤቶች ሪፖርቶችንና የቀድሞ መረጃዎችን በመስጠትና በተለይም በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሄቶች ላይ የወጡ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ለመረጃ ፈላጊዎች በሀርድና በሶፍት ኮፒ ማሰራጨት ተችሏል፡፡ የአመቱ እቅድ 3,576 ሲሆን ክንውን 2,549 (71%) ተፈጽሟል፡፡ መደበኛ የህዝብ አስተያየትን በመጠቀም የመረጃ አቅርቦትና ጥራትን ከማሳደግ አንጻር የአመቱ እቅድ 131 ሲሆን ክንውን 85 ነው፡፡ አፈጻጸም 64.88% ነው፡፡ ከተሰበሰቡት 75 የህዝብ አስተያየቶች ውስጥ 43ቱ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፣ 32 ያህሉ ደግሞ ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ናቸው፡፡ ወቅታዊ የህዝብ አስተያየት መሰብሰብን በተመለከተ ከክልል በሚሰጡ ርዕሶች ዙሪያ ወቅታዊ የህዝብ አስተያየት መሰብሰብ የአመቱ ዕቅድ 4 ሲሆን ክንውን 4 (100%) ነው፡፡ በወቀቱ በመሰብሰብ የመመለስ ስራ ተሰርቷል፡፡

## 1.10. የመልካም አስተዳደር ስራዎች አፈጻጸም

በህዝብ መድረኮች የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ቆጥሮ የመለየት እና የ1 ዓመት እቅድ አዘጋጅተን ወደ ተግባር ለመግባት ተግባሩን የሚመራ ግብረ-ሀይል አደራጅቶ ኦሬንቴሽን ሰጥቶ ከማሰማራት ጀምሮ ሰፊ ርብርብ አድርገናል፡፡ በዚህም ከመልካም አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ

ጋር የተያያዙ 326 ችግሮች ተለይተውና የእቅድ አካል ተደርገው በ2017 በጀት ዓመት 287 ችግሮች ምላሽ እንዲገኙ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም 88% ነው፡፡

የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመፍታት እየተደረገ ባለው እንቅስቃሴ የተለዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ተቋማት ወደ ራሳቸው ወስደው ከሰራተኞቸው ጋር የውል ስምምነት እንዲወስዱ የማድረግ፣ የተጠያቂነት ስርዓት ማስፈን፣ በጠራ መረጃ ላይ የተመሰረተ check and balance ስርዓት የመዘርጋት፣የመልካም አስተዳደር ግብረ ሀይል በማደራጀት ተግባሩን በየጊዜው እየገመገሙ የመምራት እና የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ትግበራ ድጋፍና ክትትል በየተቋሙ የማድረግ የአሰራር ስርዓቶች ተግባራዊ መደረግ በመጀመራቸው የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ከውሸት ሪፖርት በፀዳ መልኩ ጅምር ስራ መታየቱ፣ በየደረጃው ያለ አመራር እና ባለሙያ ተግባሩን የፖለቲካ አጀንዳ አድርጎ በትኩረት ያስያዘ እና ምላሽ ባገኙ ችግሮች የማህበረሰባችንን ተስፋ ያለመለሙ ውጤት ማስገኘት ተችሏል፡፡ ይህንኑ በቀጣዮ በጀት ዓመት ጭምር የበለጠ አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡

ሆኖም ግን እነዚህ ጅምር እንቅስቃሴዎች ቢኖሩም መንግስት የአግልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል በተፈጠረዉ የመልካም አስተዳደር እና የአገልግሎት አሰጣጥ ንቅናቄ መግባባት ልክ ወደ ተግባር የመግባት ዉስንነቶች እዳሉ አሁንም ድረስ በምንፈጥራቸው መድረኮች የህዝብ ትችቶች ይነሳሉ፡፡ በተለይም ደግሞ ህዝቡ የመንግስት ተቋማት በሚሰጡት አገልግሎት አሁንም እርካታ የሌለው መሆኑን የሚያሳዩ ዝንባሌዎች ስላሉ ቀጣይ የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነው፡፡በተይም ቀበሌ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጣችን የከፋ ችግር ዉስጥ ይገኛል፣ቀበሌ ሆኖ ህዝብን የሚያገለግል የመንግስት ሰራተኛ እየጠፋ ነዉ፣የመ/ሰራተኛዉ ወደ አቅርቢያ በሚገኙ ከተሞች በግል ስራ ተሰማርቶ ህዝብን እያገለገከ አለመሆኑን በመድረኮችም በተግባርም ጭምር ማረጋገጥ ተችሎል፡፡ ለዚህ ደግሞ በየተቋሙ ተለይተው ከታቀደ ችግሮች ውስጥ ምላሽ ያገኙ የመልካም አስተዳደር ችግሮች 69% ያህል ብቻ መሆናቸው የህዝቡን ትችት እውነታነት የሚያረጋግጡ መሆናቸውን የተረዳ አመራር ማረጋገጥ የቀጣይ ተልእኮ መሆን ይገባዋል፡፡ በሌላ መንገድ 59 ፕሮጀክቶች በጸጥታ ችግር ምክኒያት ግንባታቸው መቋረጣቸው የዞናችንን ህዝብ የልማት ተጠቃሚነት ላይ ጫና እየፈጠሩ መጥተዋል፡፡ ህዝቡ እነዚህ በተለያዩ ጊዜያት ተጀምረው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ፈጥነው እንዲጀመሩለት በየጊዜዉ በካሄድናቸዉ ታላላቅ መድረኮች ላይ ህዝቡ በተደጋጋሚ ጥያቄዎችን እያነሳ በመሆኑ ይህንን ጉዳይ ታሳቢ ያደረገ አመራር ማረጋገጥ የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫም ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

## 1.11. ክትትልና ግምገማ ስርአት አፈጻጸም

በክልል ደረጃ የተዘጋጀውን የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ መሠረት በማድረግ በየደረጃዉ ኦሬንቴሽን እንዲሰጥ ማድረግ ተችሏል፡፡ በየደረጃው የሚደረገው የኦሬንቴሽን ሂደት ተገቢው ቅድመ ዝግጅት ተደርጉበት በኦሬንቴሽን መሳተፍ ያለበት የሰው ኃይል አስቀድሞ ጥሪው እንዲደርሰው እና

ሳይንጠባጠብ እንዲገኝ ለማስቻል ምቹ የስብሰባ ጊዜ እና ቦታ ተዘጋጅቶለት ፈጻሚው ጋር መግባባት ተችሏል፡፡

የዘርፉ ተግባራት በባህሪያቸዉ የብዙ አካላት ቅንጅት የሚጠይቅ በመሆናቸዉ ከተቋም ዉስጥና ከተቋም ዉጭ ያሉት ለፓርቲዉ በጎ አሳቢ ከሆኑት አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ማከናወን ተችሏል፡፡ ችግር ፈቺ የክትትል እና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት የእቅድ አፈጻጸም ውጤታማነትን ለማሳደግ የተሰራ ሲሆን በዘርፉ የታቀዱ ግቦችን ስኬታማ በሆነ መልኩ ማስፈፀም የሚያስችል ቀጣይነት ያለውና ችግር ፈቺ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የቁልፍ ስራዎች አፈጻጸም አመልካቾችን በማዘጋጀት የዞኖችን አፈፃፀምና የፖለቲካና አቅም ግንባታ ስራዎች ውጤቶችን በመመዘን ደረጃና እውቅና መስጠት ተችሏል፡፡ የሁኔታ ትንተና ሪፖርት በወር ሁለት ጊዜ እየተዘጋጀ የስራ መመሪያ ማድረግ ተችሏል፡፡ ሪፖርቶችን የመገምገም፣ የመስክ ምልከታ ማካሄድ፣ የግምገማ መድረኮችን በማዘጋጀት ግብረ-መልሶችን መስጠት እና በተለያዩ የግንኙነት አግባቦች የመረጃ ልዉዉጥ ማድረግ ተችሏል፡፡

# ክፍል ሁለት፡- የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ

## 2.1. ርዕይ እና ተልዕኮ

### ርዕይ

በ2022 የአማራ ብሔራዊ ክልል በወሳኝ ዘርፎች ንቅናቄ ለኢኮኖሚ ልማት መመንጠቅ አስተማማኝ መሠረት የጣለ እና የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ ባለቤት የሆነ ዞን ሆኖ ማየት፣

### ተልዕኮ

ሁሉንም የዞኑ የልማት ኃይልች፣ ሁሉንም ባለ ድርሻ አካላት በተቀናጀ መንገድ በማሳተፍ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጅ እና በእውቀት መር የኢኮኖሚ ልማት በመታገዝና ያለውን ፀጋ በላቀ ደረጃ በመጠቀም፣ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትን በዘላቂነት በማረጋገጥ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትና ለክልሉ ልማት ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ የሚያበረክት ዕድገት እንደ ዞን ማምጣት፣

## 2.2. የዕቅዱ መነሻዎች፣ ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች፣ የትኩረት መስኮች እና የትኩረት አቅጣጫዎች

### 2.2.1. የዕቅዱ መነሻዎች

- **የ25 ዓመቱ እና የ5 ዓመቱ አሻጋሪ የዕድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅድ፡-** በሃያ አምስት እና በአምስት ዓመት ዕቅድ ከግጭትና ከድህነት አዙሪት ለመውጣት ያለ ተነሳሽነትና ቁጭት መኖሩ፣ በፈጣን እና አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ እንዲሁም ፍትሃዊ እና ዘላቂ የልማት ተጠቃሚነት በየደረጃው ለማረጋገጥ ያለመ በመሆኑ ይህን እውን ከማድረግ አንጻር ለዕቅዱ በመነሻነት ተወስዷል፡፡
- **ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ፣ ቀጠናዊ እና አገራዊ ሁኔታዎች፡-** በክልሉ አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገትና ዘላቂ ልማት ከማረጋገጥና ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ ከመቀነስ አንጻር የበጀት ዓመቱ ዕቅድ ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ፣ ቀጠናዊ እና አገራዊ ሁኔታዎችን ማለትም የዘላቂ ልማት ግቦችን፣ አጀንዳ 2063ን፣ የአየር ንብረት ለውጥን፣ ሉላዊነትን፣ የቴክኖልጅ ዕድገትን፣ የንግድ ትስስርን፣ የኢንቨስትመንት ፍሰትን፣ ቱሪዝምን እንዲሁም በአገር ደረጃ የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች፣ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ማዕቀፍች፣ የተለያዩ ኢኒሽቲቮች፣ የረጅም እና የመካከለኛ ዘመን ዕቅዶች፣ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች፣ የአገሪቱ ርዕይ፣ ያለፈት ዓመታት አገራዊ አፈጻጸሞች እና ትብብርን ከማጠናከር አኳያ የክልሉ የ25 ዓመቱ እና የ5 ዓመቱ አሻጋሪ የዕድገትና

የዘላቂ ልማት ዕቅድ ታሳቢ ያደረጋቸው በመሆኑ ይህንኑ ግምት ውስጥ ማስገባት የሚያስፈልግ በመሆኑ ለዕቅደ እንደ መነሻ ተወስደዋል፡፡

- ዞናዊ ሁኔታዎች እና ያለፈው ዓመት አፈጻጸም፡- ዞኑ ሰፊ የቆዳ ስፋትና እምቅ አቅሞች ያለት መሆኑ፣ ከፍተኛ የወጣት ቁጥር ያለው ዞን መሆኑና ይህም የስራ ዕድል በመፍጠር ወደ ስራ በማስገባት ኢኮኖሚውን በፈጣን ሁኔታ ለማሳደግ እንደ ዕድል የሚወሰድ መሆኑ፣ ታታሪ እና አምራች ህዝብ ያለበት ክልል መሆኑ፣ የሚታሰበውን ልማት ሊደግፍ የሚችል ጠቃሚ ባህል እና እሴቶች ያለት መሆኑ፣ ለዘመናት የተገነቡ ቁሳዊና ሰብዓዊ ሀብቶች መኖራቸው ለሚታሰበው ልማት ምቹ መደላድል የሚፈጥሩ በመሆኑ መነሻ ሆነው ተወስደዋል፡፡
- የዞናችን ህዝብ አዳድስ ፍላጎቶች፡- አሁን ላይ አንገብጋቢ የሆኑ የሰላምና የጸጥታ ችግሮች፣ የስራ አጥነት በተለይም የወጣት ስራ አጥነት ችግር፣ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት፣ ዝቅተኛ ምርታማነት፣ የመሰረተ ልማትና የማህበራዊ አገልግልቶች በሚጠበቀው ልክ ተደራሽና ፍትሃዊ አለመሆን፣ የህዝቡ ሰፋ የመልማት ፍላጎት መኖር እና እነዚህን ለመፍታት እቅድ መተግበር የሚገባ በመሆኑ የዕቅድ መነሻ ሆነው ተወስደዋል፡፡

## 2.2.2. ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

1. የተቋማት የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም መገንባት፡- ተቋማት ከዞን እስከ ቀበሌ ድረስ የመፈጸም አቅም ማሳደግ እንዱሁም የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርምን ተግባራዊ በማድረግ የተቀላጠፈ አገልግልት ተቋማት እንድሰጡ ማድረግ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡
2. የዞኑን ሠላምና ደህንነት እንዲሁም የህግ የበላይነት ማረጋገጥ፣ የዞኑን ሠላምና ደህንነት እንዱሁም የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ ችግርን በውይይት የመፍታት ልምምድን ማሳደግ፣ የፍትህና የፀጥታ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነታቸውን በሚገባ እንዲወጡ ማስቻል፣ የዞናችን ነዋሪዎች በክልሉ መንግስት ላይ ያላቸው አመኔታ እንድጨምር ማድረግ እንዲሁም ምክር ቤቶች የህዝብ ውክልናቸውን በተገቢው መንገድ እንድወጡ ማድረግ በዕቅድ ዘመኑ የሚጠበቅ ይሆናል፡
3. ዞናዊ ወጎችን ዕሴቶችን እና ባህልችን በማዳበር በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ማፍራት፣ ከዚህ አኳያ ከሥርዓታት አንፃር የመንግሥት፣ የማሕበረሰብ፣ የትምህርት ተቋማት፣ የዕምነት ተቋማት፣ የልሂቃን (የፖለቲካና የኢኮኖሚ) እና የሚዲያ ተቋማት ስርዓታትን በማጠናከር በተጨማሪም በታሪክ፣ በባህል፣ በፖለቲካል ኢኮኖሚ እሴቶቻችንን ግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን አድርጎ በስፋት መስራት ያስፈልጋል፡፡
4. ሣይንሳዊ ዕውቀትን የርትዕ ማሕበረሰብ እሴት እና የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት ማድረግ፣ የቴክኖልጂ ተወዳዳሪነት እና ለዘመኑ የሚመጥን ዲጂታል ዝግጁነትን በማሳደግ የሀብት ፈጠራን መሰረት ያደረገ ዕውቀት መር ኢኮኖሚ መገንባት ያስፈልጋል፡፡

5. ምርታማነትንና ቅልጥፍናን በማሳደግ ጥራት ያለው ኢኮኖሚ መገንባት፣ ምርታማነትንና ቅልጥፍናን ማሳደግ ላይ መሰረት ያደረገ ዘመናዊ ግብርና እና አምራች ኢንደስትሪ ላይ ትኩረት በማድረግ ጥራትና ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚ መገንባት ያስፈልጋል፡፡

## 2.2.3. የትኩረት መስኮች

2. **ዘመናዊ ግብርና፡-** ለጠንካራ የኢንዱስትሪ ልማት፣ ለከተማ የምግብ ፍላጎት መሟላት፣ እና ለገጠር ሽግግር ከፍተኛ ሚና እንድጫወት፣
3. **አምራች ኢንደስትሪ፡-** በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት መርህ ወሳኝ የመዋቅራዊ ሽግግር እና የረጅም ጊዜ የዕድገት ምንጭ እንድሆን፣
4. **የማዕድን ልማት፡-** በዋናነት የዘመናዊ ግብርና እና አምራች ኢንደስትሪ ልማትን ስትራቴጂክ ግብዓቶችን በማበልጸግ እንዲደግፍ እንዲሁም ለዘመናዊ ማዕድን ልማት መሠረት እንድጥል፣
5. **ዘመናዊ ቱሪዝም፡-** በዘርፉ የሆኑን የመልማት አቅም ታሳቢ ባደረገ መልኩ በትንሽ ጥረት የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ እንድሆን እና የአገር ገጽታ ግንባታ ሚና እንድጫወት፣
6. **የገጠር ልማት፡-** በገጠር ሽግግር (Rural Transformation) መርህ በሰፊ የኢኮኖሚ መሠረት ላይ የቆመ ከከተማ ኑሮ ጋር የሚመጣጠን ምቹ የሥራ እና የመኖሪያ አካባቢ ማድረግ፣
7. **ከተመት፡-** የወደፊቱ የአገራችን እና የክልላችን የኢኮኖሚ፣ ማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ አውድ እና ማዕከል በመሆኑ ለ21ኛው ክፍለ-ዘመን ስልጣኔ በሚመጥን ደረጃ የከተማ ልማት ዝግጁነት መሰረት መጣል፣
8. **መንገድ፣ ኢነርጂ፣ ዘመናዊ ሎጂስቲክስ እና አይሲቲ፡-** በመሠረተ-ልማትነት ለፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እና ማሕበራዊ ልማት ተደራሽነት ከፍተኛ ሚና እንድጫወቱ፣
9. **ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን፡-** በአጠቃላይ የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት ግብን እንዲያሳካ፣ በተለይም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመሠረተ-ልማትነት፣ በቢዝነስ መስክነት እና በቴክኖሎጂ ለውጥ መሣሪያነት ለእውቀት - መር እና ዲጂታል ኢኮኖሚ፣ ለማሕበራዊ ለውጥ፣ ለመንግሥታዊ አገልግሎቶች እና ማሕበራዊ ፍትህ መሳለጥ ዋና መሣሪያ መሆኑን እንዲያረጋግጥ፣
10. **ትምህርት እና ሥልጠና፡-** ከኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ግቦች አንጻር በተገቢ የትምህርት እና የሥልጠና ፖሊሲ የታረቀ ሰብዓዊ ልማት እንዲታነጽ፣
11. **ዘላቂ የልማት ፋይናንስ፡-** ራስን በመቻል መርህ የዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ልማት መሠረት እንዲሆን፣
12. **የሕግ የበላይነት፡-** የህግ የበላይነት የሰፈነበት የፍትህ ሥርዓት እና መልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ ከማድረግ አኳያ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ከላይ የተጠቀሱት የትኩረት መስኮች የርብርብ ማዕከል ሆነው ተለይተዋል፡፡

### 2.2.4. የትኩረት አቅጣጫዎች

1. ሰላምን፣ ፍትህን እና የሕግ የበላይነት ማረጋገጥ፣
2. ቅልጥፍና እና ምርታማነትን መሠረት በማድረግ በዘመናዊ ግብርና እና በአምራች ኢንደስትሪ ዘርፎች እመርታ መፍጠር፣ በውጤቱም ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ጨምሮ የመዋቅራዊ ሽግግር ዓላማዎችን ማሳካት፣
3. በሣይንስና ቴክኖልጅ ዕውቀት፣ ክህልትና አመለካከት የዳበረ የማሕበረሰብ እሴት መገንባት፣
4. ዞናዊ ወጎችን ዕሴቶችን እና ባህሎችን በማዳበር በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ማፍራት፣
5. በጥብቅ ክትትል በሚፈጸም ፕላን በሚመራ የከተማ ልማት ለማይቀረው ከፍተኛ የገጠር-ከተማ ሽግግር ለዘላቂ ክትመት ቀድሞ መዘጋጀት፣
6. በዘርፎች የበጀት አመዳደብ፣ በዘርፎች አቅም እና ቅንጅታዊ አሠራር፣ በየደረጃው ባለ የአመራር ቁርጠኝነት እና አቅም፣ በማሕበረሰብ ግንዛቤ፣ በተቋማት ሚና፣ እንዲሁም በስትራቴጂ፣ በፖሊሲ እና በሕግ ግልጸኝነት በሚገለጹ የሥርዓታት ርትዕነት ላይ ትኩረት አድረጎ መሥራት፣
7. ከዞን አስተዳደር እስከ ቀበሌ ማሕበረሰብ በሚዘልቅ አስተዳደራዊ እና ሕዝባዊ አደረጃጀት መዋቅር ችግርን በወቅቱ መፍታትን ዓላማ ያደረገ ጥብቅ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ማስፈን፣

## 2.3. የዕቅደ ዓላማ እና ዋና ዋና ግቦች

### 2.3.1. የዕቅደ ዓላማ

በፈጣን እና አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ መቀነስ፣ ፍትሃዊ እና ዘላቂ የልማት ተጠቃሚነት በየደረጃው ማረጋገጥ፣

### 2.3.2. የዕቅደ ዝርዝር ዓላማዎች

- ምርታማነትን እና ቅልጥፍናን መሠረት ያደረገ ፈጣን እና አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ መሰረት መጣል፣
- ድህነትን ለመቀነስ የሚያስችል ስራዎችን መስራት፣
- ፍትሃዊ የልማት ተጠቃሚነትን በየደረጃው ማረጋገጥ፣
- የተረጋጋ የጥቅል ኢኮኖሚ አውድ መፍጠር፣
- ጤናማ፣ በሣይንሳዊ ዕውቀት እና መልካም እሴቶች የተገነባ ርትዕ ማሕበረሰብ መፍጠር፣
- ማሕበራዊ ፍትህ ማስፈን፣

- ምቹ እና ዘላቂ የመኖሪያ እና የሥራ ቦታ በገጠር እና በከተማ መፍጠር፣
- በማልማት፣ በመንከባከብ እና በመጠበቅ በዘላቂነት የአካባቢ ሚዛንን መጠበቅ ናቸው።

### 2.3.3. ዋና ዋና ግቦች

**የእቅዱ ዋናዋና ግቦች የሚከተሉት ናቸው፡-**

1. በዞኑ ውስጥ እየታየ ያለውን የሰላምና ጸጥታ ችግር ለመፍታት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣
2. ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ አሁን ያለውን አማካይ ምርታማነት ወደ በማሳደግ አጠቃላይ ምርት ማድረስ
3. በ2018 ከድህነት ወለል በታች የሚኖረውን ሕዝብ ምጣኔ እንዱሁም የፈርጅ-ብዙ ድህነት ምጣኔን ለመቀነስ አልሞ መስራት፣
4. የሥራ አጥነት ምጣኔን በክልል ደረጃ በ2017 ከነበረበት 10.9 በመቶ በ2018 ወደ 9.9 በመቶ ዝቅ ማድረግ በሚደረገው እርብርብ የድርሻችንን በብቃት ለመወጣት መስራት
5. የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ተሳትፎን ከጥራት ጋር በማመጣጠን ማሳደግ፣
6. በተቀናጀ የጤና ልማት አማካይ በሕይወት የመቆያ ዕድሜን አሁን ካለበት ከፍ ማድረግ፣
7. በክልል ደረጃ የሚታየውን የዋጋ ንረት በጥር 2017 ከነበረበት 18.6 በመቶ ለመቀነስ በሚደረገው እርብርብ የድርሻችንን በብቃት ለመወጣት መስራት

## 2.4. ጥቅል ኢኮኖሚ

### 2.4.1. የስራ ዕድል ማስፋት

በዞኑ ተከማችቶ የቆየው የስራ አጥ ዜጋ ብዛት እና ወደ ስራ ስምሪት ገበያ የሚቀሳቀሰው አዲስ የስው ኃይል ከፍተኛ መጠን ያለው በመሆኑ የስራ አጥነት ችግር አሁንም ከፍተኛ እንደሆኑ መረጃዎች ያመለክታሱ። በመሆኑም እንደ ዓለም አቀፍ የፍልሰት ድርጅት (IOm, 2021) አጠቃላይ የዞኑ የስራ አጥነት ምጣኔ 7.5 በመቶ (በገጠር 4.9 በመቶ በከተማ 17.9 በመቶ) እንደነበር መረጃው ያሳያል።

በመሆኑም የስራ አጥነት ምጣኔው ለስራ ሥምሪት ከተዘጋጀው ኃይል አንፃር ተወስዶ ሲታይ በዞኑ አሳሳቢ ሁኔታ ያለ ከመሆኑም በላይ በከተማ እያደገ የመጣውን ሥራ አጥነት እንዲሁም በተለይ የሴቶች እና የወጣቶች የስራ አጥነት ሁኔታ በቀጣይ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ በመሆኑ ከዚህ አንፃር የስራ አጥነት ምጣኔውን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 10.9 በመቶ 2018 ወደ 9.9 ለመቀነስ ግብ የተጣለ ሲሆን ይህም በከተማ ከነበረበት 20.3 በመቶ ወደ 18.4 በመቶ በገጠር ከነበረበት 8.1 በመቶ ወደ 74.3 በመቶ ለመቀነስ ታቅዷል። ስለሆነም በበጀት ዓመቱ በገጠርና በከተማ 7,386 አዲስ

ኢንተርፐራይዞችን በማቋቋም ለ115908 (50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች ) እና በቅጥር 115908 (50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) በተለያዩ የልማት ሥራዎች ዜጎችን በማሳተፍ በግብርና ዘርፍ ለ44,918 50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች)፣ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለ33,749 50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) እንድሁም ለአገልግሎት ዘርፍ ለ37241 (50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) በድምሩ ለ115,908 (80 በመቶ ቋሚ 50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) ስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር በዕቅድ ተይዞል፡፡

### 2.4.2. የዋጋ ግሽበትን መቀነስ

በ2017 በጀት ዓመት ክልላዊ ተንከባላይ አማካይ የዋጋ ግሽበት ሁኔታ ሲታይ 15.4 በመቶ (ምግብ ነክ የሆኑ ሸቀጦች 15.5 በመቶ፣ ምግብ ነክ ያልሆኑት ደግሞ 15.4 በመቶ) የደረሰ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይህ ማለት እንደ ክልል ከፍተኛ የዋጋ ንረት መከሰቱን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በ2018 በጀት ዓመት አጠቃላይ የዋጋ ንረት ምጣኔን ከነበረበት 15.4 በመቶ ለማውረድ የታቀደ ሲሆን በዚህም ከፍተኛና የተጠናከረ ስራ መስራት ይጠይቃል፡፡ የዋጋ ንረቱን ዝቅ ሊያደረጉ የሚችሉ ተግባራትን ማለትም  ግብርናን ጨምሮ በሁሉም አምራች ዘርፎች ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ መጠን በማሳደግ በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለውን ልዩነት ማጥበብ፣ የግብይት ሰንሰለቱን የሚያሳልጡ ተግባራትን ማከናወን እንዲሁም የመንግስትን የወጪ አስተዳዳር በብቃት መምራት አስፈላጊ ተግባራቶች ይሆናሉ፡፡ የድህንት ምጣኔውን ከመቀነስ አንፃር ክልላዊ የኢኮኖሚ እድገቱን በአማካይ 9.5 በመቶ በማድረስ በ2017 በጀት አመት ከድህነት ወለል በታች ነው ተብሎ የተገመተውን 21.5 በመቶ ህዝብ በላቀ ሁኔታ ለመቀነስ የታቀደ ሲሆን በዚህ ውስጥ ዞናችን የሚኖረውን ድርሻ ባላቀ ደረጃ ለማሳድግም ታቅዷል፡፡

## 2.5. የዘርፎች ልማት

### 2.5.1. አምራች ኢንዱስትሪ

የአምራች ኢንደስትሪ ምርቶች በሁለም ዘርፍ ከመፍለጋቸው እና ረጅም የእሴት ሰንሰለትን መፍጠር የሚችሉ ከመሆናቸውም በላይ በውስን ሀብት ፊት የሚሰፋውን፣ የሚያድገውን እና የሚራቀቀውን እንደ ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ ጤና (መድሃኒት)፣ መጓጓዣ፣ መገናኛ፣ ቴክኖልጂ፣ ደህንነት እና ከፍ ሲልም ሉአላዊነት በመሳሰሉት የሚገለጹ ፍላጎቶችን ማሟላት የሚቻለው በአምራች ኢንደስትሪ ዘርፍ ልማት ነው፡፡ በቴክኒካዊ ደረጃ የአምራች ኢንደስትሪ የዚህ መሠረታዊ ሀብትን የማብዛት፣ የማሳደግ እና የማራቀቅ አቅም የዘርፍ የቋሚ ግብአቶች ምርታማነት ከፍተኛ መሆን ነው፡፡ የሌሎች

አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው የኢንደስትሪ እድገትና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር የሚወሰነው በአብዛኛው በአምራች አንደስትሪ ልማት ስኬት ላይ ነው፡፡

## ስትራቴጅክ ጉዳዮች፡-

- የመሰረታዊ ኢንዱስትሪ ምርቶችን በሀገር ውሰጥ ማምረትና በሂደትም ገቢ ንግድን መተካት በተጨማሪም የውጭ ንግድን ማሳደግ
- ለብረታ ብረት፣ ማሽኖች ልዕለ ማሽኖች የግብዓትና የኬሚካል ቴክኖልጅ መሰረት መጣል

## የትኩረት መስኮች

1. ምርታማነትና ቅልጥፍና
2. የሰው ኃይል አውቀትና ክህልት
3. የቴክኖልጂ ልማት
4. መዋቅራዊ ሽግግር

## የትኩረት አቅጣጫዎች

የአገር ውስጥ ግብዓቶችን በተለይም የግብርና ምርቶችን እና በዞን የሚገኙ የማዕድን ሀብቶችን የሚጠቀሙ የመካከለኛ እና ከፍተኛ የምግብ ነክ፣ የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት፣ የቆዳ ውጤቶች፣ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ እና መድሃኒት ንዐስ ዘርፍችን በማስፊፊት የገቢ ንግድን የመተካት ግብ ማሳካት፣ ለረጅም ጊዜ የኬሚካል እና ከፍተኛ የብረታ ብረት ኢንደስትሪ ልማት መሠረት ለመጣል በፋብሪኬሽን ኢንጂነሪነግ የሽግግር ዝግጅት ማድረግ እንዱሁም የአምራች ኢንደስትሪ ልማት የንዑስ ዘርፍችን ስብጥር ለመዋቅራዊ ሽግግር የሚወሰነው በአብዛኛው በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ስኬት ነው፡፡

**ዓላማ፡- ዘናዊ የፍጆታ የግብዓት ፍላጎት ማሟላት፣ ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የዘመናዊ ግብርና ዓላማዎችን መደገፍ፤**

**ዋና ዋና ግቦች**

**ግብ 1፡- የቋሚ ግብዓቶች ምርታማነት በመጨመር እና አዳዳስ ፕሮጅክቶችን በማስጀመር እንድሁም የመሰረተ ልማት አቅርቦት እና ሌሎች አስፍላጊ ግብዓቶችን በማሟላት የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም በ2017 ከተደረሰበት 61. ወደ 63 በመቶ ማሳደግ፡፡**

**የሚከናወን ዋና ዋና ተግባራት**

- የግብዓትና የኃይል እጥረት መፍታት እንድሁም የመሬት እና የብድር አቅርቦት ችግርን መፍታት

- የሊዝ ፋይናንስና የስራ ማስኬጃ ብድር እና የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች (ከፍተኛ፤ መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች) ብር 1.55 ቢሊዮን ተጠቃሚ እንድሆኑ ማድረግ፡፡
- በአምራች ኢንዱስትሪዎችና በሌሎች ኢንቨስትመንት ዘርፎች የሚያስፍልግ የሀገር ውስጥ ገበያ የሚሸፍን የግብዓት ፍላጎትን ለ19 አምራች ኢንዱስትሪዎች 6798.4 ቶን በማቅረብ የጥሬ እቃ ችግር መፍታት፡፡
- ለ6 መካከድኛ እና ለ2 ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፍልግ የውጭ ገበያ የሚሸፍን 934.06 ቶን በማቅረብ የግብዓት ፍላጎትን ለማሟላት 10.72 ሚሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ችግርን መፍታት፡፡
- 1 ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች ኢንቨስትመንት ፕሮጅክቶች በማጠናከር በተለያዩ ምክንያት ስራ ያቆሙትን ወደ ምርት/ አገልግልት እንድመለሱ ለማድረግ የተለያዩ ድጋፎችን መስጠት፡፡
- በ1 የአምራች ኢንዱስትሪዎችንና ሌሎች ኢንቨስትመንት ፕሮጅክቶችን ምርታማነት የሚያሻሽለ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማካሄድ እና ቴክኖልጅ በመቅዳት ማሸጋገር፡፡

**ግብ 2፡- ለአምራች ኢንዱስትሪዎችንና በሌሎች የሚገኘውን የውጭ ምርት ገቢ / ኤክስፖርት/ በ2018 በጀት ዓመት ወደ 2.3 ሚሊዮን ዶላር ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 2 መካከለኛ ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን ተጨማሪ አቅም በመፍጠር 1 ዓይነት ምርታቸውን ወደ ውጭ ገበያ እንድልኩ በመደገፍ 4.0 ቶን ለውጭ ገበያ በማቅረብ 2.3 ሚሊየን ዶላር ገቢ እንድያስገኙ ማድረግ፡፡

**ግብ 3፡- ስትራቴጂክ የገቢ ምርት የሚተኩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያድኑትን የውጭ ምንዛሬ በ2018 ወደ 10.74 ሚሊዮን ዶላር በማድረስ የሀገረ ወስጥ የገበያ ድርሻ ማሳደግ፡፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ስትራቴጂክ ገቢ ምርትን የሚተኩ 4 በአግሮፕሮሰሲንግ፣ 0 በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት፣1 በጨርቃ ጨርቅና አልባሳትና 3 በእንጨትና ብረታ ብረት በድምሩ 8 ምርቶችን በመለየት ድጋፍ ማድረግ፡፡
- ተኪ ምርት የሚያመርቱ 6 መካከለኛ እና 2 ከፍተኛ በድምሩ 8 አምራች ኢንዱስትሪዎችን መደገፍ ፡፡
- ተኪ ምርት የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍና 9034.06 ቶን ምርት እንድያመርቱ በማድረግ 10.74 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬን ማዳን፡፡

**ግብ 4፡- በአምስት ዓመቱ መጨረሻ ጥናታቸው ተጠናቆ በሁለተኛው አምስት ዓመት የልማት አቅድ በስፊት ለሚጀምሩት የብረታ ብረትና ኢንፎርሜሽን ቴክኖልጅ ዘርፎች ግብዓት የሚሆኑ ምርቶች ላይ መስራት፡፡**

- የብረታ ብረት ማሽን ምርቶችን የሚያመርቱ 1 መካከለኛ ኢንዱስትሪ ማቋቋም፡፡
- ለአማራጭ ሀይል አቅርቦትና የኢንፎርሜሽን ቴክኖልጅ ዘርፎች ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን የሚያመርቱ በዘርፌ በአድስ የሚያመርቱ ባለሀብቶችን መመልመልና ወደ ስራ ማስገባት፡፡

**ግብ 5 ፡- በዞኑ የሀገር ውስጥ ማዕድናትን የሚጠቀሙ ሆነ የውጭ የሚገቡ ማእድናት ላይ እሴት የሚጨምሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለግብርና እና ኮንስትራክሽን ዘርፍ በግብዓትነት የሚጠቀሙ የኬሚካልና ኬሚካል ዉጤቶች የሚጠቀሙ 1 መካከለኛ  አምራች ኢንዱስትሪ ማቋቋም፡፡
- ለግብርና እና ኮንስትራክሽን ዘርፍ በግብዓትነት የሚጠቀሙ ብረት ነክ ያልሆኑና ሌሎች ዉጤቶችን ማምረቻ 1 መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም፡፡

**ግብ 6 ፡- አምራች ኢንዱስትሪዉ በሚያተኩርባቸዉ ዘርፎች በዋናነት የክልሉን ሰብል እና የእንስሳት ሀብት የሚጠቀሙ አግሮ- ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎችን ከግብርና ዉጤት ጋር ማስተሳሰር**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የሰብልና የእንስሳት ሃብት የሚጠቀሙ አግሮ ፕሮሰሲንግ (ምግብና መጠጥ) መካከለኛ 1 ኢንዱስትሪ ማቋቋም፡፡

**ግብ 7 ፡- ለረጅም ጊጊ የኬሚካልና እና ከፍተኛ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት መሠረት ለመጣል በፋብሪኬሽን ኢንጅነሪንግ የሽግግር ዝግጅት ማድረግ፡፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በፋብሪኬሽን ኢንጅነሪንግ የሽግግር ዝግጅት ለማድረግ የሚያስችል ጥናት ማካሄድ

**ግብ 8፡- በማሽን፤ ለአማራጭ ሃይል አቅርቦት በግብዓትና በድጅታል ቴክኖልጅ ወጥ ትስስር ቴክኖልጅዎችን ማስገባት/ መገልበጥ ለአይቲ ዘርፍ ማሻሻልና መፍጠር**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዓለም ላይ ያለት ለዞኑ ተስማሚ የሆኑ አዳድስ ቴክኖሎጅዎችን በጥናት መለየትና ማስገባት/ መገልበጥ
- በአምራች ኢንዱስትሪዉ ዘርፍ 1 ቴክኖሎጅዎችን መቅዳት

- ከተቀዱ ቴክኖልጅዎች ዉስጥ 1 ለተጠቃሚዎች ማሸጋገር

**ግብ 9 ፡- የመንግስት የልማት ድርጅቶች በልዩ ተልኮ እና ድጋፍ በቂ የግል ዘረፍ ስምሪት በሌለባቸዉ ግን ስትራቴጅክ በሆኑ ዘርፎች ላይ እንድሰማሩ ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ብቁ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን መለየትና ዝግጁ ማድረግ
- የመንግስት የልማት ድርጅት ከመንግስትና ከግል ባለሀብቱ ጋር ተቀናጅተዉ የሚሰሩበትን አሰራር መዘርጋት

**ግብ 10 ፡- ለአምራች ኢንዱስትሪዉ ዘርፍ ልማት ወሳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ መሰረተ ልማቶች ላይ ርብርብ ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በተለያዩ ኢንዱስትሪ መንደሮች/ፓርኮች ፕሮጀክቶች ተጀምረዉ ያደሩትን የማጠናቀቅ ስራ መስራት
- 10 መካከለኛ 3 ከፍተኛ በድምሩ 13 ኢንዱስትሪዎች የውሃ እና መብራት አገልግሎት እንድያገኙ ማድረግ
- አዳድስ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶችን በመገንባት የአምራች ኢንዱስትሪዎችንና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ተጠቃሚነት ማሳደግ
- ለ1 እንስሳት እርባታ ፕሮጀክቶች ዉሃ እንድያገኙ ማድረግ
- ለ1 እንስሳት እርባታ እና 5 አገልግሎት መስጫዎች መብራት እንድያገኙ ማድረግ

**ግብ 11:- የመካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከክልል አቀፍ ያላቸውን ድርሻ ከፍ ማሳደግ!**

- በድርጅት ብዛት ከ0.67 በመቶ ወደ 1.2 በመቶ ማሳደግ፤
- በሰው ኃይል ብዛት ከ0.4 በመቶ ወደ 0.55 በመቶ ማሳደግ፤
- በቋሚ ካፒታል ከ0.27 በመቶ ወደ 0.38 በመቶ ማሳደግ፤
- በኢንቨስትመንት ከ0.7 በመቶ ወደ 1.1 በመቶ ማሳደግ!
- በምርት መጠን ከ0.7 በመቶ ወደ 0.9 በመቶ ማሳደግ!
- በተጨማሪ እሴት ከ0.2 በመቶ ወደ 0.32 በመቶ ማሳደግ!

**ግብ 12:- የመካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታማነት በክልል አቀፍ ደረጃ ያለውን ድርሻ ማሳደግ፤**

- ምርት በድርጅት (በሽህ ብር) ከ29.95 ወደ 38 ማሳደግ፤

- እሴት በድርጅት ከ0.1 ወደ 0.16 ማሳደግ
- የሰው ኃይል በድርጅት 25 ወደ 30 ማሳደግ፤
- ካፒታል በድርጅት (በሽህ ብር) ከ1.72 ወደ 3.571 ማሳደግ፤
- ካፒታል በሰውኃይል (ሽህ ብር) ከ34 ወደ 51 ማሳደግ፤
- ምርት በሰው ኃይል (ሽህ ብር ) ከ21 ወደ 25 ማሳደግ፤
- እሴት በሰው ኃይል (ሽህ ብር) ከ0.5 ወደ 1.6 ማሳደግ
- ምርት በካፒታል ከ0.8 ወደ 1.8 ማሳደግ
- እሴት በካፒታል (ሽህ ብር) ከ0.6 ወደ 1.4 ማሳደግ
- ካፒታል እሴት ጥምረት ከ0.8 ወደ 1.8 መቀነስ
- ምንዳ በሰው ኃይል (ሽህ ብር) ከ1.6 ወደ 1.84 ማሳደግ
- እሴት- ምንዳ ከ0.9 ወደ 1.5 ማሳደግ

**ግብ 13- የጨርቃ ጨርቅ አምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ድርሻን ማሳደግ**

- ድሰው ኃይል ከ0.01 ወደ 0.1 ማሳደግ
- ከድርጅት ብብት ከ0.1 ወደ 1.2 ማሳደግ
- ከምርት ከ0.003 ወደ 0.007 ማሳደግ
- ከተጨማሪ እሴት አኳያ ከ0.01 ወደ 0.05 ማሳደግ

**ግብ 14- የምግብ አምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ድርሻን ማሳደግ**

- ለሰው ኃይል ከ0.5 ወደ 1.5 ማሳደግ
- ከድርጅት ብዛት ከ0.7 ወደ 1.7 ማሳደግ
- ከምርት ከ0.3 ወደ 1.3 ማሳደግ
- ከተጨማሪ እሴት አኳያ ከ0.1 ወደ 1.5 ማሳደግ

**ግብ 15፡- የመጠጥ አምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ድርሻን ማሳደግ**

- ለሰው ኃይል ከ0.05 ወደ 0.45 ማሳደግ
- ከድርጅት ብብት ከ0.2 ወደ 0.35 ማሳደግ
- ከምርት ከ0.2 ወደ 0.58 ማሳደግ
- ከተጨማሪ እሴት አኳያ ከ0.1 ወደ 0.55 ማሳደግ

**ግብ 16፡- በበጀት ዓመቱ አሲዳማ መሬትን ለማከም የሚያስችል ኖራ ማምረት**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ወደ ዘረፉ ሊገቡ የሚችለ ባለሀብቶችን በመለየት ግንዛቤ መፍጠር

**ግብ 17፡- ሰፋፊ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ፋብሪካዎችን ፣የቆዳና መጫሚያ ፋብሪካዎችን ማቋቋም**

**የሚካናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የጨርቃጨርቅና አልባሳት የሚያመርቱ 1 መካከለኛ ኢንዱስትሪ ማቋቋም

**ግብ 18- ለመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የተለዩ ድጋፎችን በማድረግ 2 ኢንዱስትሪዎችን ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የደረጃ ሽግግር እድያደርጉ ማስቻል**

- ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት
- ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፍልግ በሀገር ውስጥ ገበያ የሚሸፍን የግብአት ፍላጎትን በመለየት መፍታት
- ኢንዱስትሪዎችን የገበያ ችግር መፍታት፤
- በኢንዱስትሪዎች መካከል ትስስር መፍጠር፤

**ግብ 19 በዘርፉ በቂ የሰለጠነ የሰው ሀይል እንድኖር ማስቻል**

**የሚካናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንተርፕራይዞቹ 3 የሰው ኃይል እንድቀርብ መስራት
- ለምግብና መጠጥ ኢንተርፕራይዞች 11 የሰው ኃይል እንድቀርብ መስራት
- ለኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአት ኢንተርፕራይዞች 101 የሰው ኃይል እንድቀርብ መስራት
- ለብረታብረትና የእንጨት ስራ ኢንተርፕራይዞች 19 የሰው ኃይል እንድቀርብ መስራት

**ግብ 20፡ የቴክኖልጅ ልማትና የመረጃ አያያዝ ውጤታማነትን 100 በመቶ ማድረስ**

**የሚካናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የአምራች ኢንዱስትሪዎች እና የሌሎች የኢንቨስትመንት መረጃዎችን ፕሮፊይል/ 100% ወቅታዊ ማድረግ
- ካሁን በፊት ኔትወርክ ያልተዘረጋባቸው 4 ጽ/ቤቶች ሙለ ለሙሉ እድዘረጋባቸው ማድረግ
- የመረጃ ልውውጥንና አያያዝን በሶፍትዌር የታገዘ በማድረግና ቴክኖልጅዎችን በመጠቀም የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል ፡፡

**ግብ 21፡- በስራ ቦታዎች (ኢንዱስትሪዎች) ውስጥ የስራ ሁኔታዎችን በማሻሻል ሰላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነትን ማሳደግ**

**የሚከናወት ዋና ዋና ተግባራት**

- በድርጅት (ኢንዱስትሪዎች) ሰላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ማማስፍን እንድረዳ አሰሪዎችና ሰራተኞች በነጻ መደራጀት እና የመደራደር መብታቸውን እድጠቀሙ የመደራጀት እና

የመደራደር አቅማቸውን ለማሳደግ የሚደረግላቸውን ድጋፍ ከ 30 በመቶ ወደ 50 በመቶ ማሳደግ

- ድጋፍ ክትትልና ቁጥጥር በማካሄድ በድርጅት /በኢንዱስትሪዎች ያለ አሰሪና ሰራተኞች አለማቀፍና ሀገር አቀፍ ህግጋትን የመፍጸም አቅማቸው ከነበረበት 25 በመቶ ወደ 32 በመቶ ማሳደግ
- በድርጅቶች የሙያ ደህንነት ጤንነት አገልግልት በማጠናከር በስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች በስራ ላይ አደጋና እና በስራ ምክንያት በሚከሰት በሽታ ጉዳት እንዳይደርስባቸው እንድሁም በድርጅት ድንገተኛ አደጋ እዳይከሰት መከላከልን ከ 25 በመቶ ወደ 35 በመቶ ማሳደግ
- በአሰሪዎችና ሰራተኞች መካከል የሚፍጠር የስራ ክርክርን በስምምነት መፍታት ከነበረበት 45 ከመቶ ወደ 55 በመቶ ማሳደግ ቀሪዎቹን የስራ ክርክሮች ደግሞ ህጉ ባስቀመጠው መሰረት በውሳኔ ማጠናቀቅ፡፡

**ግብ 22፡- በአምራች ኢንዱስትሪውና ኢንቨስትመንት ለ3418 (50 በመቶ ሴቶች 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኖች) ዜጎች ስራ እድል መፍጠር፡፡**

- ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማጠናከር እና ስራ ያቆሙ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ምርት በመመለስ ለ123 ዜጎች ቋሚ የስራ እድል እድፍጠር ማድረግ፡፡
- አድስ አምራች ኢንዱስትሪዎቸን በማቋቋም ወደ ምርት በማስገባት 1075 ለዜጎች ቋሚ የስራ እድል እድፍጠር ማድረግ
- በፕሮጀክት ደረጃ ባለ አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ቋሚ የስራ እድል እድፍጠር አልሞ መስራት 225
- በሌሎች ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች 1995 (ሆርቲ ካልቸር በዘመናዊ እርሻ ምርጥ ዘር ብዜት ፣በእንሰሳት እርባታ በደንና ንብ ማነብ በአገልግልት ) የስራ እድል መፍጠር፡፡

## የማስፍጸሚያ ስልቶች

ስትራቴጅክ አምራች ኢንደስትሪ ፕሮጀክት ልየታ፣ ጥብቅ የመዋዕለ ንዋይ ስምሪት፣ የልማት ቀጠና፣ የኢኮኖሚ ዞን፣ የውጭ ንግድና ማሳለጫ ቀጠና፣ የመሰረተ ልማት እና ቴክኖሎጅ ዝርጋታ፣ የመዋዕለ ንዋይ ማበረታቻ ስርዓት እንዱሁም ዘርፍ ተኮር የሰው ሀይል ስልጠና ዋና ዋና የማስፍጸሚያ ስልቶች ይሆናሉ፡፡

### 2.5.2. ዘመናዊ ግብርና

የግብርናው ዘርፍ ለዞናችን ያለው ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ብቻ ሳይሆን ለአብዘሃኛው የዞናችን ህዝብ የኑሮ መሰረትና መተዳደሪያ በመሆኑ እንድሁም ለውጭ ምንዛሬ ግኝት ወሳኝ ሚና ያለው በመሆኑ ለዞናችን ዕድገት የአንበሳውን ድርሻ የሚወሰድና የኢኮኖሚ ዋልታ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም በዞናችን አሻጋሪ የእድገት እና ዘላቂ ልማት ለማምጣት የዘመናዊ ግብርና ምርታማነትና ቅልጥፍና

የማሳደግ ስራ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን ከዚህ አንጻር በመቃኘት የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ እንደሚከተለው ታቅዷል፡፡

የባለ ሁለት ፍኖተ ልማት ስትራቴጅ ማለትም አንደኛው ቴክኖሎጅ መር ኮርሻላዜሽን ግብርና እና ሁለተኛው ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ የተቀናጀ የገጠር ትራንስፎርማሽን ንቅናቄ የግብርና ንኡስ ፕሮግራምን መተግበር ወሳኝ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡ በመሆኑም

**1. ቴክኖሎጅ መር ኮመርሻል ግብርና ዕውን ማድረግ**

- በየግሉ ዘርፍ በግብርና ላይ ያለውን ሚና ማሳደግ
  - የሀገር አልሚዎች
  - የውጭ ቀጥተኛ መዕዋለንዋይ
- የመንግስት የልማት ተቋማትን በግብርናው ዘርፍ ማሳማራት
- አቅም ያላቸውን አነስተኛ አ/አደሮችን ወደ ባለሃብትነት ማሳደግ

**2. ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ የተቀናጀ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ንቅናቄ የግብርና ንዑስ ፕሮግራም**

- በአነስተኛ ግብርና የተሰማሩ ዜጎችን በራስ ጥረትና ትብብር የተሻለ ገቢ ከማግኘት ባለፈ ለተሻለ ህይወት እንድተጉ ማስቻል፡፡
  - የተሻለ ገቢ መፍጠር
  - ጥራት ያለው አኗኗርና የህይወት ዘይቤ ማስፈን
  - ዘመናዊ የገጠር ኢኮኖሚና ማህበራዊ መሰረተ ልማት ማስፋፋት
  - ጠንካራ የገጠር ተቋማት መፍጠር
  - ጽዱ እና ዘላቂ የመኖሪያ አካባቢ ማረጋገጥ

**ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች**

- ዝቅተኛ የሰብል ልማት ምርታማነት
- አዝጋሚ መዋቅራዊ ለውጥ እና ዝቅተኛ የግብርና አቅሞች
- ከጥራት ይልቅ ብዛት ላይ ያተኮረ የእንስሳት ሃብት አያያዝ
- ዝቅተኛ መዋዕለ ንዋይ
- የክህሎትና የአመለካከት ችግር

**የትኩረት መስኮች**

1. የግብርና ኢንቨስትምንት፣ ቴክኖሎጅ-መር የሰብል ልማት ንኡስ ዘርፍ፣ የኮመርሻል ግብርና ልማት

2. የግብርና ኢንቨስትመንት፣ ዘመናዊ የእንስሳት ሃብት ልማት
3. የአነስተኛ ባለይዞታ ግብርና ትራንስፎርሜሽን
4. የአካባቢ ጥበቃ ልማት
5. የግብርና ምርምር ስርጸት
6. የግብርና ግብዓት፣ ግብይት እና ገጠር ፋይናንስ አቅርቦት

**የትኩረት አቅጣጫ**

ጥምር የግብርና አቅሞችን ማጎልበት፣ መስኖ፣ መካናዜሽን፣ቴክኖሎጅን ለዘርፉ የሰብል ልማት በጥምር (package) መጠቀም፣ የተሻሻለ መኖ፣ የተሻሻለ ዝርያ እና የእንስሳት ህክምና (feed breed vet) በመጠቀም የእንስሳት ሃብት ልማትን ማሳደግ፣ ምርታማነት እና ስትራቴጅካዊ ጠቀሜታ ባላቸው የግብርና ምርቶች ላይ አትኩሮ መስራት፣ የግብርና መዋዕለ ንዋይን በምርት ግብ፣ በቦታ፣ በጊዜ እና በአልሚ አቅዶ ዘመናዊ ግብርናን በፍጥነት ማስፈን፣የዘርፎችን ትስስር እና የተቋማትን ቅንጅታዊ አሰራር በማዳበር የግብርና ግብይትን ማዘመንና የእሴት ሰንሰለት ማሻሻል አደንድሁም ከኢኮኖሚ ግቦች ጋር የተቀናጀ የአካባቢ ጥበቃ ልማት ማረጋገጥ የሚሉ የበጀት ዓመቱ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ሆነው ተቀምጠዋል፡፡

**ዓላማ፡-** በግርና ዘርፍ በምግብ እራስን የመቻል፣ የፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገትና የመዋቅራዊ ለውጥ ግቦችን እንድያሳካ ማስቻል፣

**ግብ 1፡- የግብርና መዋዕለ-ንዋይን በማሳደግ የእርሻ መካናይዜሽን አጠቃቀምን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 10.41 በመቶ ወደ 13.86 በመቶ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለመካናይዜሽን እርሻ ምቹ የሆነውን መሬት አሁን ከታረሰው 18001 ሄ/ር ወዳ 30000 ሄ/ር መሬት ማሳደግ
- 500 ትራክተር፣ 10 ኮምባይነሮች፣ 20 ትሬሽር እንዲቀርብ ማድረግ እና ማሰረጨት፣
- የ20 በ80 የመካናይዜሽን መሳሪያዎች አቅርቦት ከአበዳሪ ባንኮች ጋር የብድር ትስስር መፍጠር፣
- በተለየ ሁኔታ የግብርና መካናይዜሽንን ሊደግፍ የሚችል የፋይናንስ ተቋም እንዲኖር ማድረግ

**ግብ2፡- በ2016/17 ምርት ዘመን ከመኸር ሰብሎች የተገኘውን 13398801 ኩ/ል ምርት በ2018 ወደ 15049470 ኩ/ል ማድረስ፣ አማካይ ምርታማነትን በ2017 ከነበረበት 31 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 35 ኩ/ል በሄ/ር ማድረስ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 432168 ሄ/ር የእርሻ መሬት ማልማት፣
- 173014 ሄ/ር በምግብ ሰብል በማልማት 4766979 ኩ/ል ምረት ማምረት
- የኢንዱስተሪ ግብዓት ሰብሎች 225316 ሄ/ር በማልማት 9644934 ኩ/ል ምርት ማምረት
- የኤክስፖርት ሰብሎች 33838 ሄ/ር በማረስ 637557 ኩ/ል ምርት ማምረት
- በምርት ዘመኑ 631467 ኩ/ል ሰው ሰራሽ የአፈር ማዳበሪያ መጠቀም፣
- በምርት ዘመኑ በተለያዩ አማራጮች የቀረበውን 28185 ኩ/ል ምርጥ ዘር መጠቀም፣
- የእርሻ ሜካናይዜሽን አጠቃቅምን በማስፋፋት 30000 ሄ/ር መሬት 41 ትራክተር በመጠቀም ማረስ፣
- 432168 ሄ/ር መሬት ላይ የሰብል ጥበቃ ስራ መስራት፡፡
- የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂን በመጠቀም የምርት ብክነትን 4% መቀነስ፣
    - 27 ዘመናዊ የብረት ጎተራ (ሜታል ሳይሎ) መጠቀም፣
    - 76470 ዘመናዊ ሄልማቲክ ጆንያ መጠቀም፣
    - 20 ሁለገብ መዉቂያ ጥቅም ላይ ማዋል፣
    - 3 ኮምባይነር ሀርቨስተር ጥቅም ላይ ማዋል፣

**ግብ 3፡- በ2016/2017 ምርት ዘመን በመኸር አትክልት፣ ሥራስርና ቅመማ ቅመም ሰብሎች የተገኘውን** 975144.8 **ኩ/ል ምርት በ2017/18 ምርት ዘመን 12700 ሄ/ር መሬት በማልማት ምርቱን ወደ 1126384 ኩ/ል ማድረስ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- በሥራስር ሰብል ልማት 1739 ሄ/ር መሬት በማልማትና አማካይ ምርታማነቱን 178 ኩ/ል/ሄ/ር በማድረስ 311110 ኩ/ል ምርት ማምረት፣
- በቅመማ ቅመም ልማት 5909 ሄ/ር የመሬት ሽፋን ላይ አማካይ ምርታማነትን 7.8 ኩ/ል/ሄ/ር በማድረስ 46365 ኩ/ል ምርት ማምረት፣
- በአትክልት ልማት 5052 ሄ/ር የመሬት ሽፋን ላይ አማካይ ምርታማነትን 152 ኩ/ል/ ሄ/ር በማድረስ 768909 ኩ/ል ምርት ማምረት፣

**ግብ4፡- በ2017 ከመስኖ ልማት የተገኘውን 3025476 ኩንታል ምርት በ2018 በጀት ዓመት 35365 ሄክታር መሬት በድግግሞሽ በማልማት ወደ 3730132 ኩንታል ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- በአንደኛ ዙር በነባር 30487ሄ/ር እና በአዲስ 4878 በድምሩ 35365 ሄ/ር መሬት በማልማት 3730132 ኩ/ል ምርት ማምረት፣
- በሁለተኛ ዙር 8966 ሄ/ር መሬት በማልማት 914145 ኩ/ል ምርት ማምረት፣
- የመስኖ ውሃ አጠቃቀምን ዘመናዊ በማድረግ 97 በመቶ የሚሆነውን መሬት በመስመር መዝራት
- በ35365 ሄ/ር ማሳ ላይ የሰብል ጥበቃ ሥራን ማጠናከር፣
- የድህረ ምርት ቴክኖሎጅን በመጠቀም የምርት ብክነትን መቀነስ፣

**ግብ 5፡- በ2017 በጀት አመት የበጋ ስንዴ የለማውን 20318 ሄ/ር መሬት በ2018 በጀት ዓመት 21500 ሄ/ር በማልማት አማካይ ምርታማነቱንም 40 ኩ/ል በሄ/ር በማድረስ 860000 ኩንታል ምርት ማምረት፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- ለመስኖና ለበልግ አገልግሎት ከሚውለዉ 5000 ኩ/ል ምርጥ ዘርና 18379 ኩ/ል የአካባቢ ዘር (C2) በድምሩ 23379 ኩ/ል የስንዴ ም/ዘር እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
- ወንድ 60200 ሴት 25800 በድምሩ 86000 አባውራና እማውራ ማሳተፍ
- በ21500 ሄ/ር ማሳ ላይ የሰብል ጥበቃ ሥራን ማጠናከር፣
- የድህረ ምርት ቴክኖሎጅን በመጠቀም የምርት ብክነትን መቀነስ፣

**ግብ 6፡- በ2017 በጀት ዓመት ከበልግ ሰብሎች የተገኘውን 398560 ኩ/ል ምርት በ2018 ወደ 2301332 ኩ/ል ማድረስ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 104606 ሄ/ር መሬት ማልማት፣
- ለበልግ የተዘጋጀ ኮምፖስት ሙሉ በሙሉ በማሳ ላይ እንዲበተን ማድረግ፣
- 1000 ኩ/ል ማዳበሪያና 500 ኩ/ል ምርጥ ዘር በምክረ-ሀሳቡ መሠረት አሚልቶ መጠቀም፣
- ቀድመው በተዘሩ ሰብሎች ላይ እንክብካቤ ስራ መስራት

- ቀድመው የደረሱ ሰብሎችን የመሰብሰብ ስራ መስራትና የዝናብ እጥረት ካጋጠመ ደጋፊ መስኖ መጠቀም
- 104606 ሄ/ር መሬት ላይ የተዘራን የሰብል ጥበቃ ስራ ማጠናከር
- የድህረ ምርት ቴክኖሎጅን በመጠቀም የምርት ብክነትን በ4 በመቶ መቀነስ፣

**ግብ 7፡- የአምራች አርሶ አደሮችን የመሬት ይዞታ መጠን በአማካይ በ0.5 ሄክታር በመጨመር የባለይዞታ ምርትን በዓመት በአማካይ 4.6 ኩ/ል ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ከግብርና ዘርፍ እየወጣ ያለውን የሰው ሃይል በሌላ ዘርፍ እንድሰማራ ማድረግ
- ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት ከተሞችን የተመቹ በማድረግ ማጠናከር፣
- በግብርና መዋዕለ ንዋይ በሰፊ እርሻ ወደ ዘርፉ የሚገቡ አልሚዎችን ማባዛት
- የመንግስት በመሬት ጥራት ላይ ሊወስዳቸው የሚችሉ የፖሊሲ እርምጃዎችን ማጠናከር
- ኩታ ገጠም አስተራራስን ተግባራዊ (Clustre Farming)ማድረግ

**ግብ 8፡- በዞኑ የዝቅተኛ የሰብል ምርታማነት መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን ለይቶ ርብርብ ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የአፈር ለምነትን ማሻሻል፣
    - 10296120 ኩ/ል የተፈጥሮ ማዳበሪያ (መደበኛ፣ ቨርሚ እና ባዮሳለሪ ኮምፖስት) ማዘጋጀት 283143 ሄ/ር ማሳን በማልማት የአፈርን ምርታማነት ማሻሻል፣
    - 125 ሄ/ር ማሳ በአረንጓዴ ማዳባሪያ በማልማት የአፈር ጤንነትና ለምነትን ለማሻሻል፣
    - 95578 ሄ/ር የኮትቻ አፈርን በዘመናዊ እና በባህላዊ ዘዴ በማጠንፈፍ ማልማት፣
    - የጥራጥሬ ሰብሎችን 30000 ሳቼት ህየው ማዳበሪያ በማቅረብ እና በማሰራጨት 7500 ሄ/ር ማሳ ላይ አሽቶ በመዝራት ምርታማነትን ማሳደግ
    - የሰው ሃይል ምርታማነትን ማሳደግ፣
    - የቴክኖሎጅ የዘርፍ አጠቃቀምን ማሳደግ፣
    - የሜካናይዜሽን አቅምን ማሳደግ፣
    - የምርት ብክነትን መቀነስ፣

**ግብ 9 ፡- የዞኑን የግብርና ምርታማነት በመጨመር በክልሉ የሚኖረውን ድርሻ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የአዝዕርት ምርትን ድርሻ  ከ11.10 በመቶ ወደ 11.23 ማሳደግ፣
- የአገዳና የብርዕ እህሎችን ከ 2.6 በመቶ ወደ 2.7 ማሳደግ፣
- የጥራጥሬ እህሎችን ከ 6.7  በመቶ ወደ 11.2 ማሳደግ፣
- የቅባት እህሎችን ከ0.25 በመቶ ወደ 0.34 ማሳደግ፣

**ግብ 10፡- የአግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎችን ታሳቢ ያደረገ በቂና ጥራቱን የጠበቀ የግብርና ምርት በማምረት የዘርፎቹን ትስስር ማጠናከር፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለአግሮ-ፕሮሰሲነግ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆኑ የግብርና ምርቶችን በጥናት መለየት፣
- ለአግሮ-ፕሮሰሲነግ ኢንዱስትሪዎች በቂ የሆኑ የግብርና ምርቶችን በዓይነትና በጥራት ማምረት፣

**ግብ 11፡- በ2016/17 የምርት ዘመን 30 ሄ/ር መሬት ለማከም ጥቅም ላይ የዋለውን 412 ኩንታል የኖራ መጠን በ2017/18 የምርት ዘመን ከአምራች ኢንዱስትሪዎች 10000 ኩንታል ኖራ በማስመረት 380 ሄ/ር መሬት ማከም፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- በኖራ የሚታከም መሬትን መለየት፣
- የአፈር ናሙና በወቅቱ መውሰድና ውጤቱን መግለጽ፣
- የኖራ ምርት በማቅረብ ለአድሶ አደሩ ማሰራጨ፣
- በምክረ ሀሳቡ መሰረት ጥቅም ላይ እንድውል ማድረግ

**ግብ 12፡- 52 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማትን በማጠናከር የእዉቀት፣ የክህሎት እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል እንዲሆኑ ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 10 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የሰርቶ ማሳያ መሬት እንዲሟላላቸዉ ማድረግ፣
- 14 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ቁሳቁስ ማሟላት፣
- 398 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ኦዲት ማድረግ
- 45 የአ/አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ (ICT) ተጠቃሚ ማድረግ፣
- ከመሰረታዊ ወደ መካከለኛ 280 እና ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ 12 በድምሩ 292  የአ/አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን ደረጃ ማሳደግ፣

- 20 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን በአዲስ መገንባትና 52 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን መጠገን፣
- የቀበሌ ባለሙያዎች የመኖሪያ ቤት 20 በአዲስ መገንባት እና 52 ነባሩን መኖሪያ ቤት መጠገን፣
- በአርሶደር ማሰልጠኛ ማዕከል 3,799 እና በአርሶ አደር ማሳ 6,394 በድምሩ 10,193 የተለያዩ ሰርቶ ማሳያዎችን ማካሄድ፣
- በተሰሩ ሰርቶ ማሳያዎች በቁጥር 40,772 የገበሬ በዓላትን ማዘጋጀት እና 560,562 በድግግሞሽ አርሶ አደሮች ልምድ እንዲወስዱ ማድረግ፣
- በሞዴል አ/አደሮች ተሞክረው ውጤታማ የሆኑ በዞን 5፣ በወረዳ 80 እና በቀበሌ 484 ምርጥ ተሞክሮዎችን በተመረጡ ስራዎች መቀመርና ማስፋት፣
- የቪዲዮ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመጠቀም ለ1,450 አ/አደሮች የተሸሻሉ አሰራሮችንና ቴክኖሎጅዎችን ማስተዋወቅ፣

**ግብ 13፡- የዞኑን የደን ልማት ሽፋን በ2017 ም/ዘመን ከነበረበት 15.7 በመቶ በ2018 ወደ 16.7 በመቶ ማደረስ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 25269 ሄ/ር ደን ማልማት
- 12687 ሄ/ር ጥምርት ደን እርሻ ልማት ማካሄድ
- 22710 ነባር፣ በአድስ 2004 በድምሩ 24714 ችግኝ ጣቢያዎችን ወደ ስራ ማስገባት
- 234.5 ሚሊዮን ችግኝ በጥራት ማፍላት

**ግብ 14፡ የስጋ ምርት በ2017 የምርት ዘመን ከነበረበት 211945 ቶን በ2018 በጀት ዓመት ወደ 60071.0 ቶን ስጋ ምርት ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፣**

- የሚደልቡ የዳልጋ ከብቶችን፣ በጎች፣ ፍየሎች የመኖ አቅርቦትና አመጋገብን፣ ጤና አጠባበቅንና አያያዝን በማሻሻል በ 2018 አ/ም በአማካኝ ከዳልጋ ከብት 140 ኪ.ግ፣ ከበግ 14.75 ኪ.ግ.፣ ከፍየል ከ 14.5 ኪ.ግ በማምረት፣ከተሻሻለ የቤተሰብ የዶሮ ስጋ 2 ክ/ግ ማድረስ፣
- በተለያዩ የሃብት አማራጮች በክላስተር የማድለቢያ ሼድ በመገንባት የብድር አገልግሎት በማመቻቸት በአዲስ በዘርፉ የሚሰማሩ አድላቢዎችን ቁጥር ማሳደግ

**ግብ 15፡ በ2017 በዞኑ ከአንድ የአካባቢ ላም በአማካይ በቀን የሚገኘዉን 2 ሊትር ወተት 2.1 ሊትር፣ ከተሻሻሉ ክልስ የወተት ላሞች ከ 10 ሊትር ወደ 13.5 ሊትር እንዲሁም ከፍየል ወደ 0.5 ሊትር በማሳደግ ዓመታዊ የወተት ምርትን ከ 211945 ቶን ወደ 229,350 ቶን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፣**

- የዝርያ ፣የጤና ፣የአመጋገብ ና አያያዝ ስርዓት ማሻሻል፡፡

**ግብ 16፡-** የእንቁላል ምርት በ2017 ምርት ዘመን ከነበረበት ቁጥር 86 ሚሊዮን ወደ 100.2 ሚሊዮን ማሳደግ፡፡

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ከአካባቢ፣ ከተሸሻሉ እና ከስፔሻላይዝድ ዶሮዎች በ 2018 በጀት ዓመት በአማካኝ እንደ ቅደም ተከተላቸው 68 እና 200 ና 216 እንቁላል እንዲመረት ማድረስ
- 37 ነባና እና 85 አዲስ በድምሩ 122 የአንድ ቀን ጫጩት አሳዳጊ ኢንተርፕራይዝና ግለሰቦችን በማጠናከር እና አሰልጥኖ ወደስራ በማስገባት 1,074,858.0 የአንድ ቀን ጫጩት በማሳደግ 405,678 የ45 ቀን እና ከዚያ በላይ እድሜ ያላቸውን የተሻሻሉ ዶሮዎች ለ21,773 ተሳታፊዎች በፓኬጁ መሰረት በማሰራጨት ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ
- የአንድ ቀን ጫጩት ብዜት ማእከላት የሚፈለገዉን ጫጩት በአይነትና በመጠን ማቅረብ የሚያሳችላቸዉን አሰራር እንዲከተሉ ምክክርና ግምገማ ማካሄድ እና ያሉባቸዉን ችግሮች በዉይይት መፍታት፣ የስርጭት ገበያ ትስስር አቅጣጫ ማስቀመጥ፣ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የዶሮ ዝርያ የሚቀርበብት ሁኔታ ማመቻቸት
- በስፔሻላይዝድ ደሮ እርባታ የሚሳተፉ የተሻለ ልምድ እና አቅም ያላቸውን ተሳታፊወች መለየት እና አሰልጥኖ ወደስራ በማስገባት የተሸሻሉ ደሮዎችን እንዲያረቡ ማድረግ፡፡
- በዶሮ ሞዳሊቲ ተሣታፊ አርሶ አደሮችን መለየት ማሰልጠን እና ቅድመ ዝግጅቱን በማሟላት የአርባ አምስት ቀን እና ከዚያ በላይ እድሜ ያላቸውን የተሸሻሉ ደሮወችን በመያዝ በደሮ እርባታ ስራ እንዲሰማሩ ማድረግ

**ግብ 17፡- የአሳ ምርትን በ2017 ምርት ዘመን ከነበረበት 1156.61 ቶን በ2018 ወደ 1760 ቶን ማሳደግ: እንዲሁም**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የተጠናከረ የዓሳ አስተዳደር በማካሄድና ዓሳ ባልተጨመረባቸዉ የዉሀ አካላት የአሳ ጫጩት በመጨመር በግድቦች እና በአሳ ኩሬዎች 105,600 የአሳ ጫጩቶች እንድጨመር በማድረግ የአሳ ምርት ና ምርታማነት ማሳደግ፡፡
- በዞኑ በሚገኙ ሐይቆች ዙሪያ የሚገኙ ነባርና አዲስ የዓሳ አስጋሪ ማህበራትንና ቡድኖችን በማጠናከርና በማቋቋም ዓሣ ማምረት፡፡
- በዞኑ በሚገኙ ነባርና አዲስ የዓሳ ኩሬዎች የዓሳ ግብርና ተጠቃሚ አ/አደሮችንና ቡድኖችን የአመጋገብና አያያዝ ክህሎታቸዉን ተከታትሎ በማሳደግ ዓሣ ማምረት፡፡
- በዞኑ ለአሳ እርባታ ምቹ የሚሆኑ ነገር ግን የኣሳ እርባታ ያልተጀመረባቸዉ የዉሀ አካላት በሙሉ ለይቶ ዝርዝር የማስፈፀሚያ ሰነድ እና ድርጊት መርሀ ግብር በማዘጋጀት ወደ አሳ እርባታ እንዲገቡ ማድረግ
- ሞዴል የአኳካልቸር ፋርም ከተለያዩ አካላት ድጋፍ በመጠየቅ እንዲሰራ በማድረግ ማስተዋወቅና የማስፋት ስራ ማካሄድ

**ግብ 18፡ የማር ምርትን በ2017 ምርት ዘመን ከነበረበት 3015 ቶን በ 2018 ምርት ዘመን ወደ 3319 ቶን ማሳደግ እንዲሁም የሰም ምርትን ከ 101.87 ቶን ወደ 172 ቶን ማሳደግ፡፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የማር ምርታ ማነትን በአንድ ቆረጣ ከባህላዊ ቀፎ ከ10 ኪ/ግ ወደ 11 ኪ/ግ፣ ፣ከሽግግር ቀፎ ከ 20 ኪ/ግ ወደ 22 ኪ/ግራም፣ ከባለፍሬም ቀፎ ከ35 ኪ/ግራም ወደ 38 ኪ/ግ በማሻሻል፣
- የዘመናዊ ቀፎ እና የሽግግር ቀፎዎችን በጥራት እና በበቂ መጠን በማዘጋጀት ህብረንብን ወደ ዘመናዊ ቀፎ 4618 እና ወደ ሽግግር ቀፎ 4329 በድምሩ 8927 ህብረ-ንብ በማዛወር በመንከባከብ እና በመጠበቅ የንብ ሀብታችን ምርትና ምርተማነት ማሳደግ፡፡
- የህብረ-ንብ ማዛወር ስራውን ውጤታማ ለማድረግ 8431 ኢትዮርብራብ የሽግግር ቀፎዎችን በአካባቢ ቁሳቁስ ጥራቱን ጠብቆ እንዲሰራ ማድረግ

**ግብ 19፡ የተዳቀሉ ላሞች ቁጥር በ2017 ምርት ዘመን ከነበረበት 32,355 የማዳቀል አቅም በ2018 በጀት ዓመት ወደ 62,397 ላሞችና ጊደሮች ድቀላ አገልግሎት ከፍ ማድረግ እንዲሁም የጥጃ ውልደትን ከ 18,154 ወደ 24,854 ማድረስ፡፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡**

- በተፈጥሮ ድራት 31,500፣ በሆርሞን ድራት 4,788 እና በተሻሻሉ ኮርማ 26,109 ላሞችንና ጊደሮችች ማዳቀል በዚህም የጥጃ ውልደት መረጃን በማጠናከር በመከታተል እና በመደገፍ ሞትን መቀነስ፣
- የአባላዘርና ፈሳሽ ናይትሮጅን ምርት ሳይቆራረጥ እንዲመረት በማድረግ በወቅቱ ለወረዳዎች ማሰራጨት

**ግብ 20፡- በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ የመኖ መገኛ ምንጮች በ2017 ምርት ዘመን ከነበረበት 3.969 ሚሊዮን ቶን በ2018 ምርት ዘመን ወደ 4 ሚሊዮን ቶን ድርቆ መኖ ማድረስ፣ በአግባቡ በመያዝና በመጠቀም የእንስሳትን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፡፡**

**የሚከናወኑዋና ዋና ተግባራት**

- ከግጦሽ መሬት 1.9 ሚ/ቶን ድርቆ መኖ ማዘጋጀት፣ ከተሻሻለ ድርቆ መኖ 0.3 ሚ/ቶን፣ ከተረፈ ሰብል 1.6 ሚ/ቶን ድርቆ መኖ ማምረት እነረዲሁም ከኢንዱስትሪ ተረፈ ምርት 0.1 ሚ/ቶን ማምረት፣
- በ 1,657.0 ሄ/ር መሬት ላይ በመስኖ መኖ ማልማት፣ 65,484.6 ሄ/ር መሬት ላይ የበልግ ዝናብን በመጠቀም መኖ ማምረት፣ በማሳ ድንበርና በአፈር እርከን 6,480.4 ሄ/ር በማልማት መኖ ማምረት፣ በአገዳ ሰብሎች ስር 5,744.9 ሄ/ር በማልማት መኖ ማምረት፣
- በግል ግጦሽ መሬት 13,610.0 ሄ/ር በማልማት መኖ ማምረት፣ በድብልቅ መኖ 12,180.5 ሄ/ር በማልማት መኖ ማምረት፣
- በጓሮ ዙሪያ 27,572.6 ሄ/ር በማልማት መኖ ማምረት፣

**ግብ 21**፣ የእንስሳት በሽታ መከላከልና መቆጣጠርን ለማሻሻል በ2017 የተደረሰበትን የክትባት አገልግሎት ከ6,952,460 ወደ 7,750,294 ሚሊየን እንስሳት ማድረስ እንዲሁም የቅድመ መከላከል ህክምና በ2017 በጀት ምርት ዘመን ከነበረበት 3,262,699 ወደ 3,322,020 እንስሳት የቅድመ መከላከል ህክምና ማሳደግ፡፡

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የታዳጊ እንስሳት ሞት መቀነስ፣ በአንድ ዓመት ከሚወለዱ የዳልጋ ከብት ጥጆች ጡት እከጣሉበት እድሜ የሚከሰት የሞት መጠንን ወደ 5 % መቀነስ (ዝቅ ማድረግ)፣
- በአንድ ዓመት ከሚወለዱ የበግ ግልገሎች ጡት እስከጣሉበት እድሜ የሚከሰት የሞት መጠንን ወደ 6% መቀነስ፣ በአንድ ዓመት ከሚወለዱ የፍየል ግልገሎች ጡት እስከጣሉበት

እድሜ የሚከሰት የሞት መጠንን ወደ 7% መቀነስ፣ እንዲሁም በዶሮ ጫጩት የሚከሰት የሞት መጠንን ወደ 14 % መቀነስ፡፡

- ካለንደርን መሰረት በማድረግ የቅድመ መከላከልና ቁጥጥር ክትባትና የውጭና የውስጥ ጥገኛ የቅ/መከላከል ህክምና (Strategic deworming and spraying) መስጠት፣

**ግብ 22፡ የፍየል ና የበግ ልማት ቀጠናዎችን በማቋቋም ከጥሪትነት ወደ ተከታታይ ገቢ ምንጭነት በመቀየር ከምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ባለፈ ዘላቂ ዘመናዊ የግብርና አቅም መፍጠር**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 95850 እናት በጎችን በተመረጡ አዉራ በጎች በማዳቀል 49642 ተባዕት ግልገሎች ለእርድ ሲደርሱ ለገበያ ማቅረብ
- 2400 እናት ፍየሎች በተመረጡ አዉራዎች በማዳቀል 1003 ተባዕት የፍየል ግልገሎችን ለእርድ ማቅረብ

**ግብ 23፡ ከጥራት ይልቅ ብዛት ላይ ያተኮረ የእንስሳት ሃብት አያያዝ ችግር መቅረፍ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የእንስሳት መኖ የሚያሻሽሉ ስራዎቸ መስራት
- የእንስሳት ዝርያ ማሻሻለል ስራ መስራት
- የእንስሳት ጤና አገልግሎት ማሻሻል

**ግብ 24፡ የዞኑን የእንስሳት ምርታማነት በመጨመር ከክልል ያለውን ድርሻ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የቀንድ ከበት ከ 9 በመቶ ወደ 10 በመቶ ማሳደግ
- የጋማ ከበት ከ 17 በመቶ ወደ 18 በመቶ ማሳደግ
- ዶሮ ከ 7.6 በመቶ ወደ 8.6 በመቶ ማሳደግ
- የለማ የንብ ሃብት ከ 12 በመቶ ወደ 13 በመቶ ማሳደግ

**ግብ 25፡- መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ቁጥርን በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 1204 በ2018 በጀት ዓመት ወደ 1429 በማድረስና የአባላት ቁጥርን ከ 41994 ወደ 65305 በማሳደግ የሰብል ምር ግብይትን ከ48137 ኩንታል ወደ 7223 ኩንታል ማሳደግ፡፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ስለ ህብረት ስራ ማህበራት ጥቅም ግንዛቤ ለማሳደግ እና ፍላጎት ለመፍጠር በዓመቱ 600 የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች በቀበሌ ደረጃ ይካሄዳሉ፡፡
- መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራትን ለማቋቋም 225 የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ
- ስለ ህብረት ስራ ማህበራት ጽንሰ ሀሳብ እና ጠቀሜታ ለህብረተሰቡ ማስገንዘብ፣ የወጡ አደረጃጀቶችን እና የአሰራር መመሪያዎች በተከታታይ ማስተማር፣ የአባልነት መስፈርቶችን አሟልተው አባል እንድሆኑ ማድረግ፣
- የአባልነት ግደታቸውን እንድወጡና ተጠቃሚ እንድሆኑ ማድረግ፣
- የገበያ ማረጋጋት ተግባራን አጠናክሮ በማስቀጠል የሰብል ምርት አቅርቦትን አሁን ከደረሰበት 48137 ኩንታል ወደ 72238 ኩንታል ማድረስ፣
- የግብይት ተሳታፊ ህብረት ስራ ማህበራትን ቁጥር ከነበረበት 102 ወደ 238 ማድረስ
- ጠንካራ የገበያ ትስስር መፍጠር
- የህብረት ስራ ማህበራትንን ካፒታል ከብር102395430 ወደ ብር 121695571 ማድረስ፣
- አመታዊ ቁጠባን ከብር 82290272.67 ወደ ብር 149866603 ማሳደግ፣
- አመታዊ የብድር ስርጭት ከብር 899559875 ወደ 1477247965 ብር ማሳደግ፣

**ግብ 26 ፡- የምግብና ስርዓተ-ምግብ ችግርን መፍታት የሚያስችሉ ደህነንታቸውና ጥራታቸው የተጠበቀና ስብጥሩን ያሟላ ምርት ከተደረሰበት 399900 ሽህ ኩ/ል ወደ 430400 ሽህ ኩ/ል በማሳደግ አመጋገብን ማሻሻል፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለ88,495 ተጋላጭ እጥቢና ነፍሰ ጡር እናቶችን 445 ኩንታል የተለያዩ በንጥረ ምግብ ይዘታው የበለጸጉ ዘር በማቅረብ 430400 ኩ/ል ማምረት፣
- ለ33,025 ተጋላጭ እጥቢና ነፍሰ ጡር እናቶችን 1,446,791 ቁርጥራጭ ብርቱካናማ ስኳር ድንች በማቅረብ 3,906 ኩ/ል ማምረት፣
- በንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለፀጉ ሰብሎች ላይ የድህረ ምርት ብክነት ለመቀነስ የሚያስችሉ 15,902 የተለያዩ ቴክኖሎጅ ስርጭት ማካሄድ፣
- 2,088 የምግብ ዝግጅት በማካሄድና 62,640 በማሳተፍ በተመጣጠነ ምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ላይ የማህበረሰብ የባሪ ለውጥ ማምጣት፣
- 4 የስርዓተ ምግብ ሞዴል መንደሮች በመፍጠርና 4 ነባር የስርዓተ ምግብ ሞዴል መንደሮችን ማስመረቅ፣

- ለ55,023 አጥቢና ነፍሰ ጡር እናቶች እና ባለሙያዎች በምግብና ስርዓተ ምግብ የባህሪ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
- የእንስሳት ተዋጽኦ የሚጠቀሙ የአጥቢ እና ነፍሰ ጡር እናቶች ቁጥር በ2017 ከነበረበት 29331 በ2018 ወደ30010 ማሳደግ፣
- በእያንዳንዱ ቀበሌ ያሉ ነፍሰጡርና አጥቢ እናቶች መረጃ በመያዝ ያላቸውን አቅም ያገናዘበ እንቁላል ጣይ ዶሮ፣ የወተት ላምና ፍየሎች፣ ዓሳ እና የስጋ እንስሳትን አደንድያተቡና ያመረቱትን እንድመገቡ ማድረግ፣
- አንድ ዶሮ ለአንድ ህፃን በሚል መሪ ቃል እያንዳንዷ እናት ቢያንስ ዶሮ እንድታረባ በትኩረት መስራት፣

**ግብ 27፡- የሰው ኃይል ስልጠናን በማጠናከር በዘርፉ በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማረጋገጥ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለ2,406 የቀበሌ ግብርና ባለሙያዎች በተለያዩ ግብርና ሙያ በወረዳ ደረጃ የፓኬጅ ስልጠና መስጠት፣
- የዞን፣ የወረዳ ባለሙያዎች እንዲካተቱ ታሳቢ በማድረግ 161 የፓኬጅ ስልጠና ለአሰልጣኞች በፌዴራልና በክልል ደረጃ ስልጠና መስጠት፣
- በወቅታዊ የግብርና ልማት ተግባራት ዙሪያ ለ1,608,727 አባወራዎች፣ እማወራዎች፣ ባለትዳር ሴቶችና ወጣቶች ግንዛቤ መፍጠር፣
- ለአባወራና እማወራ፣ ባለትዳር ሴቶች እና ወጣቶች እንዲካተቱ ታሳቢ በማድረግ በአርሶአደር ማሰልጠኛ ማዕከል 154,078 የፓኬጅ ስልጠና መስጠት፣
- ለዞንና ለወረዳ ባለሙያዎች ታሳቢ በማድረግ 63 ጊዜ ለ6,362 ተሳታፊዎችን በማካተት አውደ ጥናት ማካሄድ፣
- ለቀበሌ ግብርና ባለሙያዎች የትምህርት እድል መስጠት
  - ✓ ለ153 ሰርተፊኬት ያላቸውን ወደ ዲፕሎማ ማሳደግ
  - ✓ ለ26 ዲፕሎማ ያላቸውን ወደ መጀመሪያ ዲግሪ ማሳደግ
  - ✓ ለ2 መጀመሪያ ዲግሪ ላቸውን ወደ 2ተኛ ዲግሪ ማሳደግ

**ግብ 28፡- በግብርና ተቋም 27428 ዜጎች የስራ እድል መፍጠር**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በግብርና መምሪያ 27428 (50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) በቋሚና በጊዜያዊ የስራ እድል መፍጠር

## የማስፈጸሚያ ስልቶች

የግብርና ዘርፍ አሰራሮችን (ስርዓቶችን) ማለትም የመሬት አጠቃቀም ስርዓት፣ የግብርና ንግድ ስርዓት፣ የግብርና ማህበራት ስርዓት፣ የግብርና ፋይናንስ ስርዓት፣ የግብርና ትምህርት፣ ስልጠና፣ ጥናትና ምርምር ስርዓት፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ስርዓት፣ የግብርና ዘረፍ አደረጃጀት ስርዓት እንድሁም የመንግስት የግብርና ፖሊሲ ስርዓት በትክክል መተግበር ተገቢ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እንደ ሀብት መሰረታቸውና ማህበራዊ ልዩ ፍላጎት በተመረጡ የልማት ቀጠናዎች መተግበር፣ ልዩ ድጋፍ የሚደረግላቸው የአዝዕርትና የእንስሳት ዓነቶችና ዝርያዎች መምረጥ፣ ለዘመናዊ ግብርና ልማት የሚመጥን ልዩ ችሎታን በክህሎት የሚለይ የስልጠና ስርዓት መንደፍ እንድሁም ግብርና መሬት ላለው አ/አደር ብቻ የተተወ አድርጎ ከሚያዩ አስተሳሰብ በመላቀቅ በዘርፉ መክሊት እና የትምህርት ዝግጅት ላላቸው ትኩረት በመስጠት በፈቃድ አሰጣጥ፣ በመሬት ድልለድል፣ በፋይናንስ አቅርቦትና በቴክኖሎጅ መረጣ እረገድ በመንግስት ልዩ ድጋፍ ማድረግ የሚሉት የዘርፉ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

## 2.5.3. የማዕድን ሀብት

ከድህነት ወደ ተሻለ ብልጽግና ለመቀየር ለሚታትር አገር ማዕድናት እና በእጁ ላይ ያሉትን የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉ አቅሞችን በማሳደግ ብቻ ወደ ዕድገት ጉዳና መሸጋገር ይቻላል፡፡ ይህን የዕድገት መስመር በአግባቡ በመከተል በተቀመጠው የጊዜ ሠሌዳ ከድህነት የመውጣት ርዕይ ለማሳካትና ለዚህም የሚመጥን የኢንዱስትሪ ልማት አቅም ለመገንባት ሊደረስበት ለታሰበው የግብርና ዝመና እና የአምራች ኢንዱስትሪ መሳካት የማዕድን ሀብትን በአግባቡ ማበልፀግና መጠቀም ወሳኝ ጉዳይ ይሆናል፡፡

በዞኑ ውስጥ መኖራቸው የተረጋገጠ ለልማት አጋዥ የሆኑ ማዕድናት በልማት ውስጥ በሚኖራቸው የተፈላጊነት ደረጃ በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች፣ የውጭ ባለሀብቶች፣ በመንግስት እንዲሁም በመንግስትና በባለሀብቶች ሽርክና ሊለሙ ይችላሉ፡፡ የማዕድናት ቁልፍ ሚናም ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት፣ ለግብርና ዝመና፣ ለአጠቃላይ የዘርፋች ትስስር እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት ባላቸው አስተዋጽኦ ይወሰናል፡፡ በመሆኑም ይህንን ታሳቢ አድርጎ መስራት ተገቢ ይሆናል፡፡

### ስትራቴጅያዊ ጉዳዩች

- የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት፣

- የዞኑን ማዕድናት በበቂ እና አስተማማኝ ሁኔታ አለመለየት፣
- ሀብቱን ለተመረጡ አሻጋሪ ግቦች ጥቅም ላይ ማዋል አለመቻሉ፣
- በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች እና የሚፈሰው መዋዕለ - ንዋይ ዝቅተኛ መሆን፣
- በዘርፋ የዘመናዊ ቴክኖሎጅ አለመዳበር፣

**የትኩረት መስኮች**

1. የሰው ሃይል ስልጠና፣
2. የስነ ምድርና የማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናት፣
3. ስትራቴጅካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ማዕድናት ኢንቨስትመንት፣
4. የማዕድን ምርት እና ግብይት ህጋዊነት፣
5. የተቋም አደረጃጀት፣

**የትኩረት አቅጣጫዎች**

ማሽን፣ ግብዓትን፣ የኃይል ምንጭን፣ እና የአቶሜሽን ሥርዓትን ከጫፍ እስከ ጫፍ የማስተሳሰር የኢንዱስትሪ እና ቴክኖሎጂ በማዕድን ሀብት ልማት መደገፍ፣ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ልማትን የግብይት እና የማጠናቀቂያ ቁሶች ፍላጎትን በአገር ውስጥ የማዕድን ሀብት ማሟላት፣ የዞኑን ማዕድናትን ለዘመናዊ ግብርና ልማት ማዋል፣ በማዕድን ሀብት ልማት ዘላቂ ማህበረሰባዊ፣ ዞናዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣ የማዕድን ዓይነት፣ ጥራት፣ ክምችት፣ ስርጭትን ለስትራቴጂካዊ ማዕድናት ቅድሚያ ሰጥቶ በጥናት ማረጋገጥ እንዲሁም በሰው ኃይል እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረት ተወዳዳሪ የማዕድን ኢንዱስትሪ መፍጠር የሚሉት በበጀት ዓመቱ የዘርፉ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

**ዓላማ፡-** በዞኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መነሻ የሚሆን መሠረታዊ የስነ ምድር ጥናትና ካርታ በማዘጋጀት ማዕድናትን በዓይነት፣ በጥራት፣ በስርጭት፣ ክምችት መጠን በማጥናት የዘርፋን መዋለ ንዋይ አስፋፍቶ የዞኑን ፈጣን እና አሻጋሪ የኢኮኖሚ ዕድገት ግብ ማሳካት እና የዘመናዊ ኢኮኖሚ አካል የሆነ የማዕድን ኢንዱስትሪ መገንባት፣

**ዋና ዋና ግቦች**

**ግብ 1፡- በ1፡50,000 መስፈርት የስነ ምድር ጥናትና ካርታ ዝግጅት ሽፋንን ከ1,962 ካ.ኪ.ሜትር ወደ 2,812 ካ.ኪ.ሜትር ማሳደግ፡፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በአርጉባ ልዩ ወረዳ በ310 ካ.ኪ.ሜትር ቦታ ላይ በባለ 1:50,000 መስፈርት ካርታ የስነ ምድር ጥናትና ካርታ ስራ ማካሄድ፣
- በኩታበር ወረዳ በ720 ካ.ኪ.ሜትር ቦታ ላይ ባለ 1:50,000 መስፈርት የስነ ምድር ጥናትና ካርታ ስራ መካሄድ፣

**ግብ 2:- የኢንዱስትሪ ማዕድናትን (Industrial Minerals) ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናትን ከ0.077 ካ.ኪ.ሜትር ወደ 0.157 ካ.ኪ.ሜትር ማሳደግ፡፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በ1:30,000 መስፈርት በለጋምቦ ወረዳ 0.08 ካ.ኪ.ሜትር የግራናይት ማዕድን ዓይነት፣ ክምችት፣ መጠን፣ ስርጭትና ጥራት ማጥናት፡፡

**ግብ 3:- የኢነርጂ ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናትን ከ0.23 ካ.ኪ.ሜትር ወደ 0.47 ካ.ኪ.ሜትር ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በ1:30,000 መስፈርት በዞኑ በተመረጡ ወረዳዎች 0.24 ካ.ኪ.ሜትር የድንጋይ ከሰል አይነት፣ ክምችት፣ መጠን፣ ስርጭትና ጥራትን 90 በመቶ ማጥናት፣

**ግብ 4:- የኮንስትራክሽን ማዕድናት (Construction Minerals) ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናትን ከ2.47 ካ.ኪ.ሜትር ወደ 3.52 ካ.ኪ.ሜትር ማሳደግ እና ጥቅም ላይ ማዋል**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በ1:30,000 መስፈርት በዞኑ ባሉ ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች 1.05 ካ.ኪ.ሜትር የኮንስትራክሽን ማዕድን ዓይነት፣ ክምችት፣ መጠን፣ ስርጭትና ጥራት በማጥናት ጥቅም ላይ ማዋል፣

**ግብ 5:- የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናትን ከ0.11 ካ.ኪ.ሜትር ወደ 5.11 ካ.ኪ.ሜትር ማሳደግና ጥቅም ላይ ማዋል፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በ1:30,000 መስፈርት በወረኢሉ፣ አምባሰል፣ ደላንታና ተንታ 5 ካ.ኪ.ሜትር የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድን ዓይነት፣ ክምችት፣ መጠን፣ ስርጭትና ጥራት በማጥናት ጥቅም ላይ ማዋል፣

**ግብ 6፡- የማዕድን ሀብት የኢንዱስትሪ ልማትን መሠረትነት በአግባቡ ለይቶ በዘርፎች የፍላጎት እና አቅርቦት መስተጋብራዊ ቅንጅት የማዕድን ሀብትን ለተመረጡ አሻጋሪ ግቦች ማልማት የሚያስችል ትኩረት የሚሰጥ ስርዓት መዘርጋት፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- መመሪያዎችን እና አሰራር ማንዋሎችን ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ ማስጨበጥ፣
- ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራት፣
- ለአሰራር ያስቸገሩ ጉዳዩች ላይ ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር ችግሩን ለመፍታት የውይይት መድረኮችን መፍጠር፣

**ግብ 7፡- በዞኑ የሚገኝ የማዕዘን ድንጋይ ዓይነት፣ ጥራት፣ እና መጠን የጥናት ሽፋንን 5 ካ.ኪ.ሜትር ማድረስ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በ1፡30,000 መስፈርት በኩታበርና ቃሉ ወረዳዎች 5 ካ.ኪ.ሜትር የዳይሜሽን ስቶን ማዕድን አይነት፣ ክምችት፣ መጠን፣ ስርጭትና ጥራትን ማጥናት፣

**ግብ 8፡- ወደ ውጭ የሚላክ የምርት መጠኑን በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተደረሰበት 32,418.05 ኪ/ግ በ2018 በጀት ዓመት በ18,780 ኪ.ግ በማሳደግ በማዕድን ዘርፉ የሚገኝ የውጪ ምንዛሪ ገቢን በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተደረሰበት 158,200 የአሜካ ዶላር በ3,586,709 የአሜካ ዶላር ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ጥሬ /እሴት ያልተጨመረበት/ 18,217 ኪ.ግ በማምረት 2,500,791 ዶላር ሽያጭ መፈጸም
- እሴት የተጨመረመበት 563 ኪ.ግ በማምረት 1,085,918 ዶላር ሽያጭ መፈጸም፣

**ግብ 9፡-በዞናችን የሚመረተውን የኮንስትርክሽን የማዕድን ምርት መጠን በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተደረሰበት 801,048.07 ሜ3 በ2018 በጀት ዓመት በ 714,376 ሜ3 ማሳደግ (714,376) ሜ3 እንዲቀርብ መስራት)**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 458,027 ሜ.ኩብ በባለፈቃዶች የተነሳ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ምርት መጠን፣
- 118,747ሜ.ኩብ በቁርጥ ዋጋ ተመን ተመርቶ የተነሳ የግንባታ ማዕድናትን የምርት መጠን መረጃን መሰብሰብ ፣

- በነጻ የመጠቀም መብት የሚነሳ የግንባታ ማዕድናት በሜ.ኩ·ብ 137,602፣

**ግብ 10፡- ከማዕድን ዘርፍ የሚገኘውን የሀገር ውስጥ ገቢን ማሳደግ፣ (ብር 7,384,547 መሰብሰብሰ)**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ከሮያሊቲ ብር 3,612,326 መሰብሰብ፣
- ከቁርጥ ዋጋ ብር 2,855,785 መሰብሰብ፣
- ከማዕድን መሬት ኪራይ፣ ከፈቃድ አገልግሎት እና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎት ክፍያዎች ብር 916,435 መሰብሰብ፣

**ግብ 11፡- 71,685 ቶን ከውጭ የሚገቡ የኢንዱስትሪ ማዕድን ውጤቶችን በአገር ውስጥ በሚመረቱ የማዕድን ዉጤቶች በመተካት፣ በ2017 በጀት አመት ከነበረበት የዉጭ ምንዛሬ መጠኑን 8,222.72 USD በ 2018 በጀት ዓመት በ 10,437,210 USD የውጭ ምንዛሬን ማዳን፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የሚተካ ሲሊካሳንድ ምርት መጠን በቶን 300 በማምረት 15000 ዶላር ማዳን፣
- የሚተካ ድንጋይ ከሰል ምርት መጠን በቶን 71385 በማምረት 10422210 ዶላር ማዳን፣

**ግብ 12፡- በማዕድን ዘርፉ የሚስተዋለውን ህገወጥነትን 100 በመቶ ማስቆም፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የ 919 ባለፈቃድ ሰነዶችን በቢሮ ውስጥ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ
- የ 824 ባለፈቃዶችን በመስክ ላይ ቁጥጥር ማድረግ

**ግብ 13፡- የተጎዱ የፈቃድ ቦታዎችን የአካባቢ እንክብካቤ ሥራዎችን በመስራት 100% እንዲስተካክሉ ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በባለፈቃዶች መልሶ የሚስተካከል የፈቃድ ቦታ ስፋት በሄ/ር 64፣
- በባለፈቃዶች መልሶ የሚስተካከል የፈቃድ ቦታ ስፋት በሄ/ር 64፣

**ግብ 14፡- በዘርፉ በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በየደረጃው ለሚገኙ ለወረዳ፣ ከተማ አስተዳደር ባለሙያዎች እና አመራሮች የአጫጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት፣

ግብ 15፡- በበጀት ዓመቱ በማዕድን ዘርፋ ለ2461 (50 በመቶ ሰቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር፣

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለ293 ባህላዊ የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ጠያቂዎች (ኢንተርፕራይዞች) ፈቃድ መስጠት በ2267 የስራ ዕድል መፍጠር፣
- ለ12 አነስተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃድ ጠያቂዎች (ኢንተርፕራይዞች) ፈቃድ በመስጠት 194 የስራ ዕድል መፍጠር፣

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

የዞኑን የቆዳ ስፋት የሚሸፍን ሁሉን አቀፍ የማዕድን አለኝታ ጥናት የማድረግ የረዥም ጊዜ ግብ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመዋቅራዊ ለውጥ ግቦች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የሌሎች ዘርፎችን በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የግብዓት ፍላጎት ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ለቁልፍ ማዕድናት ትኩረት ሰጥቶ ጥራት ያለው የማዕድን አለኝታ መረጃ መሰብሰብ፣ በዘርፋ ልማት ፈጥኖ ተስተካካይነትን ለማረጋገጥ የዞኑን የመልክዓ-ምድር ሁኔታ፣ የትራንስፖርትና የማዕድን ቴክኖሎጂ መጠቀም፣ የዘርፋን የሥራ ድርሻ የሚወሱኑና ከሌሎች ዘርፎች ጋር ያለውን የስራ ግንኙነት ግልጽ የሚያደርጉ ህግጋት ላይ በቅንጅት በመስራት፣ ከተቋማት ጋር በጋራ የማቀድ እና የማዕድን ስራዎችን በጋራ ለማልማት የሚያስችል ሥራዓት መዘርጋት፣ አግባብነት ያለው፣ በተግባር የተደገፈ የሰው ኃይል ስልጠና ማቀድ እና ማጠናከር፣ በማዕድን ልማት ላይ የዘርፎች፣ የግሉ ዘርፍ፣ የመንግስት እና የምርምር ተቋማት ጥምረት መፍጠር እና ማጠናከር፣ በጋራ ማልማት፣ የማዕድን ልማት መዋዕለ ንዋይ እስኪመጣ ከመጠበቅ እና የመጣውን ሁሉ ከመቀበል ቀድሞ በጥናት በተረጋገጡ የመዋዕለ ንዋይ ፕሮጀክቶች፣ በተለይም የብረት እና ፌሮ ብረታ ብረት ማዕድናት ፕሮጀክት፣ የቴክኖሎጂ ነክ ቁልፍ ማዕድናት ልማት ፕሮጀክት፣ የኮንስትራክሽንና የኢንዱስትሪ ማዕድናት ፕሮጀክት፣ የከበሩ ማዕድናት ፕሮጀክት በመሳሰሉት ተጨባጭ ፕሮጀክቶች መመራት፣ ለዘመናዊ የማዕድን ሀብት መዋዕለ ንዋይ ፣ ልማት፣ እና ግብይት የሚመጥን የህግ ሥርዓት መዘርጋት እንዲሁም በዘርፋ ተፈፃሚ እና ችግርን በወቅቱ መፍታት የሚያስችል የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ማስፈን ዋና ዋናዎቹ የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

## 2.5.4. ትምህርት

ትምህርት ለሰብዛዊ ሃብት ልማት አመልካች እድገት ወሳኝ ሚና የሚጫወት ከመሆኑ በተጨማሪ የዜጎች ጤና እንዲሻሻል በማድረግ፣ ገቢያቸው ከፍ እንዲል በማድረግና በአጠቃላይም ኑሮአቸው እንዲለወጥ በማድረግ ለጤና እና የኑሮ ደረጃ አወንታዊ አስተዋጽኦ በማድረግ የሰብአዊ ሃብት ልማት

አመልካች እንዲያድግ በማድረግ ረገድ የጐላ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ ትምህርት የሰው ሃይል ምርታማነትን በማሳደግ ኢኮኖሚን ለማሳደግ፣ ገቢን ለመጨመር፣ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማምጣት እና ድህንነትን ለመቀነስ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ ትምህርት ተወዳዳሪ የሰው ሃይል በመገንባት በክልሉ እውን ለሚደረገው ልማትና ብልጽግና መሠረት የሚጥል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ባለፋት አመታት በክልሉ መንግስት ሰፊ ሃብት በመመደብ የትምህርት ተደራሽነትን ከማሳደግ፣ ጥራትን ከማረጋገጥና ከአካታችነት አንጻር ጥረቶች ሲደረጉ የቆዩ ሲሆን በዚህም አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

ይሁን እንጅ ለትምህርት ግብ አለመሳካት በዋናነት የሚጠቀሱ ተግዳሮቶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በበቂ ሁኔታ አለመስፋፋት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ወደ 2ኛ ደረጃ ያላቸው ሽግግር አነስተኛ መሆኑ፣ የተማሪዎች የማቋረጥ ምጣኔና መጠነ መድገም ከፍተኛ እየሆነ መምጣቱ፣ የልዩ ፍላጐትና የጐልማሶች ትምህርት ሽፋን ዝቅተኛ መሆን ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የትምህርት ዘርፋ በአሻጋሪ ዕድገትና ዘላቂ ልማት ዕቅዱ የቅድሚያ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ ሲሆን በሁሉም የትምህርት ደረጃ የትምህርትን ተሳትፎ ጥራት እና ፍትሃዊነት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ለማዳረስ በቀጣይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት መስራት ከሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የሚጠበቅ ሲሆን የዘርፋ የ2018 በጀት ዓመት እቅድ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

- የትምህርት ጥራት ችግር፣
- የትምህርት ሽፋንና ፍትሃዊነት በሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ፣
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት በጣም ዝቅተኛ መሆን፣
- ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትና ስልጠና በቂ ትኩረት አለማግኘት፣

### የትኩረት መስኮች (Focus Areas)

- ፍትሐዊ ተደራሽነት፣
- ጥራትና ተገቢነት፣
- ተግባራዊነት፣
- ርትዕነት፣
- የህይወት ዘመን ትምህርት፣

### የትኩረት አቅጣጫዎች

የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ትምህርት ቤቶች በሂደት በተማሪዎች የሚወደዱ እና ለሁለንተናዊ ዕድገት ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ (ትምህርት ቤቶች ከቤት ቀጥሎ ለመማሪያ እና ማዘውተሪያ ምቹ

እንዲሆኑ ማድረግ)፣ የትምህርት ተደራሽነትን እና ሽፋንን ከጥራት እና ተጨባጭ ግብ ጋር ማመጣጠን (የተደራሽነት እና ጥራት ሚዛን የጠበቀ የትምህርት ሥርዓት ማስፈን)፣ የትምህርት ሥርዓት የበቁ ዜጎች መቅረጫ መሆኑን ከሕጻንነት እስከ ወጣትነት በሚደረጉ ክትትሎች ማረጋገጥ (የሥነ ተዋልዶ፣ ጤና፣ ሥነ ምግብ ጉዳዮችን ያካተተ ትውልድን ከሥር የመቅረጽ ስትራቴጂ)፣ ትምህርትን ከኢንዱስትሪ ፍላጎት ጋር ማዘጋጀት፣ ስልጠና ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት፣ ለግብርና ልማት፣ ለቱሪዝም ልማት፣ ለቴክኖሎጂ ልማት፣ ትምህርት በሣይንሳዊ እና ቴክኖሎጂ ዕውቀት ችግሮችን በየደረጃው የመፍቻ ብቸኛ መሣሪያ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ማድረግ፣ ሣይንሳዊ ዕውቀትን ከግብረ ገብነት እና መልካም ባሕላዊ እሴቶች ጋር ማቀናጀት፣ ከታች ማብቃት፣ ከላይ ማረቅ እና መልሶ ማልማት፣ ዕውቀትን የሚሸልም፣ ተወዳዳሪነትን የሚያበረታታ የትምህርት ሥርዓት፣ የዓለም አቀፍ የዕውቀት እና የቴክኖሎጅ አቅጣጫን ግምት ውስጥ ያስገባ የትምህርት ሥርዓት፣ በመንግሥት ድጋፍ የሚታገዝ ማብቃትን እና ሣይንሳዊ ዕውቀትን ማዕከል ያደረገ የግል ትምህርት ቤቶች ሥርዓት፣ ከተግባር ጋር የተቀናጀ የጎልማሶች ትምሕርት ሥርዓት መተግበር እንዲሁም ቀልጣፋ የትምህርት አስተዳደር ሥርዓት ማስፈን የሚሉት ናቸው።

**ዓላማ፡-ጥራት ያለው ትምህርትና ሥልጠና ለሁሉም በፍትሀዊነት ተደራሽ በማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ብቁ ዜጐችን ማፍራት፣**

**ግብ 1 ፡- ጥራት ያለው የትምህርት ተደራሽነትን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- ደረጃ 3 የደረሱ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2018 በጀት ዓመት 20% ማደረስ
- ደረጃ 3 የደረሱ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2018 ዓ.ም 15% ማደረስ
- ደረጃ 3 የደረሱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2018 በጀት ዓመት 29% ማደረስ
- ደረጃ 4 የደረሱ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2018 በጀት ዓመት 1% ማደረስ
- ደረጃ 4 የደረሱ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2018 በጀት ዓመት 1% ማደረስ
- ደረጃ 4 የደረሱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2018 በጀት ዓመት 1% ማደረስ
- በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ ከነበረበት 1፡45 ወደ 1፡30 ማድረስ
- በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ ከ1፡32 ወደ 1፡40 ማድረስ
- በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ ከነበረበት 1፡54 ወደ 1፡40 ማድረስ፣
- የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህር መምሪያ፣ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች በሁሉም አንድ ለአንድ ባልደረሱባቸው የትምህርት አይነቶች የመጽሐፍት ህትመት በክልል ሲታተም ማሰራጨትና የመጽሐፍ ተማሪ ጥምርታውን ከነበረበት 1፡2 ወደ 1፡1 ማድረስ፣

- የት/ቤት ምገባ መርሀ ግብር ተጠቃሚ የሆኑ የቅድመ አንደኛ እናአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በቁጥር በ2017 ከነበረበት 8,831 (ወንድ 4231 ሴት 4600) በ2018 በጀት ዓመት ወደ 11,039 (ወንድ 5289 ሴት 5750) ደርሷል፣
- ደረጃውን የጠበቀ መፀዳጃ ቤት ያላቸው ቅድመ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 24.6% በ2018 በጀት ዓመት 69% ሆኗል፣
- ደረጃውን የጠበቀ የመፀዳጃ ቤት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 45.3% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 65% ከፍ ብሏል፣
- ደረጃውን የጠበቀ የመፀዳጃ ቤት ያላቸው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶ ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 86.7% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 100% ሆኗል፣
- ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 27.3% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 88% ከፍ ብሏል፣
- ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 40.4% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 88% ከፍ ብሏል፣
- ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 82.3% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 100% ከፍ ብሏል፣
- ደረጃውን የጠበቀ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ያላቸው አንደኛና መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 14% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 42% ከፍ ብሏል፣
- የሣይንስ ክፍል ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 50% በ2018 በጀት ዓመት 60% ከፍ ብሏል፣
- ከርቀት ለሚመጡ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የትራንስፖርት ፕሮግራም በማመቻቸት ወደ መፈተኛ ጣቢያዎች እንዲደርሱ 100% ማድረስ፣

**ግብ 2 ፡- የትምህርት ተደራሽነትን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- ጥቅል አንደኛ ክፍል ተሳትፎ ምጣኔ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 63.3% (ወ 63.29%፣ ሴ 63.34%) በ2018 በጀት ዓመት 215.84% (ወንድ 209.29% ሴት 223.16%) ማድረስ፣
- ንጥር አንደኛ ክፍል ቅበላ ምጣኔ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 54.01% (ወ 52.4፣ ሴ 54.01) በ2018 በጀት ዓመት 100% ( ወንድ 100% ሴት 100%) ማድረስ፡፡

- ከ1-6ኛ ክፍል ጥቅልየትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 47.52% (ወ 46.25%፣ ሴ 48.89%) በ2018 በጀት ዓመት 83.79% (ወንድ 82.84% ሴት 84.81%) ማደረስ
- ከ1-6ኛ ክፍል ንጥር የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 45.37% (ወ 44.11% ፣ ሴ 46.73%) በ2018 በጀት ዓመት 70.23% (ወንድ 70.29% ሴት 70.18%) ማድረስ፤
- ጥቅል ከ7-8ኛ ክፍል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 35.68% (ወ 29.99%፣ ሴ 42.28%) በ2018 በጀት ዓመት 48.29% (ወንድ 43.27%፣ ሴት 54.11%) ማድረስ
- ከ7-8ኛ ክፍል ንጥር የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 31.57% (ወ 26.37%፣ ሴ 37.6%) በ2018 በጀት ዓመት 47.28% ( ወንድ 42.59% ሴት 52.2%) ማድረስ፣
- ከ1-8ኛ ክፍል ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 44.83% (ወ 42.46%፣ ሴ 47.43%) በ2018 በጀት ዓመት 75.72% (ወንድ 73.62%፣ ሴት 78.03%) ማድረስ፣
- ከ9-12ኛ ክፍል ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 12.86% (ወ 10.30%፣ ሴ 16.28%) በ2018 በጀት ዓመት 45.94% (ወንድ 36.60% ሴት 58.39%) ማድረስ፤
- ከ9-12ኛ ክፍል ንጥር የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 10.89% (ወ 8.63% ፣ ሴ 13.91%) በ2018 በጀት ዓመት 25.94% (ወንድ 23.60% ሴት 27.39%) ማድረስ

**ግብ 3 ፡- የትምህርት ውስጣዊ ብቃትን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- አንደኛ ክፍል መጠነ መድገም 17.1 (ወ 18.55 ሴ 15.57) በ2018 በጃት ዓመት 2.0 በመቶ ዝቅ ማድረግ፣
- የአንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ - 6ኛ ክፍል) መጠነ መድገምን 11.01 (ወ 12.89 ሴ 9.04) በ2018 በጀት ዓመት ወደ 2.0 በመቶ መቀነስ፣
- የመካከለኛ ደረጃ (ከ7ኛ - 8ኛ ክፍል) መጠነ መድገምን 10.77 (ወ 13.02 ሴ 8.96) በ2018 በጃት ዓመት ወደ 2.0 በመቶ ዝቅ ማድረግ፣

- የሁለተኛ ደረጃ (ከ 9ኛ - 12ኛ ክፍል) መጠነ መድገምን 17.9 (ወ 18.2 ሴ 17.2) በ2018 በጀት ዓመት ወደ 2.0 በመቶ ዝቅ ማድረግ፣
- የቅድመ አንደኛ ደረጃ መጠነ ማቋረጥን በክትትል መረጃ ከነበረበት ወንድ 41.1 በመቶ፣ ሴት 41.4 በመቶ በድምሩ 42.3 በመቶ ወደ 2.0 በመቶ መቀነስ፣
- የአንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ - 6ኛ ክፍል) መጠነ ማቋረጥን በክትትል መረጃ ከነበረበት ወንድ 35.17 በመቶ ሴት 34.98  በመቶ በድምሩ 35.08 በመቶ ወደ 2.0 በመቶ ዝቅ ማድረግ፣
- የመካከለኛ ደረጃ (ከ7ኛ - 8ኛ ክፍል) መጠነ ማቋረጥን በክትትል መረጃ ከነበረበት ወንድ 35.82 ሴት 36.30 በመቶ በድምሩ 36.08 በመቶ ወደ 2.0 በመቶ ዝቅ ማድረግ፣
- የሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል) መጠነ ማቋረጥን ከነበረበት ወንድ 20.8 በመቶ፣ ሴት 22.5 በመቶ በድምሩ 21.7 በመቶ ወደ 2.0 በመቶ ዝቅ ማድረግ፣

**ግብ 4 ፦ የመምህራንን ሥልጠና እና ሙያዊ ብቃት ማሻሻል፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፣**

- ትምህርት ቤትን መሰረት በማድረግ አዲስ በተቀረጸው ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ (ተሙማ) የተሳተፉ የቅድመ አንደኛ፣ የአንደኛና መካከለኛ እና የ2ኛ ደረጃ መምህራን ድርሻ በመቶኛ በ2017 ዓመት ከነበረበት 80.88% (ወንድ 79.64% ሴት 82.6%) በ2018 በጀት ዓመት 100% (ወንድ 100% ሴት 100%) ላይ ደርሷል፣
- በጀማሪ መምህርነት ለሚቀጠሩ መምህራን የሙያ ትውውቅ እና ልምድ እንዲቀስሙ ማድረግ በቁጥር በ2018 ዓ.ም 289 ደርሷል፣
- የትምህርት ደረጃውን የሚያሟሉ የቅድመ አንደኛ፣ የልዩ ፍላጎት፣የአንደኛ፣ የመካለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓመት ከነበረበት 99.46% (ወንድ 99.62% ሴት 99.18%) በ2018 በጀት ዓመት 100% (ወንድ 100% ሴት 100%) ላይ ደርሷል፣
- በየትምህርት አይነቱ የይዘትና የፔዳጎጂ አጫጭር ስልጠና የተሰጣቸው የመካከለኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ብዛት በቁጥር በ2018 በጀት ዓመት 600 ሆኗል፣
- አጫጭር ስልጠና የተሰጣቸው የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አመራሮች ብዛት በቁጥር በ2018 በጀት ዓመት 25 ሆኗል፣
- የመምህራን ከስራ የመልቀቅ ምጣኔ በመቶኛ በ2017 ዓመት ከነበረበት 2.1% በ2018 ወደ 2% ዝቅ ብሏል።

**ግብ 5 ፦ የሥርዓተ-ትምህርቱን ተገቢነትና ጥራት እንዲሁም የመማሪያ ቁሳቁሶችን ማሻሻል፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፣**

- ዘመኑን የዋጀ የትም/ት ስታንዳርድ ከማሟላት አንጻር የትምህርት ሥርዓቱን ማሻሻልና ማዘመን፣
- አሳታፊ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችንና ቴክኖሎጂን በመማሪያ ክፍሎች አቀናጅቶ መጠቀም፣
- በሥርዓተ ትምህርቱ አማካይነት በጥልቀት ማሰብን፣ ፈጠራንና ችግርን የመፍታት ክህሎትን ማበረታታት፣
- የህዝብ ባህልና እሴት በስርዓተ-ትምህርቱ ሲካተት መተግበር

**ግብ 6 ፡- የተማሪዎችን የማቆየትና የማሳለፍ ምጣኔ ማሻሻል፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፣**

- ከመደበኛ ትምህርት በኂላ የተለያዩ ቲቶሪያሎችንና ሌሎች ድጋፎችን በማመቻቸት የማጠናከሪያ ትምህርት የሰጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 47 በ2018 ዓ.ም 55 ሆኗል፣
- በችግር ውስጥ የሚገኙ ህጻናትን በመለየት መደገፍ የሚያስችል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት መዘርጋት፣
- ወላጆችና ማህበረሰቡ የመማር ማስተማር ሂደቱን እንዲደግፉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- የማቋረጥ ምጣኔን ለመቀነስ የገንዘብ ድጋፍን ማጠናከርና የውጭ ትምህርት ዕድልን ማመቻቸት፣
- የ6ኛ ክፍል የማጠናቀቅ ምጣኔን በ2018 በጀት ዓመት 60 በመቶ ማድረስ
- የ8ኛ ክፍል የማጠናቀቅ ምጣኔን በ2018 በጀት ዓመት 50 በመቶ ማድረስ፣
- የ7ኛ ክፍል የመዝለቅ ምጣኔን በ2018 በጀት ዓመት 55 በመቶ ማድረስ፣
- የ12ኛ ክፍል ሀገራዊ ፈተና ተመዝነው 50 በመቶ እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓመት ከነበረበት 7.1% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 10% (ወንድ 10% ሴት 10%) ከፍ ማድረግ

**ግብ 7 ፡- የትምህርት ፍትሐዊነትንና አካታችነትን ማሻሻል፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፣**

- የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ያታዊ ምጥጥን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.02 በ2018 በጀት ዓመት 1 ማድረስ

- ከ1-6ኛ ክፍል ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥን፣ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.06 በ2018 በጀት ዓመት ወደ1 ዝቅ ማድረግ፣
- ከ7-8ኛ ክፍል ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.4 በ2018 በጀት ዓመት ወደ 1.1 ዝቅ ማድረግ፣
- ከ9-12ኛ ክፍል ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.58 በ2018 በጀት ዓመት ወደ1.15 ዝቅ ማድረግ፣
- የቅድመ አንደኛ ደረጃ የሴት መምህራን ድርሻ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 93.24% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 97% ማድረስ
- የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ የሴት መምህራን ድርሻ፣ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 38% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 50.5% ማድረስ
- የሁለተኛ ደረጃ የሴት መምህራን ድርሻ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 19.77% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 21% ከፍ ማድረግ
- የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ የሴት ር/መምህራን ድርሻ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 6.38% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 7% ከፍ ማድረግ
- የቅድመ-አንደኛ የልዩ ፍላጎት ትም/ት ተሳትፎ በመቶኛ በ2017 ዓመት ከነበረበት 0.3% (ወንድ 0.29% ሴት 0.31%) በ2018 በጀት ዓመት 0.8% (ወንድ 0.8% ሴት 0.8%) ላይ ማድረስ
- ጥቅል የአንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ - 6ኛ ክፍል) የልዩ ፍላጎት ትም/ት ተሳትፎ፣በመቶኛ በ2017 ዓመት ከነበረበት 5.79% (ወንድ 6.35% ሴት 5.19%) በ2018 በጀት ዓመት 15.2% (ወንድ 9.68% ሴት 21.16%) ላይ ማድረስ
- ጥቅል የመካከለኛ ደረጃ (ከ7ኛ-8ኛ ክፍል) የልዩ ፍላጎት ትም/ት ተሳትፎ፣ በመቶኛ በ2017 ዓመት ከነበረበት 3.4% (ወንድ 3.32% ሴት 3.5%) በ2018 በጀት ዓመት 4.47% (ወንድ 4.64% ሴት 4.27%) ላይ ማድረስ
- ጥቅል የሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ-12ኛ ክፍል) የልዩ ፍላጎት ትም/ት ተሳትፎ፣በመቶኛ በ2017 ዓመት ከነበረበት 0.88% (ወንድ 0.87% ሴት 0.90%) በ2018 በጀት ዓመት 1.88% (ወንድ 1.86% ሴት 1.9%) ላይ ማድረስ

**ግብ 8 ፦ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትን ማጠናከር፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የቅድመ አንደኛ ትምህርት ተደራሽነትን እና የህጻናት ልማት ፕሮግራሞችን ማስፋፋት

- የቅድመ አንደኛ ትምህርት ፕሮግራም በክልል ሲቀረጽ መተግበር
- በቤት ውስጥ የቅድመ አንደኛ ትምህርትን መጀመር እንዲቻል ለወላጆች ድጋፍ ማድረግ፣
- የትምህርት ደረጃውን የሚያሟሉ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንን ብዛት ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣
- ደረጃ 3 የደረሱ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በመቶኛ በ2018 በጀት ዓመት 20% ማድረስ፣
- የራሳቸው መፀዳጃ ቤት ያላቸው ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 100% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 100% ከፍ ማድረስ
- ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ተሳትፎ ምጣኔ በመቶኛ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 38.24% (ወንድ 37.91% ሴት 38.59%) በ2018 በጀት ዓመት 45.4% ( ወንድ 45.37% ሴት 45.43%) ሆኗል፣

**ግብ 9 ፡- የጎልማሶች እና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ማረጋገጥ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፣**

- ማንበብ፣ መጻፍን እና የሙያ ትምህርትን ጨምሮ የጎልማሶች መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ፕሮግራም በተገቢው መንገድ መተግበር፣
- በአጋር ድርጅቶችና ባለሀብቶች አጋዥነት የተግባር ተኮር ስልጠናና ክህሎት ማሳደግ ስራን ማጠናከር፣
- በመሰረተ ትምህርት የሚሳተፉ ጎልማሶችን ሽፋን ማሳደግ በቁጥር በ2017 ዓመት ከነበረበት 5431 (ወንድ 3421 ሴት 2010) በ2018 በጀት ዓመት ወደ 10862 (ወንድ 5431 ሴት 5431) ላይ ማድረስ

**ግብ 10፡- የትምህርት አመራርንና ተጠያቂነትን ማጠናከር፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፣**

- በአንደኛ፣ በመካከለኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ግልጸኝነት የሰፈነበትና ውጤታማ የሆነ የትምህርት ቤት አመራር ሥርዓት መዘርጋት በመቶኛ በ2018 በጀት ዓመት 65% ደርሷል፣
- በሁሉም የአንደኛ፣ የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወላጆችን፣ መምህራንን እና ባለድርሻ አካላትን በመማር ማስተማሩ ሂደት የውሳኔ ሰጭነት ሚናቸውን ከፍ ማድረግ በመቶኛ በ2018 በጀት ዓመት 4% ደርሷል፣

- በሁሉም የአንደኛ፣ የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወላጆችን፣ መምህራንን እና ባለድርሻ አካላትን በመማር ማስተማሩ ሂደት የውሳኔ ሰጭነት ሚናቸውን ከፍ ለማድረግ በ2018 በጀት ዓመት 4 ጊዜ ማካሄድ፣
- የትምህርት ሰርዓቱን ውጤታማነት ለመመዘንና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚረዱ መመዘኛዎችን መተግበር፣

**ግብ 11 ፡- የሣይንስ፣ የቴክኖሎጅ፣ የምህንድስና እና የሂሳብ ትምህርትን (STEAM) በዞኑ ማስፋትና ማጠናከር፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የተሟላ የቤተ ሙከራ አፓራተስ እና ኬሚካል ያላቸው ት/ቤቶች ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 63% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 67% ከፍ ማድረግ
- የፈጠራ ስራ ውድድር ያካሄዱ አንደኛና መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በመቶኛ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.5% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 10% ከፍ ማድረግ
- በቤተሙከራ የተደገፈ ትምህርት የሚሰጡ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 68.6% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 75% ከፍ ማድረግ
- በቤተ-ሙከራ የተደገፈ ትምህርት የሚሰጡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 87.5% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 95% ከፍ ማድረግ

**ግብ 12 ፡- ቤተ-መጽሐፍትን በማስፋፋት በክልሉ ያለውን የንባብ ባህል ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ፡-**

- ቤተ መጻህፍት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 67% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 70% ከፍ ማድረግ
- ቤተ መጻህፍት ያላቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 100% በ2018 በጀት ዓመት ወደ 100% ከፍ ማድረግ

**ግብ 13፡- በበጀት ዓመቱ ለ410 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ፡-**

- በዲፕሎማና በዲግሪ ደረጃ የተመረቁ 130 መምህራን የስራ እድል ተፈጥሯል
- ለ 80 የስርዓተ ምገባ አስተናጋጅ በቅጥር ማሟላት፣
- ለ200 ወጣቶች በጥገና ፣ ግንባታና በፈርኒቸር ዘርፍ የሚሰሩ የስራ ዕድል ይፈጠራል፤

## የማስፈጸሚያ ስልቶች

በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ ትብብር የጥራት ማዕከል ሞደል ትምህርት ቤቶችን ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መገንባት፣ የትምህርት ጥራትን ማዕከል አድርገው ለሚሰሩ የግሉ ዘርፍ ተዋንያን የመሬት አቅርቦት ድጋፍ ማድረግ፣ ተጠቃሚ ማህበረሰብን መሠረት ያደረገ የትምህርት ታክስ እንዲሁም ባለሃብቱን እና የውጭ አጋሮችን ያሳተፈ የትምህርት ፈንድ እና ፋውንዴሽን/ስኮላርሽፕ/ ኢንዱስትሪዎች የሚፈልጉትን የሙያ ክህሎት በመንግስት የስልጠና ማዕከላት እንዲያከናውኑ ማድረግ የሚሉት የዘርፉ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው።

### 2.5.5. ጤና

በሃገራችን በኢትዮጵያ በህይወት የመኖር ምጣኔ በ1968ዎቹ ከነበረበት 38ዓመት በ1995 ወደ 49ዓመት በ2018 65.5 እና በ2021 ወደ 68.7 ዓመት በከፍኛ ሁኔታ እያደገ መጥቷል። ይህ ውጤት የተመዘገበው ህፃናት ጤና ላይ በተለይም የክትባት ተደራሽነት ላይ በተሰራው ስራ የህፃናት ሞት በመቀነሱ እንዲሁም ኤችአይቪ ኤድስ ላይ በተሰራው ስራ ነው። እንደ አማራ ክልል በህይዎት የመኖር ምጣኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸሻለ የመጣ ሲሆን በ1980 ከነበረው 48 ዓመት ወደ በ2019 ወደ 69 ዓመት ከፍ ብሏል።

በአሁኑ ወቅት አንደ ክልል በሁለት ዋና ዋና የጤና ችግሮች (ተላላፊ የሆኑ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች የአእምሮ ህመምን ጨምሮ) እያስተናገደ ይገኛል። ዞናችንም በተመሳሳይ የዚህን ችግር ተጠቂ ነው። እነዚህ ችግሮች በሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ በተለይም በህጻናት እና በመውለድ የእድሜ ክልል ባሉ ሴቶች ላይ የጎላ ጫና አላቸው። ተላላፊ በሽታዎች በአብዛኛው ለሚከሰት ህመም እና ሞት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ሲሆን በእናቶች እና ጨቅላ ህጻናት ላይ የሚከሰት የምግብ እጥረት ለዚህ ችግር ከፍተኛ አስተዋጥኦ አለው ተብሎ ይገመታል።

የጤና መሰረተ ልማት የጤና ስርዓት ከተገነባባቸው አንኩዋር ምሶሶዎች አንዱ ሲሆን በደቡብ ወሎ ዞን 429 ጤና ኬላዎች፣133 ጤና ጣቢያዎች፣ 9 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች እንዲሁም 2 ጠቅላላ ሆሰፒታሎች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። በነባሩ በሀገር አቀፍ ከተቀመጠው ስታንዳርድ አንጻር በጤና ኬላ 82%፣ በጤና ጣቢያ 105%፣ እንዲሁም በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል 28.6% ደርሷል ነገር ግን በአድሱ የጤና ፖሊስ ክለሳ አንጻር ሲታይ የጤና ተቋማት የብሎክና የክፍሎች ብዛት ከሚሰጠው የህክምና አገልግሎት አንጻር ብዙ ጤና ተቋማት ማስፋፊያ ያስፈልጋቸዋል በሌላ መልኩ ከአድሱ የጤና ኤክስቴሽን ፍኖተ ካርታ ጋር በተያያዘ ጤና ኬላዎች በአድሱ ስታንዳርድ ካታጎራይዝድ የተደረጉ ሲሆን በዚህም የመሠረታዊና የአጠቃላይ የጤና ኬላዎች ግንባታ በየወረዳው ሲታይ ገና ጅምር ስራዎች ያሉ ሲሆን በቀጣይ ይህ ተግባር ልዩ ትኩረትና እርብርብ ይፈልጋል

እንድሁም የሆስፒታሎች ተደራሽነት ከዞኑ ህዝብ ብዛት አንጻር ሲታይ 22 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ያስፈልጋሉ፡፡

የጤና የሰው ሀይል ልማት በዞኑ በአጠቃላይ 6176 ሰራተኞች ሲኖሩ 4098 የተለያየ የጤና ባለሙያዎች ናቸው፡፡ ይህም ቢሆን ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋንን (UHC) ለማሳካት የአለም ጤና ድርጅት ካወጣው የህዝብ ጥምርታ ለ10000 ሲታይ የዞኑ የሰው ሀይል 13 ለ10000 ጥምርታ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

የህክምና ግብዓቶች ብክነት ለመከላከል በጤና ተቋማት የሚገኙ ለብክነት የተቃረቡ መድሀኒቶች ከተቋማት ተቋማት አዘዋውሮ ለመጠቀም ክልል ጤና ቢሮው የግብዓት ዝውውር መመሪያን ያስተዋወቀልን በሆኑ ትግበራውን በመጀመር ብክነት ለመቀነስ እየተሰራ ሲሆን አሁን ያለን የብክነት ምጣኔ በጤና ጣቢያዎች 0.35% በሆስፒታሎች ደግሞ 1.4% ነው፡፡

የጤና ፋይናንስ ለተሻለ ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን ተደራሽ እንዲሆን ለማስቻል የሚረዳ የጤና ስርዓት ዋነኛ መሳሪያ ነው፡፡ የጤና ፋይናንስ ሶስቱ ተቀዳሚ ተግባራት ለጤና ተቋሙ ሀብት ማመንጨት፥ ሀብት ማሰባሰብ እና በአንድ ቋት ማሰባሰብ እና ኣስተዳደር እንዲሁም የተሻለ ግዥ አፈጣጠም እንዲኖር ማስቻል ነው፡፡ የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ትግበራ በ 22 ወረዳዎች በማስጀመር 494,555(86.2%) አባወራዎች/ እማዎራዎች አባል በማድረግ ከ2.1 ሚሊዮን በላይ ዜጎች በማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሉዋል፡፡

የዲጂታል ጤና ሲስተሞችን ትግበራን ማጠናከር እና ማስፋፋት ሀገር አቀፍ የጤና የመረጃ ስርዓት(Ehmis/Dhis2) ኢኒሼቲቭ ትግበራ ቀደም ባሉት አመታት ተጀምሮ ተግባራዊ የተደረገ እና በ2016በጀት አመት አዲሱ ቨርዥን 2.40 በብዙ የጤና ተቋማት የተተገበረ ሲሆን በተሰሩት ጥልቅ ስራዎች(ስልጠና ክትትል እና ድጋፍ፥ የግብዓት ድጋፍ) አማካኝነት አብዛኛው የጤና ተቋማት (ጤና ጣቢያ 99.6%፥ ጤና ኬላ 97%፥ ሆስፒታል 100% እንዲሁም የግል ክሊኒክ 92%) በአዲሱ ቨርዢን ሪፖርት መላክ ጀምረዋል፡፡

እኤዘአ በ2023 የተመድ ባወጣው ሪፖርት መሰረት በኢትዮጵያ በ2020 የእናቶች ሞት ምጣኔ ከ100000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት 267 እንደደረሰ ያሳያል፡፡ ይህ ቁጥር 2016 ከነበረው 412 የእናቶች ሞት ምጣኔ ከ100000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት ሲታይ ከፍተኛ መሻሻል አሳይቱዋል፡፡ በአጠቃላይ የእናቶች እና ህፃናትን ሞት ለመቀነስ በስነተዋልዶ፥ የእናቶች፥ የጨቅላ ህፃናት እና ህፃናት ጤና እንዲሁም የአፍላ እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣቶች ጤና ላይ ከፍተኛ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ይህም በቀጣይ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል፡፡

በበሽታዎች መከላከል እና ቁጥጥር ፕሮግራም ረገድ ባለፉት ጊዜያት አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ ሲሆን ባለፉት አስርት አመታት እንደ ኤችአይቪ፥ ቲቢ እና ወባ ባሉ ዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች ምክንያት የሚከሰት ህመም እና ሞትን በከፍተኛ መጠን መቀነስ ተችሉዋል፡፡ እንዲሁም ተላላፊ ያልሆኑ ዋና ዋና በሽታዎች ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ከፍተኛ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

የጤና ዘርፍ ግቦችን ለማሳካት የማህበረሰብ ባለቤትነት ዋነኛው መርህ እና ስትራቴጂ ነው፡፡ በደቡብ ወሎ ዞን ከጤና ኤክስቴንሽን መረሀ ግብር ጋር ተያይዞ የህበረተሰቡ ተሳትፎ ከፍተኛ ነው፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሴቶች ልማት ህብረት ከማህበረሰቡ አባላት በመመልመል ማህበረሰቡን ተሳትፎ እና ባለቤትነት ለማሳደግ ተሞክሩዋል፡፡ ነገር ግን የማህበረሰቡ ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጥቱዋል፡፡ ባለፉት አመታት በክልሉ እነዲሁም በዞኑ በተከሰቱ የፖለቲካ ነውጦች፥ ግጭቶች እና አለመረጋጋቶች ጋር ተያይዞ የመጣው የማህበረሰብ አቀፍ ተሳትፎ መቀዛቀዝ ለማሻሻል በአንዳንድ ወረዳዎች የጎጥ የማህበረሰብ ጤና አመራሮች (Village Health Leaders) በማፍራት የማህበረሰብ ተሳትፎ የማጠናከር ስራ ተጀምሩዋል፡፡

በአጠቃላይ በጤናው ዘርፍ ብዛት ያላቸው አመርቂ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም ከሚፈለገው ስታንዳርድ አንጻር አሁንም ከፍተኛ ስራ በቀጣይ አመታት መሰራት እንዳለበት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

**ስትራቴጃዊ ጉዳዮች**

- መከላከል
- መጠበቅ
- ማሻሻል

**የትኩረት መስኮች**

- የጤና አገልግሎትን በጥራት እና በፍትሃዊነትን መስጠት
- የመረጃ አብዮትን ማረጋገጥ
- ተነሳሽነት ያለው፣ ብቁ እና ርህሩህ የጤና ሰራተኛ መፍጠር
- የአመራርና የአስተዳደር ሥርዓትን ማሳደግ
- የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻል

**የትኩረት አቅጣጫዎች**

የጤና መሠረተ ልማት ማሻሻል፣የክልሉን መነሻ በመውሰድ የዞኑን አሁናዊ እና የወደፊት ፍላጎት መሠረት ያደረገ የጤናው ዘርፍ የሰው ሃብት ልማት ማሻሻል፣ፈጠራ የታከለበት እና አካታች የሆነ

የጤና ፋይናንስ ስርዓት መዘርጋት፣የጤናው ዘርፍ አመራር አስተዳደር እና ተጠያቂነት ማጎልበት፣ የህክምና መድሃኒትና የህክምና መሳሪያ ተደራሽነት አያያዝና አጠቃቀምን በማሻሻል ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣የጤና ክብካቤ ጥራት ደህንነትና ፍትሃዊነትን ማሻሻል፣የጤና ክብካቤ ደህንነትን ማሻሻል ፣ድጅታል ጤና እና በመረጃ ላይ የተመሠረተ የውሳኔ አሰጣጥን ማሳደግ፣የህዝብ ጤና ድንገተኛ አስተዳድር ስርዓትን የመቋቋም እና ውጤታማነትን ማሳደግ፣የጤና ምርምርን ማሳደግና የፈጠራ ስራዎችን ማፋጠን የማህበረሰብ ተሳትፎን ማሻሻል እንድሁም የጤና ቁጥጥር ስርዓትን ማሻሻል የሚሉ የዘርፉ የበጀት አመቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ፡፡

**ዓላማ**:- ለተግዳሮት አይበገሬ የጤና ስርዓት በዞኑ በመገንባት እና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት በፍትሃዊነት ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ተደራሽ በማድረግ ጤናማና አምራች ዜጎችን መፍጠር

**ዋና ዋና ግቦች**

**ግብ 1፡ የጨቅላ ሕፃናትን እና ሕፃናትን ሞት መቀነስ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ሞተው የሚወለዱ ጨቅላ ህፃናትን ከ1000 ከሚወለዱ ህፃናት ቁጥር መጠን ከ 7 ወደ 5 መቀነስ፣
- ለህክምና ወደ የጨቅላ ህጻናት ፅኑ ህመም ህክምና አገልግሎት ተኝተው ከሚታከሙ ጨቅላ ህፃናት አገግመው (ድነው) የሚወጡ ህፃናት መጠን ከ81% ወደ 90% ማድረስ፡፡
- በሳምባ ምች ይታመማሉ ተብለው ከሚገመቱ በፀረ-ተዋህሲያን የታከሙ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ሽፋን ከ100% ማስቀጠል፣
- በጨቅላ ሕጻናት ኢንፌክሽን በሽታ (NNS/VSD) ይያዛሉ ተብለው ከሚገመቱት የታከሙ ህጻናት ሽፋን ከ61% ወደ 5,674 (70%) ማድረስ፣
- በተቅማጥ ይታመማሉ ተብሎ ከሚገመተው ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት የህይወት አድን ህክምናን (ORS & Zinc) አገልግሎትያገኙ ከ39% ወደ 268,882 (63%) ማድረስ፣
- የፔንታ ቫለንት ሶስት ክትባት ሽፋን 98,002 (100%) ማስቀጠል፣
- የማህጸን በር ካንሰር መከላከያ ክትባት ሽፋን 100% ማስቀጠል፣
- ሁሉንም ዓይነት ክትባት ያገኙ ህፃናት ሽፋን 98,002 (100%) ማስቀጠል፣
- መከላከል ለሚቻሉ በሽታዎች መጠነ ሰፊ የክትባት ዘመቻ ማካሄድ፥
- ጡት ማትባት እና ሕፃናት ስርዓተምግብ ማበረታታት እና መደገፍ፥

- ለእናቶች በልጆች ጤና አጠባበቅ እና በንጽህና አያያዝ ላይ ትምህርት መስጠት፥
- በየወሩ የእድገት ክትትልና ማበልጸግ የሚደረግላቸው እድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሽፋን ከ89% ወደ 142,938 (90%) ማሳደግ፣
- የስርዓተ ምግብ ልየታ አገልግሎት ያገኙ እድሜያቸው ከአምስት አመት በታች የሆኑ ህጻናት ሽፋን ከ 87% ወደ 396,933 (93%) ማሳደግ፣

**ግብ 2፦ የእናቶችን ጤና ማሻሻል**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በሰለጠነ ባለሙያ የሚሰጠውን የወሊድ አገልግሎት ከ64% ወደ 85% (90,266) ማድረስ፣
- የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት እና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት ትምህርትን ተደራሽነትን ማሳደግ
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች(CAR) መጠን ከ98% ወደ 99% (630,125) ማድረስ፣
- የረጅም ጊዜ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ሽፋን ከ27% ወደ 42.7% ማድረስ፥
- የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት የሚሰጡ የስብዕና መዓእከላት ቁጥር ከ3 በቶ ወደ አምስት በመቶ ማድረስ፥
- ለ 8979 ደህንነቱ የተረጋገጠ የጽንስ ማቋረጥ አገልግሎት መስጠት ፥
- የአንደኛውን ቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ያገኙ እናቶች ከ81 ወደ 100,885 (95%)
- ድንገተኛ የጽንስ ህክምና ክትትል የሚያገኙ እናቶችን ሽፋን ማሳደግ፥
- የድህረ ወሊድ ክትትል (በ2 ቀናት ውስጥ) አገልግሎት ከ75% ወደ 95,576 (90%) ማድረስ፣
- ከ12 ሳምንት እና በፊት የቅድመ ወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን ከ35% ወደ 55%ማድረስ፣
- የአምቡላን አገልግሎት ጥያቄ ምላሽ ያገኙ ታካሚዎች ከ87% ወደ 90% ማሳደግ፣
- እናቶች በወለዱ በአንድ ደቂቃ ውስጥ Utrerotonic የተሰጣቸው ሽፋን 90,266 (100%) ማስቀጠል፣
- በቀዶ ህክምና የሚወልዱ የእናቶች መጠን ከ2.9% ወደ 8.5% ከፍ ማድረግ፣
- የእናቶች ማቆያ ያላቸው ጤና ጣቢያዎች ቁጥር ከ76 ወደ 100 ከፍ ማድረግ

**ግብ 3፣- ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- የበሽታ ክትትል እና ምላሽ አሰጣጥ ስርዓቶችን ማጠናከር፥
- በኤች አይ ቪ መከላከል ጥልቅ የባህርይ ለውጥ ተግባቦት አገልግሎት ያገኙ ሴተኛ አዳሪዎች 8995 (100%) ማስቀጠል፥
- በኤች አይ ቪ መከላከል ጥልቅ የባህርይ ለውጥ ተግባቦት አገልግሎት ያገኙ ይበልጥ ተጋላጭ እና ቅድሚያ ለሚሰጣቸው (KPP) የማኅበረሰብ ክፍሎች አፈጻጸም ወደ 67,429 (100%) ማስቀጠል፣
- በኤች አይ ቪ መከላከል ጥልቅ የባህርይ ለውጥ ተግባቦት አገልግሎት ያገኙ የረጅም ርቀት አሽከርካሪዎች ከ99% ወደ 1002 (100%) ማድረስ፥
- የፀረ-ኤችአይቪ መድሃኒት አሁን እየወሰዱ ያሉትን አዋቂዎችና ሕፃናት ቁጥር ከ 17,517 ወደ 18,647 ማሳደግ፣
- የፀረ-ኤች.አይ. ቪ መድሃኒት ከሚወስዱ አዋቂዎችና ሕፃናት ውስጥ በደማቸው ያለው የኤች አይቪ ቫይረስ መጠን በሚሊ ሊትር ከ1,000 ኮፒ በታች የሆኑት ከ98% ወደ 16447 (99%) ከፍ ማድረግ።
- የቲቢ ልይታና ህክምና መጠን ሽፋን ከ62% ወደ 4417 (96%) ማድረስ፣
- የቲቢ ህክምና Bacteriologically confirmed pulmonary TB ህክምና ያጠናቀቁ (TSR) ህሙማንን ከ98% ወደ 99% ማድረስ፣
- በወባ በሽታ አዲስ የሚያዙ ሰዎችን ምጣኔ ከ14/1000 ወደ 12/1,000 መቀነስ፣
- በወባ በሽታ ምክንያት የሚሞቱ ህሙማንን 0.001/100,000 ማድረግ
- የስጋደዌ በሽታ ልየታ መጠን 9454 (100%) ማስቀጠል፣
- በሥጋ ደዌ በሽታ ምክንያት ሁለተኛ ደረጃ የሚደረሰውን አካል ጉዳት መጠን ወደ 491 (5%) ማውረድ፣
- የጤና መረጃ አጠቃቀም ኢንዴክስ ከ81 በመቶ ወደ 90 በመቶ ከፍ ማደረግ፥
- የመንግስት ጤና ተቋማት የአገልግሎት ሪፖርት ወቅታዊነት(Timeliness) ከ85% ወደ 87% ማድረስ፣ እንዲሁም ሙሉነት (completeness) ከ98% ወደ 100% ማድረስ፣
- በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቅኝትን 45% ማድረስ
    - ✓ የግል እና የአካባቢ ንጽህና እና የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ማሻሻል፥
- የበሽታ መከላከል እና የንጽህና አጠባበቅ ትምህርትን መሻሻል፥
- ከትራኮማ ቁጥጥር ስራዎች ውስጥ የቲቲ ሰርጀሪ ስራ አሁን ካለን ባክሎግ ለ4732 ሰዎች የአይን ቆብ ቀዶ ህክምና አገልግሎት መስጠት

- የቢልሃርዝያ በሽታን ለመከላከል እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህጻናት የመከላከያ ህክምና ሽፋን ወደ 100% ማሳደግ፣

**ግብ 4፦ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ዕድሜአቸው ከ30 አመት በላይ ለሆኑና ለከፍተኛ ደም ግፊት ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጠውን የከፍተኛ ደም ግፊት ቅድመ ምርመራ 100% ማስቀጠል፣
- የከፍተኛ ደምግፊት የህክምና አገልግሎት ከሚያገኙት ታማሚዎች የደምግፊቱ በቁጥጥር ስር የዋለላቸው ታካሚዎች ከ91.4% ወደ 95% ከፍ ማድረግ፣
- እድሜያቸው ከ40 አመት በላይ እንዲሁም ሌሎች ለስኳር ህመም ተጋላጭ ለሆኑት ማህበረሰብ ክፍሎች የሚሰጠውን የቅድመ ምርመራ አገልግሎት ሽፋንን ከ42.7% 60% ማድረስ፣
- በህክምና ክትትል ላይ ካሉት ከፍተኛ የደም ስኳር ያለባቸው አገልግሎት ከሚያገኙት ውስጥ የስኳር መጠናቸው በቁጥጥር ስር የዋለላቸው ታካሚዎች ሽፋን ከ92% ወደ 95% ማድረስ፤
- ዕድሜአቸው 30-49 የሆኑ ሴቶችን ቅድመ ካንሰር የማህፀን በር ምርመራ ሽፋን ከ13.5% ወደ 27.2% ማድረስ
- የቅድመ ካንሰር ምልክት ያለባቸው ሴቶች የህክምና አገልግሎት ከ76.9% ወደ 90.6% ማሳደግ፣
- በጤናማ የአናኑዋር ዘይቤ ምርጫዎች ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ ማካሄድ፥
- በተለያዩ የህብረተሰብ ማስተማሪያ ዘዴዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እና ተመጣጠነ ምግብ ጠቀሜታን ማስተማር
- ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል የህክምና ክትትል እና መድሀኒት አቅርቦትን ኣሻሻል

**ግብ 5፦ ጥራት ያለው የጤና አጠባበቅ አገልግሎትን መማሻሻል**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- መለስተኛ የቀዶ ጥገና ህክምና ብሎክ ያላቸውን ጤና ጣቢያዎች ቁጥር ከ 7 ወደ 9 ማሳደግ፤
- በጤና ተቋማት ተመላለሶ የመጠቀም ምጣኔ አሁን ባለበት 2.9 ማስቀጠል፤
- የጤና ባለሙያ ለ1000 ሕዝብ ጥምርታ ከ1 ወደ 1.15 ማድረስ፣
- የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ስልጠና ማእከላትን ቁጥር ከ2 ወደ 3 ማሳደግ፤

- የባለሙያ ፍልሰት ምጣኔ ከ1.5% ወደ 1.0 % ዝቅ ማድረግ፡
- ሁሉን አቀፍ የጤና መድን ሽፋን ማሳደግ ከ86% ወደ 100% ማድረስ፣
- ለጤና የሚመደበውን የበጀት ድርሻ ወደ 20% ማሳደግ፣
- ከጠቅላላዉ የጤና በጀት የዉስጥ ገቢ ድርሻ 40.7% ማድረስ፣
- የተሰበሰበ ውስጥ ገቢ አጠቃቀምን 100% ማድረስ፣
- ከተሰበሰበው የውስጥ ገቢ ለጥራት ማሻሻያ የዋለ ወደ 80% ማሳደግ
- የታዘዙላቸውን መድሃኒቶች ሙሉ በሙሉ ከተቋሙ ያገኙ ታካሚዎች ምጣኔ ከ 82% ወደ 92% ማሳደግ፣
- የህይወት አድን መድኃኒቶች አቅርቦት ግኝት ከተቋሙ የመድኃኒት መዘርዝር አንፃር ከ98% ወደ 100% ማሳደግ
- የኦዲቴብል ፋርማሲቲካል ትራንዛክሽን የተገበሩ ጤና ተቋማት ሽፋን ከ17% ወደ 23.4% ማሳደግ
- በወረዳ ትራንስፎርሜሽን ትራንስፎርም ያደረጉ ወረዳዎች አሁን ካለበት ሰባት ወረዳዎች ሶስት በመጨመር 10(አስር) ትራንስፎርም ያደረጉ ወረዳዎች መፍጠር
- የወረዳ ትራንስፎርሜሽን አፈጻጸምን አሁን ካለበት 81.5% ወደ85% ማሳደግ
- ለሁሉም ዜጎች በአነስተኛ ወጪ ፍትሀዊ የጤና አገልግሎትን ማረጋገጥ፥
- በቂ የጤና አገልግሎት ባለተዳረሰባቸው አካባቢዎች የጤና መሰረተ ልማትን መዘርጋት፥
- ተጨማሪ የጤና ባለሙያዎችን ማሰልጠን እና ማሰማራት፥
- የቴሌ ሜድስን አገልግሎት ከጤና ተቋማት በርቀት ለሚገኘው ህዝብ ተደራሽ ማድረግ

**ግብ 6፦ የስነምግብ እና የምግብ ዋስትናን ማሻሻል**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የስርዓተ ምግብ ልየታ አገልግሎት ያገኙ ነፍሰጡር እና የሚያጠቡ እናቶች ሽፋን ከ67 ወደ (92,389) ወደ 77% ማሳደግ
- በየወሩ የእድገት ክትትልና ማበልጸግ የሚደረግላቸው እድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሽፋን ከ89% ወደ 142,938(90%) ማሳደግ፣
- በጤና ተቋም ከተዋለዱ ህጻናት ውስጥ ክብደታቸው ከ2500 ግራም በታች በታች የሆኑ ህጻናት ከ3 በመቶ ወደ 2.7 መቀነስ፤

- የቫይታሚን ኤ ካፕሱል ሁለት ጊዜ ያገኙ እድሜያቸው ከ6-59 ወራት የሆኑ ህፃናት 405,873 (100%) ማስቀጠል፣
- በአመት ሁለት ጊዜ የፀረ አንጀት ጥገኛ ትላትል ህክምና እንክብል የወሰዱ እድሜያቸው ከ24-59 ወራት ያሉ ህጻናት ሽፋን 267,694 (100%) ማስቀጠል፣
- ከ90 በላይ የደም ማነስ መከላከያ የአይረን ፎሌት ኪኒን የወሰዱ ነፍሰጡር እናቶች ሽፋን ከ 85% ወደ 105,133(99%) ማሳደግ፡፡
- የስርዓተ ምግብ ልየታ አገልግሎት ያገኙ ነፍሰጡር እና የሚያጠቡ እናቶች ሽፋን (67%) ወደ (92,389) ወደ77% ማሳደግ
- ከአምስት አመት በታች የስረአተ ምግብ ልየታን 100%ማስቀጠል
- የምግብ እጥረት ተገኝቶባቸው ወደ ህክምና ገብተው ከታከሙት ህጻናት ድነው የወጡ ሽፋንን ከ80% ወደ 85% ከፍ ማድረግ፥
- የግብርናው ዘርፍ የስነምግብ ችግርን ለመፍታት የሚያስችል ምርትን በአይነት በማምረት እንዲያቀርብ ማድረግ፥
- ህብረተሰብን በተመመጣጠነ ምግብ እና አዘገጃጀት ላይ ማስተማር፥
- የስነምግብ እጥረትን ለመፍታት ታሳቢ ያደረገ የምግብ ስርጭት እንዲኖር ማድረግ፥

**ግብ 7፦ የስነ አእምሮ ጤና ደህንነትን ማስፋፋት**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ከባድ አእምሮ ህመም (psychosis) የአዲስ ታካሚዎች ቁጥር ህክምና አገልግሎት ሽፋን 3703(24%) ማድረስ፣
- ድባቴ (Depression) የአዲስ ታካሚዎች የህክምና አገልግሎት ሽፋን ወደ 20.6% ማሳደግ፣
- ባይፖላር (Bipola cases) የአዲስ ታካሚዎች የህክምና አገልግሎት ሽፋን 2779 (15%) ማሳደግ፣
- የሚጥል አእምሮ በሽታ (Epilepsy-GTC) የአዲስ ታካሚዎች የህክምና አገልግሎት ሽፋን 11596(37%) ማሳደግ፣
- የአልኮል ሱስ ህክምና አገልግሎት ሽፋንን (AUD) ከ0.5 በመቶ ወደ 4.6 ማሳደግ፥
- በአእምሮ ህመም ላይ የማህበረሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ የአእምሮ ህሙማን መገለል እንዳይደርስባቸው መስራት፥
- የአእምሮ ጤንነት አገልግሎት እና ድጋፍ ተደራሽነትን ማስፋት፥

- የጤና ባለሙያዎችን በማሰልጠን የአእምሮ ጤና ሁኔታን ለይቶ ማወቅ እና መቆጣጠር፥
- ለአእምሮ ህሙማን አገልግሎት የሚውሉ የማህበረሰብ ተኮር አገልግሎት መስጫ ፕሮግራሞችን መተግበር፥

**ግብ 8፦ የውሀ፥ ሳኒቴሽን እና ሀይጅን እና አካባቢ ጤና አጠባበቅን ማሻሻል**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ የሆኑ ቀበሌዎች ሽፋን ከ24% ወደ 226(48%) ማሳደግ፣
- የደረቅ ቆሻሻን በአግባቡ የሚያስወግዱ ቤተሰቦች ሽፋን ከ66% ወደ 78.3 ማሳደግ፣
- የፍሳሽ ቆሻሻን በአግባቡ የሚያስወግዱ ቤተሰቦች ሽፋን ከ65% ወደ 79.5%) ማሳደግ፣
- የተሻሻለ ሳኒቴሽን አገልግሎት ያላቸውን ቤተሰቦች ሽፋን ከ60% ወደ 72% ማሳደግ፣
- መሰረታዊ የእጅ መታጠቢያ አገልግሎት ያላቸው ቤተሰቦችን ሽፋን ወደ 70% ማሳደግ፣
- የውኃ ጥራት ምርመራ የተደረገላቸው የውኃ ተቋማት ወደ 30% ማሳደግ፣
- መሰረታዊ የሳኒቴሽን አገልግሎት ያላቸው ጤና ተቋማት ሽፋን 46% ወደ 71% ማሳደግ፣
- መሠረታዊ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ያላቸውን ጤና ተቋማትን ሽፋን ከ34% ወደ 82% ማሳደግ፣
- ጤናማ የመኖሪያ ቤት ያላቸውን ቤተሰቦች ሽፋን ከ68% ወደ 80% ማሳደግ፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ሞዴል የሆኑ አሁን ካለበት 83% ወደ 86% ከፍ ማድረግ
- የአየር እና የውሀ ብክለትን የሚቀንሱ ፖሊሲዎችን መተግበር፥
- የተፈጥሮ ጥበቃ እና እንክብካቤን በዘላቂነት መተግበር፥
- ለማህበረሰቡ በአካባቢ ጥበቃ እና አያያዝ ችግር ምክንያት የሚመጡ የጤና ጠንቆችን ማስተማር፥
- በከተሞች ፕላን ውስጥ ጥዱ እና አረንጓዴ ቦታዎች እንዲኖሩ ማድረግ፤

**ግብ፡- ለ60 ለሚሆኑ (50 በመቶ ሴቶች፤ 75 በመቶ ሴቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) ዜጎች ስራ ዕድል መፍጠር፤**

**የማስፈጠሚያ ስልቶች**

የመንግስት እና የግሉን አጋርነት በጤናው ዘርፍ ማስፋፋት፥ ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር፥ የጤናው አቅርቦት እና አደረጃጀትን ማሻሻል፤ የመረጃ አያያዝ፤ የሰው ሀይል ልማት እና የጤና አገልግሎትን ማሻሻል፥ ጥራቱን የጠበቀ እና ፍትሀዊ የእናቶች እና ህፃናት ጤና አገልግሎት ተደራሽነት ማጠናከር፣

የዘርፈ-ብዙ ስነምግብ ቅንጅታዊ አሰራር እና ግንኙነት ማጠናከር፤ ዘርፈ-ብዙ ምላሽ መከላከል ስራዎችን ማጠናከር እና ማስፋፋት፤ ሁሉን አቀፍ የቲቢ እና ኤችአይቪ መከላከል እና የህሙማን ክብካቤ ማጠናከር፤ የማህበረሰብ ተሳትፎ አቅም እና የማህበረሰብ ንቅናቄ በማጎልበት ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል፤ የልብ እና የደም ቡዋንቡዋ፤ የስኩዋር በሽታዎች፤ ስር የሰደደ የኩላሊት እና ሌሎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር አገልግሎቶችን ማጠናከር እና ማስፋፋ፤ ከአደንዛዥ እፅ አጠቃቀም፥ ራስን ማጥፋት እና ራስን ከጉዳት የመከላከል እና የማገገም ተግባራትን ማጠናከር፤ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አገልግሎት ማእቀፎችን እንደገና ማዋቀር፥ የጤና መሰረተ ልማት ግንባታ እና አመራርን ማጠናከር፤ የህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ስርዓት እና ጥገና ማጠናከር የሚሉት ዋና ዋና የማስፈጠሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

## 2.5.6. ቱሪዝም

ቱሪዝም በዓለም ላይ እያደገ ያለ የኢኮኖሚ እና ማህራዊ መስተጋብር ስርዓት ነው፡፡ነባራዊ ሁኔታው እንደሚያሳየው የዓለምን ቱሪዝም ስርዓት አቅጣጫ ግምት ውስጥ ያስገባ ቱሪዝም ልማት ዝግጁነት አልነበረም፡፡ የዓለም አቀፍ የቱሪዝም ፍላጎት ስፋት እና እድገት በሚጠይቀው ልክ የቱሪዝም ምርቶች እና አገልግሎቶችም አልለሙም፡፡ክልላዊ እውነታውም ይኸው ነው፡፡ ዞናችን ከቱሪዝም ሀብቶች የሚያገኘውን ጥቅም ለማሳደግ የቱሪዝም ገበያን ከማልማትና ተወደዳደሪነትን ከማሳደግ አኳያ በርካታ ስራዎችን መስራት የሚገባ ሲሆን በተለይም የግሉ ዘርፍ በኢንዱስትሪው ውስጥ የሚኖረው ወሳኝ ሚና እንዲጫወት ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡ የቱሪዝም ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት የቱሪስት አገልግሎቶችን በዓይነትና በመጠን ከማሳደግና አገልግሎት ጥራትን ከማጎልበት አንፃር ፋይዳ ያላቸው በርካታ ተግባራት ማከናወን ይገባል፡፡

### ስትራቴክያዊ ጉዳዮች

- ዓለማቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ ቱሪዝም ዝግጁነት አለመኖር
- የቱሪስት መስህቦች በሚጠበቀው ደረጃ አለመልማት
- ለዘርፉ የሚፈሰው መዋዕለ-ንዋይ አናሳ መሆን

### የትኩረት መስኮች

1. የቱሪዝም መዳረሻ እና መስህች ልማት
2. የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎት ጥራት
3. የቱሪዝም መሰረተ ልማት
4. ዘመናዊ የቱሪዝም መረጃ ስርዓት
5. የቱሪዝም ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት

**የትኩረት አቅጣጫዎች**

በበጀት ዓመቱ የዘርፉ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ዞናዊ የቱሪዝም ሀብት አቅሞችን ከአገራዊ እና ክልላዊ እሴቶች ጋር በማጣጣም ማነጽ፣ የተበታተን የቱሪዝም መዳረሻዎችን በአዳዲስ ተጨማሪ መስህቦች በመሠረተ ልማት እና የቱሪዝም ምርቶች አማካኝነት ወደ ቱሪዝም መስመሮች፤ ቀጠናዎች እና ጥብቅ ስፍራዎች ማሳደግ፣ የቱሪዝም ልማትን ፅዱ እና ምቹ የመኖሪያና የስራ አካባቢን ለዜጎች ለመፍጠር እና የዘላቂ ልማት ግቦች ጋር በማቀናጀት ፍትሃዊ ቱሪዝምን ማረጋገጥ፣ የውጪ ቱሪዝምን የሚተካና ዞናዊ ምርታማነትን የሚያግዝ በጠንካራ ኢኮኖሚ መሠረት ላይ የቆመ ዞናዊ ቱሪዝም ማራመድ እንዲሁም ለሰፊው የቱሪዝም ፍላጎት ትርጉም ያለው አቅርቦትን በሳይንሳዊ የገበያ ጥናት መርህ በማመቻቸት ቱሪዝም ሥርዓቱ ተጠቃሚ መሆን የሚሉት ናቸው፡፡

**ዓላማ:- የቱሪስት መዳረሻዎችን እና መስህቦችን በማልማት! ብቁና ተወዳዳሪ የቱሪዝም አገልግሎቶችን በማስፋፋት እንዲሁም የቱሪስት ፍስትን እና ገቢን በማሳደግ ዞናችን ከዘርፉ ሊያገኝ የሚችለውን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፣**

**ዋና ዋና ግቦች**

**ግብ 1:- ወደ ዞናችን የሚመጡ የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን ብዛት ከ1198 ወደ 1519 በማረስ ከአንድ ጎብኝ በአማካይ የሚገኘውን ገቢ 17 ዶላር ማድረስ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 40 በመቶ ገቢ ከዘመድና ጓደኛ ጥየቃ ለማግኘት አልሞ መስራት፣
- 37 በመቶ ገበ, ከዕረፍትና መዘናናት ለማግኘት አልሞ መስራት፣
- 20 በመቶ ገቢ ከቢዝነስና ሙያ ነክ ጉዞ ለማግኘት አል'ሞ መስራት
- 3 በመቶ ገቢ ከሌሎች ለማግኘት አልሞ መስራት፣

**ግብ 2- የሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰትን ከ2ሚሊዮን ወደ 2.4 ሚሊዮን በማሳደግ ከአንድ ጎብኝ በአማካይ የሚገኘውን ገቢ ብር 500 ማድረስ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 40 በመቶ ገቢ ከዘመድና ጓደኛ ጥየቃ ለማግኘት አልሞ መስራት፣
- 37 በመቶ ገበ ከዕረፍትና መዘናናት ለማግኘት አልሞ መስራት፣
- 20 በመቶ ገቢ ከቢዝነስና ሙያ ነክ ጉዞ ለማግኘት አልሞ መስራት
- 3 በመቶ ገቢ ከሌሎች ለማግኘት አልሞ መስራት፣

**ግብ3፡- ለውጭ ሀገር እና ለሀገር ውስጥ ቱሪስት ጎብኝዎች የሚሆን ልዩ የመጓጓዣ ስርዓት መዘርጋት፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የግል ጉብኝት ድርጅችን ማጠናከር
- ለግል አስጎብኝ ድርጅቶች ድጋፍ ማድረግ፣

**ግብ 4:- የዞኑን የተሪስት መዳረሻዎች እና መስህቦች መረጃ የዘመኑን ቴክኖሎጂ ሥርዓት በመጠቀም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራሽ ማድረግ፣**

**የሚክናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 320 ዘመኑ ያፈራው ቴክኖሎጅ በመጠቀም የቱሪዝም መስህብ ሃብቶችን በስፋት ማስተዋወቅ፣
- 4 የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን በካርታና በጅፒእስ በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ
- 1 በዓለም አቀፍ ሜንስትሪሚንግ ሚዲያዎች የቱሪስት ሀብቶችን ማስተዋወቅ

**ግብ 5- ባህላዊ ምግቦችንና መጠጦችን በሆቴሎች፣ በሬስቶራንቶችና በመዳረሻ ቦታዎች እንደ አንድ የቱሪስት መስህብ ሆነው በሜኑ እንዲቀርቡና እንዲለመዱ ማድረግ፣**

**የሚክናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 1200 የሆቴሎችንና የመጓጓዣ ጥራትና የመስተንግዶ ደረጃን ማሻሻል
- 300 ባህላዊና ዘመናዊ ምግብና መጠጥ ላይ ለቱሪዝሙ በሚመጥን ደረጃ ባለሙያዎችን በማሰልጠን ባህላዊና ዘመናዊ ምግብና መጠቶችን በሰፊው ማቅረብ፣

**ግብ 6:- የመስህብ ሀብቶችን በማልማትና በማስፋፋት ቱሪስት በስፋት እንዲጎበኛቸው ማድረግ!**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ብዝሃነትን የሚያንጸባርቁ የህዝብ ለህዝብ ትስስር ያለባቸን ቦታዎች (አርጎባ ወረዳ ቡርቃ ገበያ ላይ መስራት)፣
- 20 የመስህብ ሀብቶችን መሰረተ ልማት በሚሟላት ወደ ቱሪስት መዳረሻነት ማሳደግ፣

**ግብ 7፡- የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን በመገንባት የቱሪስት መዳረሻዎች በማሟላት ወደ ቱሪስት መዳረሻነት ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 1 ባህላዊ በዓላትን ለቱሪስት መዳራሻነት እንዲውል በሰፊው መስራት

- 4 የእምነት ቦታዎችን ለቱሪስት መዳረሻነት ማዋል
- 3 ታሪካዊ ቦታዎች ለቱሪስት መዳረሻነት እንዲሆኑ መስራት
- 2 አዳዲስ የቱሪዝም ጥብቅ ስፍራዎችን በጥናት በመለየት ወደ ቱሪዝም መስመር ማስገባት
- ዞኑ ያለውን ሀብት በዓይነትና በብዛት በመለየት "የቱሪዝም ሀብት ልየታ"(Tourism resoures mapping and destination inventory) ስራ መስራት፣

**ግብ 8- የቱሪዝም የሰው ኃይል ሥልጠናን በማጠናከር ለ3022 የዘርፉ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት:**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 3000 በሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎቶች ዘርፍ ለተሰማሩ ሙያተኞች የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት
- ለ22 ባለሙያዎች ስለ ድጅታል ማርኬቲንግ ስልጠና መስጠት፣

ግብ 9፦ ለ13332 (50 በመቶ ሴቶች፤ 75 በመቶ ወጣቶች፤0.27 በመቶ አካል ጉዳተኛ) የስራ ዕድል መፍጠር

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

የዞኑን የቱሪዝም ልማት የሀብት መሰረት ላይ በመመሥራት የቱሪዝም ልማት መስመሮች ኮሪደሮች እና ቀጠናዎች በስፓሻል ጥላን ማመላከት፣ የዘርፉን ኢንቨስትመንት በጥናቶች እና በመሠረተ ልማት መምራት፣ ትልልቅ የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች፣ የከተማ መሰረተ ልማት አውታሮች፤ የመኖሪያ እና የቢዝነስ ግንባታዎች እና ዘመናዊ የገጠር መኖሪያ ቤት ግንባታዎችን የመሳሰሉ የሌሎች ዘርፎች የልማት ግንባታዎች የቱሪዝም ምርቶችን በመፍጠር ከቱሪዝም ልማት ግቦች ጋር እንዲጣጣሙ ከዘርፎች ጋር በቅንጅት መሥራት የኢትዮጵያን ዲያስፖራ በትውልድ አገር ጉብኝት እና በሪል አስቴት መጠጦች እንዲሁም በትራንስፖርት የሚገለጹ ተወዳዳሪ የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎቶች መረጃን ለዓለም ተደራሽ ማድረግ እና ሣይንሳዊ የክትትል የድጋፍ እና ግምገማ ሥርአት በመዘርጋት የዘርፉ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ሆነው ተለይተዋል፡፡

## 2.5.7. ንግድና ገበያ ልማት

የተጀመረውን የብልፅግና ጉዞ ለማፋጠን ኃላፊነት ከተሰጣቸው የኢኮኖሚ ልማት ዘርፎች መካከል የንግድና ገበያ ልማት አንዱ ነው፡፡ በዚህም በንግድ ዘርፉ የተጣሉ ግቦችን ለማሳካት የንግድ አሰራሮችና አገልግሎት አሰጣጥን በዘመናዊ የንግድ አሰራሮች መከተል እና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ የኤክስፖርት ምርትን የማሳደግ፣ ተኪ ምርትን የማስፋት እንዲሁም በአምራቹና በሸማቹ መካከል ያለውን ግብይት ያልተንዛዛና ጣልቃ ገብነት ያልበዛበት እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

## ስትራቴጅክ ጉዳዮች፡

- የግብይት ሰንሰለቱ መራዘም እና በንግድ አሰራር ስርአቱ የህገ-ወጥ ንግድ መበራከት
- የግብይት ስርዓትና ደካማ የሬጉሊቶሪ አሰራር መኖር
- የወጪ ንግድ ምርት በመጠን፣ በዓይነትና በጥራት አለማደግ
- የግብይት መሰረተ ልማት አለመስፋፋት እና የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ችግር መኖሩ
- የሸማቹን ህብረተሰብ መብት ማስከበር አለመቻል

## የትኩረት መስኮች

በአምሥት ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን ሁለት የዘርፉ የትኩረት መስኮች

- ዘመናዊ፣ ተወዳዳሪና ህጋዊ የንግድ ስርዓት መገንባት
- ተደራሽ፣ ቀልጣፋና በቴክኖሎጅ የተደገፈ የግብይት ስርዓት ማስፋፋት ናቸው፡፡

## የትኩረት አቅጣጫዎች

ንግድን በማዘመን የዘመናዊ አገልግሎት እና የኢንዱስትሪያላዊነት አካል ማድረግ፣ ትርፍን ከከፍተኛ የመሸጫ ዋጋ ሳይሆን ከምርት ወይም ከሽያጭ ብዛት (economies of scale) ማግኘትን ግብ ያደረጉ ከፍተኛ አቅም ያላቸው የዋና ዋና ምርቶች አቅራቢዎች እንዲቋቋሙ በማድረግ ገበያውን ማጥገብ፣ ከአስመጪዎች ይልቅ በአገር ውስጥ ምርት ንግድን የሚያሳልጡ አቅራቢዎችን፣ ከአስመጪዎችም የቴክኖሎጂ እና አምራች ካፒታል እቃዎችን የሚያስገቡ አስመጪዎችን በማበረታታት ንግድን የረጅም ዘመን የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ማድረግ፣ የፍጆታም ሆኑ የግብዓት እቃዎች እንደ ዓይነታቸው በአንድ ማዕከል ለሸማቾች ተደራሽ የሚሆኑበትን የገበያ ማዕከላትን በልዩ ሁኔታ በማስፋፋት ቀልጣፋ የንግድና ግብይት ሥርዓት መፍጠር፣ በመሠረተ-ልማት፣ በሕግ እና በአሠራር የተደገፈ የግብይት ስርዓት ማስፋፋት፣

**አላማ፡- ጠንካራና የላቀ የማስፈፀም አቅም ያለው ተቋም መገንባት፣ የንግድ መሠረቱን በማስፋት፣ ህጋዊ የንግድ ሽፋንን በማጠናከር፣ የሸማቹን መብት በማስከበር፣ የገበያ መሠረተ ልማቱን በማስፋፋት፣ የግብይት ስርዓቱን በማዘመንና ሰንሰለቱን በማሳጠር፣ የኑሮ ውድነትን ማረጋጋት እና የኤክስፖርት ምርት ግብይትን ማሳደግ፣**

**ግብ 1፡- ትኩረቱን ምርት በብዛት እና በጥራት በማቅረብ በኩል ተፅዕኖ ያላቸውን የንግድ ተዋንያን ላይ በማድረግ እንድሁም ለአዳዲስ የንግድ ሀሳብ፣ ፈጠራና ክህሎት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የንግድ መሰረቱን ማስፋት**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ምርት በስፋትና በጥራት የሚያቀርቡ ጅምለኛ ነጋዴዎችን 600፣ የቸርቻሪ ነጋደዎችን 5,668 ማድረድ
- አዲስ የንግድ ምዝገባ 8,300፣ አዲስ የንግድ ፈቃድ መስጠት 9,700፣ ነባር የንግድ ፈቃድ ዕድሳት 39,463
- በአጠቃላይ በኦን ላይ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ከ 49817 ወደ **59137 ከፍ ማድርግ፣**

**ግብ 2፦ የንግድ ውድድሩንና ቁጥጥሩን በማሳደግ ህጋዊ የንግድ ሽፋኑን ከ61.15 ወደ 65 በመቶ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በ39,463 ንግድ ድርጅት ላይ የበር ከበር ቁጥጥር በማድረግ ፕሮፋይል አዘጋጅተው እንዲሰሩ ማድረግ፣
  - ✓ ሁሉንም የንግድ ድርጅቶች የፀና የንግድ ስራ ፈቃድ በመያዝና በሚታወቅበት የንግድ አድራሻ እንዲሰሩ መቆጣጠርና መከታተል፣
  - ✓ ሁሉንም የንግድ ድርጅቶች ባዕድ ነገር ሳይቀላቅሉና የአገልግሎት ዘመኑ ያላለፈበት ምርት እንዲያቀርቡ መቆጣጠርና ማስተካከል፣
  - ✓ ሁሉንም የንግድ ድርጅቶች ደረጃውን የጠበቀና ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የመለኪያ መሳሪያ እንዲጠቀሙ መከታተል፣ መቆጣጠርና ማስተካከል፣
  - ✓ ወቅታዊ የመሸጫ ዋጋን መሰረት አድረጎ ዋጋ ዝርዝር እንዲለጥፉ መከታተል፣ መቆጣጠርና ማስተካከል፣
  - ✓ ግብይቱን በደረሰኝ መፈፀማቸዉን መከታተል፣ መቆጣጠርና ማስተካከል፣
  - ✓ ምርቶችን ሳይቀላቀሉ በየአይነት በማስቀመጥ ደህንነቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ ምርት/ አገልግሎት ለሸማቹ እንዲቀርብ ቁጥጥር ማድረግ፣
- የመለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት ኢንስፔክት ማድረግ 41448
- የመለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት ቬሪፋይ ማድረግ 41121

**ግብ 3፦ የአነስተኛ ባለይዞታ አርሶ አደሮችን የገበያ ተደራሽነት በማሳለጥ የሰብል ምርቶችን ከ379,721 ኩ/ል ወደ 458,194 ኩ/ል ማሳደግና አምራቹንና ሸማቹን ተጠቃሚ ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ብዕርና አገዳ እህል ከ176,733 ወደ 176,828 ኩ/ል ማድረስ

- ጥራጥሬ ከ 99,400 ወደ 99,400 ኩ/ል ማድረስ
- ቅባት እህል ከ5,201 ወደ 7,000 ኩ/ል ማድረስ
- ቅመማ ቅመም ከ6,663 ወደ 8,514 ኩ/ል ማድረስ
- አትክልትና ፍራፍሬ ከ91,724 ወደ 166,452 ኩ/ል ማድረስ

**ግብ 4:- የአገር ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ ውጤቶችን ተፈላጊነት በማሳለጥ የገቢ ንግድ በአገር ውስጥ ምርት እንዲተካ ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ተኪ ምርት ለሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች የግብርና ምርት ግብዓት ማቅርብ
    - ✓ ስንዴ 30,613 ኩ/ል፣
    - ✓ በቆሎ 47,123 ኩ/ል፣
    - ✓ የቢራ ገብስ 26,000 ኩ/ል፤

**ግብ 5:- የንግድ ዘርፉን በማቀላጠፍ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲፋጠን መስራት እና የንግድ ኢንቨስትመንት ስራዎችን ማበረታታትና ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ክልሉ በአሸጋሪ ዕድገትና በዘላቂ የልማት ዕቅዱ የቅድሚያ ቅድሚያ በሰጣቸው የኢንቨስትመንት ንግድ ስራዎች ላይ የሚመጡ ባለሃብቶችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ተገቢውንአገልግሎት በወቅቱ እንዲያገኙ ማድረግ፣

**ግብ 6:- አነስተኛ፣ ግን በርካታ ቅራቢዎች ባሉበት የገበያ ሥርዓት ውስጥ መንግሥት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር ያልተገቡ የዋጋ ጭማሪዎችን እና የዘርፉ ወሳኝ ጉዳዮችን ለማስተካከል ስለሚቸገር ትልልቅ የንግድ ኩባንያዎች /ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ሁለንተናዊ አቅም ያላቸውን ነጋዴዎች በመለየት በገበያ አቅርቦቱ ላይ ኩባንያዎችን /ድርጅቶችን አቋቁመው ወደ ስራ ለመግባት የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን መስራት፣

**ግብ 7:- በደላላ ብዛት የተጨናነቀውን ረጅም እና የተንዛዛ የግብይት ሰንሰለት በመቁረጥ የግብይት ሥርዓቱ ቀልጣፋ እንዲሆን በማድረግ የዋጋ ንረት እንዲረጋጋና ዘርፉ የድርሻውን አስተዋጽዖ እንዲወጣ ማድረግ፣**

**የሚከናዎኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በግብርና ምርት (በሰብል፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም በእንስትና እንስሳት ተዋፅኦ) እንድሁም በፍጆታ የኢንዲስትሪ ምርቶች ግብት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ደላላዎችን 100% ከገበያ ማስወጣት
- በተቻለ መጠን በከተሞች በቴክኖሎጅ የተደገፈ የግብይት ትስስርን ማስጀመርና ማጠናከር፣

**ግብ 8፡- የኬላ ላይ ቀረጥን ጨምሮ የባለ ድርሻ ተዋንያን መበራከት በአቅራቢዎች ወጪ መብዛት ምክንያት ሸማቹ ለኑሮ ውድነት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ማድረግ፣**

**የሚከናዎኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በየአካባቢው በህገ-ወጥ መንገድ ተከፍተው የሚገኙ ኬላዎችን ለይቶ 100% በማስወገድ ያልተገቡ ክፍያዎችን/ ቀረጦችን በማስቀረት የምርት ዝውውር ቀልጣፋ እንዲሆን እና ሸማቹ ለኑሮ ውድነት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ማድረግ፣

**ግብ 9፡- የገበያ ተዋንያን አቅም በማሳደግ የግብርናና ኢንዱስትሪ ምርት በትስስር በማቅረብ፣ የንግዱ ዘርፍ ለመዋቅራዊ ሽግግር የድርሻውን እንድወጣ ማድረግ**

**የሚከናዎኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር፣ ግብዓቶችን ማሟላት፣ፈጣን አገልግሎት አመላካቾችን ማደስ፣ ቅልጥፍና በመጨመር የደንበኞች እርካታ ከ71.6% ወደ 75% ማሳደግ
- የተቋሙን የንግድና ግብይት ስርዓት ለማሳለጥ ለ155223 የገበያ ተዋንያንን እና ባለድርሻ አካላት ስልጠናና ግንዛቤ መፍጠር (በሰብልና ኢንዱስትሪ ምርት ግብይት ዘርፍ 66079፣ በሸማች ጥበቃ ዘርፍ 74684 (ግንዛቤ 69304፣ ስልጠና 5380)፣ እንስስሳትና እንስሳት ተዋፅኦ ግብይት ዘርፍ 10080፣ ንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዘርፍ 2000፣ 2384 ለአጋር አካላት)
- ንግድ ምክር ቤትና የዘርፍ ማህበራት አደረጃጀቶችን ማጠናከር በቁጥር ከ162 ወደ 170 ማድረስ፣
- የአገልግሎት አሰጣጣችንን በስታንዳርድ፣ በመርህ እና አሰርር እንድመራ ማድርግ
- የግልፅነትና ተጠያቂነት አሰራሮችን ማጠናከር፣ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በመፍጠር አፈፃፀሞችን ማቀራረብ

**ግብ 10፡- የገበያ ማዕከላትን በማስፋፋትና የመረጃ ስርዓትን በማዘመን ግብይቱን ማሳለጥ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 28 ነባር የእሁድ ገበያን ማጠናከር፣
- 11 የግብይት ማዕከላትን ማቋቋም
- 110 የግብይት ማዕከላትን ማጠናከር
- 18 አድስ የመረጃ ቦርድ ማሰራት
- 92 ነባር የመረጃ ቦርዶች ማጠናከር
- 29 ሁለተኛ ደረጃ የአምራች ገበያ ማዕከል መቋቋም (20 አድስ ማቋቋም፣ 9 ነባር መጨረስና ስራ ማስጀምር)
- 2 አንደኛ ደረጃ የኤክስፖርት ምርት የግብይት ማዕከላትን ማቋቋም
- በ5 ተገንብተው በተጠናቀቁ የገበያ ማዕከላት ምርት በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት እንዲቀርብባቸዉ ማድረግ

**ግብ 11፡- የግብይት ትስስሩን በማጠናከርና የፋይናንስ አቅርቦቱን በማሳደግ ገበያውን ማረጋጋት፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ተዘዋዋሪ ብድር ከ146.3 ሚሊየን ወደ 150 ሚሊየን ብር እንዲቀርብ ማመቻቸት፣
- 230,103 ኩ/ል ሸማች ተኮር የሰብል ምርት በትስስር ማቅረብ /ብርዕርና አገዳ 125381 ጥርጥሬ ምርቶች 17305፣ ቅመማ ቅመም 8583፣ አትክልትና ፍራፈሬ 78834/
- የኢንዱስትሪ ምርት በትስስር በኩ/ል 72,421፣ በሊትር 780,933 ማቅረብ
- 15 የንግድ ትርኢትና ባዛር እንዲሁም ኢግዚቢሽን በማዘጋጀት ምርት ማቅረብ ፣
- እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽዖ በትስስር ማገበያየት (አሳ በቶን 246፣ ስጋ በቶን 11፣ ማር በቶን 1,600፣ ወተት በሊትር 4,700,000፣ ዶሮ በቁጥር 334,000፣ እንቁላል በቁጥር 3,220,000 ማቅረብ)፣ የተቀነባበር የእንስሳት መኖ 180 ቶን
- የቁም እንስሳት ሽኘት በቁጥር 254,555 ማድረስ (ዳልጋ ከብት በቁጥር 41,400፣ በግና ፍየል በቁጥር 197,813፣ ጋማ ከብት በቁጥር 13,972 እና ግመል በቁጥር 1,370)፣
- ቆዳና ሌጦ ሽኘት በቁጥር **324873** (ዳልጋ ከብት 40000፣ በግ ሌጦ 107118፣ ፍየል ሌጦ 177755)

**ግብ 12፡- የኤክስፖርት ምርት በዓይነትና በመጠን እንዲሁም በጥራት በማቅረብ ወደ ውጭ የሚላከውን የምርት መጠን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 429,971 ኩንታል ቅባትና ጥራጥሬ እህል መላክ እና 44.56 ሚሊየን ዶላር የዉጭ ምንዛሬ ማግኘት
    - ✓ የቅባት እህል ጥቅል 9351 ኩ/ል (0.88 ሚ. ዶላር) ማለትም ሰሊጥ 3091 ኩ/ል (0.42 ሚ. ዶላር) እና ኑግ 6260 ኩ/ል (0.46 ሚ. ዶላር)፣
    - ✓ የጥራጥሬ ምርት ጥቅል 420620 ኩ/ል (43.68 ሚ. ዶላር) ማለትም ነጪ ቦለቄ 177000 ኩ/ል (15.53 ሚ. ዶላር) እና ማሾ 243620 ኩ/ል (28.15 ሚ. ዶላር)
- የቁም እንስሳትን ቁጥር ከ0 ወደ 1,200 ማድረስ (129513 ዶላር )

**ግብ 13፡- ዘመናዊ የገበያ መሠረተ-ልማት እና የመረጃ ስርዓትን በመዘርጋት የንግድ ስርዓቱ በቴክኖሎጅ የተደገፈ እንዲሆን ማድረግ፣**

**የሚከናዎኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 30 የኦንላይን አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን በማጠናከር አገልግሎቱን ማሳለጥ፣
- ሁሉም የነዳጅ ማደያዎች (14ቱም) የሽያጭ አገልግሎት በቴሌና ሲቢኢ ብር ብቻ እንድሆን ማድረግ
- ስራ ላይ ያሉ ቴክኖሎጅዎችን ማሻሻልና ዉጤታማ ማድረግ፣
- የገበያ መረጃ ተደራሽነትን በማስለማት ለግብይት ተዋንያን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

**ግብ 14፡- ዘርፈ ብዙ/ አካቶ ትግበራትን ማሳለጥ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለ50 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር፣
    - ✓ በኢንተርኔት ካፌ 2
    - ✓ በነዳጅ ማደያ አገልግሎት 14
    - ✓ በመሠረተ-ልማት ግንባታ ተግባራት 25
    - ✓ በሽርክና ለዜጎች የስራ ዕድል ማመቻቸት 9 የስራ ዕድል መፍጠር

## የማስፈፀሚያ ስልቶች

ቅንጅታዊ አሰራርን በማሳደግ እና ህገ-ወጥነትን በመከላከል የኑሮ ዉድነቱን ማረጋጋት፣ የአገር ዉስጥና ኤክስፖርትን ግብይትን በጥራት፣ በመጠንና በአይነት ማሳደግ፣ የንግድ ሪፎርሙንና ህጋዊ አሰራሮችን አጠናክሮ መቀጠል፣ ስራዎችን በፈጠራና በምርምር ማስደገፍ፣ ተግባራትን በቴክኖሎጂ

በማስገደፍ መፈፀም፣ ተግባራትን በጠንካራ የቡድን ስሜትና የስራ ባህል መፈጸም፣ ዉጤታማነት፣ ቅልጥፍና ችግር የመፍታት አቅምን ማሳደግ፣ የፋይናንስ ውጤታማነት ሀብትን በቁጠባ እና ውጤት በሚያመጣአግባብ መጠቀም፣ ጠንካራ የክትትል እና ድጋፍ ስርዓት መዘርጋት፣ ተግባራትን በጠንካራ የቡድን ስሜትና የስራ ባህል የመፈጸም አቅጣጫ፣ ዉጤታማነት፣ ቅልጥፍና ችግር የመፍታት አቅምን የማሳደግ አቅጣጫን መከተል፣ የፋይናንስ ውጤታማነት ሀብትን በቁጠባ እና ውጤት በሚያመጣ ተግባር መጠቀም፣ ጠንካራ የክትትል እና ድጋፍ ስርዓት መዘርጋት፣

## 2.5.8. ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ

ትራንስፖርት እና ሎጅቲክስ የዘመናዊ ኢኮኖሚ አገልግሎት ማሳለጫ ዘርፍ ነው፡፡ ስለ ኢንዱስትሪያላዊነት ሲታሰብ የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ስፋት፣ የአገልግሎት ቅልጥፍና እና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ወሳኝ ባሕሪያት ናቸው፡፡ የማሳለጫ መንገዶች፣ ለወደብ ቅርብ መንገዶች፣ በአማካይ ርቀት የሚገነቡ ስትራቴጂካዊ ደረቅ ወደቦች፣ የባቡር እና የመርከብ ትራንስፖርት ስርዓቶች መኖር  የቅልጥፍና  ተወዳዳሪነትን ይወስናሉ፡፡

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት፣ የማጓጓዣ መሣሪያዎች እና ተያያዥ አገልግሎቶች የተካተቱበት ረጅም የእሴት ሰንሰለት ሥርዓት በመሆኑ ትልቅ ኢንዱትስትሪም ነው፡፡ የትራንስፖርት ስርዓት የማጓጓዣ ስልቶች ማለትም የየብስ፣ የውሃ፣ የአየር፣ የትራንስፖርት መሰረት ልማትን ለምሳሌ መንገድ፣ የባቡር ሃዲድ፣ የፈሳሽ ማስተላለፊያ ቱቦዎች፣ ወደብ፣ የአየር ማረፊያዎች የብስክሌት እና ስኩተር ማሳለጫዎች፣ የእግረኛ ማስተላለፊያዎች፣ የትራፊክ ምልክቶች፣ የትራንስፖርት ማጓጓዣዎችን እና ኮንቴነሮችን፣ ኦፕሬሽን (ማሸከርከር፣ ማብረር ፣ መቅዘፍ) የትራፊክ ማኔጅመንት (ቁጥጥር እና ሲግናል)፣ ፕሮግራም (ማቀድ እና ማሳለጥ )፣ማቀናጀት (ኢንተርሞዳል)፣ ተሸከርካሪዎች የኃይል ምንጭ፣ ቴክኖሎጂ እና የሰለጠነ የሰው ሃይል  የተካተተበት ሰፊ ስርጭት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ተግባራዊ በማድረግ አገልግሎቱን ለማሳለጥ ትኩረት በማድረግ የበለጠ ሊሰራበት የሚገባ የኢኮኖሚ ዘረፍ ነው፡፡

## ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

- ቀልጣፋና ውጤታማ የሎጅስቲክስ አገልግሎት አለመዘርጋት
- የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት አለመስፋፋት
- የትራንስፖርትና የሎጂስቲክስ ዘርፍ በሚፈለገው ደረጃ በመረጃና በቴክኖሎጂ አለመዘመን
- የመንገድ ትራፊክ ደህንነት በሚፈለገው ደረጃ አለማረጋገጥ

## የትኩረት መስኮች

1. የምርት እና ዕቃዎች አያያዝ፣ ስትራቴጂካዊ መጋዘን፣ ድህረ ግብርና ምርት አያያዝ
2. ምርትን ማሸግ (ፓኬጂንግ እና ዩኒታይዜሽን)
3. ቀልጣፋና የዘመነ የትራንስፖርትና የሎጂስቲክስ አገልግሎት
4. የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት
5. መረጃ እና ቁጥጥር

## የትኩረት አቅጣጫዎች

ምርታማነትን እና ቅልጥፍናን መሠረት ላደረገው የኢኮኖሚ ዕድገት ስትራቴጂካዊ ድጋፍ ማድረግ፣ በተለይም ግብዓትን እና ምርትን ተደራሽ ማድረግ፣ ለወጪ እና ገቢ ንግድ መሳለጥ ስትራቴጂካዊ የመንገድ ትንስፖርት ኮሪደሮችን መለየት እና በክልል መንግስት፣ እንድሆም ከአጎራባች ዞኖች ጋር በጋራ ማልማት፣ ወረዳዎችን እና አጎራባች ዞኖችን በመንገድ ትንስፖርት በማገናኘት ትስስሩ ማጠናከር፣ የከተሞች ዕድገት ቀድሞ በመተንበይ እና በመተንተን ከረጅም ዘመን የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ፍላጎት አንጻር ማመቻቸት እንድሁም ለዕድገት ደረጃቸው የሚመጥን የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ መሠረተ ልማቶችን መዘርጋት በበጀት ዓመቱ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ሆነው ተለይተዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪም የገጠር ነዋሪዎች ወደ አንድ አዳጊ የከተማ ማዕከል ይሰባሰቡ ዘንድ ቀድሞ በተነደፈ ፕላን በትራንስፖርት መሰረተ ልማት መምራት፣ የደረቅ ወደቦች ሚና ከልማት ቀጠናዎች ጋር ማስተሳሰር፣ ከተሞች እንደ ጅኦግራፊያዊ አመችነታቸው፣ በትራንስፖርትና ሎጅስቲክ ዘርፍ የልዩ ልዩ አገልግሎቶች ማዕከላት እንዲሆኑ ማመቻቸት፣ ድህረ ምርት ብክነትን በዘመናዊ ክዘና መቀነስ እንድሁም በአስተሻሸግ ስርዓት የንግድ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

**ዓላማ፡- የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎትንና መሰረተ ልማትን የተቀናጀ፣ ፍትሃዊ፣ ደህንነቱ የተረጋገጠ እና ተደራሽ በማድረግ ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪ እንሆን ማስቻል፣**

**ግብ 1፡- የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎትን ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለ1658 የህዝብ ትራንስፖርት ተሽከርከሪዎች 1,092,121 ጊዜ በድግግሞሽ ስምሪት በመስጠት 23,301,108/ ወንድ 15,145,720 ሴት 8155388 /ህዝብ በማጓጓዝ 77369300 ኪሎ ሜትር መሸፈን፣

- 2180 የከተማ ታክሲ መርሃ ግብር በማጽደቅ 10803774 የከተማ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች በድግግሞሽ ስምሪት በመስጠት 40127547 (ወንድ 24076529 ሴት 16051019) ህዝብ በማጓጓዝ 83862922 ኪሎ ሜትር መሸፈን፣
- ለ7 የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ ማረጋገጨ ማደስ፤
- ለ1 አዲስ ከተማ ትራንስፖርት ማህበራት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠትና 20 ፈቃድ ማደስ ፣
- 9 አዲስ የህዝብ ትራንስፖርት የስምሪት መስመሮች መክፈት፣
- ለ 85 (ወንድ 70 ሴት 15 ድምር 85) አዲስ የተሽከርካሪ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠትና ለ1696 ኦፕሬተሮች ፈቃድ ማደስ ፣
- በ6 መናኸሪያዎች የኢ- ቲኬቲንግ አገልግሎት በማስጀመር የመናኸሪያ ስታንዳርድ 87 በመቶ ማድረስ ፣
- በዞን 1 ህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎች ላይ ለአካል ጉዳተኞች የዊልቸር አገልግሎት መስጠት፣
- የከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘት አማካይ የመጠባበቂያ ጊዜን ከ 5 ደቂቃ እንዳይበልጥ ማድረግ ፣
- 30 መናኸሪያዎችን አገልግሎት አሰጣጡን ኢንስፔክት ማድረግ፣ ስታንዳርዱን ማስከበር

**ግብ 2፡- ለወጪ እና ገቢ ንግድ መሳለጥ ስትራቴጅካዊ የመንገድ ትራንስፖርት ኮሪደሮችን መለየት እና በፌደራል መንግስት እና ከክልሉ መንግስት ጋር በጋራ ማልማት፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- ነባር ኤርፖርት መካነ - ሰላም አገልግሎት እንዲጀምሩ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ፣

**ግብ 3፡- የዞኑን የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ መሠረተ-ልማት ማስፋፋትና ማዘመን ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግበራት**

- በ2017 የተጀመረውን የደሴ - ገራዶ አዲስ መናኸሪያ ግንባተ 100 በመቶ እንዲጠናቀቅ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
- 1 ደረጃ ሶስት አዲስ መናኸሪያዎችን መናኸሪያ ግንባታን ማካሄድ፣
- 2 ነባር መናኸሪያምችን የማስፋፊያ ግንባታ እና የጥገና ስራ ማከናወን ፣
- በትራንስፖርት ዘርፍ የሚገነቡ ግንባታዎች በሙሉ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ እንዲሆኑ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ፣

- የተጀመሩትን የደሴ ትራፊክ ኮምኘሌክስ ህንጻ ጥገና ትራፊክ ኮምኘሌክስ ግንባታ እንዲጠናቀቅ ማድረግ ፤

**ግብ 4፡- የትራንስፖርት እና ሎጆስቲክስ ዘርፉ በቴክኖሎጅ የዳበረ እና በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲመራና እንዲሰራ ማድረግ ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግቦራት**

- የሎጆስቲክስ ስትራቴጅውን መሰረት በማድረግ ወጥ የሆነ አደረጃጀት እንዲሰራ ማድረግ
- ግልጽነትና ፍትሀዊነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪት 100 በመቶ መፈጸም
- ለ300 አመራሮች እና ሰራትኞች ልዩ ልዩ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠት የዘርፉን አቅም ማሳደግ ፤

**ግብ 5. ከዓለም አቀፍ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ሥርአቶች ጋር የማያገናኝ ስትራቴጅካዊ የትራንስፖርት እና የሎጆስቲክስ ሥርዓት መዘርጋት ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በ ዞን ደረጃ ካውንስል ማቋቋምና ወደ ስራ ማስገባት፣
- የ590 የጭነት ተሽከርካሪዎችን መረጃ ማሰባሰብና በዝንና ከተሞች የሚገኙ የጭነት ተሽከርካሪዎች በ1 /ማህበር፣ አክሲዮን፣ PLC/ መመሪያውን መሰረት በማድረግ ማደራጀት፣
- የጭነት ትራንስፖርት ፍላጐትና አቅርቦትን በዘመናዊ መንገድ ማሻሻልና አሰራሩንና አደረጃጀቱን በማዘመን ቀልጣፋና ተደራሽ ማድረግ፣
- ለ 85 የጭነት ተሽከርካሪዎች የኦኘሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በመስጠት የጭነት ተሽከርካሪዎችን ብቃት በማረጋገጥ የሚደርስን አደጋና የንብረት ውድመት መቀነስ ፤
- የዳሜሬጅ አዋጅን መሰረት በማድረግ ሁሉም ጭነቶች በህጋዊ መንገድ በአደረጃጀቱ መሰረት ያለምንም መዘግየት 100 በመቶ እንዲጓጓዙ ማድረግ ፤

**ግብ 6- በመንገድ ትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚደርሰዉን የሰው ሞት በ10 ሽህ ተሽከርካሪ አሁን ካለበት 35 ወደ 23 መቀነስ በቁጥር**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለ13228 ወንድና ለ409 ሴት በድምሩ ለ 13637 ነባር አሽከርካሪዎች አደጋን ተከላክሎ ማሽከርከርን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣
- 67945 ተሽከርካሪዎችን በድግግሞሽ በራዳር ቁጥጥር ማድረግ ፤
- 279960 ተሽከርካሪዎችን በድግግሞሽ መደበኛ ቁጥጥር ማድረግ ፤

- 3580 ተሽከርካሪዎች ድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ በማከናወን የቴክኒክ ብቃታቸው እንደረጋገጥ ማድረግ ፣
- 11 የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት እና 7 የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራትን አገልግሎት አሰጣጥ በኢንስፔክሽን በማረጋገጥ ህግን ማስከበር፣
- 1880 ተሽከርካሪዎች የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን እንዲገቡ ማድረግ ፣

**ግብ7፡- የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጅ አሰራርንና ውጤታማነት በማሻሻል የመረጃ ስርዓትን ማዘመን እና ዘርፋን ተወዳዳሪና ውጤታማ ማድረግ ፣**

- **የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የትራንስፖርት ሎጀስቲክስ የመረጃ ቋት 100 በመቶ ማደራጀት ፣
- ወረቀት አልባ አሰራርን 40 በመቶ መተግበር ፣
- በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን 35 በመቶ አውቶሜት ማድረገ ፣
- የመረጃ አያያዝና አስተዳዳር ሶፍት ዌርን እና የቅጣት ሪከከርድ አያያዝ ሶፍትዌርን በቀላሉ ለመተግበር የሚያስችል የሞባይል አፕልኬሽን በማስለማት 10 በመቶ ወደ ስራ ማስገባት ፣
- የለሙ እና ወደፊት የሚለው ሲስተሞተን ከፌደራል እና ከለሎች ተዛማጅ ሴክተር መስሪያ ሴቶች ጋር በማስተሳሰር 10 በመቶ ወደ ስራ ማስገባት ፣
- በዞን 1 መናኸሪያ CCTV ካሜራና ዲስኘለይ አንድገጠምላቸው ማድረግ ፣
- በ6 የዞን መናኸሪያዎች የኢ - ቲኬቲንግ አገልግሎት በማስጀመርና 100 በመቶ ወደ ሥራ ማስገባት ፣
- የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ በሚሰጥባቸው ሁሉም ዞኖች የተግባር ፈተና አሰጣጡን በሲሲቲቪ ካሜራ ክትትል እና ቁጥጥር ውስጥ እንዲሆን 100 በመቶ ወደ ስራ ማስገባት፣
- ለባካኘ (Backup) አገልግሎት የሚሆን ዳታ ሴንተር በማቋቁም 100 በመቶ ወደ ሥራ ማስገባት ፣

**ግብ 8፡- ለ2420 (50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) ዜጐች የስራ ዕድል መፍጠር ፣**

**የሚከናወኑ ወና ዋና ተግባራት**

- በአሽከርካሪ 8 (ወንድ 6 ሴት 2 / ፣/ ወንድ 1545 ሴት 157 / በተሽከርካሪ 1702 ፣በስምሪት 110/ ወንድ 49 ሴት 61/ ፣ በመሰረተ - ልማት ዘርፎች 600/ ወንድ 200 ሴት 400 የስራ እድል መፍጠር ፣

## የማስፈጸሚያ ስልቶች

በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ፣ የተጀመረውን የቴክኖሎጅ አሠራር በማጠናከር ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣ አጋር አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር፣ የስነ-ምግባርና የሌብነት ችግር ያለባቸውን ቁርጠኛ አቋም ይዞ እርምጃ መውሰድ፣ በመንግስት እና የግል ለሃብቱን በማሳተፍ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት እና የሎጂስቲክስ ማዕከላት እንዲገነቡ ማድረግ፣ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎትን ለማስፋፋት የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ፣ ከአጎራባች ዞኖች ጋር የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ትስስር መፍጠር የሚሉ ስልቶች ተለይተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ህጎችን የማስፈፀምና መቆጣጠር አቅምን ማሳደግ፣ ችግር ፈች የሆነ የክትትልና ድጋፍ ስራ መስራት፣ በዘርፉ የሚገኙ የማሰልጠኛ ተቋማትን፣ ምርመራ ተቋማትን፣ ትራንስፖርት ድርጅቶችን ብቃት ማሳደግ እና ከሀገር ውስጥና ከውጪ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራት፣ በዘርፉ የሴቶች፣ የሕፃናት፣ ወጣቶች፣ የአረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞችና የኤችአይቪ ኤድስ ጉዳዮችን አካቶ ለመስራት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ መመሪያዎችንና አለም አቀፍ ስምምነቶችን መተግበር፣ የዘርፉን ተልእኮ ለማስፈጸም የሚያስችል መዋቅራዊ የአደረጃጀት ማሻሻያ እና አሠራር መዘርጋት፣ በጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ ህገ-ወጥ ደላሎችን ለማጥፋት የህጋዊ የጫኝና አስጫኝ አገናኝ ስርዓት መዘርጋት፣ የጭነት ተሽከርካሪዎች በገቡት የማጓጓዝ ውል መሰረት ብቻ የሚሰማሩበት አሰራር መዘርጋት፣ በትራንስፖርት ደህንነት ዘርፍ የህብረተሰቡን ተሳትፎ፣ ድጋፍና ተጠቃሚነት የሚያሳድግ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ፣

## 2.5.9. ኮንስትራክሽን

የዞኑን የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ጤናማ በማድረግ የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪው ማበርከት የሚጠበቅበትን ሚና መጫዎት እንድችል የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ፖሊሲ፣ የህንጻ አዋጅ፣ ኮዶችንና ስታንዳርዶችን በተሟላ መንገድ ተግባራዊ በማድረግ የመንግስትና የግል ግንባታዎችን በተቀመጠላቸው የጥራት ደረጃ፣ ጊዜና በጀት እንድጠናቀቁ ማስቻል እና የሚገነቡ ግንባታዎች የህዝቡን ደህንነትና ጤንነት ያገናዘቡ እና አካታች መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የሬጉላቶሪ እና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን ከኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚጠበቁ ቁልፍ ሥራዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት በተሰጣቸው እንደ ግብርና፣ አምራች ኢንደስትሪ፣ ማዕድን፣ ቱሪዝም፣ መሠረተ-ልማት እና በርካታ የአግልግሎት ዘርፎች ከሚደረግ መዋዕለ-ንዋይ ውስጥ ከ30 እስከ 40 በመቶ የሚሆነው የኮንስትራክሽን ድርሻ እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪው ብቃት በእነዚህ ዘርፎች ላይ የሚገነቡ የማምረቻ አቅሞችን ጥራት እና ቅልጥፍና ይወስናል፡፡ በመሆኑም በኮንስትራክሽን ዘርፍ አጥብቆ የሚሠራ ሥራ በሌሎች ዘርፎች የሚታዩ የቅልጥፍና ጉድለቶች ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቅረፍ ያስችላል፡፡

## ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

- ለዘሁ ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋፅዖ ማድረግ የሚችል የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ዝቅተኛ መሆን
- ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ በሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ
- የፕሮጀክት አስተዳደር፣ ድጋፍ ክትትልና ግምገማ አናሳ መሆን
- የመዋዕለ ንዋይ እና የቴክኖሎጅ እጥረት

## የትኩረት መስኮች

1. የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ የአሰራር ስርዓት
2. ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ግንባታ
3. የኢንቨስትመንትና መዋዕለ-ንዋይ ፍሰት
4. ተቋማዊ አደረጃጀትና የሰው ኃይል ልማት

## የትኩረት አቅጣጫዎች

- ኢኮኖሚ አቀፍ ምርታማነትን እና ቅልጥፍናን የሚያረጋግጥ የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማት መገንባት፣ ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ መፍጠር፣ ተደራሽ እና ማሕበረሰብ-ተኮር የኮንስትራክሽን አቅም መፍጠር፣ መሠረታዊ እና ድጂታል ቴክኖሎጂን የሚጠቀም ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማትን ማስፋፋትት እንድሁም ጠንካራ የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ሥርዓት መዘርጋት የሚሉት በበጀት ዓመቱ የዘርፉ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ሆነው ተለይተዋል፡፡

**ዓላማ፡- ለጠንካራ ኢኮኖሚ ግንባታ የሚመጥን ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ መሠረት መጣል፤**

**ግብ 1፡- የኮንስትራክሽን ዘርፉን በመዋቅራዊ ሽግግር ሂደት እንደ አንድ አዋጭ ኢንዱስትሪ በማዘመን ለኢኮኖሚ ዕድገት የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ማድረግ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ጠቅላላ ካፒታል እድገት በ2017 ከነበረበት 6.604 ሚሊዮን ብር በ2018 ወደ 17.354 ሚሊዮን ብር እንዲያድግ ማድረግ፣
- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ 5 በመቶ ማሳደግ፣

- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለከተማ መሰረተ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ በ10 በመቶ ማሳደግ፣
- በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በሚሰማራው የሰው ሃይል 60 በመቶ ተቀጣሪ፣ 30 በመቶ ራስ ቀጣሪ፣10 ሌሎችን ቀጣሪ እንዲሆኑ ማድረግ፤

**ግብ 2፡- የዘርፉን ሚና እና እምቅ አቅም በቅጡ በመለየት ለመጠቀም የሚያስችል ዘመናዊ አደረጃጀት መፍጠር**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የዘርፉን ሚና እና እምቅ አቅም በቅጡ ማጥናትና መለየት፤
- የህንጻ አዋጅ አደረጃጀት የተፈቀደላቸው 27 (በ9 ከተማ አስተዳደሮች ፣ በ18 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች) በተፈጠረው አደረጃጀት መሰረት የሰው ሃይል ተሚልቶ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣

**ግብ 3፡- የዞኑን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጤናማ በማድረግ ለኢኮኖሚው ማበርከት የሚጠበቅበትን ሚና መጫወት እንዲችል የሬጉላቶሪ እና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞኑ የሚገነቡ የመንግስትና የግል ግንባታዎች 100 በመቶ የህንፃ ኮድና የጥራት ደረጃዎች ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥና ጥራታቸውን ጠብቀው በተያዘላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ ማድረግ፣
- የኮንስትራክሽን ዲዛይንና ኮንትራት አስተዳደር ስራዎች ውጤታማነትን በማጠናከር በዘርፉ የሚታየውን ምዝበራ  ለመታገል የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣

**ግብ 4፡- የአገር በቀል የስራ ተቋራጮችንና የአማካሪ ድርጅቶችን የካፒታልና መሳሪያዎች ፣ የፕሮጀክት ማኔጅመንት፣የቴክኖሎጂና የፋይናንስ አቅም ውስንነትን መፍታት፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞኑ የሚገኙ 100 ተቋራጮችን እና 50 አማካሪዎችን በካፒታል፣በመሳሪያና በቴክኒካል ክህሎት ያሉባቸውን ክፍተቶችን ለመለየት የሚያስችል 1 የዳሰሳ ጥናት ሰነድ ማዘጋጀት፣
- የስራ ተቋራጮች በካፒታል እንዲሁም በማሽነሪ አቅማቸው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሊዝ ወይም የብድር ድጋፍ እንዲያገኙ ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ጋር መግባባቶችን መፍጠር፣

**ግብ 5፦ በዘርፉ የስራ ተቋራጮች፤ አማካሪዎችና ባለሙያዎች አቅም ግንባታ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ ስራዎች እንዲሁም የኮንስትራክሽን ግብዓትና ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ስራዎችን ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞኑ የሚገኙ 114 ተቋራጮችን፣ 23 አማካሪ ድርጅቶችን፣ 100 ባለሙያዎችን ብቃት የማረጋገጥ ስራ በሶፍት ዌር የታገዘ እንዲሆን ማድረግ፣
- በዞኑ ለሚገኙ 100 ፕሮፌሽል ባለሙያዎች፣114 ስራ ተቋራጮች እና 50 አማካሪ ድርጅቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣
- የቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ስራዎችን ማካሄድ፤

**ግብ 6፦ በዞኑ ያሉትን 2 የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ጥራት ምርምር እና የፍተሻ ማዕከላት ዘመኑ ባፈራው ቴክኖሎጂ እና ብቃት ባለው የሰው ሃይል በማጠናከርና ተጨማሪ ላብራቶሪዎችንና የምርምር ማዕከላትን በማቋቋም በዘርፉ የግብዓትና ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ስራዎችን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞኑ ውስጥ የሚገኙ 25 የግንባታ ግብአት መገኛ ካባ ቦታዎች ተለይተው የጥራት ደረጃቸው እየተረጋገጠ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፤
- በጥራት ፍተሻ ላቦራቶሪዎች ለ4 የኮንስትራክሽን ግብአቶች የጥራት ፍተሻ ማድረግ ፣

**ግብ 7፦ የኮንስራክሽን ኢንደስትሪው ለጥቂቶች በተለይም በአንጻራዊነት ለህንጻ ግንባታ ያጋደለ እና በበርካታ ትንንሽና መካከለኛ የዘርፉ ተዋንያን የተሞላ በመሆኑ ከዘርፉ የሚጠበቀውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም ለማግኘት በኢንዱስትሪው ትልልቅ አቅም ያላቸውን ተዋንያን እንዲኖሩ በማድረግ ዘርፉን በአካታችነትና በወጥነት ባለቤት ሰጥቶ በትኩረት መምራት፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 10 የስራ ተቋራጮችና 2 አማካሪ ድርጅቶች በአፈጻጸማቸው የደረጃ ልየታ ተደረጎላቸው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ፣

**ግብ 8፦ በራስ አቅም ቤት የሚገነቡ አርሶ አደሮችና የከተማ ነዋሪዎች የገንዘብና የጉልበት ግምት ፣ የማህበረሰብ የነጻ ጉልበት የመንገድና የአካባቢ ጥበቃ ግንባታዎች የጉልበት ግምትን ሁሉ በማጠቃለል በዘርፉ በበጀት አመቱ በአማካይ 2.3 ቢሊየን ብር መዋዕለ ንዋይ ፍሰት እንዲኖር ማስቻል፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የመዋዕለ ንዋይፍሰቱ በሚከተሉት ተግባራት ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

- በራስ አቅም የሚሰሩ የገጠር ቤቶች፣ የገጠር ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ፣የከተማ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ፣የኮሜርሻል ህንጻዎች ግንባታ፣የተቋማት ህንጻዎች ግንባታ፣የመሰረተ ልማት ግንባታ (መስኖ፣መንገድና ድልድዩች)፣
- የማህበራዊ መሰረተ ልማት (ትምህርት ቤቶች ፣የጤና ተማት)፣
- የቱሪዝም ልማት ግንባታዎች፣
- የኢንዱስትሪ ኮንስትራክሽን (ውሃ፣ ኢነርጅ፣ ማእድንና ኳሪንግ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች የፋብሪካ ግንባታ)፣
- ሌሎች የኮንስትራክሽን ስራዎች፣

**ግብ9፡- በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን የአስወገደ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መገንባት፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በኢንዱስትሪው ውስጥ የሚታየውን ባልተሟላ ዲዛይንና የስራ ዝርዝር ወደ ስራ የመግባትና የዋጋ ተገማችነት(cost predictability)ችግር በመቅረፍ 80 በመቶ ፕሮጀክቶች ያለዋጋ ልዩነት እንዲጠናቀቁ ማድረግ፣
- በዞኑ በሚከናወኑ የግንባታ ፕሮጀክቶች የጊዜ ብክነትን (time over run)በመቀነስ 90 በመቶ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የውል ጊዜ እንዲጠናቀቁ ማድረግ፣

**ግብ 10. በከተሞች በተለያዩ አማራጮች 10,975 መኖሪያ ቤቶች እንዲገነቡ ማድረግ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በከተሞች በህብረት ስራ ማህበራት 8515 ቤቶች ፣በግለሰቦች 2334 ቤቶች ፣ለዝቅተኛ ነዋሪዎች 126 ቤቶች መገንባት ፣
- የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ኩባንያዎችን በማሳተፍ የተሻሻሉ፣ወጭ ቆጣቢና ፈጣን የግንባታ ዲዛይኖችና ቴክኖሎጅዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ፣
- አዳዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶች ማኔጅመንት ቴክኖሎጅዎችን በመፍጠር ወይም በማላመድ እንዲሁም ለአካባቢ ተስማሚ ቴክኖሎጅዎችን አጠቃቀም በማስፋፋት በቤቶች ግንባታ ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

**ግብ 11፡- በየደረጃው ያለው አመራር የዘርፉን ልዩ ፋይዳ ተገንዝቦ ድጋፍና ክትትል በማድረግና በተለይም የህንጻ አዋጁን በማስፈጸምና በመፈጸም ረገድ ያለውን የእውቀትና የክህሎት ክፍተት መፍታት ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለ25 አመራር እና የህንፃ ሹም ባለሙያዎች በኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ፖሊሲ፣ በህንጻ አዋጅ ፣ኮዶችና እስታንዳርዶች ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል።

**ግብ 12፡- ለ6,484 (50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) ዜጎች የስራ እድል መፍጠር፤**

## የማስፈጸሚያ ስልቶች

የሲሚንቶ፣የብረት፣መስታዎት፣ ሴራሚክስ፣የወለል ንጣፎች፣ የተዘጋጁ እምነበረድ፣ግራናይት የመሳሰሉት ለኮንስትራክሽን የሚውሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች ገበያው እስኪፈጥራቸው ከመጠበቅ በእቅድ አመላክቶ መመረታቸውን በፖሊሲ ማረጋገጥ ፣ለዘርፉ መዘመን የመንግስት፣የግሉ ዘርፍ ፣የምርምርና የትምህርት ተቋማት የውጭ አጋሮችና እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ትብብርን በማሳደግ ወሳኝ ሚና እንድጫወቱ ማድረግ ፣በስራ ላይ ያለ የዘርፉ ህጎችን በመፈተሽ አስቻይ ማድረግ፣በኮንስትርክሽን ዘርፍ ለሚታዩ ከልክ ያለፍ መዘግየትና የወጭ መናር እንድሁም የጥራት መጓደል መፍትሄው ችግርን በወቅቱ መፍታትን ግብ ያደረገ ጥብቅ የክትትልና ግምገማ ስርአት ማስፈን የሚሉት ዋናዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው።

## 2.6. ማሕበራዊ ፍትህ

## ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

- ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትህ ተደራሽና ፍትሃዊ ተጠቃሚ አለመሆን
- ስር የሰደደ ድህነትና ተጋላጭነት መጨመር፣
- በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ አለመሆን፣
- መብት፣ ተሳትፎንና ውክልና እና ተጠቃሚነት በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን
- ውጤታማ የህፃናት እና የማህበራዊና ጥበቃ ስርዓት  አለመሆን፣
- የአካቶ ትግበራ ስራ ተቋማዊ አለመሆን፣

## የትኩረት መስኮች

- የስራ እድልና የኑሮ ሁኔታን ማሻሻል
- የመሰረታዊ አግልግሎትና የማህበራዊ መድን ተጠቃሚነትን ማሳደግ
- አሻጋሪ ልማታዊ ሴፍትኔትን ማስፋፋት
- መብትን፣ ተሳትፎንና ውክልና እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣

- ለጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ዜጎች የህግ ጥበቃና ድጋፍ ማድርግ

## የትኩረት አቅጣጫዎች

የኢኮኖሚ ስርዓት አቅሙ ያለው ሁሉ በራስ አቅም መተማመን ዘላቂ የኑሮ መሰረት መሆኑን እንድያረጋግጥ መስራት፣ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ጥራት ተደራሽነት እና ፍትሃዊነት ማጎልበት፣ የማህበራዊ ሴፍትኔትና የማህበራዊ ድጋፍ ተጠቃሚዎችን ከስራ እድል እና ኑሮ ማሻሻያ ጋር በማስተሳሰር በረጅም ጊዜ ዘላቂነትን ማረጋገጥ፣ ለድሃ እና ለመስራት ጉልብት እጥረት ላላቸው ቤተሰቦች በሁሉም አካባቢዎች ማህበራዊ ድጋፍን በየደረጃውና በኢኮኖሚ አቅም ልክ ማስፋፋት እንድሁም በሴቶች ኢኮኖሚ ተሳትፍ የኢኮኖሚ አቅምን በማሳደግ ማህበራዊ ፍትህን ማረጋገጥ የሚሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣቻዎች ናቸው፡፡

**ዓለማ፡- ለማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለተጋለጡ በተለይ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህፃናት፣ ሴቾች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ስራ አጥ ወገኖች ለችግርና አደጋ ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን የማህበራዊ ፍትህ ስርዓት መዘርጋትና ተጠቃሚ በማድረግ የተመጣጠነ ዕድገት ማምጣት**

**ግብ1፡- የማህራዊ ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው የተለያዩ የህብረተስብ ክፍሎች የማህበራዊ ፍትህን ተደራሽ እና ፍትሃዊ ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ለተጋለጡ 23922 የህብረተሰብ ክፍሎች በማሰባሰብ የእለት ምግብ ድጋፍ በማቅረብ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ
- በልማታዊ ሴፍትኔት ፐሮግራም 89369 የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ማድርግ
- 89369 የሴፍትኔት ተጠቃሚዎችን ክፍያቸው በኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ዘዴ እንድያገኙ ማድርግ
- ወቅታዊ የሆነ የገንዘብ ክፍያ ማሰራጨት

**ግብ 2 ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋለጡ እና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን ብዝሃነትን/አካታችነትን እና አሳታፊነትን ማጎልበት**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በገቢ ማስገኛ ስራዎች የተሰማሩ ተጠቃሚዎችን ቀጣይነት ባለው አግባብ መከታተልና መደገፍ

**ግብ 3:- የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ ምላሽና የመጠባበቂያ ክምችትን ለማሳደግ በ2017 በጀት ዓመት ከደረስነበት 10435 ኩ/ል በ2018 ወደ 32829 ኩ/ል እህል ወይም 133000000 ብር መሰብሰብ፡፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ስለ ተረጅነት አስከፊነትና አሳፋሪነት ከህብረተሰብ ጋር መግባባት፤

- ትክክለኛ የድሃ ድሃ የሆኑ ህብረተሰብ ክፍሎችን መለየት፤
- ለተለዩት ድሃዎችና የችግር ተገለጭ የህብረተሰብ ክፍሎች፤ የሚሆን 32829 ኩ/ል እህል ማሰባበሰብ፤
- የተሰበሰበውን እህል ከብክነት በጸዳ መልኩ ለተጎጂዎች ማድረስ፤

**ግብ 4፡- የህፃናት የሴቶች፣አካል ጉዳተኛና የአረጋውያን ፣የስራ አጥ እንድሁም ለችግርና አደጋ ተጋላጭ የሆኑ ዜጎች የሰብአዊ መብታቸው እንድከበር ማድረግ**

**የሚከናወኑ ተገባራት**

- ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ ህብረተሰብ ክፍሎችን ከጥቃት፣ ከበደል፣ ከአድሎና መገለል መከላከል እና ተበዳዮች ለጉዳታቸው ማካካሻ እንድያገኙ ማድረግ
- ለችግር ለተጋለጡ እና ለስራ አጥ ወገኖች የስራ እድል እና የገቢ ማስገኛ ስራዎችን ማስፋፋት
- ለተለያዩ የመድን ሥራዎችን በማስፋፋት ህብረተሰቡ ከማህበረሰብ መድን ተጠቃሚ እንድሆን ማድረግ
- የማህበረሰብ ጥበቃዎችን በማድረግ የጤና ፣የትምህርትና ሌሎች የመሰረታዊ አገልግሎቶችን ሽፋንና ተደራሽነትን ማሳደግ

**ግብ 5፡- የትምህርት ስራዎችን በማጠናከርና በማስፋት በድህነት እና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህፃናት ጧሪ ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያ እና ሌሎች ግለሰቦችና ቤተሰቦችን በመደገፍና በመንከባከብ ተጠቃሚ ማድረግ**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- 41 ተቋማት በማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት አባል እንዲሁኑ ይደረጋል፣
- 12 የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረቶች እንዲቋቋሙ ይደረጋል፣
- 519 የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረቶች እንዲጠናከሩ ይደረጋል፣
- 11,752,265 (በገንዘብ 8,760,473 እና በዓይነት 2,991,792) በማህበረሰብ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረት አባላት ሀብት መሰብሰብ፣
- ከተሰበሰበ ኃብት ውስጥ 18,021 የህብረተሰብ ክፍሎችን (3574 አካል ጉዳተኛ፣ 1144 አረጋዊያን፣ 8764 ህፃናት፣ 1082 ጉዳና ተዳዳሪ፣ 1082 ለምኖ አዳሪ፣ 1325 ኤች.አይ.ቪ በደማቸው የሚገኝ እና 1050 ሴተኛ አዳሪዎች ተጠቃሚ እንዲሁኑ ይደረጋል፣
- የ89,369 በገጠር የሚኖሩ የመስራት አቅም የሌላቸውና እና በአስከፊ ድህነት ውስጥ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች እና የሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ዳግም ልየታ ማድረግ፣

- 71,495 የቋሚ ቀጥታ ድጋፍ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች የቤት ለቤት ጉብኝት ማካሄድ፣
- 71,495 የቋሚ ቀጥታ ድጋፍ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች ጉዳያቸውን (casemanagmnet) በመከታተል ልየታ ማካሄድ፣
- 71,495 የቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ ቤተሰቦች የማህበራዊ አገልግሎት ትስስር እንድፈጠርላቸው ማድረግ፣

**ግብ 6፡- የሴቶች፣ የህፃናት፣ የወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዉያንና ሌሎች ህብረተሰብ ክፍሎች መብት፣ ተሳትፎን፣ ውክልና እና ተጠቃሚነት ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 235,372 ሴቶች በአድስና በነባር የሴቶች ልማት ህብረት እንዲፈረጁ ማድረግ፣
- 9710 ነባርና አድስ የሴቶች ልማት ቡድን ህብረትን በመስፈርቱ መሰረት እንድመዘኑ ማድረግ ፣
- 61 ቀበሌዎች የሴቶች ልማት ህብረትን በመስፈርቱ መሰረት ሞደል እንድሆኑ ማድረግ
- 102,514 (ሴት.51257) ህፃናት በአዲስ በህጻናት ፓርላማ እና በትምህር ቤቶች በሚቋቋሙ ክበባት እንዲደራጁ ማድረግ ፡፡
- 120,446 (ሴት 60,223 ) ወጣቶች በአድስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች እንድደራጁ ማድረግ
- ለ852 አስፈፃሚ አካላት በአረጋዊያን ዙሪያ እና ለ1,2000 አስፈፃሚ አካላት በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ በወጡና በሚወጡ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወ.ዘ.ተ. የአድቮኬሲ ስራዎችን ማከናወን፣
- የመብት ጥሰትና በተቋማት አግልግሎት አሰጣጥ ቅሬታ ይዘዉ የሚመጡ ሴቶችን፣ህፃናት፣ ወጣቶች፣አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን 100 % ተቀብሎ ማስተናገድ
- በየደረጃው ለሚገኙ 368 ለሴት፣ ለአካል ጉዳተኛና አረጋዉያን አደረጃጀት አመራሮች ከሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዉያን ጋር ተያይዞ በወጡ መመሪያዎች ደንቦች የህግ ማዕቀፎች ጋይድላይን ፓኬጅ ዙሪያ ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፣
- በዞን ደረጃ ለሚገኙ ወንድ 12 ሴት 12 ድምር 24 ለሚሆኑ ስራ አስፈፃሚዎች፣ ህግ ተርጉሚዎችና ህግ አውጭ አካለት አመራሮች በሴቶች፣ በህፃናት፣ በአካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ዙሪያ በወጡ ህጎች፣ መብት፣ ተሳትፎና ውክልና ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ከተሳትፎና ውክልና አኳያ

- 226431 (67929 ወጣት) ሴቶች በሠላም ተሳትፎ ዙሪያ ግንዛቤ ይፈጠርላቸዋል፣

- በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት 615,000 (ሴት 307,500) ወጣቶች እንድሳተፉ ማድረግ፣
- በክረምት 1,834,000 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ በማድረግ በክረምት ብር 834ሚ. የመንግስት ወጪን ማዳን፣
- ለ 185,000 (ሴት 92500 )ወጣቶች በተለያዩ የንቅናቄ መድረኮች እንድሳተፉ ማድረግ፣
- ከተጠቃሚነት አኳያ
- 66,566 ሴቶች በሴቶች ልማት ህብረትና በራስ አገዝ ቡድን ብር 79,879,674 እንዲቆቡ ማድረግ፣ 33,283 ሴቶች 66,566,395 ብር በሴቶች ልማት ህብረትና በራስ አገዝ ቡድን እንዲበደሩ ይደረጋል፣
- 140,520 (ሴት 70,260 ) ወጣቶች 505,871,948 ብር እንድቆጥቡ እና 43,822 (ሴት 21911) ወጣቶች ብር 501,857,091 የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንድሆኑ ማድረግ፣
- ለ 134,842 (ሴት 67421) ወጣቶች ስራ እድል እንድፈጠርላቸው ክትትልና ድጋፍ ማደረግ
- 12,606 (ሴት 6303) ህፃናት በተለያዩ አማራጭ የህጻናት ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎቶች አይነቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማደረግ
- 11 የህፃናት ማቆያዎች በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንዲቋቋሙ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡
- ለ350 አረጋውያና 256 ለሚሆኑ አካል ጉዳተኞች በቋሚ የገቢ ማስገኛ ሥራ እንዲሠማሩ ማድረግ፣
- 256 አካል ጉዳተኞች በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ፣
- 2,500 ጧሪና ደጋፊ ለሌላቸው አረጋዊያን ቋሚ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ፕሮጀክቶችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረግና ሌሎች የሀብት ማሰባሰቢያ ስልቶችን በመጠቀም 10.82 ሚሊዮን ብር መሰብሰብ
- ለ385 ሴቶችና ለ54 አካል ጉዳተኛች የስራ ትስስር መፍጠር

## 2.7. የከተማና ገጠር ልማት

### 2.7.1. የከተማ ልማት

## 2.7.1. ከተማ ልማት

የከተሞች እድገት የአንድን ሀገር ኢኮኖሚ ለማሳደግ ከፍተኛ ድርሻ ያለውና የእድገት ምልክት ቢሆንም በሌላ መልኩ ከተሞችን በእቅድ መምራት ካልተቻለ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንድሁም ኣካባቢያዊ ቀውሶችን ያስከትላል፡፡ በተለይ ደግሞ የመንግስት አቅምና ምላሽ ከከተሞች እድገትና መስፋፋት

ፍጥነት ጋር መራመድ ካልቻለ ችግሩ የከፋ ይሆናል፡፡ የከተሞች መስፋፋትና እድገት ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት እንድጨምር የሚያደርግ በመሆኑ የኢንዳስትሪና አምራች ዘርፎች በቂ የሰው ኃይል እንድኖራቸው በማድረግ ለኢኮኖሚ እድገት መሳለጥ ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ የዞናችን፣ የክልል ብሎም የኢትዮጵያ ከተሞች ለነዋሪዎች ሁለንተናዊ ለውጥ፣ ምቹ ምኅዳር መፍጠር የሚያስችል ዕድሎችን የተጎናጸፉ ሆነው ሳለ እንድሁ ረጅም የዕድሜ ጥንታዊነት፣ ስምና ዝና ብቻ ታቅፍው ቆይተዋል፡፡ ከተሞች የፖለቲካል ኢኮኖሚ ማዕከል እንዱሁም የዜጎች የስራ ዕድልና ቴክኖሎጂ ፈጠራ መናኸሪያ መሆናቸውን ታሳቢ ያደረገ ውበት፣ ጽዳትና ለኑሮ ምቹ መዋቅራዊ ድዛይን በማላበስ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

- ከተሞች መቶ በመቶ በተዘጋጀላቸው የትግበራ ፕላን አለመመራት
- የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ችግር
- ዘላቂ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ችግር
- የመሰረተ ልማት አቅርቦትና አስተዳደር ችግር
- የፅዱ፣ ለኑሮ ተስማሚና የአረንጓደ ከተሞች ግንባታ ውስንነት
- የመልካም አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ችግር

## የትኩረት መስኮች

1. የከተሞች መልካም አስተዳደርና ፋይናንስ
2. ዘመናዊ የከተማ ፕላንና መሬት አስ/ር
3. ተደራሽ የቤት ልማትና አስተዳደር
4. የተቀናጀ ምርታማና ዘላቂ የከተማ መሠረተ ልማት
5. ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት እና ኢንስቲቲዩሽን ግንባታ

## የትኩረት አቅጣጫዎች

የከተማ ልማት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ከተሞችን እንደሀብት መሠረታቸው የልማት ማዕከላት ማድረግ፣ የከተሞችን መስፋፋት ቀድሞ የሚመራ የከተማ ፕላን እንድኖር ማድረግ፣ በዜጎች ተሳትፎ የሚገነቡ ዘላቂ የመኖሪያ ቤቶችን ማስፋፋት፣ የከተማ መሠረተ ልማትን ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት እና ጥራት ማረጋገጥ፣ በከተሞች የምግብ ዋስትናን ጨምሮ ማሕበራዊ ጥበቃን (social protection) ማረጋገጥ፣ ከተሞች ለኑሮ ምቹ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገሩ፣ ውብ፣ ጽዱና አረንጓደ እንድሆኑ ማድረግ፣ ዘመናዊ የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደርን ማስፈን፣ የማዘጋጃ ቤት

አገልግሎቶችን በማዘመን መልካም አስተዳደርን ማስፈን እንድሁም ዘመናዊ የከተማ መረጃ አያያዝ ሥርዓት ማስፈን የሚሉት ይሆናሉ፡፡

**ዓላማ፡- ከተሞችን ምቹ እና ዘላቂ የመኖሪያ እና የሥራ አውዶች ማድረግ፤**

**ግብ 1፡- በዞኑ የተመጣጠነ አከታተም ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ የክትመት ምጣኔን በ2017 ካለበት 19.68% በ2018 ወደ 22.18% ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በዞኑ ከሚገኙ ነባር ከተሞች መካከል በአቅራቢያቸው ወዳለ ትልቅ ከተማ ሊዋሀዱ የሚችሉ 4 ከተሞችን መረጃ በማደራጀት ለክልሉ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡
- በጥናት ላይ ተመስርቶ የከተማነት መስፈትቱን የሚያሟሉ 2 የገጠር የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት የከተማነት እውቅና እንዲያገኙ ይሰራል፡፡
- ከተሞችን በፈርጅ የማደራጀት ስርዓቱን በማጠናከር 10 ከተሞች የፈርጅ ለውጥ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

**ግብ 2፡- በአንድ ከተማ አስ/ር ስማርት ሲቲን እና በ9 ከተማ አስተዳደሮች የኮሪደር ልማትን ተግባራዊ ማድረግ**

የሚከናወኑ ተግባራት

- አንድ ከተማ አስ/ር ስማርትሲቲን ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር( ጊምባ)
- የኮሪደር ልማት ስራዎችን ቅድመ ዝግጅት በወቅቱ እንድጠናቀቅ ማድረግ
- ለኮሪደር ልማት ስራ የሚሆን በቂ በጀት መያዝና ተጨማሪ ሀብት የማፈላለግ ስራ መስራት

**ግብ 3፡- ከተሞች ለመሰረተ-ልማትና አገልግሎት እቅርቦት የሚያስፈልጋቸውን ወጪ በራሳቸው የመሸፈን አቅም ከ31% ቢያንስ ወደ 50% ማድረስ፣**

የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት

- በ98 ከተሞች በህብረተሰቡና በመንግስት በጋራ በሚከናወኑ የአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ የህብረተሰብ ተሳትፎ ምጣኔው 282,242,001 (55%) እንዲደርስ ይደረጋል፡፡
- 89 ከተሞች ገቢ መሰብሰብ ባለባቸው በአመካኝ 45 የገቢ አርዕስቶች አገልግሎት ገቢ የመሰብሰብና የመጠቀም አቅማቸው 973,764,000 እንዲደርስ ይደረጋል፡፡
- ያልተማከለ የፋይናንስ ስርአት በመዘርጋት ማዘጋጃቤት ያላቸው ከተሞች ከወጪያቸው 50 በመቶ በራሳቸው ገቢ መሸፈናቸውን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል፡፡

**ግብ 4፡- በሁሉም ከተሞች ፕላን ወሰን ውስጥ የሚገኘውን የመሬት ሀብታቸውን 100% ቆጥረውና መዝግበው እንድይዙ በማድረግ የመሬት ወረራንና ህገወጥነትን መከላከል**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- የ98 ከተሞችን የፕላን ወሰን የተሟላ መረጃ ተደራጅቶ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡
- በዞኑ የሚገኙ 98 ከተሞች በፕላን ወሰናቸው ውስጥ የሚገኘውን መሬት 3000 ሄ/ር በአገልግሎት አይነት ቆጥረውና መዝግበው እንዲይዙ ይደረጋል፡፡
- በ98 ከተሞች ክልል ውስጥ የሚገኘውን 440 ሄ/ር የመሬት ሀብት በመቆጠር እና በዘመናዊ ቴክኖሎጅ የታገዘ በመሬት ባንክ አሰራር ስርዓት መሰረት መረጃውን አደራጅቶ በመያዝ ወጪና ገቢ የማድረግ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡
- በ98 ከተሞች የሚገኙ የተሟላ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ የሌላቸው 5100 ይዞታዎች ተጣርተው የከተማ ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
- አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ በህገ-ወጥ መንገድ የተያዙ 2,300 ይዞታዎችን መረጃ በአግባቡ በመለየት፣2,300 ህገወጥ ግንባታዎችን በማፍረስ በህጉ መሰረት ከሶስተኛ ወገን ነጻ በማድረግ 3.3 8ሄ/ር መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

**ግብ 5፡- በዞኑ የሚገኙ 98 ከተሞችን በተሟላ ፕላን መምራት**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- ፕላን ተዘጋጅቶላቸው ያላጸደቁ ከተሞችን መረጃ በመለየት ያላጸደቁ ከተሞች 100% ኘላናቸውን አጸድቀው ወደ ትግበራ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡
- ከከተሞች ለሚቀርቡ የፕላን ማስተካከያ ጥያቄዎችና የፕላን ምደባ ለውጥ ጥያቄዎች 100% ምላሽ ይሰጣል፡፡
- በከተሞች በሚፈጠሩ የፕላን ጥሰቶች ላይ እርምጃ በመውሰድ 100% እንዲስተካከሉ ይደረጋል፡፡
- የከተሞችን ፕላን አፈፃፀም አቅም ለማሳደግ ለ10 ከተሞች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለከተሞቹ ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡
- በከተማ ፕላን አፈጻጸም ዙሪያ የህብረተሰቡን ተሳትፎና ባለቤትነት ለማሳደግ 40,000 (35% ሴቶች) የከተማው ነዋሪ ህዝብ በፕላን አፈፃፀም ወቅት ግንዛቤ እንዲያገኝ ይደረጋል፡
፡

- መዋቅራዊ ፕላን ያላቸዉ 9 ከተሞች ወደ ትግበራ ሲገቡ የሰፈር ልማት ፕላን እያዘጋጁ መተግበራቸዉን በክትትልና ድጋፍ ይረጋጣል፣
- በሁሉም ከተሞች የፕላን መንገድ ከሶስተኛ ወገን ነጻ እንዲሆን ማድረግ እና 130 ኪ/ሜ መንገድ እንዲከፈት ማድረግ፣
- በፕላን አፈፃፀም ዙሪያ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን፣ የፍ/ቤት እና ከፀረ ሙስና የሚጠየቁ ማብራሪያዎች ተቀብሎ 100% ምላሽ መስጠት፣
- በ2 ከተሞች በመስክ በመገኘት የፕላን አፈፃፀም ኦዲት ማድረግ፣
- የፕላን ዘመናቸው ያለፈና 29 ከተሞች ፕላን እንድከለስ ከሚመለከተው ተቋም ጋር በመነጋገር ድጋፍ ይደረጋል
- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች በከተማው ፕላን መሰረት ስለመሆኑ እየተረጋገጠ ለ2000 የከተማ ፕላን ስምምነት ይሰጣል፡፡

**ግብ 6፡- በከተሞች የመሬት ፍላጎትን ቢያንስ 50% በመቶ እንድቀርብ በማድረግ 10 በመቶ በጫረታ፣ 90 በመቶ በምደባ እንድተላለፍ ይደረጋል**

የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት

- ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 63 ሄ/ር መሬት ለጨረታ እና 630 ሄ/ር መሬት ለምደባ በድምሩ 693 ሄ/ር መሬት እንዲዘጋጅ በትብብር በመስራት ለተጠቃሚዋች ማስተላለፍ፡፡
- በጨረታ እና በምደባ ለተለያየ አገልግሎት ተወስደው በውላቸው መሰረት ጥቅም ላይ ያልዋሉ (ወደ ልማት ያልገቡ) 45 (6.61ሄ/ር) ቦታዎች እንዲነጠቁ ይደረጋል፡፡
- በዞኑ የሚገኙ 2 ከተሞች የቦታ ደረጃና የቀጠና ዋጋ በማዘጋጀት እና ነባር 96 የሊዝ ከተሞች የሊዝ ስርዓቱን እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡

**ግብ 7፡- በ4 ከተሞች የሚመነጨውን ቆሻሻ 15 በመቶ በመልሶ መጠቀምና 10 በመቶ ለመልሶ ኡደት እንዲያልፍ በማድረግ እና ቀሪውን 140,000 ሜትር ኪዩብ ደረቅ ቆሻሻ በተገቢው ቦታ በማስወገድ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሽፋንን 60 በመቶ ማድረስ፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በ9ከተሞች ደረቅ ቆሻሻ የሚያስወግዱ 9 አዲስ ማህበራትን በማደራጀት ቆሻሻን በአግባቡ የማስወገድ ስራ ይሰራል፡፡
- በ9 ከተሞች አዲስ የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ገቢና የፋናንስ አቅርቦት ስርዓት ይዘረጋል፡፡

- በከተሞች ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ 140,000 ሜትር ኪዩብ የሚሆነው በተገቢው ቦታ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

**ግብ 8፡- በ28 ከተሞች በፕላን ከተመላከቱ አረንጓዴ ቦታዎች መካከል 30% የሚሆኑት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲለሙ ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በ98 ከተሞች የአረንጓዴ መሰረተ ልማት ሽፋን በፕላን ላይ ከተቀመጠው የመሬት ድርሻ 10 ከመቶ ሆኖ እንዲለማ ይደረጋል፡፡
- በ30 ከተሞች በፕላን የተመላከቱ አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት 150 አረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲያገኙ እና በስታንዳርድና ዲዛይን እንዲለሙ ይደረጋል፡፡
- በ5 ከተሞች 5 አዲስ አገልግሎት የሚሰጡ የመዝናኛ ፓርኮች በስታንዳርድ ዲዛይን እንዲለሙ ይደረጋል፡፡
- የራሳቸው ችግኝ ጣቢያ የሌላቸው 2 ከተሞችን በመለየት 2 አዲስ ችግኝ ጣቢያዎች እንዲለሙ ይደረጋል፡፡
- በሁሉም ከተሞች የለሙ 620 ሄ/ር ነባር አረንጓዴ ቦታዎች ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ ተገቢው እንክብካቤ ይደረጋል፡፡

**ግብ 9፡- በ5 ከተሞች ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሁሉን አቀፍ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት የተገልጋዮችን ሰነዶች /ፋይል ወደ ዲጂታል መረጃ እንዲቀየሩ ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በ5 ከተሞች ወረቀት አልባ አሰራር ስርዓት (ኢ-ሰርቪስ) በመዘርጋት ሁሉም የከተማ አገልግሎቶች ማለትም የመሬት፣ የቤት፣ የመሰረተ ልማት፣ የኮንስትራክሽን አስተዳደር… ወዘተ) ከዘልማዳዊ አሠራር ወጥተው ወደ ዲጂታል አሠራር እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡
- በ5 ከተሞች የደንበኛ ሰነዶች (የከተማ ነዋሪዎች የቤተሰብ ሁኔታና አድራሻ፣ የከተሞች የመሬት እና የቤቶች ይዞታ እንዲሁም ሌሎች ወሳኝ የከተማ ነክ መረጃዎች) 100% ወደ ዲጂታል መረጃ እንዲቀየሩ ይደረጋል፡፡
- በ5 ከተሞች ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሁሉን አቀፍ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት መረጃዎች በኔትዎርክ አማካኝነት በአስተዳደር ደረጃዎች እና በተቋማት መካከል እንዲተሳሰሩ ይደረጋል፡፡

**ግብ 10. የቤት አስተዳዳር ስርዓትን በማዘመን 4150 ቤቶች በዘመናዊ መረጃ ቋት እንዲደራጁ ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የከተማ ቤቶች100 በመቶ በዘመናዊመረጃ ቋት ማደራጀት
- በከተሞች 950 የመንግስት ቤቶች፣የግለሰብ ቤቶች 3200 ድምር 4150 ቤቶች በዘመናዊ መረጃ ቋት እንዲደራጁ ይደረጋል፡፡
- በከተሞች በመንግስት ባለቤትነት የሚከራዩ 4163 ቤቶችን በየዓመቱ የውል እድሳት በማድረግ 300 የመንግስት ቤቶች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንድዘጋጀላቸው ይደረጋል
- 20 ያለአግባብ የተያዙ ቤቶችን መለየት፣20 ስርዓት በማስያዝ የመንግስት የቤቶች አስተዳዳር በህግ አግባብ እርምጃ እንድወሰድ፣ 98 ቤቶች ተነጥቀው ለአድስ ተከራዮች እንድተላለፍ ይደረጋል፡፡

**ግብ 11፡- በከተሞች የአገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻልና በማዘመን የተገልጋዮችን የዕርካታ መጠን ከ58% ወደ 65% ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ላይ በየደረጃው ለሚገኙ 63 አመራሮችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፡፡
- በ9 ከተማ አስተዳደሮችና 4 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ስታንዳርድ እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡
- በ28 ከተሞች ስታንዳርድ ለወጣላቸው የከተማ አገልግሎቶች የዜጎች ቻርተር እንዲዘጋጅ፣ ለዜጎች ተደራሽ እንዲሆንና አገልግሎቱም በስታንዳርዱ መሰረት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

**ግብ 12፡- በከተሞች በሚከናወኑ የልማት ስራዎች ለ14,966 ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር የከተማ ሥራ አጥነትን መቀነስ፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በከተማ ልማት ዘርፍ (በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድና በአረንጓዴ ልማት) ለ540 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ይፈጠራል፡፡
- በኮንስትራክሽን ዘርፍ (በቤት ልማት እና መሰረተ ልማት ግንባታ) (ለ14,426 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ይፈጠራል፡፡

## የማስፍጸሚያ ስልቶች

በከተሞች የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግልት አሰጣጥን ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ እንድቻል በጥናት ላይ ተመስርቶ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ የሰው ሀይል ስምሪት እና ተደራሽ የህግ ማዕቀፎች በአድስ

እንድዘጋጁ እና እንድሻሻሉ ማድረግ፣ የከተሞች ያልተማከለ ተቋማዊ አደረጃጀት እና አስተዳደርን ተግባራዊ ማድረግ፣ ከተሞች ሚናቸውን የሚመጥን እና የሚያጠናክር አደረጃጀትና የአገልግሎት ስታንዳርድ እንድኖራቸው ማድረግ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ተደራሽ፣ ግልጽ፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለበት የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት፣ የከተሞችን እምቅ የገቢ አቅም መሰረት በማድረግ ሀብት አሰባሰባቸውን ጥራት ባለው የገቢ ማሳደጊያ ዕቅድ እንድመሩ የተጀመረው ስርዓት ጥልቀትና ጥራት አግኝቶ እንድሰፉ ማድረግ፣ የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና ውጤታማነት ባለው አኳኋን እንድመራ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትና የሕብረተሰቡን ተሳትፎ እና ባለቤትነት ማሳደግ፣ ለከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በማከናወን በከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ያለውን የማስፈጸምና የመፈጸም አቅም ማሳደግ፣ የፕላን፣ የመሬት፣ የካዳስተር እና የግንባታ ፍቃድ ሰጪ ተቋማት በቅንጅት እና በመናበብ እንድሰሩ ማድረግ እንድሁም ዞን አቀፍ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት በፕሮጀክት አፈፃፀምና አስተዳደር ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዝርዝር በመለየት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት መፍትሔ እንድያገኙ ማድረግ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ የዕቅድ ማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

## 2.7.2. የገጠር ልማት

በደቡብ ወሎ ዞን  ውስጥ ይኖራል ተብሎ ከሚገመተው 2,935,926 ህዝብ ውስጥ 2,661,793 ወይም 90.6% የሚሆነው በገጠር ይኖራል፡፡ የኢኮኖሚ መሰረቱ በዋናነት ግብርና፣ የማምረቻ አቅሙ በእንስሳት ጉልበት ላይ የተመሰረተ እና ለዘመናት ያልተሻሻለ የአመራረት ስልት፣ የሀብት መሰረት የሆነው የመሬት  ይዞታው በአብዘሀኛው የተበጣጠሰና ለዘመናዊ ግብርና የማያመች ነው፡፡ ለችግሮቹ መፍትሄ ሰጥቶ የገጠሩን ማህበረሰብ ኑሮ ማሻሻል እንዳይቻል ስለ ገጠር ልማት የተያዙ የቆዩ ኋላቀር አመለካከቶችና ስትራቴጅዎች አሉታዊ አስተዋጽዖ አድርገዋል፡፡ ስለሆነም የገጠር ሃብትን ጨምሮ የገጠር ልማት ፕሮግራሞችን የሚያስተባብር ተቋም በመፍጠር የገጠሩን ህብረተሰብ ኑሮ ማሻሻልና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት ጠንክሮ መስራት ተገቢ ይሆናል፡፡

### ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

- የገጠር መሰረተ ልማት
- ግብርናን ላልተማረ አርሶ አደር ብቻ አድርጎ የማየት ችግር
- የኢንቨስትመንት አማራጮችን አለማስፋት
- የደን መጨፍጨፍና የአፈር ክለት ችግር

### የትኩረት መስኮች

1. አምራች የገጠር መሰረተ ልማትን ማስፋፋትና ማዘመን

2. ምርታማነትን በገጠር መጨመር እና የኢንቨስትመንት አማራጮችን ማስፋት
3. አዋጭ የደን ልማት እና የአፈር ጥበቃ ስራዎች
4. ለመኖር ምቹ የሆነ እና የጸዳ ቤትና አካባቢ መፍጠር

## የትኩረት አቅጣጫዎች

የገጠር ስልተ ምርትን ማሻሻል፣ በተለይም ድህነትን የሚጠየፍ እና በጥረቱ ከድህነት ለመላቀቅ የሚቆጭ ማህበረሰብ በመፍጠር በራስ ጥረት እና በራስ መተማመን ከበለጸጉ ማህበረሰቦች ጋር መስተካከል እንድያልም እና እንድደርስ ማመላከት፣ መደገፍ፣ በዞኑ በከተማና በገጠር የተመጣጠነ ልማት ማረጋገጥ፣ በገጠር የኢኮኖሚ እድገት ከአካባቢ ጥበቃ እና መልካም ባህላዊ እሴቶች ጋር ተመጋግቦ እንድዘልቅ ማሳለጥ የሚሉ ዋና ዋና ዎቹ ናቸው፡፡

## ዋና ዋና ግቦች

**ግብ 1፡- 10000 የገጠር ጎጆዎችን በማሻሻልና በመገንባት የአ/አደሩን የአኗኗር ዘይቤ መቀየር፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- የገጠር ጎጆዎች ስታንዳርድ ድዛይን ማዘጋጀት፣
- ለሚገነቡ የገጠር ጎጆዎች ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣

**ግብ 2፡- የገጠር ቤቶችን በፕላን እንድመሩ በማድረግና ሁሉን አቀፍ የገጠር መሰረተ ልማትን በማስፋፋት ለገጠር - ከተማ ሽግግር ምቹ መሰረት መጣል፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለገጠር ከተሞች ምቹ የሆነ ፕላን ማዘጋጀት
- አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን መለየትና መዘርጋት፣

**ግብ 3፡- የተበታተነውን የገጠር የመኖሪያ አሰፋፈር በማሰባሰብ ለመሰረተ ልማት ዝርጋታ እና ተደራሽነት አመች እንድሆን ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለአሰፋፈር ምቹ የሆኑ ቦታዎችን በጥናት መለየት
- ለማህበረሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር የማሳመን ስራ መስራት
- ሞደል መንደሮችን መመስረት

**ግብ 4፡- በጥናት ላይ በመመስረት በዞኑ ውስጥ በከተማ እና በገጠር የተመጣጠነ ልማት ማረጋገጥ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በገጠርና በከተማ መካከል ያለውን ክፍተት በጥናት መለየት
- ክፍተቱን ለማጥበብ የሚያስችሉ የተለያዩ ስራዎችን ማከናውን

**ግብ 5፡- ከግብርና በተለይም ከአነስተኛ ባለይዞታ ግብርና ጋር የተያያዘውን የገጠሩን ማህበረሰብ የኑሮ መሰረት ከግብርና ውጭ በሆኑ ሌሎች የኢኮኖሚ አማራጮች በማገዝ ኑሮውን እንድሻሻል ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ስለማንኛውም ስራ ክቡርነት ለማህበረሰቡ በስፋት ግንዛቤ መፍጠር
- ከግብርና ውጭ በሆኑ የኢኮኖሚ አማራጮች ላይ ለማህበረሰቡ ስልጠና መስጠት
- ከግብርና ውጭ የሆኑ የአካባቢውን መክሊቶች በመለየት እና በስልጠና በማዳበር የኢኮኖሚ አምራቾች እንድሆኑ መሰራት

**ግብ 6፡- ለገጠር የሚስማሙ የሃይል አማራጮችን እና ተስማሚ የግንባታ ቁሳቁሶችን በማቅረብ የማህበረሰቡን የአኗኗር ዘይቤ ማሻሻልና ለአካባቢ ጥበቃ ተስማሚ እንዲሆን ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- ለገጠሩ ማህበረሰብ የተለያዩ የሃይል አማራጮችን ማቅረብ
    - ✓ 35,000 የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን በሰለጠኑ አምራቾችን ማስመረትና ማሰራጨት
    - ✓ 4,000 የኤሌክትሪክ ምድጃ ምርቶችን ማሰራጨትና የኃይል አጠቃቀም ቁጥጥር ስራ ማከናወን፣
    - ✓ 2,000 የኤሌክትሪክ የምጣድ ምርቶችን ማሰራጨትና የኃይል አጠቃቀም ቁጥጥር ስራ ማከናወን፣
- በሶላርና በባዮጋዝ አቅርቦት ላይ በስፋት መስራት
    - ✓ 8000 በሶላር ማሾዎች ስርጭት (solar lantems) ለህብረተስቡ ማሠራጨት
    - ✓ 5005 የቤተሰብ ሶላር ሆም ሲስተም ተጠቃሚ ማድረግ (solar home system)
    - ✓ 345 የቤተሰብ የባዮጋዝ ቴክኖሎጂዎችን በግንበኞች ማስገንባት፣

**ግብ 7፡- ቴክኖሎጅን መሰረት ያደረገና ዘመኑን የዋጀ የገጠር ልማትን ማስፋፋት**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- ለገጠሩ ምቹ እና ዘመናዊ የሆኑ ቴክኖሎጅዎችን በጥናት መለየት
- የሚመረጡ ቴክኖሎጅዎችን በስፋት ማቅረብ
- በዘመናዊ ቴክኖሎጅ አጠቃቀም ላይ ግንዛቤ መፍጠር

**ግብ 8፡- ቀድመው ወደ ተግባር በመግባት የገጠር ሽግግር ከተሳካላቸው የሀገራችን አካባቢዎች ልምድ በመቀመር ከዞናችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ተግባራዊ ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የገጠር ሽግግር በሚመለከት የተሻለ ጅምር እንቅስቃሴ ካላቸው አካባቢዎች ልምድ መቀመር፣

**ግብ 9፡- ገፊ በሆኑ ምክኒያቶች ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት መቀነስ፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለፍልሰት መንስኤ የሆኑትን ምክኒያቶች በጥናት መለየት
- ፍልሰትን የሚቀንሱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ማስፋፋት

**ግብ 10፡- የግል ባለሀብቱና የተማረው ማህበረሰብ በገጠር ልማት ላይ እንድሳተፉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የገጠር ልማቱን ለማሳደግ በመንግስትና በባለሃብቱ ትብብር የገጠር ልማት ንቅናቄን መፍጠር፣
- ባለሃብቱና የተማረው ማህበረሰብ በዘርፉ እንድሰማሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር
- ማህበረሰቡን የሚያሳትፉ የተቀናጀ የማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ አሰራርን መዘርጋት

## የማስፈጸሚያ ስልቶች

ከቀበሌዎች እና ጎጦች የሚጀምር፣ በማዕከላትና በዙሪያው የገጠር መካከል የተሳሰረ ልማትን፣ የተቀናጀና ሁሉን አቀፍ የገጠር ልማትን፣ በመንግስትና በአልሚዎች ትብብር የሚካሄድ የገጠር ልማት ንቅናቄ መፍጠር፣ ታታሪነትን እና በራስ የመተማመን ባህሪያትን ለጋራ እጣ ፈንታ እና ብልጽግና በፍጹም መደጋገፍ የመስራት ባህል የማስረጽ ስራ ይሰራል፡፡

በመካከለኛ ጊዜ ስልጡን የገጠር መኖሪያ ለመገንባት ለረጅም ጊዜ የከተማ ልማት ጥሩ መሰረት ለመጣል በገጠር ባለ ሁለት ፍኖተ ስልት መከተል ያስፈልጋል፡፡ አንደኛው ማዕከልና ዙረያ ገብ፣ገና ለከተማ ማዕከልነት ያልበቁ ማዕከላትን በመምረጥ በዙሪያው ያሉ ጎጦችን በሳቢ ምክኒያቶች እንድሰባሰቡባቸው ማድረግ- ቀድሞ በፕላን መምራት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለከተማነት ባይበቁም የገጠር መሰረተ ልማትን በአማካይ ቦታ ለማድረስ የሚያስችል ጎጦችን በመለየት ማልማት የሚሉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በገጠር ኢንተርፕራይዝ፣ አካባቢ ጥበቃ፣ የባህል ልማት ተሃድሶ እና ንቃት፣ የጎጦች ማስተካከል እና ማዋዋጥ፣ በገቢ ማሳደግ እንድሁም ከመንደር ባለፈ ማሳየት እና አብሮ መስራትን ያስቀደመ የማስተማር ስልት  መከተል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ስልቶች ናቸው፡፡

## 2.8. የአካባቢ ጥበቃ ልማት

አካባቢና በውስጡ ያሉ ብዛ ህይወትና መስታጋብራቸው የህይወት መሰረት ነው፡፡ ሰው ኑሮውን ለማሻሻል እና ለመዘመን በሚያደርገው ጥረት የተፈጥሮ ሃብቶችን ይጠቀማል፤ ምርት ያመርታል፤ የፍጆታ ስርዓቶችን ይፈጽማል፡፡ እነዚህ መስተጋብሮች መጠን ሲያልፍ ከአካባቢ እስከ አለም የሚያደርሱ ዳፋዎችን ያስከትላሉ፡፡ በዚህ ዘመን በዓለም አቀፍ ደረጃ የአየር መዛባትና ብክለት፤ በአገር ደረጃ ደግሞ የደን መመናመን፤ የአፈር መከላት፤ የአካባቢ መበከልና የመሳሰሉት ፈታኝ ኩነቶች ተከስተዋል፡፡ ዞናችን መጠኑ ቢለያይም በሁሉም ተግዳራቶች የሚጠቃ ዞን ነው፡፡ በአጠቃላይ የአካባቢ ጉዳይ የዘላቂ ልማት አንዱና ዋነኛው ምሰሶ በመሆኑ የአሻጋሪ ልማት ዕቅደን ከማሳካት አንጻር አካባቢን በመጠበቅና መንከባከብ እንድሁም የሚካሄዱ የልማት ስራዎች ከአካባቢ ጋር የተጣጣሙ እንድሆኑ ማድረግ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ በመሆኑ ይህንን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ የ2018 በጀት ዓመት የዘርፉ ዕቅድ  እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች

- የአየር ንብረት ለውጥ አሳሳቢነት
- የአካባቢ ክለትና ብክነት መጨመር
- የተፈጥሮ ሥርዓተ- ምህዳር ሃብት መራቆትና መመናመን

## የትኩረት መስኮች

1. የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን መቀነስ
2. ዘላቂነት ያለው የአካባቢ አያያዝና አጠቃቀም
3. የብዝሃ-ህይዎት ጥበቃና ልማት
4. የአካባቢ ህግ ተከባሪነተና ተፈጻሚነጽ

## የትኩረት አቅጣጫ

በአካባቢ መራቆት ላይ ጫና የሚፈጥሩ የባዮ ማስ፤ የገጠር ቤት ግንባታ፤ ባህላዊ ግብርና መሳሪያዎች፤ የእንስሳት መኖ እና የከተማ ግንባታ የመሳሰሉት ፍላጎቶች በገጠር-ከተማ ሽግግር፤ የኃይል አማራጭ፤ በዘመናዊ ግብርና ስልተ-ምርት የሚፈቱ በመሆናቸው የረጅም ጊዜ የአካባቢ ጥበቃ ዓላማና ግቦችን ከአጠቃላይ የኢኮኖሚ  እና ማህበራዊ ሽግግር ዓላማ እና ግቦች ጋር እንድጣጣም ማድረግ፤  የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የአካባቢ ጥበቃ እርምጃዎች በአንድ በኩል በህዝብ ተሳትፎ እና በዘመቻ የሚሰሩ በሌላ በኩል ዘላቂነታቸው ከትግበራ  እና ሰልቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በዕቅድ እና ጥብቅ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት የሚከናወኑ ተግባራትን በሚለይ ሁኔታ መተግበር፤ የአፈር መከላትን ለመከላከል ከሚደረጉ እርምጃዎች መካከል አንዱ ለሆነው የእርከንና የክትር ስራ በህዝብ ተሳትፎ በዘመቻ

ሊከናወኑ የሚችል ተግባር እንደሆነ ሁሉ የአካባቢ ደን ልማት ስራዎች ከማህበረሰብ ዘላቂ ጥቅም፤ የደን ሃብት ፍላጎቶችን ከሚተኩ አማራጭ አቅሞች የመፍጠር ዕቅድ፤ ለዘመናት የታረሰ መሬትን የሚተካ የኢኮኖሚ መሰረት ከመፍጠር እንድሁም ካላሰለሰ የክትትል እና ግምገማ ስርዓት ጋር የመያያዛቸው እውነታን ግምት ውስጥ ማስገባት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**ዓላማ፡- በዞኑ ውስጥ በአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓደ ኢኮኖሚ ግንባታን ዕውን ለማድረግ የአካባቢ፤ የደን፤ የዱር እንስሳትና ሌሎች የብዝሀ-ህይወት ሃብቶችን በማልማት፤ በመጠበቅ እና የአጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት ጤናማ የስርዓ-ምህዳር መስተጋብር በማሳደግ ዘላቂ ልማትና ዕድገት ማረጋገጥ፤**

**ዋና ዋና ግቦች**

**ግብ 1፡- የደን ዘርፉን በመጠበቅ ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞኑ ውስጥ የሚገኘውን 24700 ሄክታር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደን እና በ2018 በጀት ዓመት በአድስ የሚለማውን 22577 ሄ/ር ጨምሮ በድምሩ 269587 ሄ/ር የሚሆነውን ደን በመከለልና በመለካት ይዞታ ማረጋገጫ እንድኖረው ማድረግና በዘላቂነት ማልማት፤
- በ2018 በጀት ዓመት የመንግስት 15 ሄ/ር፤ የማህበረሰብ 635 ሄ/ር፤ እና የማህበራት 15 ሄ/ር በድምሩ 665 ሄ/ር ደኖች የደን አያያዝ እና አጠቃቀም ዕቅድ እንድዘጋጅላቸው ማድረግ
- የተቀናጀ ዘላቂ የደን ልማትና ጥበቃ ስራዎችን በመተግበር የዞኑን የደን ሽፋን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 247000 ሄ/ር በ2018 በጀት ዓመት ወደ 269587 ሄ/ር ከፍ ማድረግ፤
- በ2018 በጀት ዓመት ወደ 29453 ኩንታል የከሰል ምርት፤ 80282 ሜ/ኩብ የእንጨት ነክ ምርቶች ምርት ማሳደግ፤
- የተቀናጀ የደን ልማት ስራዎችን በማከናወንና እሴት በመጨር (ለጣውላ፤ አጣና፤ ዕጣንና ሙጫ፤ ቀርቀሃ፤ የጫካ ማር፤ ከሰል፤ ፍራፍሬ፤ካርቦን ትሬድንግና ሌሎች ምርቶችን) ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ በ2017በጀት ዓመት ከነበረበት 120.5 ሚልዮን ብር በየዓመቱ 10 በመቶ በማሳደግ በ2018 በጀት ዓመት ወደ 132 ሚሊዮን ብር ማሳደግ፤
- በ2017 በጀት ኣመት ከደን ዘርፍ ተጠቃሚ የሆኑ 69596 የህብረተሰብ ክፍሎች ከዓመታዊ የገቢ ድርሻቸው ከ5-10 በመቶ የሆኑ ቤተሰቦችን በበጀት ዓመቱ በ10 በመቶ በማሳደግ በበጀት ዓመቱ ወደ 69,596/ ከዚህ ውስጥ እማወራ 20,879/ ማድረስ፤

**ግብ 2፡- የዞኑን የደን ኢንዱስትሪዎች ሙሉ አቅም ለማሳደግ ለደን አልሚዎች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የደን ኢንዱስትሪዎችን በየሩብ ዓመቱ ድጋፍና ክትትል ማድረግ።
- የደን አልሚዎችን ጥራት ያለው ምርት እንዲያመርቱ 200 አልሚዎች ስልጠና በመስጠት ምርታቸውን በቀጥታ ለደን ኢንዱስትሪዎች እንዲያቀርቡ ትስስር መፍጠር፤

**ግብ 3፡- በ2018 በጀት ዓመት 18857 ሄ/ር መታረስ የሌለበት ተራራማ እና በሰፋፊ ውሃ አካላት ዙሪያ ያለ መሬትን እንድከለልና እንድያገግም ማድረግ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በ18,231 ሄ/ር የተራቆተ ተራራማ መሬት ከንክኪ ነፃ ሆኖ እንዲያገግም እና እንዲለማ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል።
- 18,857 ሄ/ር የተጋጋጠ ተራራማ እና በውሃ አካላት ዙሪያ ያሉ መሬቶችን የአካባቢውን ማህበረሰብ በማሳተፍ መለየት፤መከለል እና ካርታ እንዲዘጋጅ ማድረግ
- በ726 ሄ/ር በሰፋፊ ውሃ አካላት ዙሪያ ያሉ መሬቶችን እንዲለማና እንዲያገግም ይደረጋል።

**ግብ 4፡- የዞኑን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት እንዳይጨምር በበጀት ዓመቱ የአረንጓዴ ቴክኖሎጂ ተግባራት እንዲሰሩ ማድረግ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የዘርፉ የተቋማት የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ሰጭ ተግባራትን አካቶ ትግበራ ተግባራዊ እንድያደርጉ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን እንድቀንሱ የሚመለከታቸውን አካላት ማስተባበር
- የአረንጓዴ ቴክኖሎጅ ትግበራ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤

**ግብ 5፡- የአካባቢ ብክለትንና ብክነትን መቀነስ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በከተሞች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻአያያዝና አወጋገድ ዙሪያ 52 ( ከዚህ ውስጥ 18 ሴቶች) ባለሙያዎችና በየደረጃው ያሉ አካላት የሚሳተፉበትን የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፤
- የአደገኛ ኬሚካልመረጃ በማሰባሰብና በማደራጀት እንድወገዱ ለማድረግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር መስራት፤
- በአካባቢና በማህበረሰብ ላይ ተጽዕና በሚፈጥሩ አካባቢብክለት ችግር አይነቶች ጥናት በማካሄድ 1 የጥናት ሰነዶችን ለውሳኔ ሰጭ አካላት ማቅረብ፤

- በስርዓት ምህዳር ግልጋሎት ዋጋ ትመና አዋጅ ላይ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ማስተዋወቅና ግንዛቤመፍጠር፤

**ግብ 6፡- በ2018 በጀት ዓመት ለ887 ፕሮጀክቶች የአካባቢ ይሁንታ ፈቃድ መስጠት**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- **ለ887አዳዲስ ፕሮጀክቶች የአካባቢ ይሁንታ ሰርተፊኬት በሚያሟሉት በተለያየ ም ድብ (ESIA, PESIA, Screening) ይሰጣል**
- **የ427 ነባር ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድ እድሳት ይደረጋል**
- **ለ7 ነባር ፕሮጀክቶች የተዘጋጀላቸው የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እንዲጸድቅ ይደረጋል**
- የተሰጡ ፈቃዶች ስራ ላይ መዋላቸውን መከታተልና መቆጣጠር፤

**ግብ 7፡- የማምረቻ አገልግሎት መስጫ የልማት ፕሮጀክቶች የሚካሄድ ክዋኔ ኦድት ከነበረበት 294 በ2018 በጀት ዓመት ወደ335 ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- የማምረቻ፤ የአገልግሎት መስጫ እና የልማት ፕሮጅክቶች የአካባቢ ህግ አክብረው መስራታቸውን ማረጋገጥ፤
- 335 ፕሮጅክቶች (180 ለማምረቻ፤ ለ 90 የአገልግሎት መስጫ እና 65 የልማት ፕሮጀክቶች)ላይ የአካባቢ ክዋኔ ኦድት ማድረግ፤
- 146 ፕሮጅክቶች (80 የማምረቻ፤46 የአገልግሎት መስጫ እና 20 የልማት ድርጅቶች) ቁጥጥር ማድረግ
- 421 ፕሮጀክቶች ላይ (225 የማምረቻ፤ 112 የአገልግሎት መስጫ እና 84 የልማት ድርጅቶች) የአካባቢ ብክለት ክትትል ስራ ማካሄድ
- የህግ ጥሰት በፈጸሙ 18 ፕሮጀክቶች ላይ አስተማሪ እርምጃ መውሰድ፤

**ግብ 8፡- በልማት ፕሮጀክቶችና ተቋማት ላይ በ2017 በጀት ዓት ተደርጎ የነበረውን 130 የአካባቢ ቁጥጥር በ2018 በጀት ዓመት ወደ 146 በማሳደግ የህግ ተከባሪነትን ማረጋገጥ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞንና በወረዳ ለሚገኙ 38 የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያዎችና 17 ባለድርሻ አካላት ስልጠና መስጠት፤
- ከ 25/10ሩ ሰቶች/ ባለድርሻ አካላት ጋር የአካባቢ ጉዳይ ምክክር ማድረግ፤
- ለ 470 የልማት ድርጅቶች ቆጠራ ማካሄድ
- ለቀረቡ የብክለት ይወገድልኝ ጥቆማዎች 100 በመቶ ምላሽ መስጠት፤

**ግብ 9፡- በከተሞች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ላይ የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞኑ በሚገኙ 9 ከተሞች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዕቅድ በማዘጋጀት መተግበር፤
- በዞንኑ በሚገኙ ሁሉም ከተሞች የተሸሉ እንድሆኑ ከማድረግ አንጻር የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፤ አያያዝና አወጋገድ መልሶ ጥቅም ላይ አንድውል ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- በደረቅ ቆሻሻአያያዝና አወጋገድ ላይ የሚሰሩ 8 ማህበራት 200 (112 ሴቶች)አባላት ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- በከተሞች ቆሻሻበመሰብሰብ መልሶ መጠቀም ላይ የሚሰሩ 112 ድርጅቶችና ግለሰቦች በማህበር ተደራጅተው እንድሰሩ ማድረግ፤

**ግብ 10፡- በዞኑ እስከ አሁን የነበረውን 4766ሄ/ር የውሃ አዘል መሬቶች የአያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት በመዘርጋት በ2018 በጀት ዓመት 61 በመቶ ያህሉን በመጠበቅ የሚሰጡትን አገልግሎት ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የውሃ አዘል መሬቶች፤ ወንዞችና ሀይቆች ሁሪያ ለ51(19 ሴቶች) ባለሙየዎችና የአጋር አካላት ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፤
- በዞኑ የሚገኙ ውሃ አዘል መሬቶች ማለትም ወንዞችና ኃይቆችን በዘላቂነት ለማልማትና ለመጠበቅ የሚያስችል ዕቅድ እንድዘጋጅ ጉዳዩን ለሚመለከታቸው አካላት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- በዞኑ ውስጥ ያሉ ውሃ አዘል መሬቶችን መረጃ ማደራጀት፤ የማጠናከርና የማጥናት ተግባራት የውሃዘል መሬቶች ባሉበት አካባቢ እንድፈጸም ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- ከአባይ እና አዋሽ ተፋሰስ ጽ/ቤቶች እንድሁም ከመሬት መምሪያ ጋር በውሃ አዘል መሬቶች በተፋሰስ ልማትና ተስማሚ የአየር ንብረት ለውጥ ዘደዎች ላይ በቅንጅት መስራት፤

**ግብ 11፡- መጤ ወራሪ፤ ተስፋፊና አደገኛ የአረም ዝርያዎችን በመቆጣጠር የማወገድ አቅምን በ2018 በጀት ዓመት ከነበረበት 38 በመቶ ወደ 42 በመቶ ከፍ ማድረግ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በበጀት ዓመቱ 21000 ሄ/ር የሚሸፍን መጤና ተስፋፊ አረም 147000 (66150 ሴቶች) ህብረተሰብ በማሳተፍ ማስወገድ፤

- 75 (22ቱ ሴቶች) ተሳታፊዎች የሚሳተፉበት መጤ ወራሪና ተስፋፊ አደገኛ የአረም ዝርያዎች ላይ ያተኮረ የምክክር መድረክ ማዘጋጀት
- የመጤ ወራሪና ተስፋፊ አደገኛ የአረም ዝርያዎችን 59/ ወ 36 ሴት 23/ ለባለድርሻ አካላትና ለባለሙያወች ስልጠና በየደረጃው መስጠት

**ግብ 12፡- ለ18825 (50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች ) ዜጎች የስራ እድል መፍጠር፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለወጠቶች፣ ሴቶችና ገቢያቸው አነስተኛ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በደን ልማት፣ ማምረትና ውጤቶች ዝውውር የስራ ዕድል እንድፈጠርላቸውና ተጠቃሚ እንድሆኑ ማድረግ፤

## ማስፈጸሚያ ስልቶች

ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ ሰፊ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በማከናወን በየደረጃው የሚገኙ አካላትን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም መገንባት፣ የዘርፉን የተቋማት የስራ አፈጻጸም በሚዲያና ኮሙኒኬሽን ስራዎች በማስደገፍ ለህብረተሰቡ ማቅረብና በዚህም ሰፊ የህብረተሰብ ንቅናቄ እና የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ እንድፈጠር ማድረግ፤ የዘርፉን ስራ ለማሳለጥ ከሚንቀሳቀሱ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑድርጅቶች፣ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ሃብት በማፈላለግ ለስራ የሚያስፈልጉ ግብዓችን ማሟላት፣ በዘርፉ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየት እና በመቀመር ማስፋት፣ የመረጃና ቴክኖሎጅ አቅርቦት እና ሽግግርን ማሳደግ፤የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፣ ሴክተር ዘለል ተግባራትን አካቶ በመተግበር (ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ኤች አይቪ/ኤድስ፣ ስነ-ህዝብ ወዘተ)በልዩ ትኩረት መፈጸም፣ የተቀናጀና የተናበበ አሳታፊ ዕቅድ ዝግጅት፣ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ አሰራር ስርዓ ማዕቀፍ በመቅረጽተግባራዊ ማድረግ እንድሁም ለስራ ማስፈጸሚያ የሚያግዙ ስትራቴጅዎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ የዘርፉ ማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

# ክፍል ሶስት የልማት አቅሞች

## 3.1. ተፈጥሮ ሀብት (መሬት)

### ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

- የመሬት ባለይዞታነት መብት በሚፈለገው ደረጃ አለመረጋገጥ፣
- ሣይንሳዊ በሆነ መንገድ ዘላቂ የመሬት አጠቃቀም ስርዓት ዝርጋታ ውስንነት፣
- ለልማት ተነሽዎች ካሳ የመክፈልና በዘላቂነት መልሶ የማቋቋም ስራ ውስንነት፣
- የተበታተነውን አርሶ አደር ወደ አንድ ማዕከል ማሰባሰብ አለመቻል፣
- በገጠር መሬት ላይ የሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች አለመስፋፋት፣

### የትኩረት መስኮች

- የመሬት አስተዳደርና ካዳስተር፣
- ዘላቂ የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ፣
- የልማት ተነሽዎች ካሳ፣ ምትክና መልሶ ማቋቋም፣
- የገጠር ቀበሌ ማዕከላት ግንባታ፣
- የገጠር መሬት ኢንቨስትመንት፣

### የትኩረት አቅጣጫዎች

ተቋማዊ የማስፈፀም አቅምን ለማጎልበት አንዱ ቁልፍ ጉዳይ ትክክለኛ አደረጃጀት መፍጠርና አሰራሮችን መዘርጋት ሲሆን ከዚህ አኳያ ባሉት አመታት የዞኑ መንግስት መሬትን ፍትሃዊና ዘመናዊ በሆነ መንገድ ለማስተዳደር የገጠርና የከተማ አደረጃጀቶን ወደ አንድ ተቋም የማዋሀድ ስራ የተሰራ ቢሆንም ወደ ተግባር ሲገባ በአሰራር ሂደት ችግሮች አጋጥመዋል፡፡ በመሆኑም የሚታየውን የአደረጃጀት ክፍተት ለመሙላት በዞኑ መንግስት ትኩረት ተሰጥቶ ሊፈታ ይገባል፡፡

ጥራት ያለው እቅድ የማዘጋጀት የመከታተልና የመገምገም፣ የገንዘብና የንብረት እንቅስቃሴ በልዩ ሁኔታ ክትትል የማድረግ፣ የግዥ ስርአቱን በማዘመን ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ፣ የሀብት አጠቃቀም እንቅስቃሴ ጤናማ መሆኑን ለማረጋገጥ ለውስጥ ኦዲት ትኩረት የመስጠት፣ ፕሮጀክቶችን የመምራትና የማስተዳደር አቅም የማሳደግ፣ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ተደራሽ ለማድረግና ተጠያቂነትንም ለማስፈን የዜጎች ቻርተር ቃል ኪዳን ሰነድ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

**ዓላማ፡- በዞኑ ዘመናዊ የመሬት አስተዳደር ስርዓትን በመገንባት ከመሬት ጋር በተያያዘ የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታትና ፍትሃዊ የመሬት ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ የማህበረሰቡን የኑሮ ደረጃ በዘላቂነት ማሻሻል፣**

**ግብ1. 1110 ሄ/ር የኢንቨስትመንት መሬት በመለየት በባለሀብቶች አሁን የሚለማውን መሬት ከ 2834.84 ሄ/ር ወደ 3934.84 ሄክታር በማሳደግ ምርታማነትን መጨመር፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ 100 ሄ/ር መሬት ማቅረብ
- በግብርና እና ከግብርና ውጭ ኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚሰጥ 1000 ሄክታር ነፃ መሬት ይለያል፡፡
- ለአገልግሎት ዘርፍ 10 ሄ/ር መሬት ማቅረብ
- ለ45 በግብርና ኢንቨስትመንት ለተሰማሩ ነባር ባለሀብቶች የመሬት አያያዝና አጠቃቀም በመገምገም ዓመታዊ ፕሮፋይል ተዘጋጂቶ ይላካል፣
- 4 የነባር ባለሃብቶች ውል ይታደሳል፡፡
- በግብርናና በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ 67 ባለሃብቶች ድጋፍና ክትትል ማድረግ
- 62 በኢንቨስትመንት የተሰማሩ ነባር ባለሀብቶች ዝርዝር መረጃ ኮምፒተራይዝድ ይደረጋል

**ግብ2. ለ24115 ባለይዞታዎች 95,084 የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ካርታ በመስጠት የይዞታና የመጠቀም መብት ዋስትና ማረጋገጥ እንዲሁም የማሳ ካርታን የብድር ዋስትና በማድረግ ባለይዞታዎች የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፣**

- ለ 482 የወል መሬቶች 1,902 የማሳ ካርታ፣
- ለ432 የመንግስት ተቋማት ለ391 የማሳ ካርታ፣
- ለ121 መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ለ475 የማሳ ካርታ መስጠት
- ለ23,117 የግልና የጋራ ባለይዞታዎች ለ 92,232 የማሳ ካርታ በማዘጋጀት የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ይሰጣል፡፡ የተጋላጭ ህብረተሰቦች ድርሻ 1206፣(ወላጆቻቸዉን በሞት ያጡ ህፃናት 205፣ አካል ጉዳተኞች 458፣ አረጋዉያን 47_አካባቢያቸዉን የለቀቁ 72) ናቸዉ፡፡
- በበጀት አመቱ የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረገገጫ ደብተርን የብድር ዋስትና በማድረግ 2,685 (ወንዱ 1,625 ሴት 1,060) ባለይዞታዎች ብር 30,860,900 የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፣ ብድር ያገኙ አርሶ አደሮችም የቁጠባ መጠን ብር 1,920,000 እንዲደርስ ይደረጋል፣

**ግብ3. የመሬት መረጃ ወደ NRLAIS (ብሄራዊ የገጠር መሬት መረጃ ስርአት) ሲስተም እንዲያሽጋግሩ በማድረግ የሚቀርቡትን 7410 የመሬት ግብይቶች ማረጋገጥ፣ ማጽደቅ በ Analogue (ባህር መዝገብ)**

**በመመዝገብ በNRLAIS በሲስተሙ በመመዝገብ አገልግሎቱን በማሳለጥ የመሬት መረጃ ስርዓት ደህንነትንና ቀጣይነትን ማሻሻል፣**

- የሚቀርቡትን ሁሉንም የመሬት የመሬት ግብይቶች (ስጦታ፣ ዉርስ፣ ኪራይና ልዉዉጥ) በማረጋገጥ፣ ማጽደቅ እንድሁም በመመዝገብ አገልግሎት መስጠት
- በ1 ወረዳ 100% የማሳ መረጃ በማጥራት 4000 ማሳዎችን ወደ የመሬት መረጃ ወደ NRLAIS ( ብሄራዊ የገጠር መሬት መረጃ ስርአት) ሲስተም እንዲያሽጋግሩ በማድረግ
- የመሬት ምዝገባ መረጃው ወደ ሲስተሙ በተሸጋገረባቸው ወረዳዎች የ7,410 (ወንድ 4,315፣ ሴት 3,095) ባለይዞታዎችን ግብይት በአገር አቀፍ የገጠር መሬት አስተዳደር የመረጃ ስርዓት ሶፍት ዌር (NRLAIS) አማካኝነት የግብይት ስራ ይሰራል፣

**ግብ4. በገጠር መሬት ያለውን ህገ-ወጥ ተጠቃሚነትን በመከላከል የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቀነስ 11,506 አቤቱታና መልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በተሳሳተ ማስረጃ ይዞታቸውን ያጡ 48 (ወንድ 21፣ ሴት 27) ተጎጅ የህብረተሰብን ክፍሎችን መረጃ በማጥራት ይዞታቸው እንዲመለስላቸው ይደረጋል፣
- የተወረሩ የወል መሬቶችን ከ4524 (ወንድ 4017፣ ሴት 502 ከህገ ወጦች 1096 ሄ/ር መሬት እንዲመለስ ይደረጋል፣
- ከመሬትጋር ተያይዘዉ የሚነሱ አቤቱታና ቅሬታዎችን 11,506 ተገልጋዮች አቤቱታና ቅሬታዎችን በመፍታት የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ጉዳዮችን በማካተት መስራት
- ለ3628 (ወንድ 993፣ ሴት 247) ወጣቶችና አዲስ መሬት ጠያቂዎች በቡድንም ይሁን በተናጠል በቋሚነትና በጊዜ አዊነት 856 ሄ/ር መሬት በማቅረብ በገጠር ያለዉን ስራ አጥነት ለመቀነስ የሚደረገዉን ጥረትም ለመደገፍ በዘርፉ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል፡፡

**ግብ 5፡- የመሬት አጠቃቀም እቅድ ከተዘጋጀላቸዉ ዉስጥ 126646 ባለይዞታዎች ወደ ተግባር በማስገባት ከዚህ በፊት ወደ ተግባር የገቡ 654081 ባለይዞታዎችን ቁጥር 780727 ማሳደግ፡፡**

- የመሬት አጠቃቀም እቅድ ተዘጋጅቶ ርክክብ ከተደረገላቸው በተደረገው ተከታታይ ክትትልና ድጋፍ ወደ ተግባር የገቡ (ምክረ-ሀሳብ የተገበሩ) 83949 ባለይዞታዎች 472312 ማሳ ብዛት እና 96726 ሄ/ር መሬት ወደ ተግባር ለማስገባት ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በመፍታት በታቀደላቸዉ መሰረት ወደ ተግባር ማስገባት፡፡

**ግብ6. ለ3550 የልማት ተነሽዎች ብር 1,243,154,981 ቢሊየን ተመጣጣኝ ካሳ በመገመት የካሳ ማስከፈል ሂደቱን ማሻሻል፡፡**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በልማት ምክንያት የይዞታ መሬታቸውን ለሚነሱ 3550 3,550 (አባወራና እማወራ 1,980፣ አባወራ 638፣ እማወራ 730 እና 193 የወል ተጠቃሚዎች) ባለይዞታዎች የሚለቀቅ **546 ሄ/ር** የመሬት መጠን 1,243,154,981 ብር በመገመት ካሳ እንድከፈላቸዉ መረጃቸዉን ለከፋይ ተቋም እንድላክ ማድረግ፡፡

**ግብ7. 1593 በልማት ምክንያት የይዞታ መሬታቸውን ለሚነሱ የልማት ተነሽዎች በማቋቋም ከተደረሰበት 3183 ወደ 4676 ከፍ በማድረግ በዘላቂነት የተቋቋሙ የልማት ተነሽዎች ቁጥር ማሳደግ፡፡**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- ለ 637 የልማት ተነሽዎች ባለይዞታዎች (አባወራና እማወራ 382፣ አባወራ 115፣ እማወራ 140) ለእያንዳንዳቸዉ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ማድረግ እና ለ 956 (ወንድ 669 ሴት 287) ዕድሜያቸዉ 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ልጆቻቸዉ ደግሞ በከተሞች የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበራት ስታንዳርድ መሰረት የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንደሚያገኙ ይደረጋል፡ ፡
- ለ333 (ወንድ 233፣ ሴት 100) 333 የመስሪያ ቦታ ተጠቀሚዎች የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ይደረጋል፣
- ለ1,775 ግለሰቦች ባላቸዉ የካፒታል አቅም መሰረት በተለያዩ የስራ ዘርፎች (በንግድ 910፣ በአገልግሎት ዘርፍ 665፣ በግብርና 186፣ በኢንዱስትሪና ማኑፋክቸሪንግ 13) እንዲሳተፉ ድጋፍ ይደረጋል፣
- በልማት ምክንያት ለሚነሱ ለ 1,775 ባለይታዎች የሚሰማሩበትን የኑሮ አማራጭ ዘርፎች በመምረጥ እንዲሰማሩ ድጋፍ ይደረጋል (በተናጠል 1243 ፣ በሽርክና 200፣ በአክሲዮን 200፣ በህ/ስራ 132)፣
- ለ 102 (ወንድ 71፣ ሴት 31) ባለይዞታዎች የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፣ ብር 6,630,000 እንዲያገኙ ይመቻቻል፡፡
- ለ 1,108 (ወንድ 775 ፣ሴት 332) ተጠቃሚዎች የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸዉ ድጋፍ ይደረጋል፣

**ግብ8፡ በተበታተነ ሁኔታ የሚኖረውን አ/አደር በቀበሌ ማዕከል ለማሰባሰብ በ26 ቀበሌዎች 5200 ተጠቃሚዎች የቤት መስሪያ ቦታ በመስጠት የተጠቃሚዎችን ሽፋን 1437 ከነበረዉ ወደ 6637ማሳደግ፡፡**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በ26 የቀበሌ ማእከላት 5200 የቤት መስሪያ ቦታዎችን 313 ሄ/ር መሬት ላይ በፕላናቸው መሰረት ይሸነሸናሉ፣
- ለ2000 ግለሰቦች (ለመኖሪያ 1800፣ ለተቋማት 100 ፣ ለንግድ 100) 50 ሄ/ር ቦታ ማስረከብ፣
- ለ2000 ግንባታዎች ላጠናቀቁ ግለሰቦች ቋሚ ካርታ ተዘጋጅቶ እንድሰጣቸዉ በማድረግ 1124 ተጠቃሚዎች ወደ 3124 በማሳደግ የተማከለ መሰረተ ልማትና የአገልግሎት መስጫ እንድያገኙ ማስቻል፣

## 3.2. የሰዉ ኃይል ልማት

የሰዉ ሃብት ሀገራዊ ርዕይን ዕዉን ለማድረግና የዕድገትና የልማት ግቦችን ለማሳካት ወሳኝ ነው፡፡ የደቡብ ወሎ ዞን በክልል ደረጃ ወሳኝና ሰፊ ሰራተኛ ሃይል ካላቸዉ ዞኖች አንዱ ነዉ፡፡ የሰዉ ሀብት ልማት ዜጎች አቅማቸዉን እንዲያጎለብቱና በዕለት ተዕለት ኑሯዉና በስራቸዉ ጥቅም ላይ እንድያዉሉ በማድረግ የጎላ ኢኮኖሚዊ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ተሳትፎ እንዲኖራቸዉና ተጠቃሚነታቸዉ እንዲረጋገጥ ያስችላል፡፡ በሌላ በኩል የእድገትና ልማት ግቦችን ለማሳካት እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ተወዳደሪነትን ለማጎልበት እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያሰችል እና የአገልግሎት ጥራትና ተደራሽነት በማረጋገጥ ዜጎች ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አቅም የማሳደግ የተመዘገበዉን እድገት ለማስቀጠል እና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትና የመንግስት ሰራተኞች ወቅቱ የሚጠይቀዉን ብቃት አሟልተዉ እንዲገኙ ለማድረግ በልማታዊ አስተሳሰብ የታነፀ፣ የመልካም አስተዳደር ጥያቄን መመመለስ የሚችል እና ተወዳዳሪ የሆነ የሰዉ ሀብት ለማፍራት በአመለካከቱ፣ በክህሎቱ፣ በእዉቀቱ የበለፀገ፣ ታታሪ፣ ምርታማ እና ተወዳዳሪ የሆነ የመንግስት ሰራተኛ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ተቋማት የረጅምና የመካከለኛ ጊዜ ዕቅዳቸዉን ለመተግበር የሚያስፈልጋቸዉ የሰዉ ሃብት በዓይነት፣ በብዛትና በብቃት ደረጃ ለይተዉ ማቀድ እንዲችሉ የትምህርትና ስልጠና ተገቢነት ጥራት ያለዉ እንዲሆን፣ ለእያንዳዱ የሙያ መስክ እና የአመራር እርከን ዓለም አቀፋዊ ልኬቶችን እና ሀገራዊ፣ ክልላዊና ዞናዊ ፍላጎቶችን ከዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ ስምምነቶችና ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ በሙያ ብቃት ደረጃ እንዲመራ ለማድረግ የሰዉ ሃይል በብቃት ለመጠቀም ጠንካራ ጥርቶች ማድረግ ይገባል፡፡

## ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

- የሰለጠነ የሰዉ ኃይል በሚፈለገዉ ደረጃ አለመኖር፣
- የእውቀት እና የክህሎች ጥራት ችግር፣
- የዞኑን የሰዉ ሃብት በዉጤታማነት መጠቀም አለመቻል፣

## የትኩረት መስኮች

1. የሰዉ ሃብትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ማልማት፣
2. ብቁ፣ በቂ እና ተወዳዳሪ ሰዉ ሀብት ማፍሪያ ተቋማት ግንባታ፣
3. የስራ እድል ፈጠራ፣ የሰዉ ሃብት ፍልሰት እና ስራ አጥነት፣
4. ከዕድገትና ከልማት ግቦች ጋር የተሳሰረ ሰዉ ሃብት ልማት፣

## የትኩረት አቅጣጫዎች

ኢኮኖሚዉ የሚፈልገዉን የሰዉ ኃይል ዓይነት እና መጠን በበቂ ሁኔታ ማፍራት ዋና ቀጣሪ የግል ዘርፍ መሆኑን ማረጋገጥ፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከፍተኛ እና እዉቀትን በተግባር ስልጠና እና በቅጥር ስርዓታቸዉ እንዲያበረታቱ ማድረግ፣ የስልጠና ዓይነት ስምሪት እና ጥራት ከእቅዱ የመዋቅራዊ ለዉጥ አቅጣጫ እና ግቦች ጋር እንዲጣጣም ከዘርፎች ፍላጎት አንፃር በጋራ ማቀድ እና መተግበር፣ የባለ ሶስት ደረጃ የስልጠና ስርዓት ማስፈን (ከፍተኛ የቴክኖሎጅ ሽግግር የማድረግ፣ የቴክኖሎጅ ፈጠራ ሀሳብ የማፍለቅ እና የማበልፀግ ሚና ዝንባሌ ያለው የባለሙያ ግንባታ ትኩረት የሚሰጣቸዉ ይሆናል፡፡

በተጨማሪም የልማት ዘርፎች በእዉቀት እና ክህሎች ይመሩ ዘንድ ስልጠናን ከዘርፎች ልዩ ፍላጎት ጋር በማገጣጠም ስልጠናን ልምድ ከዉጭ ከማሸጋገር ግብ ጋር ማቀናጀት በመንግስት እና በግል ዘርፍ ትብብር የመዋቅራዊ ለዉጥን ተግባር ተኮር ማድረግ፣ የተበታተኑ የተናጠል ስልጠናዎችን በማዕከል መምራት እና መግራት የሚለዉ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸዉ፡፡

**ዓላማ፡- የሰዉ ሀብት ልማቱ ሳይንሳዊ ዘዴዎችንና ሂደቶችን የተከለ፣ ፍትሃዊ፣ ተደራሽ፣ ጥራት ያለዉ በማድረግና ብቁና ተወዳዳሪ ዜጎችን በማፍራት የዞናችንን ህብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል፣**

**ግብ 1፡- ከተለመደዉ የጤና ትርጓሜ በዘለለ በደባል ሱሶች ያልተበረዘ እና ያልቆዘመ እነዲሁም በወንጀል እና ስርዓት አልበኝነት ያልተተበተበ ሰብዓዊ ካፒታል መገንባት፡፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች**

- ለአደንዛዥ ዕፅ፣ ለደባል ሱስ እና ወንጀል ተጋላጭ የሆኑ ሲቪል ሰርቫንቶችን በጥናትና በጥራት መለየት፣

- ከችግሩ ሊያወጡ የሚችሉ አሰራሮችን በመዘርጋት የመፍትሄ እርምጃዎችን እንድወሰዱ ከተቋማት ጋር በቅንጅት መስራት፣

**ግብ 2፡- የዞኑን የሰዉ ኃይል ለልማት በቁጭት እንዲነሳሳ በማነቃቃት፣ በማበረታታት እና በመደገፍ የማምረት አቅሙን ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የሰዉ ኃይሉን አቅም ለማሳደግ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች የረጅም ጊዜ ስልጠና መስጠት (በመመሪያው መሰረት በድምሩ 100 ለሚሆኑ ሰራተኞች)፣
- በየደረጃዉ ባሉ የመንግስት ተቋማት ለሚገኙ 4,500 ለሚሆኑ ሰራተኞች ንቅናቄ በመፍጠር በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ አጫጭር ስልጠና መስጠት፣
- በዉጤታቸዉ የላቀ አፈፃፀም ላሳዩ የመንግስት ሰራተኞች የትምህርት ዕድል በማመቻቸት ማበረታቻ መስጠት፣
- ተቋማት ለሰራተኛዉ እየተሰጡ ያሉ የአጭርና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎችንና ያመጡትን ውጤት በዳሰሳ ጥናት በመለየት ማረጋገጥ፣
- ለሲቪል ሰርቪስ ሪፎርሙ ማስፈፀሚያ የተዘጋጁ ስትራቴጅዎችና መመሪያዎችን ለባለሙያው ማስተዋወቅና መተግበር፣

**ግብ 3፡- የገጠር ሴቶችን በማስተማርና አቅማቸውን በአጫጪር ስልጠናዎች በመገንባት የሴቶችን የስራ ዝግጁነት ምጣኔን ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- ለ32849 የገጠር ስራ ፈላጊ ሴቶች ስለስራ ፈጠራ ግንዛቤ መፍጠር
- 26279 የገጠር ስራ ፈላጊ ሴቶችን የስራ ፈጣሪነት ስልጠና መስጠት
- ለ11298 የገጠር ስራ ፈላጊ ሴቶች የቴክኒካል ክህሎት ስልጠና መስጠት
- ለሴቶች ምቹ የሆነ የኢኮኖሚ አማራጮችን በማቅረብ በኢኮኖው የሚኖራቸውን ሚና ማሳደግ

**ግብ 4፡- በልዩ ልዩ ንቁዑስ ዘርፎች እና ንዑስ-ንዑሳን ዘርፎች የሙያ፣ የቴክኒክ፣ እና ቮኬሽናል ተግባራት ስልጠና እንደየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ የሚሰጥባቸው ማዕከላትን ማደራጀት፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ማዕከላት የሚቋቋሙባቸውን ቦታዎችን እና የስልጠና ዓይነቶችን መለየት
- ማዕከላት እንዲቋቋሙ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር

**ግብ 5፡- አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሰው ኃይል ድርሻ በ2013 ከነበረበት 3.3 በመቶ አገልግሎት ዘርፉን ከ27.7 በመቶ በ2018 ማሳደግ**

**ግብ 6፡- ለዘመናዊ ግብርና፣ አምራች ኢንዱስትሪ፣ ለኮንስትራክሽን እና ለሌሎች ልዩ ልዩ የከተማ እና የገጠር ኢንተርፕራይዞች የሚሆን የሰው ኃይል አቅም መፍጠር**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለየዘርፉ የሚመጥን የሰው ኃይል ፍላጎትን በመለየት ማሰልጠን

**ግብ 7፡- በዞኑ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች አጫጭር ተግባር ተኮር ስልጠናዎን በግብርና፣ በአገልግሎት፣ በአነስተኛ አምራች ዘርፎች፣ ወዘተ በስፋት በመስጠት ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- አሁን ያሉት 15 የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ወደ 16 እንዲሁም የአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያዎችን ከ42 ወደ 52 በማሳደግና ግብዓት በማሟላት የስልጠና ጥራትንና የኢንተርፕራይዞችን አገልግሎት ተጠቃሚነት ማሻሻል፡
- 10548 መደበኛ እና 141382 በአጫጭር ስልጠና ሰልጣኞችን በመቀበል ማሰልጠን
    - ✓ ለአርሶ አደሩ በመስኖ አጠቃቀምና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ አጫጭር ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን መስጠት
    - ✓ ከእርሻ ስራ ውጭ በሆኑ የገቢ ማመንጫ ዘርፎች የአርሶ አደሩን ገቢ ማሳደግ እንዲቻል የሚያግዙ የተለያዩ አጫጭር ስልጠናዎችን መስጠት
    - ✓ ለጎልማሶች ትምህርት የበቁ አርሶ አደሮች የተለያዩ ሙያዊ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ማደረግ፣
    - ✓ የዞኑ የወጣት ብዛት ታሳቢ ያደረገ አጫጭርና መከከለኛ ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን በመስጠትና የዕድል መስኮቱን (Demographic Dividend) በመጠቀም ትኩረት በሚሰጣቸው በአሻጋሪና በዘላቂ የልማት ዘርፎች ማሰማራት፣
    - ✓ ትኩረት በሚሹ ሙያዎች የሴት ሰልጣኞች ተሳትፎ 20 በመቶ እንዲሆን ማድረግ
    - ✓ 573 (20 በመቶ) ነባር ሰልጣኞች የብሌንድ ለርኒግ (ቅይጥ ስልጠን) ስልጠና ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
    - ✓ በመደበኛ መርሃ-ግብር ወደ ቴክኒክ ሙያ የሚገቡ ነባር ሰልጣኞች ቁጥር በመንግስት 825 በግል 740 በድምር 1565 ፣ የአዲስ ሰልጣኞችን ቁጥር በመንግስትና በግል ኮሌጆች አዲስ ሰልጣኝ ቅበላ 8983 ሰልጣኞችን ተቀብሎ ማሰልጠን

- ✓ በአጫጭር ስልጠና በኢንተርፕርነርሽፕ 96,875 እና በቴክኒካል 22,646 ዕራ ፈላጊዎችን በማሰልጠን ከእነዚህ መካከል ለ20800 ከስደት ተመላሾች የአጫጭር ስልጠና መስጠት
- ✓ 15 የሚሆኑ ኮሌጆች ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት ምቹ እንዲሆኑ በማድረግ 100% ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሰልጣኞች አጫጭር ስልጠናዎችን ማሰልጠን፣

**ግብ 8፡- የመንግስት ተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ ዉጤታማነትን ከ75 በመቶ ወደ 80 በመቶ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በየደረጃዉ የሚገኙ 725 የመንግስት ተቋማት የዜጎች ቻርተር በማዘጋጀት በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- በዞናችን የሚገኙ 725 የመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥና መረጃ አያያዛቸዉን በቴክኖሎጂ የታገዘ በማድረግ እየተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- በየደረጃዉ የሚገኙ የመንግስት ተቋማት በአገልግሎት አሰጣጡ ያሉ የመልካም አስደተዳደር ችግሮችን በመለየትና በማቀድ 100% ተገቢ ምላሽ እየሰጡ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- በየደረጃዉ የሚገኙ የመንግስት ተቋማት በተገልጋዮቹ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች /አቤቱታዎች/ 100% ምላሽ እየሰጡ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ተቋማዊ የስራ አካባቢ ስነ-ምኞት /ኤርጎኖሚ/ሪኢኖቬሽን/ ስራዎችን 100% ማከናወን፣

**ግብ 9፡- በሲቪል ሰርቪስ ተቋም ለ800፣ (በሁሉም 300 ሴቶች፣ 400 ወጣት ስራ ፈላጊዎች እና 12 አካል ጉዳተኞች እንዲሁም ሌሎች ይሆናሉ)**

## የማስፈፀሚያ ስልቶች

የሰው ሀይል ልማት ዓላማዎችና ግቦች ለማሳካት በየጊዜው የሚደረጉ የዳሰሳ ጥናቶችን መሰረት በማድረግ የዞኑን የልማት ፍላጎት የሚያሟሉ የስልጠና አጀንዳዎችን የመለየት ስራ የሚሰራ ሲሆን በተለዩ የስልጠና መስኮች ስልጠና የሚሰጡ ተቋት በመቀናጀት የዞኑን የሰው ኃይል በማሰልጠን ተገቢውን ተግባር ተኮር እውቀትና ክህሎት የማስጨበጥ ስልት በመንደፍ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ እንድሁም ለሰራተኞች ስለ ስራ ምነነት፣ የስራ ባህል፣ ተነሳሽነት እና ስለ ስራ ፈጣሪነት የአመለካከት ለውጥ እንዳመጡ አስፈላጊውን የስልጠናና የማማከር አገልግሎት መስጠት፣ በሰው ሀብት ልማቱ የሰለጠነውን የሰው ሀይል የስራ ስምሪት በሁሉም ዘርፎች በአግባቡ እንድያዝ ለሚመለከታቸው አካላት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠትና መደገፍ እንድሁም በተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ውስጥ የተካታቱ የሰው ሀብት ልማት ስራዎችን በመተባበር ረገድ ያሉትን ክፍተቶችና ተግዳሮቶች መገምገምና መለየት የሚሉት ስልቶች ተቀምጠዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከሰው ሀብት ልማት ጋር በተገናኘ ተግባር ተኮር እና ችግር ፈች ምርምሮችን እና ጥናቶችን በማካሄድ በግኝቶቹ መሰረት የማሻሻያ እርምጃዎችን በዞን ደረጃ የመውሰድ፣ በሌለች አጎራባች ዞኖች እንደሁም በክልሉ በሰው ሀብት ልማት ዙሪያ ያሉ ተሞክሮዎችን በመቀመር ከዞኑ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ተግባራዊ የሚሆንበትን ስልት የመከተል፣ የስልጠና ተቋማት ጥራት የሚፈተሸበት ሁኔታ በመዘርጋት፣ በማዘመንና በመገምገም የማሻሻያ ሀሳቦችን አደራጅቶ ግብዓት መስጠት፣ የቴክኖሎጅና ኢኖቬሽን ልማት የሚከናወንበት አደረጃጀት በመፍጠር ተግባራዊ የማድረግ እንድሁም የሰው ሀብት ልማቱ ቀልጣፋና ውጤታማ እንደሆን የሰው ሀብት ልማት መረጃን ዲጅታላይዝ የማድረግ ስልቶች ተነድፈዋል፡፡

በሲቪል ሰርቪስ ፖሊሲ የተያዙ የሪፎርም ፕሮግራሞችን ከዞናችን ነባራዊ ሁኔታ ሁኔታ አኳያ የሚተገበሩበትን ስልት መንደፍ፣ የብቃት ማዕቀፍ ትግበራን ትኩረት በመስጠት የሲቪል ሰርቪሱን የስራ ስምሪት ማካሄድ፣ በሚሰጡ የሰው ሀብት ልማት ስልጠናዎች ለሴቶች ልዩ ትኩረት በመስጥት ማብቃት፣ የሰው ሀብት ልማት ስራ ዓመታዊ ዕቅድ እንድዘጋጅ ማድረግና በየጊዜው ክትትልና ግምገማ በማድረግ የሰው ሀብት ልማት እቅድ በሁሉም ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች በጥራት ታቅዶ እንድተገበር ድጋፍና ክትትል ማድረግ የበጀት አመቱ የዘርፍ ማስፈፀሚያ ተጨማሪ ስልቶች ሆነው ተቀምጠዋል፡፡

## 3.3. ቴክኖሎጅ

ሀገራት ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽንን በመጠቀም የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገትን ፈጣን፣ ቀጣይነት ያለው እና ተወዳዳሪ ማድረግ እንደቻሉ የዕድገት ታሪካቸው ያሳያል፡፡ በቅርብ ዓመታት ውስጥ አስደናቂና ፈጣን እድገት ያስመዘገቡት የደቡብ ምሥራቅ እስያ ሀገራት ስኬት ዋናው ምክንያት ሀገራቱ የቴክኖሎጅ እውቀትና ክህሎትን በመጠቀም ገበያ መር ኢኮኖሚን መገንባታቸውና የቴክኖሎጅ አቅም ማካበታቸው መሆኑ እንዱ ማሳያ ነው፡፡

በመሆኑም ሳይንስ፤ ቴክኖሎጅ እና ኢኖቬሽን ለዞኑ  መዋቅራዊ የኢኮኖሚ እድገት እና ሽግግር ለማምጣትም ሆነ እድግቱን ቀጣይ ለማድረግ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ለእድገቱና ለሽግግሩ መሳካት ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጅ እንደ ወሳኝ የማስፈጸሚያ መሳሪያ ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ ነው፡ ፡ በዚሁ መነሻነት ለአዳዲስ ለውጦች እና ፍላጎቶች ምላሽ መስጠት የሚችል የሳይንስ፣ ቴክኖሎጅና

ኢኖቬሽን ስትራቴጅያዊ ጉዳይ እና የትኩረት መስክ የተለዩ ሲሆን ዓላማና ግቦችን ለማሳካት ርብርብ ማድረግ የሚገባ በመሆኑ ይህ እቅድ በአጭሩ ተዘጋጅቷል፡፡

ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች

- አስተማማኝ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ውስንነት
- በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት
- የሲስተም ልማትና አውቶሜሽን ውስንነት
- የቴክኖሎጅ ቁጥጥር ስርዓት በሚጠበቀው ልክ አለመዘርጋት
- ፈጠራን መህበረሰባዊ ባህል የማድረግ ውስንነት

የትኩረት መሰኮች

- የቴክኖ-ጅ መሰረተ ልማት
- አቅም ግንባታ
- የቴክኖሎጅ ባለቤትነት እና የህግ ማዕቀፍ ላይ ለተግባራዊነት መትጋት

የትኩረት አቅጣጫዎች

ብቁ የሰው ኃይል እና የተቋም አቅም ግንባታ፣ ሁለንተናዊ የትብብር' ትስስር እና ቅንጅት አቅምን ማሳደግ፤ ምቹ የኢኖቬሽን ስነ-ምህዳርን ሽፋንን ማሳደግ፤ ደረጃቸውን የተጠበቁ መሰረተ ልማቶችን መዘርጋት፤ ቴክኖሎጅን ማበልጸግ፣ ማላመድ እና ማሸጋገር እንዲሁም የተቀናጀ እና ተናባቢ የሆነ የአሰራር ስርዓት ማጎልበት የሚሉት በበጀት ዓመቱ የዘርፉ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ፡

ዓላማ፡-

በማሽን ቴክኖሎጂ በተለይም በፋብሪካ ምህንድስና፥ በአማራጭ ሃይል አቅርቦት በተለይም በኤሌክትሮ መካኒካልና አማራጭ የሃይል ቴክኖሎጂ፣ በስትራቴጂያዊ ግብዓት በተለይም በስትራቴጂካዊ ማዕድናት ልማት ቴክኖሎጂ! በዘረ-መል ቴክኖሎጂ እንዲሁም በኦቶሜሽን በተለይም በዲጂታል ቴክኖሎጂ የበቃ

የሠው ሃይል ዝግጅት ማድረግና ለቴክኖሎጂ መሠረት የሚሆን በቴክኖሎጂ የሚያምን በሣይንሳዊ ዕውቀት የበለፀገ ትውልድ መፍጠር፤

**ዋና ዋና ግቦች**

**ግብ 1፡- በማሽን፤ በግብዓት፡ በኃይል እና በኦቶሜሽን ዝግጅት ማድረግ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 1 ማንዋል በማዘጋጀት ጽንሰ-ሀሳቡን በሚገባ መረዳት፣
- አደረጃጀት መፍጠር፣
- በቅንጅት መስራት፣

**ግብ 2፡- በኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ፣ በሲስተም ልማትና በሳይበር ደህንነት ዘርፍ ተወዳዳሪና ብቁ የሰው ኃይል መገንባት፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለዞን ተቋማት ICT ባለሙያና አመራሮች ለ120 ሰዉ ከትምህርት ተቋማት ጋር በመቀናጀት አጫጭር ስልጠናዎችን መስጠት፤
- 800 ዜጎች የተለያዩ ስርዓቶች በኢትዮ ኮደርስ (Online platforms, simulation software, e-learning platforms, mobile learning apps, AI powered educational tools....)

በማስፋፊት በዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ እና ቴክኖሎጂ ትራንስፎርሜሽን ተወዳዳሪነት አቅም ማሳደግ፣

- አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ እና ከወረዳ የአይቲ ማእከሎች ጋር በመቀናጀት አጫጭር ስልጠና መስጠትና ማገዝ፣

**ግብ 3፡- የማምረት አቅምን የሚያሳድጉ የቴክኖሎጅ ውጤቶችን በማሸገርና በማላመድ በአምራችና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት መካከል በቴክኖሎጅ የታገዘ ትስስር መፍጠር!**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 1 የአምራች ኢንዱስትሪዎችንና አገልግሎት ስጪ ተቋማትን በቴክኖሎጅ የታገዝ ትስስር መፍጠር የሚያስችል ሲስተም በማበልጸግ ስራ ላይ ማዋል፤

**ግብ 4፡- የዞኑን ልማት ሊያፋጥኑ የሚችሉ የቴክኖሎጅዎች ፈጠራ ላይ በማተኮር በዞኑ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸውን መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች አሰራራቸውን ማዘመን፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- መቶ በመቶ በተመረጡ የልማት ዘርፎች ላይ ትኩረት በማድረግ በተለይም መካከለኛ ኢንዱስትሪውን ሊያሳድጉ የሚችሉ የቴክኖሎጅ ፈጠራዎች ላይ የስልጠና እና የሙያ ድጋፍ ማድረግ፣

**ግብ 5፡- የቴክኖሎጅ ማእከላት ለመገንባት አቅም እስከሚገኝ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችን በመጠቀም እና ከዚሁ ወስጥ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸዉን ወጣቶች በመለየት የፈጠራና የምርምር ስራዎቻዉን እንዲያጎለብቱ መደገፍ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዘርፉ ልዩ ተስጥዖ ያላቸውን ተሳታፊዎች መለየትና ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ 2 ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ጋር በመቀናጀት መደገፍ፤
- በ1 በዞናችን የመንግስት አይሲቲ ተቋም የቴክኖሎጅ እውቀቶችን የመማር ማስተማር (knowledge café) ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፤
- በቁጥር 29 የሚደርሱ ት/ቤቶች ላይ በፓይለት ደረጃ የትምህርት መዋቅርን በመጠቀም የሳይንስና ፈጠራ ክበባትን በመቋቋም ተሰጥዖ ያላቸውን ታዳጊዎች ማበረታታትና ፈጠራቸው የሚበለጽግበትንና ጥቅም ላይየሚውልበትን መንገድ ማመቻቸት፤

- 3 በሰርቶ ማሳያ ማዕከል እና በሌሎች ማዕከላት የስልጠና እድሎችን በተለያዩ ፕላትፎርሞች (E-learning, virtual, AI learning path) ተደራሽ በማድረግ በዞናችን ቀጣይ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር እንዲኖር ማስቻል፣

**ግብ 6፡- ግብርናውን እና አምራች ኢንዱስትሪውን በማዘመን ምርትን የሚያሳድጉ እና አገልግሎትን የሚያሳልጡ የማሽን ቴክኖሎጅዎች በመምረጥ ማላመድ!**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 1 ችግር ፈች የጥናትና የምርምር ስራ መስራት፤
- ከግብርና ጋር በመቀናጀት 2 ዘመናዊ ግብርናን ለማምጣት የሚያግዙና በቀላሉ ተደራሽ ሊሆኑ የሚችሉ በተለይም የቅድመ ምርት፣ የድህረ ምርት፤ የአፈር ለምነት ማሻሻያ፤ የመስኖ፣ የእንሰሳትና እጽዋት ዝርያ፤ የተሻሻሉ የቴክኖሎጅ ፈጠራ ላይ መሰረት አድርጎ መስራት፤

**ግብ 7- በዞናችን የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ቅልጥፍናንና ውጤታማነትን ሊያረጋግጡ የሚያስችሉ የፋይናንስ ቴክኖሎጅ ውጤቶችን ማላመድ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የመንግስት ተቋማትን የክፍያ ስርዓቶች የዲጅታል ስርዓትን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲያደርጉ በቴክኖሎጅ መደገፍ የሚያስችል 1 ጥናት ማካሄድ፣

**ግብ 8፡- የዞናችንን ከተሞች ስማርት/ዘመናዊ ለማድረግ በትራንስፖርት ትስስር፣ በውሃ አቅርቦት፣ በቆሻሻ አወጋገድ፣ ለመሬትና ሌሎች ሃብቶች አስተዳደርና ለኃይል ቁጠባ የሚያግዙ ቴክኖሎጅዎችን መፍጠር!**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 1 የኃይል አማራጭ ቴክኖሎጅ መምረጥና ማሸጋገር፣
- ለ1 የስማርት ሲቲ ከኮሪደር ልማት ግንባታ ጋር በተያያዘ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣

**ግብ 9፡- የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ ሲስተሞችን ማልማትና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረግ!**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- አገልግሎትን የሚያዘምኑ 2 የተለያዩ ሲስተሞችን ማልማትና 2 ሲስተሞችን ማሸጋገር፤
- ለ1 ተቋማት የሶፍትዌር ልማት የማማከር አገልግሎት መስጠት፤

- አዲስ እና ነባር የቴክኖሎጅ እውቀቶችን በዳታ ቤዝ ማደራጀት፣

**ግብ 10፡- የቴክኖሎጂ ፈጠራ ላይ ያተኮሩ ዓመታዊ የቴክኖሎጅ ኤክስፖዎችን በማዘጋጀት ፈጣሪዎችን ማበረታታትና የማህበረሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ተጠቃሚ ማድረግ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 1 የቴክኖሎጅ ማስተዋወቂያ ኤግዚቢሽን ማዘጋጀት እንዲሁም 1 የቴክኖሎጅ ፎረም ማዘጋጀት
- በአገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ የቴክኖሎጅ አውደ ርዕዮች ላይ ለመሳተፍ ራስን ብቁ ማድረግ፣

**ግብ 11- የዘርፉን ዕድገት ተከትሎ የሚከሰቱ ሁነቶችን በህግ ማዕቀፍ መምራት፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የግል ዘርፉን ለማበረታታት እና የዘርፉን መሪ ሚና ለማጎልበት 1 የአሰራር ስርዓት እና የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣
- 2 ሀብት የሚያስገኝ ፕሮፖዛል ማዘጋጀት፣

**ግብ 12፡- በቁጥር ለ74 (50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በማህበረሰብ አቀፍ የመረጃ ማዕከላት የስራ ዕድል መፍጠር፣
- በስታርታፕ እና ተያያዥ አቅሞች ዙሪያ ለ4 ኢንተርኘራይዞች የስራ ዕድል መፍጠር፣

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

በተግባር ስልጠና የሚደገፍ ብዙሃን ወጣቶችን ያማከለ ሰፊ የፋብሪኬሽን ኢንጂነሪንግ እና ኢኖቬሽን ንቅናቄ የመፍጠር፣ በከፍተኛ ልዩ የንድፈ-ሃሳብ እና የተግባር ስልጠና፣ የኢንዱስትሪዎች ምርምር እና ልማት (research and development) የሚደገፍ የረቀቀ ቴክኖሎጂዎች ሽግግር መሠረት የመጣል፤ የዲጂታላይዜሽን ተወዳዳሪነት ማበልጸጊያ ማዕከል እና የአይቲ ኢንዱስትሪ ልማት የማስፋፋት አቅጣጫዎችን መከተል፣ ቴክኖሎጂን እና ስልጠናን ከተጨበጠ የኢንዱስትሪያላይዜሽን ግብ እና ከፕሮጀክቶች ጋርበማስተሳሰር ተተግባሪነቱን ማረጋገጥ፣ የሣይንስ ትምህርትን ከተግባር ጋር በሚያስተሳስር፣ ችግር ፈቺነትን ማዕከል ባደረገ ንቅናቄ የማሕበረሰብ ባሕል አካል እንዲሆን ንቅናቄ መፍጠር እንዲሁም በዋናነት የሜካናይዜሽን፤ የኃይል፤ የግብዓት፣ የኦቶሜሽን (ዲጂታላይዜሽን)

ቴክኖሎጂዎችን እና ለዚህ ቴክኖሎጂ ሕዝባዊ መሠረት መጣል የሚሉት ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ሆነው ተለይተዋል፡፡

## 3.4. መሰረተ ልማት

መሠረተ-ልማት ለዕድገት እና ልማት ሦስት እጥፍ ዕድል እንደሚሰጥ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በመሠረተ ልማት ዝርጋታ ወቅት ዜጎች ተቀጥረው ገቢ ያገኛሉ፤ በሚፈጠረውም የፍላጎት ማደግ እንደ ግብርና እና አምራች ኢንደስትሪ ያሉ አምራች ዘርፎች እንድሁም የአገልግሎት ዘርፎች በአጸፋው እንድነቃቁ ያደርጋል፡፡ በተለይም የኢኮኖሚ መሠረተ-ልማት ሲስፋፋ መነሻው ምርት እና ምርታመነትን መጨመር በመሆኑ የእነዚህ አቅሞች መገንባት የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰትን በመጨመር የተገነቡ እና የሚገነቡ የኢኮኖሚ ተቋማት ምርታማነት እንድጨመር ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ኢንፎርሜሽን እና ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጅ ዓይነቶቹ የመሠረተ-ልማት አውታሮች በአዳጊ እና ተለዋዋጭ ቴክኖሎጂ የሚመሩ በመሆናቸው በድጂታላይዜሽን ከታገዘ ዘመናዊ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ (e-Governance) እስከ ዘመናዊ የፋይናንስ አገልግሎት (FinTech) የሚደርሱ የማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴዎችን በማሳለጥ ምርታማነት እንድያድግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ፡፡ በሌላ በኩል የውሃ እና ኃይል፣ የመስኖ፣ የመንገድ እና ሎጂስቲክስ አገልግሎት፣ ፈጣን የግብርና ልማት ሲታሰብ የመስኖ ልማት፣ ምርትን ከማሳ ወደ ገበያ ለማጓጓዝ የሚያግዙ መንገዶች፣ ለግብርና ሜካናይዜሽን የሚውሉ ማሽኖች በቀላሉ ወደ ማሳ የሚደርሱበት አማካይ የማሳ ውስጥ መንገድ፣ ለእንስሳት ሀብት ልማት የሚውል የውሃ፣ የእንስሳት ጤና እና የኳራንቲን አገልግሎት ማሳለጫ፣ በኮመርሻል ግብርና የተመረቱ የኢንደስትሪ ግብዓቶች እና የወጪ ንግድ ምርቶች፣ ከውጭ የሚገቡ የግብርና እና የኢንደስትሪ ግብዓቶች፣ እንድሁም የአምራች ኢንደስትሪ ምርቶች ዞኑን ከሌሎች ዞኖች እንድሁም ከወደብ በአቋራጭ ርቀት የሚያገናኙ መንገዶች እና የባቡር ሃድድ ልማቶች፣ የማይቆራረጥ እና በቂ የኃይል አቅርቦት ለታቀደው የአምራች ኢንደስትሪ ልማት እና ዘመናዊ ግብርና፣ የዘላቂ ከተማ ልማት እንድሁም የገጠር ትራንስፎርሜሽን ወሳኙ መሠረተ-ልማት በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## ስትራቴጅክ ጉዳዮች

- የተቀናጀና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ አለመሆን
- የፍትሃዊነትና የተደራሽነት ችግር
- የቅልጥፍናና ውጤታማነት ችግር
- የመፈጸምና የማስፈፀም አቅም ውስንነት

## የትኩረት መስኮች

1. የመሰረተ ልማት ጥራት፣ ፍትሃዊነት፣ ተደራሽነትና ዘላቂነት
2. የመሰረተ ልማት ቁጥጥርና ክትትል ስርዓት
3. አማራጭ የኢነርጅ አቅርቦት
4. የመሰተረ ልማት የቴክኖሎጂ አቅርቦት
5. የህብረተሰብና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ

## የትኩረት አቅጣጫዎች

የመሠረተ ልማት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት እና ጥራት ማረጋገጥ፣ ቅልጥፍናን እና ውጤታማነትን ማሳደግ፣ የግል ባለሃብቱና ህብረተሰቡ በዘርፍ ላይ ያለውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ የፋይናንስ አቅምን ማሳደግ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራር መዘርጋት፣ ችግር ፈቺ የሆነ የክትትል፣ ግምገማና ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፣ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች የአየር ንብረት ለውጥን ግምት ውስጥ ያስገቡ እንድሆኑ ማድረግ እንድሁም የአካባቢ አየር ንብረትን በዘላቂነት ለመጠበቅ ታዳሽ ኢነርጂዎችን በስፋት መጠቀም፣ የልማት ኮሪደሮችን እምቅ አቅም ማዕከል ያደረገ የመስኖ መሰረተ ልማት አቅርቦትን ማረጋገጥ፣ የመንግስት ወጪን ሊቆጥቡ የሚችሉ ቴክኖሎጅዎችን ጥቅም ላይ እንድውሉ ማድረግ፣ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ጥናት፣ ምርምርና ስልጠናን የሚያስተባብርና የሚመራ ጠንካራ ዞናዊ ተቋም ለማቋቋም ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንቶች መረጃ ላይ የተመሰረተ እንድሆን ማድረግ፣ ምቹ የኢኖቬሽን ስነ-ምህዳርን ማስፋት፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የቴክኖሎጅ መሰረተ ልማቶችን መዘርጋት፣ የቴክኖሎጅ ማበልጸግ፣ ማላመድ እና ማሸጋገር የመሰረተ ልማት ዘርፉ ሰፊ ቀጣይነት ያለው፣ ምርታማ የሆነ ፍትሃዊ ገቢ የሚፈጥር፣ የስራ ዕድል እንድፈጥር ማድረግ እንድሁም የዘርፉን የመፈፀምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ የዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች ሆነው ተለይተዋል፡፡

**ዓላማ፡- የመሠረተ ልማቱን የተቀናጀ፣ ፍትሃዊ እና ተደራሽ በማድረግ አገልግሎቱ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ አስተማማኝና ጥራት ያለው እንድሆን ማድረግ፤**

**ግብ 1፡- በዞኑ ውስጥ በተለያየ ዘርፍ የወደሙ መሰረተ-ልማቶችን መልሶ መጠገንና መገንባት**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- ውድመት የደረሰባቸውን አካባቢዎችና ተቋማት የመለየት ስራ መስራት
- የተቋማትን የጉዳት ደረጃ መለየትና መጠገን

**ግብ 2፡- አጠቃላይ የዞኑን የመንገድ ሽፋን በ2017 ከደረሰበት 3897.54 ኪ/ሜትር በ2018 በጀት ዓመት 119.01 ኪ/ሜ በመገንባት ወደ 4013.55 ኪ/ሜትር ማሳደግ፡፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- በወረዳ አስተዳደር መ/ቤት እና በህበረተሰብ ተሳትፎ በጀት 40 ኪ/ሜ አድስ መንገድ መገንባት፣
- ገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ኮርኬ አቤት ውሃ ጋስጫ ግንደወይን መገንጠያ መንገድ ፕሮጀክት ላይ 10 ኪ/ሜ አድስ መንገድ መገንበት፣
- በገጠር ትስስርና ተደራሽነት ፕሮግራም በታቀፉ ወረዳዎች በበ2017 በጀት አመት ያልተሰራውን አድስ መንገድ ጨምሮ 11 የመንገድ ፕሮጀክቶች 83 ኪ/ሜ መንገድ ግንባታ፤ 5 ተንጠልጣይ ድልድይ፣10 ስፔሻል ስትራክቸር ግንባታ ግንባታ ማካሄድ፣
- የመንገድ ጥግግትን በ1000 ካሬ ኪ/ሜትር በ2017 ከደረሰበት 210.02 ኪ/ሜትር በ2018 በጀት አመት ወደ 212.71 ማድረስ፣
- የመንገድ ጥግግት በ1000 ህዝብ በ2017 ከደረሰበት 1.289 ኪ/ሜትር በ2018 በጀት አመት ወደ 1.305 ኪ/ሜትር ማድረስ፣
- በበጀት አመቱ በክልሉ ካፒታል በጀት አንድ(!) ኮንክሬት ደልድይ እና ሁለት (2) ጠተልጣይ ድልድይ መገንባት፣
- በወሎ ጥገና ፅ/ቤት በመንገድ ፈንድ የበጀት ድጋፍ በወቅታዊ 117.11 ኪ/ሜ፤ መደበኛ ጥገና 835.89 ኪ/ሜ (መደበኛ በመሳሪያ 584.29 ኪ/ሜ፤ መደበኛ በሰው ሃይል 251.6 ኪ/ሜ) በድምሩ 953 ኪ/ሜ መንገ ድን ጥራቱን ጠብቆ መጠገን፣
- በወረዳ አስተዳድር መ/ቤትና በህብረተሰቡ ተሳትፎ በጀት 1350 ኪ/ሜ (225 በማሽንና 1125 በሰው ሃይል) መንገ ድ መጠገን፤
- 5 የተለያየ አይነ ትና መጠን ያላቸውን ስትራክቸሮች መጠገን፣
- በፌደራል መንገዶች አስተዳደር 200 ኪ/ሜ የአስፓልት እና የጠጠር መንገድ እንዲጠገን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- በገጠር ትስስር ምግብ ዋስተና ፕሮግራም 75 ኪ/ሜ መንገደ መጠግን፣

**ግብ 3፡- የተለያዩ የትራንስፖርት መሰረተ- ልማቶችን ቁጥር ከ 0 ወደ 1 ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የተጀመረውን የገራዶ ትራፊክ ኮምፕሌክስ ግንባታ ማጠናቀቅ
- በ 1 ደረጃ ሶስት በ ከተሞች የህዝብ መናኸሪያ መገንባት፣

**ግብ 4- የነባር አውሮኘላን ማረፊያዎች ደረጃቸው እንዲያድግ ከፌደራል መንግስት ጋር በትብብር መስራት ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግበራት**

- 1 ነባር ኤርፖርቶች ( መካነ ሰላም ) አገልግሎት እንድጀምር ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

**ግብ 5፡- ከፌደራል መንግስት ጋር በጋራ በመስራት የክልሉን የባቡር መንገድ ግንባታ በ2017 በጀት ዓመት ከደረሰበት 335 ኪ.ሜ በ2018 ወደ 350 ኪ.ሜ ማድረስ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ከፌደራልና ከክልል ጋር በመናበብ እንደ ደቡብ ወሎ ዞን የባቡር መንገዱ በሚያልፍባቸዉ ወረዳና ከተሞቻችን ለግንባታው አስፈላጊውን ትብብርና ድጋፍ ማድረግ፣

**ግብ 6፡- የብልሽት ምጣኔን በ2017 ከነበረበት 23.78% በዕቅድ ዘመኑ 3.83% በመቀነስ ወደ19.99% ዝቅ በማድረግ፤የውሃ ብክነት በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 16.23% በዕቅድ ዘመኑ በ1.06% በመቀነስ ወደ 15.24% ዝቅ በማድረግ፣ዞናዊ የመጠጥ ውሀ ሽፋንን ከ2017 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት 70.5% በዕቅድ ዘመኑ1.25% በማሳደግ 71.15% ማድረስ፡፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 179 አነስተኛ የውሀ ተቋማት ግንባታ ማከናወን
- 1 ቀበሌ አገናኝ የውሃ ተቋማት መገንባት
- 4 መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ መገንባት
- 2 ጥልቅ ገድጓድ መገንባት
- 4 የከተሞች የመጠጥ ውሃ ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን መገንባት
- 451 ቀበሌዎችን ተጠቃሚ ማድረግ፤

**ግብ 7፡- በ2018 በጀት አመት 12 የተለያዩ ግንባታዎችን በመገንባት የከተማን ስነ-ንፅህና ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋናዋማ ተግባራት**

- 11 የህዝብ መፀዳጃቤቶችን መገንባት
- 1 የህዝብ መፀዳጃ ቤት መጠገን

**ግብ 8፡- የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን ሽፋን በ2017 ዓ.ም ከተደረሰበት 65.28% በዕቅድ ዘመኑ 3.2% በማሳደግ በ2018 ወደ 68.48% ማድረስ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 8000 በሶላር ማሾዎች ስርጭት (solar lantems) ለህብረተሰቡ ማሠራጨት
- 5005 የቤተሰብ ሶላር ሆም ሲስተም ተጠቃሚ ማድረግ (solar home system)

- 35,000 የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን በሰለጠኑ አምራቾችን ማስመረትና ማሰራጨት
- 345 የቤተሰብ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂዎችን በግንበኞች ማስገንባት፣

**ግብ 9 ፡- በበጀት ዓመቱ የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታን በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 476 ወደ 491 በማሳደግ የሚለማውን መሬት ከ19,172.55 ሄ/ር ወደ 19,800.55 ሄ/ር ማድረስ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በበጀት ዓመት 2 ነባር አነስተኛ መስኖ ፕሮጀክቶችን ግንባታ በማጠናቀቅ 78 ሄ/ር ማልማት፣
- 8 አድስ አነስተኛ ፕሮጀክቶች ግንባታ በመገንባት 550 ሄ/ር ማልማት፣
- በክልል መንግስት የተጀመሩ 5 መካከለኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ እንዲጠናቀቁ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣
- 26 የመስኖ ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይን ስራዎች በማጠናቀቅ ወደ ግንባታ እንድገቡ ማድረግ፣
- 2 የመስኖ ተቋማትን የጥገና ስራ ዘመናዊ የመስኖ አውታር ጥገና ማከናወን፣

**ግብ 10፡- አንደ ዞን የተደራጀ የቴክኖሎጅ ኢኖቬሽን ፓርክ እና 11 ልዩ ልዩ የቴክኖልጂ ማዕከላትን መገንባትና ደረጃቸውን ማሻሻል፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 2 ተቋማት አዲስ የቴክኖልጅ መሰረተ ልማት የሚዘረጋላቸው ይሆናል
- 1 ስማርት ከተማ፣3 የቴክ-እስታርታፕ ማዕከላትን ማደራጀት፣
- 8 አዲስ የወረዳኔት ማዕከላት ማጠናከር፣
- 1 የማህበረሰብ ቴክኖልጅ መረጃ ማዕከላት መገንባት፣
- 1 የወጣቶች ሳይንስ ካፌዎች መገንባት፣
- የፍትህ ስርዓቱን አገልግሎት ለማሻሻል የሚዘምኑ 2 ነባር የወረዳኔት ማዕከላትን ማሳደግ፣

**ግብ 11፡- በዞን የቴሌኮም መሰረተ ልማት ሽፋንን ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የስልክ ኔትዎርክ ሽፋንን ከ68 ፐርሰን ወደ 75 ፐርሰንት ማሳደግ፣
- የሞባይል ጣቢያዎች አቅምና ደረጃን ማሻሻል፣
- የኢንተርኔት አገልግሎትን ማሻሻል፣
- 5G የሞባይል ኢንተርኔትን ማስፋፋት፣

**ግብ 12፡- የትምህርት ቤቶች ቁጥር በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1387 ወደ 1422 ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- የተገነቡ አዲስ ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በቁጥር በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 6 በ2018 በጀት ዓመት 11 ሆኗል፣
- የተገነቡ አዲስ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በቁጥር በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 2 በ2018 በጀት ዓመት 33 ሆኗል፣
- የተገነቡ አዲስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በቁጥር በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1 በ2018 በጀት ዓመት 1 ሆኗል፣
- በነባር ቅድመ አንደኛ ፣አንደኛና መካከለኛ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ 301 ተጨማሪ ክፍል መገንባት፡፡

**ግብ 13፡- በትምህርት ቤቶች የትምህርት ፋሲሊቲ ማሟላት**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- ደረጃውን የጠበቀ የመፀዳጃ ቤት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 548 በቁጥር ወደ 787 ማሳደግ፣
- ደረጃውን የጠበቀ የመፀዳጃ ቤት ያላቸው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶ ብዛት ከነበረበት 59 በቁጥር ወደ 68 ከፍ ማድረግ፣
- ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት ከነበረበት 489 በቁጥር ወደ 666 ከፍ ማድረግ፣
- ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት ከነበረበት በቁጥር 56ወደ 68 በመቶ ከፍ ማድረግ፣
- ደረጃውን የጠበቀ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ያላቸው አንደኛና መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት ከነበረበት 202 በቁጥር ወደ 539 ከፍ ማድረግ፣
- የኤሌክትሪክ ሽፋን ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት በመቶኛ በ2017 ከነበረበት 25.3% በ2018 በጀት ዓመት 27% ላይ ነው
- የተደራጀ ኮምፒተር ላቦራቶሪ ያለቸው በመለስተኛ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህት ቤቶች በመቶኛ በ2017 ከነበረበት 5% በ2018 በጀት ዓመት 6% ላይ ነው፤
- የሣይንስ ክፍል ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት ከነበረበት 607 በቁጥር ወደ 727 ከፍ ማድረግ፣

- በሶስቱም የትምህር አይነቶች የሳይንስ ላብራቶሪ የተሟላላቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት ከነበረበት 46 በቁጥር ወደ 54 ከፍ ማድረግ፣

**ግብ 14፡ የጤና ተቋማትን ማስፋፋት**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በግንባታ ላይ ያሉ 2 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎችን ማጠናቀቅ (ለገሂዳ፣ መ/ሳይንት) ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ቁጥር ከ 9 ወደ 11 ማድረስ
- በግንባታ ላይ ያሉ ሁለት የእናቶችና ህጻናት የማሰፍፊያ ግንባታዎችን ማጠናቀቅ /አቀስታ ጠቅላላ ሆስፒታል፣ መካነሰላም ጠቅላላ ሆስፒታል/
- የመለስተኛ ጥገና ላይ ያሉ ሁለት ሆስፒታሎችን እንድያጠናቅቁ ማድረግ/ሀይቅ እና አማራ ሳይንት ሆስፒታሎች/
- 18 የጤና ጣቢያ ደረጃ ማሳደግ ግንባታ ማጠናቀቅ(አስፈላጊዉን በጀት ክልል እና ወረዳ ከመደቡ)
- በግንባታ ላይ ያሉ የተኙቶ መታከሚያ ግንባታወችን ማጠናቀቅ/ደንሳ ጤና ጣቢያ/
- ወረዳውና ክልሉ በጀት ከመደበ  በግንባታ ላይ ያለ አንድ ጤና ጣቢያ ማጠናቀቅ(ግሸን)
- መለስተኛ የቀዶ ጥገና ህክምና ብሎክ ያላቸውን 2 ጤና ጣቢያዎች ማጠናቀቅ (ገነቴ እና ቆተት)
- መለስተኛ የቀዶ ጥገና ህክምና ብሎክ ያላቸውን ጤና ጣቢያዎች ቁጥር ከ7 ወደ 13 ማድረስ
- የባለሙያዎች መጠለያ ያላቸው ጤና ጣቢያዎችን ቁጥር ከ 6 ወደ 12 ማድረስ
- በግንባታ ላይ የሚገኙ 6/ስድስት/ የባለሙያዎች መጠለያ ያላቸው ጤና ጣቢያዎችን ማጠናቀቅ/ጭራ፣ ዋሮ፣ የጀርሳ፣ አድስ አምባ፣ በታ፣ አረጋይ/
- በግንባታ ላይ ያሉ የአጠቃላይ ጤና ኬላ ማጠናቀቅ/ገደራ፣ ሀደሬ-ፈንታሌ፣ ኩታበር 023፣ ኩታበር 011፣ ኩታበር 012፣ ኩታበር 015 /
- በግንባታ ላይ ያለ የመሰረታዊ ጤና ኬላ ማጠናቀቅ/ሀራ፣ ቡልቡሎ፣ ፊቶ፣ ጉቢሳ፣ ኩታበር 021፣ ኩታበር 09፣ ኩታበር 010፣ ኩታበር 014/
- በግንባታ ላይ ያለ የማህበረሰብ አቀፍ መድሀኒት ቤት ማጠናቀቅ/ደላንታ/
- በግንባታ ላይ ያለ የመድሀኒት እስቶር ማጠናቀቅ/ቢስቲማ ጤና ጣቢያ/
- በግባታ ላይ ያሉ የእናቶች እና ህጻናት ማስፋፊያ ግንባታወች ማጠናቀቅ/ቢስቲማ፣ ሀራ፣ ኩታበር፣ ገልሻ ጤና ጣቢያ/
- በግንባታ ላይ ያሉ የድንገተኛ ህክምና መስጫ ማስፋፊያ ግንባታወችን ማጠናቀቅ/ሱሉላ፣ ሀይቅ፣ ማርየ፣ እና ዉጫሌ /

- በጤና ጣቢያዎች ግንባታ ላይ ያሉ 3 የዉሃ አቅርቦት ማጠናቀቅ/አቡየጉርባ፣ ረሳ እና ቁንድ/

**ግብ 15:- የጤና መሰረተልማት (የኤሌክትሪክ፣ ውሃ) በማሟላት አሁን ካለበት 50.93 በመቶ በ2018 ወደ 55.4 በመቶ ማድረስ**

- የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሻሻል በጤና ጣቢያዎች ከ 62 በመቶ ወደ 81 በመቶ፣ የጤና ኬላዎችን ወደ 39.5 በመቶ ማሳደግ፣
- የዉሃ አቅርቦት በጤና ጣቢያዎች ከ58 በመቶ ወደ 88.6 በመቶ እና በጤና ኬላዎች ደግሞ ወደ 38 በመቶ እንዲደርስ ማድረግ፣

**ግብ 16:- ወደ ትግበራ ለገቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መሠረተ ልማት አቅርቦትን ሽፋን ማሳደግ።**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- 47 ኘሮጀክቶች መሠተ ልማት እንድሟላላቸው በመደገፍ ወደ ስራ ማስገባት
- 5ኪሎ ሜትር መንገድ፣ 1ድልድይ ማጠናቀቅ፣ 4ነባር የመብራት መስመር ዝርጋታና ትራንስፈርመር ተከላ ስራ ማከናወን
- 25 አነስተኛ 41 መካከለኛ ና 10 ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የውሃና የመብራት አገልግሎት እንድያገኙ ማድረግ
- 1ነባር ሆልቲ ካልቸር የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራን ማጠናቀቅ
- ለ 1 ሆልቲካልቸር ና ለ2 እንስሳት እርባታ ፕሮጀክት በአድስ ውሃ እንድያገኙ ማድረግ
- ለ1ሆልቲካልቸርና ለ3 እንስሳት ርባታና ፕሮጀክቶች በአድስ የመብራት አገልግሎት እንድያገኙ ማድረግ
- ለ4 ኢንዱስትሪ መንደር የጠጠር መንገድ መገንባት

**ግብ 17:- በከተሞች የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታ ሽፋንን በ2017 ካለበት 6,525.9 ኪ.ሜ በ2018 ወደ 6,735.29 ኪ.ሜ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በእቅድ ዘመኑ 8.07 ኪ.ሜ የኮብል ስቶን መንገድ፣ 59.77 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ፣ 98.68 ኪ.ሜ ጥርጊያ መንገድ ግንባታ ይከናወናል።
- በእቅድ ዘመኑ 13.06 ኪ.ሜ የጎርፍ ማስወገጅያ ካናልና መከላከያ ግንብ፣ በቁጥር 1 ከፍተኛና መለስተኛ ድልድይ፣ በቁጥር 20 የስላብ ከልቨርት ግንባታ ይከናወናል።
- የእግረኛ መንገድ ግንባታ 1ኪ/ሜ፣ የሳይክል መንገድ ግንባታ 1ኪ/ሜ፣ በከተሞች የሚገነባ የአስፓልት መንገድ 1.12 ኪ/ሜ ይገነባል

**ግብ 18፡- በከተሞች የንፁህ መጠጥ ውሀ መሰረተ ልማት ዝርጋታ ሽፋንን በ2017 ካለበት 1,473 ኪ.ሜ በ2018 ወደ 1530.31 ኪ.ሜ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በእቅድ ዘመኑ 44.18 ኪ.ሜ የውሃ መሰረተ ልማት ዝርጋታ እና በቁጥር 19 የውሃ ቦኖ እንዲገነባ ይደረጋል፡፡
- በከተሞች ለአረንጓደ ልማት የተዘረጋ የውሀ መስመር በኪ/ሜ 13.13 ይገነባል

**ግብ 19፡- በከተሞች የመንገድ መብራት መሰረተ ልማት ዝርጋታ ሽፋንን በ2017 ካለበት 910 ኪ.ሜ በ2018 ወደ 940.07 ኪ.ሜ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በእቅድ ዘመኑ 30.07 ኪ.ሜ የመንገድ መብራት አቅርቦት መሰረተ ልማት ዝርጋታ ይከናወናል

**ግብ 20፡- በከተሞች ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ መሰረተ ልማትን በ2017 ካለበት 41 በ2018 ወደ 49 ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በ8 ከተማ አስተዳደሮች ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ መሰረተ ልማት ግንባታ ይከናወናል፣
- በከተማ አስተዳደሮች እና በመሪ ማዘጋጃቤት ከተሞች በቁጥር 11 የጋራ መፀዳጃ ቤት ግንባታ ይከናወናል፣

**ግብ 21፡- በከተሞች ደረጃውን የጠበቀ 1 የገበያ ማዕከላትና 268 የመስሪያና የመሸጫ ሸድ በመገንባት በድምሩ በቁጥር በ2017 ከነበረበት 2906 በ2018 ወደ 3175 ማሳደግ፣**

- በተመረጠ ከተማ 1 የገበያ ማዕከላት ግንባታ እንዲከናወንና አስፈላጊው መሰረተ ልማት እንዲሟላ ይደረጋል፡፡
- በከተሞች 268 ክፍል የመስሪያና የመሸጫ ሸድ ግንባታና አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡

**ግብ 22፡- በተመረጡ ከተሞች የወጣቶች ማዕከላት ማስፋፋት እንድሁም ስማርት ሲቲ ትግበራ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ-ልማቶችን ማሟላት**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- አንድ ከተማ አስ/ር ስማርትሲቲን ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር( ጊምባ)
- በተመረጠ ከተማ 1 የወጣቶች ማዕከላት ተገንብቶ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል

- በ9 ከተማ አስ/ሮች የኮሪደር ልማትን ማስፋፋት

**ግብ 23፡- 1ብቁ የሆነ የፖሊስና ማረሚያ ቤት ተቋማት መገንባትና ግብዓቶችን እንድሟሉ ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- አንድ(1) የዞን ፖሊስ መምሪያ ስታንዳርዱን አሟልቶ  እንድገነባ ይደረጋል
- 2ደረጃውን የጠበቀ የፖሊስ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን መገንባት እና ግብዓትና መሰረተ-ልማት ማሟላት
- አንድ ስታንዳርዱን የጠበቀ የአድማ መከላከል ካምፕ  እንድገነባ ይደረጋል

**ግብ 294፡- በመንገድ ለ2,500 ፣ በመስኖ ለ3,000 እንድሁም በውሃና ኢነርጅ 1,592 ዜጎች የስራ እድል መፍጠር**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- በመንገድ፣በመስኖ እንድሁም በውሃና ኢነርጅ 7,092 የስራ እድል መፍጠር

## የማስፈጸሚያ ስልቶች

ዞናዊ የመሠረተ ልማት ቅንጅት ማስተር ፕላንና ማስፈጸሚያ ስታንዳርዶች ማዘጋጀት፣ የመሠረተ ልማት አገልግልቶች አቅርቦት በመሠረተ ልማት የቅንጅት ድዛይን ጋይድላይን መነሻነት በተቀናጀ ፕላን እንድመራ ማድረግ፣ የመሠረተ ልማት ፈንድ እንድቋቋም ማድረግ፣ የሎጂስቲክስ ማዕከላት እንድገነቡ ማድረግ፣ የመንግስትን፣ የግል ባለሃብቱን እና የአጋር አካላትን ተሳትፎ ማጠናከር፣ የመልካም አስተዳ ደር ችግሮችን በመፍታት የመሰረተ ልማት አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ፣ የመሰረተ ልማት አገልግሎቱን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ፣ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮች ማፍላለግ፣ የፌደራል መንግስት በዞኑ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ ያለውን ድርሻ ማሳደግ፣ የተዘረጉ የህብረተሰብ ተሳትፎ አሰራሮችን ማጠናከር፣ በአሠራር ሥራን ማሳለጥ የሚያስችል የቴክኖሎጅ የህግ ማዕቀፎች፣ ስታንዳርዶች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች፣ የአሠራር ልምዶችና የመሳሰሉትን ማደራጀትና እነዚህ በተሟሉበት ሁኔታ ሥራን መሥራት የሚችል በቴክኖሎጅ ዕውቀትና ክህሎት የሠለጠነና የበቃ የሰው ኃይልና ተቋም ማፍራት፣ ችግር ፈች የሆነ የክትትል፣ ግምገማና ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት እንድሁም በዘርፉ የማሰልጠኛና የምርመራ ተቋማትን እንድኖር ማድረግና ያሉትን ማጠናከር የሚሉት ዋና ዋና የማስፈፀሚያ ሥልቶች ናቸው

# ክፍል አራት፡- ስርዓታትና ልማት

## 2.1. የዳኝነትና የፍትህ ዘርፍ

የዳበረ የሕግና ፍትህ ሥርዓት ከድህነትና ግጭት አዙሪት ለመውጣት ብሎም የተሳካ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ እና ርትዕ ማህበረሰብ ለመፍጠር በያኝ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ የዳኝነትና የፍትሕ ዘርፍ የመንግስትን ስልጣን በህግ የተገደበ ከማድረግ፣ ሙስናን ከመከላከል እና ከመቆጣጠር፣ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራር ከመዘርጋት፣ ለመሰረታዊ መብቶች ጥበቃ ከማድረግ፣ የህዝብ ሰላም እና ደህንነት ከማረጋገጥ፣ የተሻሻለ የህግ ቁጥጥርና ትግበራን ዕውን ከማድረግ እንዱሁም ውጤታማ የወንጀል፣ የፍትሃብሄር እና የአስተዳደር ፍትህ ከመዘርጋት፣ አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ፣ ተገማች፣ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት የተላበሰ፣ እርካታን ያረጋገጠ እና አመኔታ የተቸረው ለማድረግ አገልግሎትን በኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖልጂ በማስደገፍ ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓትን መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ሌላው በዘርፉ ትኩረት የሚሻው ጉዳይ የህግ ብዜሃነት እና የመሰረተ-ማህበረሰብ ፍትህ አገልግልት ሲሆን የህብረሰብን ተሳትፎ ከማረጋገጥ እና የህዝብን አቅም ከመጠቀም አንፃር ያላቸውን ሚና ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሊሰራበት ይገባል፡፡

## ስትራቴጂያዊ ጉዲዮች

- ተደጋጋሚ ግጭቶች የወለዱት የፀጥታና የወንጀል ክስተቶች መበራከት
- የተቋማዊ ነጻነት እና የሙያዊ ገለልተኛነት በተሟላ ሁኔታ አለመኖር
- የሙያዊ ብቃት ችግር
- የስነ-ምግባር እና ተጠያቂነት ችግር
- የሰብአዊ መብቶች በሚጠበቀው ደረጃ አለመከበር

## የትኩረት መስኮች

1. ሁለንተናዊ ዘላቂ ሠላም
2. የሕግ የበላይነት እና የዳኝነት ነጻነት
3. የላቀ ፍትሕ አገልግሎት
4. የፍትሕ ተደራሽነት እና ሰብአዊ መብት

## የትኩረት አቅጣጫዎች

ሁለንተናዊና ዘላቂ ሰላምን በማስፈን የዞኑን ሠላምና የህዝቡን ደህንነት ማረጋገጥ አንደ ወሳኝ የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን ተቋማዊ አቅምን መገንባት፣ የህብረተሰቡን የንቃተ ህግ ግንዛቤን ማሳደግ

እንዲሁም የፍትህ ተቋማትን ቅንጅታዊ አሰራር ማሳደግ የሚሉትም ተለይተዋል፡፡ በተመሳሳይ የፍትህ ተቋማትን ነጻነትና የሙያ አገልግሎት የተሟላ ማድረግ፣ ማህበራዊ ሀብቶችን፣ እሴቶችንና አካባቢያዊ ዕውቀቶችን ማሳደግ፣ ህግ የማስከበርና የሰብዓዊ ደህንነት አቅምንና ተዓማኒነትን ማሳ ደግ፣ በዞኑ የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ የሰብዓዊ መብት ማክበር እና ማስከበርን አጠናክሮ ማስቀጠል፣ የፍትህ ስርዓቱ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ፍትሃዊና ግልጸኝነት የሰፈነበት እነድሆን ማስቻል እንዲሁም የቅድመ መከላከልና ፈጣን ምላሽ ሥርዓትን ማሳደግ የሚሉት የዘርፉ የበጀት ዓመቱ ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫዎች ሆነው ተቀምጠዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሥነምግባር ግንባታ እና ሙስናን የመከላከል ተልዕኮን ለመወጣት በሥነምግባር የታነጹ፣ ሙስናን የሚጠየፉና በጽናት የሚታገለ አመራሮች፣ ሠራተኞች እና ዜጎች እንዲበራከቱ መሥራት የሚሉት በዘርፉ የተመረጡ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

**ግብ 1:- ተቋማዊ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- ጥራት ያላቸዉ 1 ዓመታዊ እቅዶችን እና 4 የድጋፍና ክትትል ስራ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ብቃት ያለዉ አመራር ለማፍራት የሚያስችል አንድ/1/ የአሰራር ስርዓት መቅረፅ፣
- በወረዳና በዞን የሴት አመራሮችን ቁጥር ለማሳደግ ሴት ሰራተኞችን ወደ አመራር በማምጣት ድርሻቸዉን 20 በመቶ ማድረስ ፣
- ግልፅነት የሰፈነበት የሰው ሀይል ስምሪትን 100% ጥራት እንዲኖረዉ ማድረግ፣
- 23 የህግና 7 የኦዲት ኢንስፔክሽን /Legal Auditing/ ስራ መስራት፣
- የስነ-ምግባር ጉድለት የታየባቸው ፈፃሚዎችን ተገቢውን ማጣራት በማድረግ 100% በዲሲፕሊን ተጠያቂ ማድረግ፣
- ለ70 አመራሮች የአጫጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት፣
- ለ80 ፈፃሚ አካላት (አስተዳደር ሰራተኞች) የአጫጭር ጊዜ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
- 50 ሴት ሰራተኞች ስልጠና መስጠት፣
- የሙስናና ብልሹ አሰራር ምንነትን ይዘትና አደጋዎችን በተመለከተ ለመምሪያው አመራርና ሰራተኞች 1 የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና መስጠት
- በውጤት የተመዘነ አመራር፣ ባለሙያ እና ሰራተኛ 100% ማድረስ፣
- የዘርፉን ሳቢነትና ማራኪነት ለመጨመር የሰራተኛ ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣
- ለተቋም አቅም ግንባታ በሀገር ውስጥ አጋርነት የሚገኝ ድጋፍ 100,000 መቶ ሽህ ብር ማድረስ፣

- የተመደበዉን መደበኛ በጀት 100% በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል፣
- የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን ወደ 4% መቀነስ፣
- ተከታታይ የኦዲት ስራ በመስራት ነቀፌታ ያለበትን የኦዲት ግኝት 100% መቀነስ፣
- የመፈጸምና ማስፈጸም አቅምን ለማሳደግ የሚያስችለዉን የዞን የዳኝነትና የፍትህ ተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር የሚያስችል 2 መድረክ ማካሄድ፣
- አፈጻጸመን ዉጤታማ ማሳደግ የሚያሰችሉ ባለድርሻና አጋር አካላትጋር ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር የሚያስችሉ 4 መድረኮችን በባለቤትነት ማካሄድ/መፍጠር፣

**ግብ 2፡-ውጤታማ የቴክኖሎጂ አቅርቦት እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- አሰራርን ለማዘመን የሚያስችል 1 የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅን ወደ ስራ ማስገባት
- የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ዝርጋታ 10% ማሟላት
- የተዘጋጀውን 1 የተቋሙን የመረጃ ቋት ስራ ላይ ማዋል፣
- የተዘጋጀውን 1 የተቋሙን ዌብሳይት ስራ ላይ ማዋል፣
- ወረቀት አልባ አሰራርን 10% መተግበር ፣
- የሪፖርት እና መረጃ አያያዝን ድጅታላይዝድ 10% ማድረስ፣

**ግብ 3. የፍትሕ አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነት ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- የአቃቤ ህግ አካላዊ ተደራሽነት ከስራው መጠንና ስፋት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን 5 ዐቃቢያነ ህግ የሰው ሀይል ፍትህ ቢሮ እንዲያሟላ ማድረግ፣
- በራሳቸዉ አቅምና ገንዘብ ለመከራከር ለማይችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የነፃ ህግ ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥን 100% ማጠናከር፣
- ለ200 የማህበራዊ ፍ/ቤት እና ባህላዊ የዳኝነት አካላት ስልጠና መስጠት
- መሰረተ ማህበረሰብ ፍትህ ሰጪ ማዕከላትን 20% በጥናት መለየት፣ መደገፍና ማጠናከር፣
- በክልል ደረጃ የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍና እና ጥራት መለኪያ ስርዓት ሲዘጋጅ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የዜጎች ቻርተር በማዘጋጀት የተገልጋዮችን የእርካታ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት በመፍጠርና በመተግበር የተገልጋዮችን እርካታ 90% ማሳደግ፣

- የአቤቱታ አቀባበልና አፈታት መወሰኛ ስርዓት በክልል ደረጃ ሲዘጋጅ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአቤቱታ አቀባበል ውሳኔ አሰጣጥ እና የአቤቱታ ተፈጻሚነት ምጣኔ 98.5% ማሳደግ፣

**ግብ 4፡- የሕግ ግንዛቤ እና የህብረተሰብ ተሳትፎ ማረጋገጥ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- የንቃተ ሕግ ትምህርት የተሰጣቸው ዜጎች ብዛት /ስልጠና ሊሰጠው ከሚገባው ህዝብ /10% ማሳደግ፣
- የሙያና ሲቪል ማህበራት በፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ የሚሳተፉበት ፕሮግራም መንደፍ እና መተግበር
- የፍትህ ስርአቱን የሚያጠናክሩ 2 የህዝብ ምክክር መድረኮችን ማካሄድ፣
- የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን በማጠናከርም መረጃዎችን በተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች ተደራሽነትን 85% ማሳደግ፣
- ለህብረተሱ የህግ ግንዛቤን የሚፈጥሩ 2 የተለያዩ ብሮሽሮችን ማሰራጨት፣
- ለህብረተሰቡ የህግ ግንዛቤን የሚያሳድጉ እና ለተቋሙ የሚቀርቡ የሚዲያ ጥያቄዎች 100% ምላሽ መስጠት፣
- የህግ ግንዛቤን የሚያሳድጉ 1 የተመረጠ ተሞክሮ በመቀመር ማስፋፋት፣

**ግብ.5. በፍትሐብሄር የፍትህ አስተዳደር የመንግስትና የህዝብ ጥቅሞችን ማስጠበቅ ዉጤታማነት ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፣**

- የመንግስትን እና የህዝብን ጥቅሞች ማስጠበቅ የሚያስችል የውል አስተዳደር ተግባረዊ ማድረግ፣
- ከመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ያሉትን ችግሮች መለየትና መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግ፣
- በዞን እና በወረዳ ለ529 የመንግስት መ/ቤቶችን ክትትልና ድጋፍ ማጠናከር፣
- በፍትሐብሔር ጉዳዮች የቅድመ መከላከል ስራን
- የፍትሐብሄር ጉዳዮችን በድርድር የመፍታት ምጣኔን 30% ማድረስ፣

- በፍትሐብሄር ጉዳዮች በከሳሽና ተከሳሽነት በቀጥታ ክስ፣ በይግባኝና ይግባኝ መልስሰ ጭነት ክርክሮች የዐቃቤ ህግ መዛግብት የማጥራት/ቅልጥፍና ምጣኔ 100% ማድረስ፣
- ይግባኝና ክስ አያስቀርም የመመርመርና የመወሰን ምጣኔ 100% ማድረስ፣
- በፍትሐብሄር ጉዳዮች የቀጥታ ክስና መልስ የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ ምጣኔን በመዝገብ 90.5% ማድረስ፣
- በይግባኝ ባይነት መዝገቦች የዓቃቤ ህግ የክርክር ውጤታማነት በመዝገብ 65% ማድረስ፣
- በይግባኝ መልስ ሰጭነት መዝገቦች የዓቃቤ ህግ የክርክር ውጤታማነት በመዝገብ 75% ማድረስ፣
- የፍትህ ተቋሙ ክስ ባቀረበባቸው ጉዳዮች አስቀድሞ ንብረት ፈልጎ ማሳገድ 50%፣
- የተወሰደን የመንግስትና የህዝብ ሃብት ተመላሽነት ለማሳደግ የአፈጻጸም ክስ ከቀረበባቸው ጉዳዮች ውስጥ የማስፈጸም አቅም 97% ማድረስ፣
- ሰነዶችን በጥራትና በፍጥነት የመመዝገብና የማረጋገጥ ስራወችን በትኩረት በመያዝ ለምዝገባና ለማረጋገጥ  የቀረቡትን ሰነዶች 100% ጥራታቸዉን በመጠበቅ ማከናወን፣
- የምዝገባ ጥያቄ ያቀረቡትን የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች 100% በመመዝገብ አፈጻጸሙን ማሳደግ፣
- የተመዘገቡትን የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ክትትል የማድረግ ስራን 100% ማሳደግ፣
- የተመዘገቡትን ጠበቆች ድጋፍና ክትትል የማድረግ ስራን 96% ማሳደግ፣

**ግብ 6፡- የህግ አገልግሎት አሰጣጥ ዉጤታማነትን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- የሌሎች የመንግስት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች ነገረ ፈጆችን የህግ ገልግሎት  አሰጣጥ 1 ጊዜ መከታተል፣
- በጠበቆች የሚደገፉ ነጻ የህግ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ቁጥር ድርሻ 100% ማሳደግ
- በጠበቆች የሚያዙ ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ጉዳዮች ውጤታማነት 90.5% ማድረስ፣
- በጠበቆች የነፃ ህግ ድጋፍ አገልግሎት የደንበኞች እርካታ ምጣኔ 85% ማድረስ፣
- የስነ ምግባር ግድፈት የሚፈፅሙ ጠበቆችን በማስረጃ እያጣሩ 100% እርምጃ እንዲወሰድባቸው ማሳደግ፣

- ከጠበቆች ማህበር ጋር በመቀናጀት 192 ከሚሆኑ ጠበቆች ጋር ውይይት በማድረግ ችግሮችን መፍታት፣

**ግብ 7፡- የአስተዳደር ፍትህን ዉጤታማነት ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- የአስተዳደር ፍትሕ ስርዓትን የማስተዋወቅ እና የማስረፅ ተግባራትን 100% መፈፀም፣
- የሚወጡ መመሪያዎችን በዘላቂነት የመመርመር እና የመመዝገብ ተግባራትን ለመፈጸም የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በክልል ደረጃ ሲዘረጋ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በአስተዳደር ተቋማት የሚወጡ መመሪያዎችን ህጋዊነት በክልል ደረጃ ተመርምሮ ምዝገባ ሲካሄድ እና በዌብሳይት ላይ ሲጫን ለሚመለከታቸው ተቋማት 100% የማሳወቅ ስራ መስራት፣

**ግብ 8፡- የሰብአዊ መብትን ማሳዎቅ፣ ማክበር፣ማስከበር እና ማሟላት አፈፃፀምን ማሻሻል፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፣**

- 12 (በዞን እና በወረዳ በወር 1 ጊዜ ጉብኝት ማድረግ) ጊዜ ማረሚያ ቤቶችን ጉብኝት በማድረግ በህግ ቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች አያያዝና አጠባበቅ ህግን የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ
- 264 (በወረዳ በሳምንት 5ቀን ጉብኝት ማድረግ) ጊዜ የፖሊስ ጣቢያና ጊዜአዊ ማረፊያ ቤቶች በህግ ቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች አያያዝና አጠባበቅ ህግን የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ
- በሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የሚወጡ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የምርመራ ሪፖርቶች ተከታትሎ ምላሽ መስጠት 100% ማሳደግ፣
- በሰው መነገድ ሰዎችን ድንበር ማሻገር ወንጀልን መከላከልና ምላሽ መስጠት 80% ማሳደግ፣

**ግብ 9፡- የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውጤታማነትን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ከፍተኛ የህዝብ እና መንግስት ጥቅም ያለባቸው ወንጀሎችን ለይቶ እና ቅድሚያ ሰጥቶ ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በክልል ደረጃ ሲዘጋጅ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ከፍተኛ የህዝብና የመንግስት ጥቅም ያለባቸውን የወንጀል ጉዳዮች (grand corruption, economic crimes, organized crimes) 100% ቅድሚያና ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት
- የወንጀል ምርመራ መዛግብት የመወሰን ቅልጥፍናን 100% ማድረስ፣

- የክስ አይቀርብም የውሳኔ አሰጣጥ የክትትል ምጣኔ 100% ማድረስ፣
- የክስ አይቀርብም የውሳኔ ጥራት ምጣኔ 100% ማድረስ፣
- በቀጥታ ክስ የወንጀል መዛግብት የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት ምጣኔን በማሳደግ 96% ማድረስ፣
- በሰው መነገድ እና ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል የመከላከልና አጥፊዎችን በህግ የመጠየቅ ውጤታማነት 96% ማድረስ፣
- በቀረቡ የዋስትና ጥያቄዎች በወቅቱ እና በአግባቡ ያለው የዋስትና አስተያየት መስጠት ውጤታማነት 100% ማድረስ፣ ዋስትናቸው ይነፈግ ያልናቸውን ተከራክሮ የማሸነፍ አቅምን 77% ማድረስ፣
- የዓቃቤ ህግ ይግባኝ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነት 90% ማድረስ፣
- የፍርደኛ ይግባኝ መዝገቦች የክርክር  መርታት ውጤታማነትን 95% ማድረስ፣
- ተከሳሽ እና ምስክር በማቅረብ የመዛግብትን መቋረጥ ምጣኔ ለመቀነስ የሚያስችል  አሰራር ስርዓት በክልል ደረጃ ሲዘጋጅ ተግባረዊ ማድረግ፣
- በተከሳሽና ምስክር አለመቅረብ የመዛግብት መቋረጥ ምጣኔን ለመቀነስ የሚያስችል 100% ክትትል ስራ መስራት እና የማቋረጥ ምጣኔን  ማስቀነስ 12% ማድረስ፣
- በሌሉበት የተፈረደባቸውን ፍርደኞች ለሕግ ለማቅረብ የሚያስችል  አሰራር ስርዓት በክልል ደረጃ ሲዘጋጅ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በሌሉበት ውሳኔ የተሰጠባቸውን ፍርደኞች የፍርድ ውሳኔ ተፈፃሚነትን ዉጤታማ ለማድረግ በሌሉበት የተፈረደባቸዉን ፍርደኞች ለፖሊስ ማሳወቅና 100% ክትትል ማድረግ፣
- የኤግዚቢት አያያዝ፣ አስተዳደርና አወሳሰን 1 ስርአት በማዘጋጀትና በመዘርጋት ኤግዚቢት አወሳሰንን ዉጤታማ ማድረግ፣
- በወንጀል የገንዘብ ቅጣት የተቀጡ ሰዎችን ከቅጣቱ እንዲማሩ ለማድረግ የወንጀል የገንዘብ ቅጣት አፈጻጸም 100% ተፈጻሚ ማድረግ፣
- የወንጀል መንስኤ እና ተጋላጭነትን በጥናት በመለየት የመከላከያ አማራጮችን መተግበር፣
- በወንጀል የተመዘበረን የመንስትና የህዝብ ሃብት ለማስመለስ የሚያስችል የሀብት ምርመራ መዛግብት መርምሮ የማጠናቀቅ ምጣኔን 74% ማሳደግ፣

- ምርመራ የሚደረግባቸውን መዛግብት ላይ የወንጀል ፍሬ እና የማካካሻ ንብረት 90% ማሳገድ፣
- የሀብት ምርመራ መዛግብት ላይ ውሳኔ የመስጠት አፈጻጸምን 100% ማሻሻል፣
- የሀብት ማስመለስ ክስ የተመሰረተባቸውን መዛግብት የመርታት ምጣኔ 91% ማድረስ፣

**ግብ 10፡- የሴቶች፣ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞች እንዲሁም ለአደጋ ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- በሴቶች፣ በህጻናት፣ በወጣቶች፣ በአረጋውያንና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ በቀጥታ ክስ አፈጻጸም ውጤታማነት 91% ማድረስ፣
- የልጅነት ጋብቻንና በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚደርሰውን የሃይል ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል 1 የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተቋማትን ማቋቋም፣
- በሴቶች፣ በህጻናት፣ በወጣቶች፣ በአረጋውያንና በአካል ጉዳተኞች በፍትሐብሄር የቀጥታ ክስና መልስ የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅም 90.5% መፈፀም፣
- በሴቶች፣ በህጻናት፣ በወጣቶች፣ በአረጋውያንና በአካል ጉዳተኞች በፍትሐብሄር ተከራክሮ በማሸነፍ የተወሰኑት ውስጥ የማስፈጸም ምጣኔ 97% ማድረስ፣
- 2 ወላጆቻቸውን ያጡ እና አቅም የሌላቸው ህፃናትን መደገፍ፣
- ወላጆቻቸውን ያጡ እና አቅም የሌላቸው ህፃናትን 10,000 ብር ድጋፍ ማድረግ፣
- 1 የህጻናት ማቆያ ቦታን መገንባት፣
- የአካል ጉዳተኞችን ለስራ 85% ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- **ግብ 11፡- ቅንጅታዊ አሰራር ማሳ ደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- አገልግልት አሰጣጥ ውጤታማ የሚያደርጉ የአደረጃት፣ አሰራር፣ ሕግ እና ስትራቴጅ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ ስትራቴጅክ ዕቅድ በጋራ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የጋራ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ማድረግ፣
- ተናባቢ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት መተግበር፣

- የተከሳሽና ምስክር አቀራረብ ሥርዓት በተቀመጠበት አግባብ መተግበር፣
- ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ትብብር እና አጋርነትን ማጠናከር፣
- በቴክኖሎጂ የታገዘ የዳኝነትና የፍትህ  ዘርፍ የጋራ የመረጃ ማዕከል ማደራጀት፣
- የዳኝነት እና ፍትሕ ተቋማቱ የተቀናጀ ቴክኖልጅ ተጠቃሚነት እና የመረጃ ልዉዉጥ ስርዓትን መተግበር፣

**ግብ 12፡- የግጭት እና የፀጥታ ስጋት የሆኑ እንቅስቃሴዎችን መከላከልና መቆጣጠር፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የግጭት እና የፀጥታ ስጋት የሆኑ እንቅስቃሴዎችን መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችል አስቻይ አሰራር መቅረፅና መተግበር፣
- በዞን የተደረጀ የህገወጥ መሣሪያ ዝውውርን፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን፣ የተደራጁ የዘረፋ እና ቅሚያ ወንጀሎችንና በትምህርት ተቋማት የሚከሰቱ ግጭቶችን እንዱሁም መሰል ወንጀልችን በቅድመ መረጃ ላይ ተመስርቶ መከታተልና መቆጣጠር፣
- ከአጎራባች ዞኖች የመራር  ለአመራርና ህዝብ  ለህዝብ ግንኙነቶችን በማጠናከር ችግሮችን ቀድሞ የመፍታት ባህል ማዳበር፣

**ግብ 13፡- በክልለ የሰላምና ግጭት አፈታት ባህል መገንባት፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የሰላምና ግጭት አፋታት ማዕከላት፣ የሰላም ምክር ቤቶች፣ ክበባት እና ፎረሞች በየደረጃዉ እንዲመሰረቱና እንዲስፋፉ ማድረግ እና ማጠናከር፣
- በዞን የሚከሰቱ ችግሮችን በምክክርና ሰላማዊ መንገዶች የመፍታት ባህል እንድሆን ማድረግ፣
- ከአጎራባች ዞኖች ጋር ሊፈጠሩ የሚችሉ ጉዳዮችን በምክክርና ሰላማዊ መንገዶች መፍታት፣
- ተሞክሮዎችን ማስፊት፣

**ግብ 14፡- የትጥቅና ጦር መሣሪያ አስተዳደርን ማሻሻል፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ተፈፃሚነት ያላቸዉን ህጎች መሰረት በማድረግ በክልለ የጦር መሳሪያ አያያዜና አጠቃቀም በሚወርደው አሰራር መሰረት መተግበር፣
- የመንግስትና የግል ጦር መሳሪያዎች እና ተተኳሾች ልየታና ቆጠራ፣ ፍቃድ ዕድሳት፣ ጥገና እና ኦዲት ማከናወን፣

- አገልግሎት የማይሰጡ የጦር ማሳሪያዎችንና ተተኳሾችን በመለየት እንድወገዱ ማድረግ፣
- ህገ-ወጥ ትጥቅ፣ የጦር መሳሪያ አያያዝና ዝውውርን ጥናትና ህግን መሠረት በማ ድረግ መከሊከልና
- መቆጣጠር፣

## የማስፈፀሚያ ስልቶች

- ዕቅደን ማስተዋወቅ፣ ማስገንዘብና የጋራ መግባባት መፍጠር፣ የዳኝነትና ፍትህ እንዱሁም የፍትህና ፀጥታ ዘርፍ የጋራ መድረኮችን መጠቀም፣
- የተቀናጀ የድጋፍ እና ክትትል ስርዓት መቅረፅና መተግበር እንዱሁም ግብረ መልስ በተከታታይ መስጠት የሚሉት ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ይሆናሉ፡፡

## 4.2. የባህል እና እሴት ልማት

ባህሎች እሴቶችና ልምዶች በእኩልነት እንዲጐለብቱ በማድረግ በዞኑ ውስጥ ተፈጥሮአዊ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው አስተዋፅኦ በማድረግ በኩል የዘርፉ ሚና የላቀ ነው፡፡ እንዲሁም ግበረ ገባዊ ዕሴቶችንና ባህልን በመፍጠር ወይም በመቅረፅና በማሳደግ፣ በማክበርና በማስከበር በማወቅና በማሳወቅ፣ በመቀበልና በማስፈን በመረከብና በማስተላለፍ ለሠላምና የህግ የበላይነት አስተዋጽኦ በማድረግ ረገድ ዘርፉ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ይህን ትልቅ ማህበራዊ ካፒታል ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለመልካም ገፅታ ግንባታ ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ፣ ብዘሃ እሴትና ባህል የማንነት መገለጫ እንደመሆን: ይህን በእኩል በማክበርና በመጠቀም ለአገር አንድነት ለዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ግንባታ እና ፍትህና ሰላምን ለማስፈን እንዲውል ማድረግ እንዲሁም ባህልንና ዕሴትን ለዘናዊ፣ ክልላዊና አቀጠናዊ ትስስር ማዋል፡፡ ባህልን በማጥናት በመጠበቅና በማልማት ለዕድገት የሚኖራቸውን ድርሻ ማጎልበት ከዘርፉ የሚጠበቅ ነው፡

## ስትርቴጅያዊ ጉዳዮች

- የባህልና እሴት መሸርሸር
- ባህልናን እሴትን የማልማት ውስንነት
- የተቋማዊ አቅም ግንባታ ውስንነት

## የትኩረት መስኮች

1. የባህልና እሴት ጥናት ምርምርና ልማት
2. የአሰራር ስርዓትና የተቋማዊ አደረጃጀት ግንባታ

3. ዘላቂ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ
4. ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር

## የትኩረት አቅጣጫዎች

የተቋም ግንባታና አደረጃጀት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣ ዞኑ ያለውን ተፈጥሮአዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ሀብትን እንዲሁም እሴቶችን በሚገባ መለየትና ማልማት የባህል እና እሴት ሀብቶችን በማጥናት በመንከባከብ እና በመጠበቅ ለዞን ልማት ያላቸውን አስተዋጽዖ በማጉላት በአግባቡ መጠቀም፣ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ህብረተሰብን ለመፍጠር የንባብ ባልን የሚያዳብሩ ድጅታል ቤተ-መፀሀፍትን ማስፈፋትና ተደራሽ ማድረግ፣ የህብረተሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ስራ መስራት፣ በዘርፉ የተሰማራዉን የሰው ኃይል በእውቀትና በክህሎት ማብቃት በዞኑ በተከሰተው ግጭት ጉዳት የደረሰባቸውን ቅርሶች መልሶ ማልማት፡ ጠንካራ የገበያና የፕሮሞሽን ስትራቴጅዎችን መተግበር እንዲሁም የመረጃ አያያዝ ስርዓት እና የቴክኖሎጅ አጠቃቀም ማሳደግ፣

ዓላማ፡፡ በዞኑ ውስጥ የሚገኙ ባህሎችን' እሴቶችን እና ቅርሶችን በማጥናት፣ በመጠበቅ! በመንከባከብና በማልማት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በዘላቂነት ማረጋገጥና ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ፣

## ዋና ዋና ግቦች

**ግብ 1፡- በዞኑ የሚገኙ ቅርሶች በበቂ ሁኔታ መንከባከብና መጠገን ባለመቻሉ ለተፈጥሮና ሰው ስራሽ አደጋ እየተጋለጡ የሚገኙ በመሆኑ የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ ለቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ጥገና በማድረግ ዘላቂ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤን ማሳደግ፤**

**የሚከናዎኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለ12 ቋሚ ቅርሶችን የጉዳት መጠን በደረጃ መለየት፣
- ለ3 ቋሚ የጥገና ስራ መስራት ቋሚ ቅርሶቹም በተንታ ወረዳ መከና መካነ ሂወት ቤተ ክርስቲያን ፣ በአርጎባ ወረዳ ለገደል አምባ መሰጅድ እና በተሁለደሬ ወረዳ ደብረ ልኡል አቦ ቤተክርትቲያን ናቸዉ፡፡
- ለ30 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን የጥገና ስራ መስራት
- የደንቀ'ዝ ቤተ-መንግስት፣ የእጺ ሰስኒዮስ ቤት መንግስት (ጎርጎራ)) የይባባ እና ግንብ ጊዮርጊስ (ሰሜን ጎጃም) ጥግናና እንዲሁም የጋፋት ኢንዱስትሪ መንደርን መልሶ ግንባታ ስራ መስራት፤
- ለ48 ቋሚ ቅርሶች፣ የአርኪወሎጅ እና ፓሊዮንቶሎጂ ስፍራዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲያገኙ ማድረግ፣

- ለ24 ቋሚ ቅርሶች፣ የአርኪዎሎጅ እና ፓሊዮንቶሎጂ ስፍራዎች የወሰን ክለላ እንዲሰራላቸው ማድረግ፣

**ግብ 2- የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ በቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ ምዝገባ በማድረግ ዘላቂ የቅርስ ጥበቃና እክብካቤ ማሳደግ**

**የሚከናዎኑ ዋናዋና ተግባራት**

- 16 ቋሚ ቅርሶችን መመዝገብ፣
- 800 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን መመዝገብ
- 20 የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን መመዝገብ፣
- 1 ተንቀሳቃሽ የጽሑፍ ቅርስ (ጤፉት) በአለም አቀፍ ቅርስ ዝርዝር ሚሞሪያል ዉስጥ እንዲመዘገብ ከኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ፣ከዩኒቨርሲቲዎችና ከቢሮው ጋር መስራት
- ከኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን እና ከአብክመ ባህል ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ ጋር በመተባባር የአሆላሎ የልጅ አገረዶች ባህል በዩኒስኮ አለም አቀፍ ቅርስነት ማስመዝገብ፣
- የቅርስ አዋጆችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ በማደረግ ህገ-ወጥ ወጥ የቅርስ ዝውውር 99 በመቶ መቀነስ፣
- ከመቅደላ አምባ ታሪካዊ ቦታ የተዘረፉ ቅርሶችን ለመስመለስ ከኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣንና ከኢትዮጵያ ቅርስ ባላዳራ ማህበር ጋር በጋራ መስራት፣

**ግብ 3፡- የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚገነቡ ሙዚየሞች**

**የሚከናዎኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በዞኑ 2 አዳዲስ ሙዚየሞችን መገንባት
- በዞኑ የተድባበ ማርያም ሙዚየም ላይ ቅርሶን በማሰባሰብ በዘላቂነት ማደራጀት

**ግብ 4፡- ዞናዊና አካባቢያዊ ወጎችን ዕሴቶችን እና ባህሎችን በማዳበር በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ማፍራት:**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የዞኑን ባህል ወጎች እና አሴቶች በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ እንዲካተቱ ምቹ ሁኔ መስፍጠር!
- በ20 ወረዳዎች ሀይማኖታዊ ተቋማት፣ ሚዲያዎች በስነ-ምግባር ቀረፃ ላይ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማስቻል፣

**ግብ 5፡- የተመረጡ እሴቶችን (ሙያዊ ብቃት፥ አገልጋይነት፣ ባህልን መጠበቅ፣ ህግን ማክበር፣ ህዝባዊ ወገንተኝነት፣ አርበኝነት፣ ሀብትን በአግባቡና በቁጠባ መጠቀም፣ ለልዕለ ሐሳብ ተገዥነት፣**

**ግብ ተኮር ብዝሀነትን መቀበል፣ ምርምርና ፈጠራ፣ ቅንጅታዊ አሰራር እና ግልፅነትና ተጠያቂነት) ሁሉም አካል ይዞ እንዲተገብራቸው ማድረግ!**

**የሚናከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞኑ የሚገኙ የትምህርት ተቋማት፣ የእምነት ተቋማት፣ የልሂቃን(የፖለቲካና ኢኮኖሚ) እና የሚዲያ ተቋማት በስፋት ኃላፊነቱን ውሰደው እንዲተግብሩት ማስቻል እና መከታተል፡፡

**ግብ 6፡፡ ከዞኑ እምቅ ባህልና ቋንቋ! የቅርስ ከምችት፣ የማንነት መገለጫዎች የሆኑትን ባህላዊ ትውፊቶችንና ቅርሶችን ለገቢ ማመንጫ በማዋል እና በማስተዋወቅ የዞኑን መልካም ገፅታ መገንባት!**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞኑ እምቅ የባህል፣ የቅርስ የማንነት መገለጫዎች የሆኑትን ባህላዊ ትውፊቶችንና ቅርሶችን በጥናት በመለየት የማስተዋወቅ ስራ መስራት
- የዞኑ ባህል ቅርስ እና የማንነት መገለጫዎች ለገቢ ምንጭነት ማዋል እንዲችሉ መስራት፡

**ግብ 7፡- የዞኑ የባህል፣ እሴት እና ቋንቋዎች ልማትና አጠቃቀምን ማሳደግ!**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞኑ 2 እየተገነቡ ያሉትን የባህልና የቅርስ መዚየሞች ማጠናቀቅ፣

**ግብ 8፡- የዞኑ የስነ-ጥበብና የኪኒ-ጥበብ ስራዎችን በማጎልበት የእድ ጥበብ ምርትን በማስፋፋት የዞኑን የገበያ ድርሻ ማጎልበት**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞኑ 1 የባህል ፌስቲቫል በማዘጋጀት የእደ ጥበብ ውጤቶችን በማቅረብ የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ማድረግ፣
- 1 የዕደ-ጥበባት ማምረቻ እና መሸጫ መንደሮች መመስረት፣

**ግብ 9፡- በዞኑ የሚለሙ ባህላዊ አሌቶችን ለይቶ በማሳደግ የዞኑን የባህል ተቋማትን ቁጥርን ማሳደግ!**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በወረዳዎች አዳዲስ የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር

**ግብ 10፡- በዞኑ የሚዘጋጁ የኪነ-ጥበብ ስራዎችን ትኩረት ሰጥቶ ማሳደግ፣**

**የሚናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 1 የባህልና ኪነ ጥበብ ሲምፖዚየሞችን ማካሄድ፣

- በዞኑ 112 የኪነ ጥበብ ስራዎች ውድድሮን በስፋት ማካሄድ!
- 700 የኪነ-ጥበብ የፈጠራ ስራዎችን ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ

**ግብ 11. በባህል ኢንዱስትሪ የገበያ ትስስር በመፍጠር ባህሉ ለዞኑ ልማት የድርሻውን እንዲወጣ ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞኑ 20 ወረዳዎች እሴትና ባህልን በማጥናት በመጠበትና በማልማት ለኢኮኖሚው ያላቸውን አስተዋጽዖ ማሳደን
- በ20 ወረዳዎች በባህል ኢንዱስትሪው የገበያ ትስስር ላይ የተጠናከረ ስራ መስራት
- በዞኑ የሚከበሩ ነባርና አዳዲስ ባህላዊ ክብረ በዓላትን በሁሉም ወረዳዎች ማልማት

**ግብ 12፡- የዞኑን የህዝብ ቤተ-መጽሐፍት ቁጥር በማሳደግ በቴክኖሎጂ፣ በቁሳቁስ እና በአደረጃጀት ማጠናከር፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በዞኑ ለሚገኙ 20 ወረዳዎች የህዝብ ቤተ መጽፍትን በቴክኖሎጅ ማደራጀት
- በዞኑ 1 ቤተ መፅሀፍት ማስገንባት፣

**ግብ 13፡- መጤ ባህሎችን፣ ጎልድ እና አመለካከቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ አሰራሮችን በመዘርጋት የዞኑን ባህልና እሴት ከመሸርሸር ማዳን፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በ20 ወረዳዎች መጤ ባህሎች) ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እና ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉትን በጥናት መለየት፣
- በዞኑ መጤ ባህሎችን በተቀናጀ አግባብ መከላከል(የጎልድ አስወጋጅ ጥምረት ጋር)
- በዞኑ ለህብረተሰቡ የተለያዩ አማራጮች በመጠቀም ለ12000 ሰዎች ግንዛቤ መፍጠር

**ግብ 14፡- በባህል ዕሴቶች ልማት እና በማህበራዊ ዕድገት ውስጥ ፋይዳቸው ጉልህ የሆነ አገር በቀል ዕውቀቶችን እና ባህላዊ ዕሴቶችን ማልማት እና መጠበቅ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በ20 ወረዳዎች የአገር በቀል እውቀቶችን በጥናት መለየት

**ግብ 15፡- በባህልና እሴት ዙሪያ የሚደረጉ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማጎልበት :**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በ20 ወረዳዎች በባህልን እሴት ዙሪያ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በትኩረት መስራት!
- በ4ቱ የሙዚቃ ቅኝቶች ዙሪያ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ከክልሉ ቢሮ ጋር በቅንጅት ማጥናት

**ግብ 16፡- አዳዲስ አደረጃጀትና አሠራርን በመፍጠር ተቋማዊ አቅምን መገንባት**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ቢሮው ጋር በመቀናጀት የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድ

## የማስፈፀሚያ ስልቶች

አደረጃደቶችን መፍጠርና የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት፣ በክልል የሚዘጋጁ ፖሊሲ ማስፈፀሚያ የህግ ማእቀፎችን ወደ ትግበራ እንዳገቡ ማድረግ፣ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ብዝሀ ባህላዊ ሀብቶችነና የታሪክ ቅርሶችን በማጥናት፣ በመጠበቅ፣ በማልማት፣ ለመልካም ገጽታ ግንባታና ለዘላቂ ፍትሐዊና ተደራሽ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥቅም ማዋል፣ ከባለ ድርሻ እና አጋር አካላት ጋር መግባባት መፍጠርና ቅንጅታዊ አሰራርን ማዳበር፣ በባህል ዘርፉ የህብረተሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፤ የህልና ቋንቋ ጥናትና ምርምር ስራዎችን ማከናወን፣ የቅርስ ጥበቃ ልማት የባህል ልማት ስትራቴጅ ማውጣት እንዲሁምቴክኖሎጅነና የባህል እሴቶችን የመረጃ ስርጭትን ማዘመን የሚሉት ዋና ዋናዎቹ የዞኑ የማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

## 4.3. የመንግስት ተቋማትና የአመራር ሚና

ኢትዮጵያ የሥልጣኔ ተምሳልት ተደርገው እንደሚወሰዱት የአውሮጳና የእስያ ሀገራት ሁሉ በረጅም የመንግስትነት ታሪኳ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት የመሰረተች ቢሆንም በታሪኳ የተሟላ የህግ የበላይነትና ተጠያቂነት ያለበት ፖለቲካዊ ስርዓት ለማስፈን አልቻለችም፡፡ በዚህም ምክንያት ፖለቲካዊ መረጋጋቷን በዘላቂነት ለማስጠበቅ አቅቷት በታሪክ አቻዋ ከሆኑ ሀገራት ተለይታ በሁለንተናዊ ኋላቀርነትና ድህነት ውስጥ እንድትማቅቅ ሆናለች፡፡ ምንም እንኳን ላለፉት ዓመታት የልማታዊ መንግስት ፈለግን እንከተላለን ብንልም የልማታዊ መንግስት ዋነኛ መለያና የጥንካሬ ምንጭ የሆነውን ብቁ ተቋማትን የመገንባት ውስንነታችን ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የአመራር የፖለቲካ ቁርጠኝነት መረጋገጥ በቀጣይ የዕቅድ ዓመታት እደርስበታለን ያለውን ርዕይ ለማሳካት ከፍተኛ ዕድል የሚሰጥ ይሆናል፡፡ የአመራሩ የፖለቲካ ቁርጠኝነት መገለጫው ደግሞ ህዝቡን በማስተባበር በየደረጃዉ የታቀደዉን ዕቅድ በማሳካት ሂደት ምን አይነት የአመራር ዘይቤ ወይም ስልት መከተል አለበት ለሚለው ወሳኙ ጉዳይ ተረድቶ መተግበር ነው፡፡ ይህም ሲባል ህዝቡ በአሁኑ ሰዓት ቀርቦ የሚያገለግለው ቁርጠኛ አመራር ስለሚፈልግ ያለማሰለስ ተግቶ በመስራት ሰላሙን በማስፈን ከድህነት ማላቀቅ ያስፈልጋል፡፡

## ስትራቴጅዊ ጉዳዮች

- በተቋማት ብልሹ አሰራር ምክንያት የተገልጋዮች እርካታ ከጊዜ ወደ ጊዜ መቀነስ
- የግጭትና የድህነት አዙሪትን መስበር አለመቻል
- የፖለቲካ ቁርጠኝነትና አመራር ሰጭነት በበቂ አለመጎልበት
- የተቋማት ሚና መደበላለቅ

## የትኩረት መስኮች

1. የመንግስት ተቋማትና አስተዳደርን ማሻሻል
2. ተዘጋጅተው የሚወጡ ችግር ፈቺ ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ
3. አመራር ሰጭነት /Political will and leadership/

## የትኩረት አቅጣጫዎች

ግልጸኝነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን፣ የተገልጋዩን እርካታ ማሳደግ፣ የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ ተቋማት ሲደራጁ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፉነት በብቃት መወጣት፣ የፐለቲካ ቁርጠኝነትና አመራር ሰጭነት ሚናን ማጎልበት እንዱሁም የተቋማት ግንባታ የሪፍርም ስራዎችን በጥንቃቄ መተግበር የሚለት ዋና ዋናዎቹ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

**ዓላማ፡- ቁርጠኛና ውጤታማ የፖለቲካ አመራር በመገንባት ዞኑን ከድህነትና ከግጭት አዙሪት ማውጣት፣**

**ዋና ዋና ግቦች**

**ግብ 1፡- በዞኑ ውስጥ የተረጋጋ የፖለቲካ አውድ በመፍጠር ዞኑን ከድህነትና ከግጭት አዙሪት ማውጣት፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለዞን አለመረጋገት መንስዔ የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት መለየት፣
- በጥናት ግኝቱ መሰረት ፐለቲካዊ መፍትሔ መስጠት፣

**ግብ 2፡- በየደረጃው ያለው አመራር የዞኑን ህዝብ ከድህነት ለማላቀቅና ወደ ተሟላ ሰላም ለመመለስ መሰረታዊ ችግሮችን በየጊዜው እየለየ መፍትሄ እንዲሰጥ ማስቻል፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የመንግስት ተቋማትን የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል፣

- ለአመራሩ ዘመኑን የዋጀ የአቅም ግንባታ ስራ መስራት፣

**ግብ 3- የህብረተሰቡን ተሳትፎና አደረጃጀት በማጠናከር ዞኑ ከድህነትና ከግጭት አዙሪት እንዲወጣ ሚናውን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በሁሉም ዘርፍ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ፣
- የህብረተሰቡን ተሳትፎ በተገቢው አቅጣጫ መምራት፣

**ግብ 4፡- ከዞነን እስከ ቀበሌ ድረስ የሚገኙ ተቋማት በሙሉ አቅማቸው አገልግልት እንዲሰጡ ጠንካራ የተቋማት ግንባታ ሪፍሮም ማድረግና የተጠያቂነት ስርዓትን መዘርጋት፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ጠንካራ የተቋማት አደረጃጀቶችን በየደረጃው ለመፍጠር ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- የተቋማት የአቅም ግንባታ ስራዎችን በስፋት መስራት፣
- በየደረጃው ግልጸኝነትንና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣

**የግብ 5፡- የፖለቲካ ቁርጠኝነትንና አመራር ሰጭነትን በየደረጃዉ ማረጋገጥ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በህግ የበላይነት የሚያምን መልካም አስተዳደርን የሚያሰፍን ቁርጠኛ የፖለቲካ አመራር ማፍራት፣

# ክፍል አምስት፡- የልማት ፋይናንስ

## 5.1 መዋዕለ ንዋይ

መዋዕለ ንዋይ የስትራቴጅካዊ ውሳኔዎች እና የፖሊስ ግብ ማስፈጸሚያ መሣሪያ ሲሆን ፈጥኖ ሀብትን ወደ ልማት በማስገባት መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም የመቼ እና እንዴት ጥያቄዎች የሚመለሱት በፈጣን የመዋዕለ- ንዋይ ውሳኔ ነው፡፡ መዋዕለ ንዋይ በልቶ ከማደር በላይ ለሆኑ የሉዓላዊነት፣ እኩልነት፣ ኃያልነት ግቦች ማረጋገጫ መሣሪያ ነው፡፡ በአጭር የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ መዋዕለ ንዋይ የጥቅም ኢኮኖሚ መዛባት ምንጭም መፍትሄም ሊሆን ይችላል፡፡ ለዜጎች የሥራ እድል እና ገቢ መፍጠሪያ በሂደቱም የማክሮ ኢካኖሚ ማትጊያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ መዋዕለ-ንዋይ የገንዘብ ፖሊሲ ከገንዘብ ኢኮኖሚው ውጪ ባሉ ዘርፎች /አምራች እና አገልግሎት ዘርፎች/ ተጽዕኖ ለመፍጠር (transmission mechanism) ዋናው ድልድይ ነው፡፡ ስለዚህ መዋዕለ-ንዋይ ከአጭር ጊዜ የፖሊሲ መሣሪያነት እስከ የረጅም ዘመን የዕድገት ምንጭነት ምን፣ ለማን፣ ስንት፣ ለምን፣ በማን፣መቼ የት እና እንዴት ለሚሉት የእቅድ ጥያቄወች መልስ መስጪያ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ጥራት ያለው መዋዕለ ንዋይ ጥራት ያለው አገራዊ ቁጠባ ያስፈልገዋል፡፡ መዋዕለ-ንዋይ በአንድ ወቅት ከተመረተው ገቢ ውስጥ የፍጆታ ወጪን በመቀነስ ስለነገ የማሕበራዊ ደህንነት እና ኢኮኖሚያዊ አቅም የዛሬን ምኞት ቀንሶ የማምረቻ አቅሞችን ወይም ካፒታል ለመጨመር የሚደረግ ወጪ ነው፡፡ ይህ ማለት ጥራት ያለው መዋዕለ ንዋይ ጥራት ያለው ቁጠባ ያስፈልገዋል፡፡ በመሆኑም የመዋዕለ ንዋይ ፍሰቱን በእቅድ መምራት ተገቢ ይሆናል፡፡

አጠቃላይ ኢንቨስትመንት (Gross capital Formation) እድገት እና ለሚፈለገው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ እውን መሆን እንደ መነሻ የሚወሰድና ለአጠቃላይ ዘናዊ ልማት አስቻይ ሁኔታ ተደርጎ የሚታይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የኢንቨስትመንት ምጣኔ ከጥቅል የዞን ውስጥ ምርት አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ የኢንቨስትመንት ምጣኔውን ማሳደግ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በ2018 በጀት ዓመት የመዋዕለ ንዋይ ምጣኔ ከክልሉ ጠቅላላ ምርት /RGDP/ የወቅቱ የገበያ ዋጋ የሚኖረው ድርሻ ወደ 31.03 በመቶ እንደሚደርስ ታቅዷል፡፡ ይህም አጠቃላይ መዋዕለ ንዋይ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ወደ 2.5 ቢሊየን ብር የሚደርስ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የግልና የልማት ድርጅቶች ከፍተኛ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡

በሌላ በኩል በቂ ኢንቨስትመንት እንዲኖር ለማስቻል  የቁጠባ መጠንን ማሳደግ ተገቢ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ኢንቨስትመንትን ከማሳደግ ጎን ለጎን ቁጠባን ማሳደግ ለኢንቨስትመንት በሚያስፈልገው መዋዕለ-ንዋይ እና በቁጠባ መካከል ያለውን ሰፊ ክፍተት የማጥበብ ስራ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡
:

## ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች፡-

- የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪያሊስቶች በስፋት አለመፈጠር
- የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት ዝቅተኛ መሆን
- የመዋዕለ-ንዋይ ስምሪት በተጠና መልኩ አለመሆን
- ጠንካራ የመዋዕለ ንዋይ ተቋም አለመኖር

## የትኩረት መስኮት፡-

1. አምራች ኢንዱስትሪ
2. ዘመናዊ ግብርና
3. አይቲ ቴክኖሎጂ
4. ማዕድን
5. የቱሪዝም
6. ሰብዓዊ ሀብት
7. መሠረተ- ልማት

## የትኩረት አቅጣጫዎች፡-

የመዋዕለ ንዋይ የትኩረት አቅጣጫ የመዋዕለ-ንዋይ ስምሪትን ምክንያታዊ እና መነሻ ያለው ማድረግ፣ በተለይም የመዋዕለ ንዋይ ፍላጎት በካፒታል መጠን፣ በዘርፍ፣ ስምሪት፣በምንጭ ለመወሰን የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ ፣የመዋቅራዊ ለውጥ አቅጣጫ ፍላጎት ፣ የቴክኖሎጂ እና የስትራቴጂካዊ አቅም፣ የተመጣጠነ ቀጠናዊ ልማት፣ የሀብት መሠረት እንዲሁም የስራ ዕድል ፈጠራ መነሻዎች ላይ መመሥረት የሚሉት ናቸው፡፡

**ዓላማ፡- ዞኑን ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ በማድረግ እና የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም በማሳደግ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣**

**ዋና ዋና ግቦች፡-**

**ግብ 1፡- በበጀት ዓመቱ የዞኑን የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት መጠን ወደ ብር 2.5 ቢሊየን ( ከመንግስት የካቲታል ወጪ 14 በመቶ ፣ ከግልና የልማት ድርጅት 86 በመቶ ) ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ብር 12.36 ቢሊየን ፍሰት እንዲኖር ማድረግ ፣
    - ✓ ለምግባና መድሃኒት ማቀነባበሪያ ብር 5 ሚሊየን፣
    - ✓ ለጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ብር 1.46 ሚሊየን፣

- ✓ ለኬሚካልና ኮንስትራክሽን ብር 3.4 ሊሊየን፣
- ✓ ለብረታ ብረት እና ማሽን ቴክኖሎጅ ብር 2.5 ቢሊየን፣

- በዘመናዊ ግብርና ዘርፍ ብር 6.332 ሚሊየን ፍሰት እንዲኖር ማድረግ፣
  - ✓ ለሆርቲካልቸር ብር 2.9 ሚሊየን
  - ✓ ለመስኖና ምርጥ ዘር ብዜት ብር 0.25 ሚሊየን፣
  - ✓ ለእንስሳት ሃብት ልማት ብር 3.06 ቢሊየን፣
  - ✓ ለደን ልማትና ንብ ማነብ ብር 0.122 ቢሊየን
- በአገልግሎት ዘርፍ ብር 6.12 ቢሊየን ፍሰት እንዲኖር ማድረግ፣
  - ✓ ለሆቴልና ቱሪዝም ብር 4.5 ቢሊየን
  - ✓ ለትምህርት ጤና ብር 1.62 ሚሊየን

**ግብ 2፡- ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል 862.62 ሄ/ር የመሬት መጠን ለአልሚዎች ማቅረብ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ 200 ሄ/ር መሬት ማቅረብ፣
- ለዘመናዊ ግብርና ዘርፍ 654.125 ሄ/ር መሬት ማቅረብ ፣
- ለአገልግሎት ዘርፍ 8.37 ሄ/ር መሬት ማቅረብ ፣

**ግብ 3፡- ውጤታማ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ስራዎችን በመስራት 176 ኢንቨስተሮችን በማሳብ ወደ ልማት እንዲገቡ ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ 85 አልሚወችን በማሳብ ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገቡ ማድረግ፣
- በዘመናዊ ግብርና ዘርፍ 26 አልሚዎችን በመሳብ ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገቡ ማድረግ፣
- በአገልግሎት ዘርፍ 65 አልሚዎችን በመሳብ ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገቡ ማድረግ

## 5.2. የመንግስት ፋይናንስ

## የገቢ በጀት አስተዳደር

የዞኑ የታክስ ገቢ እያደገ ቢመጣም ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ያህል ለመሰብሰብም ሆነ ፍትሃዊ የታክስ አስተዳደር ለማስፈን ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ስርአት መዘርጋት ያስፈልጋል። ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ስርአት ለማስፈን ደግሞ የተቀናጀ ዘመናዊ የመረጃ ስርአት መዘርጋት ይኖርበታል። ከዚህ አንጻር ባለፉት አመታቶች አጠቃላይ ገቢ፣ የታክስ ገቢ፣ እና ሌሎች ገቢዎች የጨመሩ ቢሆንም

የሌሎች ገቢዎች እድገት እና በሚፈለገው ልክ አላደገም። የታክስ ገቢ ከጠቅላላ ምርት GDP አንጻር ያለው እድገት ሲታይ ዝቅተኛ ነው።

## የወጪ በጀት አስተዳደር

የመንግስት ፋይናንስ ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ዋና መሳሪያ ነዉ።መንግስት ከህዝብ ጋር በገባዉ ማህበራዊ ኮንትራት መሰረት በፖሊሲዉ ሶስት ዋና ዋና ግቦችን ያሳካል የኢኮኖሚ ዕድገት ማህበራዊ ፍትህ እና የተረጋጋ ኢኮኖሚ የዚህ ዕቅድ ዋና አላማ እነዚህ ግቦች በተሻለ ደረጃ እንዲሳኩ ማድረግ ነዉ። የመንግስት የፋይናንስ አቅም ስራ ለመስራት እንደተከማቸ ጉልበት አቅም ይቆጠራል።
ይህ አቅም እንደዋለበት የዘርፍ ስምሪት ሊባክን በመጠኑ ሊያለማ ወይም ባለዉ ሀብት እና የዕዉቀት ደረጃ ከፍተኛ ስራ ሊሰራበት ይችላል።ይህ የሚረጋገጠዉ በምደባ ወቅት ኢኮኖሚ ዕድገትን በማነቃነቅ ደረጃ የተሻለ አቅም ባላቸዉ ዘርፎች እና በትንሽ ጥረት አብዛሀኛዉን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ሊያደርጉ በሚችሉ ዘርፎች ላይ መሆኑን በማረጋገጥ አፈፃፀም ወቅት የሀብት እና የጊዜ ብክነትን በመቀነስ እና ጥራትን በማስጠበቅ ቅልጥፍናን ማረጋገጥ ነዉ።

## ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች

- የገቢ አቅም ዉስንነት
- የታክስ ህግ ተገዥነት ችግር
- የካፒታል ወጪ ድርሻ አናሳ መሆን

## የትኩረት መስኮች

1. ያደገ የገቢ አቅም
2. ዲጂታላይዝድ አሰራር
3. ቀልጣፋና ዉጤታማ ወጪ በጀት አስተዳደር

## የትኩረት አቅጣጫዎች

የመንግስት ገቢን በህዝብ ተሳትፎ በተጠቃሚነት ደረጃ በሚጣሉ ከተጨባጭ ፕሮጀክቶችን ማዕከል ያደረጉ የፋይናንስ፣የዓይነት እና የጉልበት መዋጮዎችን ያካተቱ የፊዚካል ፖሊሲዎችን ማስፈን ፣ የተቀናጀ ዘመናዊ የመንግስት የፋይናንስ የመረጃ ስርአትን ማስፈን፣የመንግስት ወጪን የትኩረት መስክ ለሆኑት ዘርፎች በተለይም ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ማስፈን፣ የመንግስት ወጪን የትኩረት በሚሰጥ አግባብ መደልደል፣ የመንግስት ወጪን የዘርፎች ስምሪት ምርታማነት እና ቅልጥፍና በአግባቡ እና በጊዜ መገምገም፣ ዉጤታማነታቸዉንም በገለልተኛ አካል ጥናት መፈተሽ፣ የመንግስት መደበኛ ወጪን የመንግስት ማህበረሰብ አገልግሎትን በተወዳዳሪ ሲቪል ሰርቪስን ከማላቅ ግቦች ጋር ማናበብ ናቸዉ።

**አላማ፡- ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ስርአት በመዘርጋትና የልማት ሀብት አቅርቦትን በማሳደግ እንዲሁም ውጤታማ የፋይናስ ወጪ አስተዳደር ስረአትን በማዘመን ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ፣**

## ዋና ዋና ግቦች

**ግብ 1፡- የገቢ አቅምን ከብር 2.843 ቢሊዮን ወደ ብር 4.656 ቢሊዮን በማሳደግ የዞኑን ልማት ማፋጠን**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በበጀት አመቱ 3.941 ቢሊዩን ብር ታክስ ገቢ መሰብሰብ
- የቀጥታ ታክስ 3.037 ቢሊዩን
- ቀጥታ ያልሆኑ ታክስ 903 ሚሊዮን
- ከምንግዜውም በተለየ መልኩ የተጠናከረ ስራ በመሰራት ብር 164ሚሊዮን ታክስ ካልሆነ ገቢ መሰብሰብ ፣
- የከተማ አገልግሎት ገቢ 550ሚሊዮን ብር መሰብስብ ፣
- የግብር ከፋዩ ህብረተሰብ ግብሩን በወቅቱ እንዲከፈል መቀስቀስና የግብር ትምህርት መስጠት፣
- የታክስ ህጎችን ማስከበርና በዘርፍ የሚታየውን ብልሹ አሰራር ችግር መታገል፣
- አጋርና ባለድረሻ አካለት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር 100 በመቶ በማሳደግ የአጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል፣

**ግብ 2፡- የመረጃ ቴክኖሎጅ ተደራሽነት እና አጠቃቀምን በማዘመን በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶች 100በመቶ ድጅታላይዝ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡን ማሻሻል፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የተቀናጀ የመንግስት ግብር አስተዳደር ስርአት sigtas አጠቃቀም በሁሉም የታክስ አይነቶች 100% ማድረስ
- የኤሌክትሮኒክስ ታክስ ስርአት ተደራሽ በማድረግ ኢ-ፋይሊግ እና ኢ-ፔይመንት በመጠቀም ሪፖርት የሚያደረጉ ተቋማት ብዛትን 1 ወደ 29 የታክስ ማዕከላት ማሳደግ፣
- የኤሌክትሮኒክስ የታክስ አስተዳደር ስርአት (e-tas) በመጠቀም የክፍያ ስርአቱን ድጅታላይዝ በማድረግ የሚችሉ መሰረተ ልማት 50 በመቶ የታክስ ማዕከላት ማሟላት፣

**ግብ 3፡-ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ለማጠናከር የሰራተኛውን ስነምግባር ግድፈት በ2017 ከነበረበት 2 በመቶ ወደ 2.5 በመቶ በመቀነስ፣**

**የሚከናውኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በየደረጃው ለሚገኙ የገቢ ተቋማት ፈጻሚዎችና አመራሮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንድሰጥ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ፣
- በሙስናና መልካም ስነመግባር ዙሪያ የግንዛቤ መፈጠሪያ ህትመት ማሳተም፣
- ሲቨልሰርቨስ አስተዳደር ፍ/ቤት የቀረቡ ይግባኞችን 100 በመቶ መከታተል፣
- የስነምግባር ችግር የሚታይባቸውንና የብልሹ አሰራር አመለካከትና ተግባር ዝንባሌ የሚታይባቸውን ሰራተኞች የምክር አገልግሎት መሰጠት እና ህግ የማስከበር ስራ መስራት፣

**ግብ 4 ፡- የግብር በዛብኝ ቅሬታ በማፅናት ምጣኔ ከ78.28 በመቶ ወደ 85 በመቶ እና የግብር የይግባኝ የማጽናት ምጣኔ ከ63.13 በመቶ ወደ 80 በመቶ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርቡ ይግባኞች ፈጠንና ፍትሃዊ ውሳኔ እንዲያገኙ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- በግብር ይግባኝ አሰረጅ ሙያተኞች በተደራጀ መረጃ ላይ ተመስርተው እንዲያስረዱ ማድረግ፣
- በገቢ ተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን መሰረት ያደረገ የደሰሳ ጥናት መጠይቆችን ሚከታተላቸው ሌሎች የስራ ሂደቶችን ጋር በማቀናጀት ማዘጋጀት፣
- ደረጃው ጠብቀው በአገልግሎት አለመርካት በዞን ደረጃ የሚቀረቡ ጥያቂዎች /ቅሬታዎች ሲኖሩ ህጉ ተከትሎ በፅሁፍ/በቃል ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ፣

**ግብ 5፡- የ3ኛ ወገን የግብይት መረጃ ከነበረበት 1.399 ቢሊዩን ወደ 2.400 ቢሊዩን በመሰብሰብ የመረጃ አስተዳዳር አፈጻጸም ማሻሻል፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ዳታዌርሀውስ እና ሌሎች መረጃ ከሚገኝ ተቋማት መረጃውን በጥራት ሰብስቦ ለግብር ውሳኔ እንዲውል ማድረግ፣
- የተሰበሰበውን ግብይት መረጃ በማሰረጨት ከ92.13 በመቶ ወደ 100 በመቶ ጥቅም ላይ ማዋል፣
- የግብር ከፋዩች መረጃ ድጅታላይዝ ማድረግ፣

**ግብ 6፡- የቀረቡ ክሶችን መርምሮ የመወሰን እና ተከራክሮ የመምራት አቅምን 100 በመቶ ወደ 100 በመቶ ታክስ ወንጀል ምርመራ ሽፋንን መቶበመቶ እና ጥራትን 100 በመቶ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ይግባኝ የተጠየቀባቸውን የወንጀል  የፍትሀብሔር ጉዳዩችን ተከራክሮ የማሸነፍ አቅምን ወደ 100 በመቶ ማድረስ፣

- በወንጀልና በፍትሃብሔር የሰበር አቤቱታ ጉዳዩችን ተከራክሮ የመረታት አቅምን ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣
- ከግብር ወንጀል መርማሪ የሚቀረቡ ሁሉንም የወንጀል ጉዳዩችን የመረጃ እና ማስረጃውን ብቃት ከታክስ ህጉ ጋር በማገነዘብ ሰነስርአቱ የሚያዘው መሰረት 5 ቀን ውሳኔ መስጠት፣
- ተመርምሮ የቀረበውን የወንጀል ጉዳይ የመረጃውንና ማስረጃውን ብቃት ተመዝኖ በቂ ሆኖ ሲገኝ በ3 ቀን ውስጥ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ለለው ፍ/ቤት ክስ ማቅረብ ፣
- በይግባኝ በታረም ያልቻሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለባቸውን ክሶች 100በመቶ በሰበር እንዲታረሙ አቤቱታ ማቅረብ፣
- ሁሉንም መዝገቦች በጥራት በመመርመር ምርመራውን ሲጠናቀቅ ከበቂ አስተያየት ጋር ለአቃቢ ህግ ማቅረብ ፣

**ግብ 7፡- የንግድ ትርፍ ግብር ከፋዩች ቁጥርን 40,340 ወደ 42,285 ማድረስ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የደረጃ ሀ እና ለ ግብር ከፋዩችን ቁጥር መረጃ በማጥራት በሂደቶች መካከል ተናባቢ ማድረግ፣
- ወቅታዊ የገበያ ዋጋውን መሰረት አድረጎ በማጥናት የደረጃ ሽግግር ማድረግ ያለባቸውን ግብር ከፋዮችን ደረጃቸውን እንደዲያሻሽሉ ማድረግ፣
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ግብር ከፋዮችን ቁጥር በ2017 ግብር ዘመን ከተመዘገበው 78 ወደ 110 ከፋ ማድረግ፣
- ወደ መረቡ ያልገቡ ግብር ከፋዮችን በማጥናትና ከንግድ ተቋማት ጋር በማቀናጀት ወደ ንግድ መረቡ ማስገባት፣

**ግብ 8፡- ከውዝፍና ከዘመኑ 818 የሂሳብ መዝገብ በመመርመር የኦዲት ውጤታማነት 69.524 ሚሊዩን ወደ 73.620 ሚለዩን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 300 ፋይሎችን ላየ የኢንቨትጌሽ ስራ በመሰራት የህግ ተገዥነትን ማሳደግ፣
- 25 ድረጅቶች ላይ የመጋዘን ቆጠራ በመሰራት የህግ ተገዥነትን ማሳደግ፣
- ከዘመንና ከውዝፍ የሚቀርቡ የሂሳብ መዝገቦችን 100 በመቶ በመመርመር የተስተካከለ ኦዲት ሽፋንን ማሳደግ፣

**ግብ 9፡- የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ተጠቃሚ ግብር ከፋዩች ከነበረው 3.6 በመቶ ወደ 25 በመቶ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ተጠቃሚ ግብር ከፋዩች መሳሪያውን ገዝተው እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መግዛት ያለባቸው 28 ግብር ከፋዮች መሳሪያውን ገዝተው እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
- የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ተጠቃሚ ግብር ከፋዮች ፈጣን አገልግሎት እንዲያገኙ ማመቻቸት፣
- በግብር ከፋዩ የሚቀረቡ ስህተት ይስተካከልልን ቅሬታዎችን 100 በመቶ ምላሽ መስጠት
- የኤሌክትሮኔክስ ደረሰኝ ተጠቃሚዎችን የሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር፣

➢ የኤሌክትሮኔክስ ደረሰኝ እንዲቆርጡበት ጠንካራ ክትትል ማድረግ፣

**ግብ 10፡-በጀት አስተዳሩን ቀልጣፋና ዘመናዊ በማድረግ በጀቱ ለታለመለት አላማ እንዲውል ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- **ለዞን የልማት ማስፈፀሚያ የፀደቀዉን ብር10575824794- በጀት መደልደል**
- ብር4105298676 ቢሊየን/ 38.8 በመቶ/ በወረዳ የሚሰበሰብ
- ብር 46470526118 ቢሊየን/ 61.2-በመቶ/ ከክልል መንግስት ጥቅል የቀመር ድርሻ
- ብር11192414 /0.1በመቶ/ ከዉጭ እርዳታ
- ከፀደቀዉ በጀት ዉስጥ 979443153 ብር / 11 በመቶ ለካፒታል በጀት መደልድል
- የበጀት አጠቃቀም ለታለመለት ዓላማ እየዋለ ስለመሆኑ ድጋፍና ክትትል ማድረግ
- የ2018 በጀት አመት የዞን መምሪያዎችን ክልል ተጠሪዎችን ወረዳዎችንና ከተማ አስተዳደሮችን በጀትን ማጠቃለልና ማሳወቅ
- ብድር የወሰዱ ወረዳዎችን ብድሩን ማስመለስ

**ግብ 11 ፡- በቴክኖሎጅ የታገዘ አሰራር በመከተልና የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን 100 በመቶ በመደገፍ ሂሳብ ጥራትና ወቅታዊነት ማሻሻል**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ከክልል የሚላከውን 6470526118 ቢሊዮን ብር ድጉማ ወቅቱን ጠብቆ መቀበል፣
- የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት መምሪያዎችና ክልል ተጠሪዎች ብሬክ ዳዉን እንዲያቀርቡ ማድረግ ፣
- ወጭ የተፈፀመውን ክፍያ /የጥሬ ገንዘብ ዝውውርና ድጋፍ/ በIBEX መመዝገብ፣
- ወርሃዊ የባንክ ማስታረቅና ዕለታዊ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እንዲከናወን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- በየወሩ ፋይናንሺያል አፈጻጸማቸዉን የሚያሳይ ሪፖርት ወቅታዊ አድርጎ ለመምሪያዎች መላክ
- የገቢ ሪፖርት በየወሩ ለገቢዎች ሪፖርት መላክ፣
- የበጀት ድጎማ ክልል ጋር መናበብ

- የ2017 ዓመታዊ ሂሣብ በመዝጋት ፣የተጠቃለለ ዓመታዊ የገቢና ወጪ ባንክ ማስታረቂያ ጨምሮ መስራት
- በየደረጃው ያለውን የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳብ በእድሜ በመለየት ማወራረድ

**ግብ 12፡- የመንግስታትና በየነ-መንግስታት ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ አጠናክሮ በማስቀጠል የሀብት አጠቃቀሙን ከ97 በመቶ ወደ 98 በመቶ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በUN ኤጀንሲ ለሚካሄዱ ፕሮጅክቶች የፀደቀ የእቅድ ሰነድ መቀበልና ለፈጻሚ ሴክተሮች ማሳወቅ
- በUN ኤጀንሲ ለሚካሄዱ ፕሮጅክቶች የፀደቀ በጀት በመቀበል ለፈፃሚዎች በማስተላለፍ አፈፃፀሙን መከታተል
- የማጠናቀቂያ ጊዜያቸው የደረሱ ፕሮጀክቶችን በመለየት መገምገም
- ወደ ዞኑ የሚገቡ አዳዲስ ፕሮጅክቶችን መለየት
- በተመረጡ ወረዳዎችና ሴክተሮች ድንገተኛ ጉብኝት ማካሄድ
- የሩንዳፍ ዞናዊ የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ
- ሩንዳፍ የቴክኒክና ስትሪንግ ኮሚቴ ስብሰባዎችን ጊዜውን ጠብቆ ማካሄድ
- በሚመጡ ፕሮጅክቶችና ፕሮግራሞች የሴቶችን፣ወጣቶችን የህፃናት የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት መከታተል
- የባይላተራልና መልቲ ላተራል ፕሮፋይል እንዲዘጋጅ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- የብድርና እርዳታ በሚመለከት የአፈጻጸም ሂደቱን መከታተል ለተጠቃሚ ሴክተር መ/ቤቶች ግብረ-መልስ መስጠት፣
- የእርዳታና ብድር ፍሰቱንና አጠቃቀሙን ዞን እና ወረዳ የቴክኒክ ኮሚቴ በየ ሩብ አመቱ በመገምገም ለስትሪንግ ኮሚቴ ግብአት መስጠት፣
- በፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች የሃብት አጠቃቀም እና እየመጣ ያለውን ውጤት ወረዳዎች በምክርቤት ራሱን አስችለው እንዲገመገሙ ማድረግ፡፡
- ፕሮጀክቶችን በመስክ ከፈፃሚ ተቋማት ጋር በመቀናጀት መገምገም፡፡

**ግብ 13 -፡ ብር 60 ሚሊየን አቅም ያላቸው አዳዲስ ፕሮጀክቶች ጋር ስምምነት በመፍጠር የልማት ሀብት አቅርቦትን ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 1 አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ስምምነት መፈፀም
- ከአዳዲስ ፕሮጅክቶች 60 ሚሊየን እንዲገኝ ማድረግ

- በአዳዲስ ፕሮጀክቶች 45 ሽህ የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ማድረግ
- ለ8 ፕሮጀክቶች የቅድመ ትግበራ ግምገማ፣
- ለ4 ፕሮጀክቶች አጋማሽ ዘመን ግምገማ ማድረግ
- ለ6 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቂያ ዘመን ግምገማ ማድረግ
- በሚቀርቡ ጥያቄዎች መሰረት የፕሮጀክት ማሻሻያ እና የማራዘሚያ/No-cost Extension/ማስተናገድ
- በዞን ደረጃ 2 ጊዜ የትብብር ፎረም ማካሄድና አፈጻጸሙን መከታተል
- በዞን ደረጃ አንድ ጊዜ የተጠናከረና በአግባቡ የተደራጀ የመንግስትና ሲማድ የትብብር ፎረም ማካሄድ፣
- 2 ጊዜ የሲማድ ፕሮጀክቶች ይዘውት የገቡትን ሃብት ለታለመለት ዓላማ መዋሉንና አጠቃላይ አፈፃፀሙን በመስክ መገምገም፣
- በዞኑ የሚንቀሳቀሱ ሲማድ በህጋዊ መንገድ የተመዘገቡ መሆናቸውን በማረጋገጥ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት እንዲሁም ሲማድ በስራ ሂደት ለሚገጥሟቸው ችግሮች ትኩረት ሰጥቶ መፍታት፣
- በየግማሽ አመቱ 2 ጊዜ የስትሪንግ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በማካሄድ ስራዎችን መገምገም፣
- 4 ጊዜ በየሩብ አመቱ የቴክኒክ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በማካሄድ ስራዎችን መገምገም፡፡

**ግብ 14 -፡ የማያገለግሉ የመንግስት ንብረቶችን በሽያጭ በማስወገድ ለዞን እና ለወረዳ ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኝ በማድረግ የመንግስት ንብረት አወጋገድ ስርዓት ውጤታማ ማድረግ ፡**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በመንግስት መ/ቤቶች ያለ አገልግሎት የተቀመጡና እንዲወገዱ ውሳኔ የተላለፈባቸውን ንብረቶች መረጃ መሰብሰብ ፣
- ለሚወገዱ ንብረቶች ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት ማድረግ ፣
- የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት የሚወገዱ ንብረቶችን በሽያጭ ፣ በስጦታ፣በመቅበር በማቃጠል ማስወገድ፣

**ግብ 15 ፡- የግዥና ንብረት አሰስተዳደር በአዋጅና ደንቡ መሰረት በመፈፀም ውጤታማ የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- በግዥና ንብረት አስተዳደር አፈፃፀም ወቅት ከ29 ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በማጣራት ውሳኔ መስጠት ፡፡

- ሙያዊ ድጋፍ ለሚጠይቁ ለክልል ተጠሪ መቤቶች እና ለወረዳዎች ግዥ ፈፃሚ አካላትና አቅራቢዎች ሙያዊ ድጋፍ መስጠት
- የ2017 በጀት ዓመት ግዥ አፈፃፀም የ29 ወረዳዎና ከተማ አስተዳደሮች ሪፖርት በማዘጋጀት ለክልል መላክ
- ከ29 ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ ለተመረጡ ተቋማትን የግዥና ንብረት ኦዲት በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት

**ግብ 16 -፡ የግዥ ውል ስምምነት የተፈፀመባቸውን ግዥዎች 100% መረከብና ለተጠቃሚዎች መ/ቤቶች ተደራሽ ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለ38 ለዞን ሴክተር መቤቶች የቤትና የቢሮ እቃዎችን የአገልግሎት ግዥዎችን ማለትም የተሽከርካሪ የመድን ሽፋን ፣ የጥገና ተቋም የተሽከርካሪ የመኪና እቃዎች ግዥ በመፈጸም አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ ።
- የህትመት ስራጭትን ለ29 ሴክተር መ/ቤቶች እና ለ 16 የክልል ተጠሪ  ተቋማት ለዞን ሴክተር መ/ቤቶች  አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ
- ለ38 ዞን ሴክተር መቤቶች ለ66 ተሽከርካሪ የነዳጅ አጠቃቀም በኖርማላይዤሽን መሰረት መሆኑን መከታተል እና መቆጣጠር ሲሆን ለክልል ተጠሪ ተቆማት የጥገና አገልግሎት መስጠት

**ግብ 17፡- የቴክኖሎጂ አቅርቦትን በማሟላት የኦን ላይን ተጠቃሚ የተቋማትን ከ15 ወደ 20 ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 5 አዲስ ወረዳ መስመር የተዘረጋላቸውን ተቋማት ክልሉ ሲፈቅድ ወደ ተማከለ /IBEX/ ስርዓት ማስገባት
- አዳዲስ ለተፈጠሩ ፕሮግራሞች የአይቤክስ ስርዓት መዋቅር መፍጠርና ተግባራዊ ማድረግ
- 5 ሆስፒታሎችን የ IBEX ሲስተምን በመጫን የ/IBEX/ ተጠቃሚ ማድረግ
- የIBEX እና ደመወዝ መስሪያ ሲስተሞችን የሚጠቀሙ ተቋማትን ድጋፍና ክትትል ማድረግ
- አገልግሎት ላይ ያሉትን አፕልኬሽን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
- ያልተቆራረጠ የወረዳ ኔት አገልግሎት እንዲኖር መከታተል
- በዞናችን ለሚገኙ የወረዳ ኔት መስመር አገልግሎት የማይሰጡ 2 ለሚደርሱ ተቋማት ችግሩን ከክልልና ቴሌ ጋር በመነጋገር ማስተካከል የኢኮቴ መገልገያ መሳራዎችን ጥራትና ደህንነት መጠበቅ

## የማስፈፀሚያ ስልቶች

በጥናት ላይ የተመሰረተ የታክስ አሰባሰብ መከተል በፊስካል ፖሊሲ አማካኝነት በተለይ ዞናዊ ምርት ከ50 በመቶ በላይ ድርሻ ካለው የግብርናው ዘርፍ ለገጠር ልማት የሚሆን ሀብት ማሰባሰብ የሚያስችል ስረዓት መዘርጋት የአካባቢ ጥበቃ የዕንሰሳት ሀብት ታክስ በጉልበት የሚተመን የልማት መዋጮ ተተግባሪ ስትራቴጂካዊ ፕሮጀክቶችን እና የአካባቢ ልማትን ማዕከል ያደረገ ህዝባዊ መዋጮ /crown funding/መጠቀም ፕሮጀክቶችን ጸድቀው ወደ ልማት ከመግባታቸው በፊት የአዋጭት እና የተተግባሪነት ጥናት ማካሄድ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማህበረሰቡ እና በባለ ድርሻ አካላት ማስተቸት የሚሉት ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ይሆናሉ፡፡

# ክፍል ስድስት፡- የማስፈጸሚያ ስልት

## 6.1. የቀጠና ልማት

ዞኑ በተለያዩ አካባቢዎች የዞኑን ብሎም ክልሉን ሊለውጡ የሚችሉ የተለያዩ ፀጋዎች እንዳሉት ይታወቃል፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ አካባቢ ያለውን ሀብት መሰረት አድርጎ በየትኛው ዘርፍ ቅድሚያ ሰጥቶ መስራት እንዳለበት የሚያመላክት ክልላዊ የስፓሻል ፕላን ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም ዞናችን በሁለት ቀጠናዎች ማለትም **የምስራቅ አማራና መካከለኛው አማራ የልማት ቀጠና** ውስጥ ይገኛል፡፡ በሁለቱ የልማት ቀጠናዎች አማራጭ አቅሞችን ተጠቅሞ ዞኑን ከችግሮቹ ማለቀቅ የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ስለሆነ ይህንን ታሳቢ ያደረገ የማስፈጸሚያ ስልት ሆኖ ተለይቷል፡፡

ስልጡን መንደር በገጠራማ አካባቢ የሚገኝ ማህበረሰብ የህይወት ጥራትን ለማሻሻል፣ የኢኮኖሚ እድሎችን ለማሳደግ እና የአካባቢን ዘላቂነት ለማረጋገጥ፣ ቴክኖልጂን፣ ፈጠራን እና ዘላቂ ልምዶችን በመጠቀም ስልጡን ሰው፣ ስልጡን አካባቢ፣ ስልጡን ኢኮኖሚ፣ ስልጡን አኗኗር እና አመራር ያለው መንደር ለመፍጠር በዞኑ በሚገኙ በ9 ከተሞች እና በ20 ገጠር ወረዳዎች በእያንዳነደዳቸው 1 ስልጡን መንደር በከፍተኛ ትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡ በዞኑ ውስጥ የሚሰሩ መሰረተ ልማቶች ጠራታቸውን ጠብቀ፤ በተቀመጠላቸው ጊዜ መሰረት እንድፈጸሙና በአተገባበር ሂደት ከሌብነትና ከብክነት በጸዳ መልኩ ይሰራል፡፡

## 6.2. ልዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች

በሁኔታ ትንተናው ላይ እንደተገለጸው በዞኑ አአንዳንድ አካባቢዎች ሰላም ባለመኖሩ ወይም ፀጥታው ባለመረጋጋቱ የሀገር ዜጋ ማፍሪያ የሆኑት ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል በጦርነቱ ወድመዋል፣ የህሙማን መፈወሻና የእናቶች ማዋለጃ የሆኑት የጤና ተቋማት በጦርነቱ የተጎደና የህክምና ቁሳቁሶችም ተዘርፈዋል፣ አርሶ አደሩ ከግብርና ስራው ተደናቅፏል እንድሁም በከፍተኛ በጀትና ገንዘብ የተገነቡ መሰረተ ልማት ግንባታዎች ፈርሰው እንዳልነበሩ ሆነዋል፡፡ እነዚህንና ሌሎች በጦርነቱ የደረሱ ጉዳቶችን መልሶ ለመገንባትና በጦርነት የተጎደ አካባቢዎች በዘላቂነት እንድያገግሙና ህብረተሰቡ ወደ መደበኛ ህይወቱ እንድመለስ ለማድረግ የመንግስትና የህብረተሰቡን ፍላጎትና ተቀባይነት መሰረት ያደረጉ በበጀት ዓመቱ በልዩ ሁኔታ መተግበር ያለባቸው የሚከተለት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ተለይተዋል፡፡ እነሱም፡-

1. **የሀገር አቀፍና ክልል አቀፍ ኢኒሽቲቭ ፕሮጀክቶች፡-** በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቀርጸው እየተተገበሩ ያሉ ኢኒሽቲቮችን በሙለ አቅም ሳያንጠባጥቡ መተግበር፤ በተጨማሪም የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅድን ውጤታማ የሚያደርጉ ዞናዊ ኢኒሽቲቮችን ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ይሆናል

2. **ሰብአዊ ድጋፍ አስቸኳይ ምላሽ ፕሮግራም፡-** የሚያካትታቸው ፕሮጀክቶች የምግብ አቅርቦት ፕሮጀክት፣ የመጠለያ ግንባታና አቅርቦት ፕሮጀክት፣ የህክምናና የጤና አገልግልት ፕሮጀክት፣ የህክምና መሳሪዎች እና የመድሃኒት አቅርቦት ፕሮጀክት፣ ንጹህ ውሃና ስነ-ንፅህና አቅርቦት ፕሮጀክት እንድሁም የትራንስፖርት አገልግልት ማሻሻያ ፕሮጀክት ናቸው፡፡

3. **መልሶ ግንባታና መሠረተ ልማት ፕሮግራም፡-** በዚህ ፕሮግራም የሚካተቱ ፕሮጀክቶች የመኖሪያ ቤቶች መልሶ ግንባታና አቅርቦት ፕሮጀክት፣ የኤላክትሪክ ኃይል አቅርቦት እና የቴሌኮም አገልግልት መስጫ ፕሮጀክት፣ የመንገድች እና ድልድዮች ፕሮጀክት፣ የውሃ እና የንፅህና አጠባበቅ አገልግልት ፕሮጀክት፣ የትምህርት ቤቶች መልሶ ግንባታ እና ቁሳቁሶች ማሟላት ፕሮጀክት፣ የጤና ተቋማት መልሶ ግንባታና ቁሳቁሶች ማሟላት ፕሮጀክት፣ የማህበራዊ አገልግልቶች መስጫ ተቋማት ጥገና ፕሮጀክት፣ የኢንደስትሪ ተቋማት መልሶ ግንባታ ፕሮጀክት፣ የንግድ ተቋማትና ሸዶች መልሶ ግንባታ ፕሮጀክት፣ የቅርስ ጥበቃ ተቋማት እና ሙዜየም መልሶ ግንባታ ፕሮጀክት፣ ቅርስ እና ልዩ ልዩ ሃብቶች የማስመለስ ፕሮጀክት ናቸው፡፡

4. **የኢኮኖሚ ማገገሚያና የኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም፡-** የሚያካትታቸው ፕሮጀክቶች የግብርና ግብአት አቅርቦት እና ድጋፍ ፕሮጀክት፣ የስራ ፈጠራና የክህልት ስልጠና ፕሮጀክት፣ የስራ እድል ፈጠራና ድጋፍ ፕሮጀክት፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ ፕሮጀክት፣ የገበያ ትስስር ማጠናከር ፕሮጀክት እንድሁም የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ናቸው፡፡

5. **ማህበራዊ መልሶ ማቋቋም እና ስነ- ልቦናዊ ድጋፍ ፕሮግራም፡-** የሚያቅፋቸው ፕሮጀክቶች የስነ-ልቦና ድጋፍና የምክር አገልግልት ፕሮጀክት፣ የማህበረሰብ እርቅና ሰላም ግንባታ ፕሮጀክት እና የተፈናቀለ የህብረተሰብ ክፍልችን ወደቀያቸው መመለስ እና ማቋቋም ፕሮጀክትን ነው፡፡

6. **መልካም አስተዳደርና ፍትህ ማስፈን ፕሮግራም፡-** የሚይዛቸው ፕሮጀክቶች የፍትህ ሥርዓት ክትትልና ድጋፍ ፕሮጀክት፣ የፀጥታ ተቋማት ማጠናከር ፕሮጀክት፣ ሰላም ግንባታና እርቅ ፕሮጀክት እና ለተፈናቀል ዜጎች የህግ ከለላ አገልግልት ፕሮጀክት ናቸው፡፡

7. **የጉዳትና የመልሶ ማቋቋም ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ፕሮግራም፡-** የተጎዱ አካባቢዎች ልየታ እና ጥበቃ ፕሮጀክት እንድሁም የውድመት መረጃ አሰባሳብና ጥናት ፕሮጀክት በዚህ ፕሮግራም የተካተቱ ናቸው፡፡

8. **ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍልች ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ፕሮግራም፡-** የአካቶ ትግበራ ፕሮጀክት፣ የአካል ጉዳተኞች ድጋፍ እና እንክብክቤ ፕሮጀክት፣ የአረጋዊያን ድጋፍ እና እንክብክቤ ፕሮጀክት፣ የሴቶች እና ወጣቶች አቅም ግንባፕሮጀክት እና የህፃናት ድጋፍ እና እንክብክቤ ፕሮጀክት በዙህ ፕሮግራም ተካተዋል፡፡

9. **የእንስሳት ምርት ልማት ፕሮግራም፡-** በዚህ ፕሮግራም የእንስሳት እርባታ ልማት ፕሮጀክት፣ የእንስሳት መኖ ልማት ፕሮጀክት፣ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ፕሮጀክት እና የእንስሳት ጤና አገልግሎት ፕሮጀክት ተካተዋል፡፡

10. **በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎች የገዘንብ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም፡-** ከዓለም አቀፍ ድርጅቶችና መንግስታዊ ተቋማት ድጋፍ ማሰባሰብ ፕሮጀክት፣ ከልማት ድርጅቶችና በጎ አድራጎት ተቋማት ድጋፍ ማሰባሰብ ፕሮጀክት፣ የድጅታል ገንዘብ ማሰባሰቢያ ፕሮጀክት እንድሁም ከማህበረሰብ ተሳትፎ ገቢ ማሰባሰብ ፕሮጀክት በዚህ ፕሮግራም የተካተቱ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡

11.**የተቀናጀ የልማት ፕሮግራም፡-** ይህ ፕሮግራም የገጠር ልማት ፕሮጀክትን እና የከተማ ልማት ፕሮጀክትን ያካትታል፡፡

በአጠቃላይ ሥራውን በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ እንድመራ ማድረግ፣ ጉዳቱ በደረሰበት አካባቢ የተፈናቀለና ቀያቸውን ለቀው የተሰደደ የህብረተብ ክፍልች ወደ ነበሩበት አካባቢ እንድመለሱ በማድግ መደበኛ ኑሮአቸውን እንድቀጥሉ ማድረግ፣ በተጎደ አካባቢዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ የደረሰውን ውድመት ሊያካካስ በሚችልና ከዚያም በተሻለ ደረጃ ላይ እንድደርሱ የሚያስችል የልማት፣ መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ስራዎችን መስራት፤ የተለያዩ አካላትን ማለትም የዞንና የክልል መንግስትን፣ በዞኑ የሚሰሩ የልማት ድርጅቶችን፣ ረጂ ድርጅቶችን፣ የግል ባለሀብቶችን እንድሁም ህብረተሰቡን በማስተባበር በተጠናከረ መልኩ ሀብት የማፈላለግና የማሰባሰብ ስራ መስራት፣ የተገኘውን ሀብትም በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ እንድውል ማድረግ፣ የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ስራውን በተቀናጀ አግባብ ለመፈጸሚ የሚያግዘ አደረጃጀቶችን በማቋቋም ወደ ተግባር እንድገቡ ማድረግ፣ ተቋማዊ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን መገንባት፣ከዋናው ዕቅድ የተቀዳ የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ተግባራትን የሚመለከታቸው ፈጻሚ ተቋማት በዕቅዳቸው አካተው እንድያቅዱና እንድተገብሩ ማድረግ፣ ተያያዥ የሆኑ ስትራቴጂዎችን እና የአሰራር መመሪያዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ተፈጻሚ የሚሆኑበትን አሰራር መፍጠር፣ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋትና የተደራጀ የመረጃ ቋት እንድኖር በማድረግ ጥቅም ላይ እንድውል ማድረግ፣ የደረሰውን ውድመትና በዚህ ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎችን በሚመለከታቸው አካላት እንድታወቅ ከሚድያ አካላት ጋር በጋራ መስራት እንድሁም ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ የሚለት ዋና ዋና የማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

## 6.3. የተቋማት አደረጃጀትና ሚና

**የተቋም እሪፎርምና ቅንጅታዊ አሰራር ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል፤**

- የመንግስተ ተቋማት ስርዓት ማሻሻያ ትግበራ

- የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም
- ዞን- ወረዳ/ከተማ አስተዳደር - ቀበሌ ቅንጅት
- የአስፈጻሚ ተቋማት ቅንጅት

**ችግርን በጊዜ የመፍታት ሚና ያለው አሳላጭ የክትትል ኮሚቴ**

- አስተዳዳሪ (ምክትል አስተዳዳሪ)
- የክላስተር አስተባባሪዎች
- የፕላን ኮሚሽን
- የመንግስት ተቋማት
- የክልል ተጠሪና የዞን  የመሰረተ-ልማት ተቋማት
- ፕሮጀክት የሚገነቡባቸው አካባቢዎች የመንግስት አስፈጻሚዎች እና የማህበረሰብ ተወካዮች

**የግምገማ እና ኦዲት ኮሚቴ**

- የክላተር አስተባባሪዎች - ለቅንጅት
- የክላስተር አስተባባሪዎች
- የፕላን ኮሚሽን ለፊዚካል ኦዲት እና የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት አፈጻጸም ግምገማ
- ገንዘብ መምሪያ እና የኦዲት መስሪያ ቤት -ለፋይናንስ ኦዲት

የተቋማት አደረጃጀት መሰረታዊ መነሻዎች ለተቋማት አደረጃጀት እና ግንባታ ትኩረት ሳይሰጥ ውጤት መጠበቅ ረብ የለሽ በመሆኑ፣የተቋማትን ቀጣይነት በማረጋገጥ ሃላፊነታቸውን በብቃት የሚወጡና ሲያጓድሉ ጠጠያቂ የሚሆኑ ተቋማት ማደራጀት በማስፈለጉ፣በፍጥነት እየተለወጡ ካሉ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ የሚጓዝና የህዝብን ችግር የሚፈታ ተቋም አደረጃጀት መፍጠር በማስፈለጉ፣ ወደ ነገ የሚያሻግሩ ዘመኑን የዋጁ ተቋማት ማደረጃት አስፈላጊ በመሆኑ እንድሁም በክልሉ ብሎም በዞኑ ነጻ፣ ገለልተኛ እና ብቁ ተቋማትን መገንባት አስፈላጊ መሆኑ የሚሉት ሲሆኑ የተቋሙ ሚና ደግሞ የ5 ዓመቱን እቅድ መሬት በማስነካት የኢኮኖሚ እድገት ብልጽግና እንድረጋገጥ ማድረግ፣ በዞኑ ተሰራፍቶ የቆየውን የድህነትና የግጭት አዙሪት መስበር እንዲሁም ቀበሌዎች ላይ እግር በመትከል ዘላቂ ሰላምና ልማት ማረጋገጥ ይሆናል።

በተለይም ቀበሌዎች ሰፊ ማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች የሚከናወንባቸውና መንግስት ህዝበን ከድህነት ለማውጣት ያለው ፍላጎት ተግባር የሚተረጉምባቸው ሁነኛ የአስተዳደር እርከኖች ሲሆኑ ሰፊ ህዝብ

ሚኖርባቸው ከመሆናቸውም በላይ በተለያዩ ጊዚያት የሚቀረጹ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ልማት አጋር ድርጅቶች የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ውጤታማነትና ተገቢነት በተግባር የሚፈተንባቸውም ናቸው፡፡ በተጨማሪም ቀበሌዎች ቁጥሩ ቀላል የማይባል በግብርና እና ከግብርና ውጭ በሆኑ የስራ ዘርፎች የተሰማራ ህዝብ የሚኖርባቸው፣ መንግስት ህዝቡን ከድህነት ከኂላ ቀርነት ለማላቀቅ በምርጫ ቃል ሲገባና ሲያቅድ ቃሉን በተግባር እንድፈጽም የሚተማመንባቸውና ዓይኑን የሚጥልባቸው ዘርፈ ብዙ ጸጋዎችን የተጎናጸፉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ለቀበሌዎች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ዞኑ ያቀደውን የ2018 በጀት ዓመት የአሻጋሪ ዕድገትና ዘላቂ ልማት ግቦች ለማሳካት፣ የህግ የበላይነት የተረጋገጠበትና አስተማማኝ ሰላም የሰፈነበት ዞን ለመገንባት እንድሁም መንግስታዊ አገልግሎቶችን ለህዝቡ ለማቅረብና ቀበሌዎች ላይ በአስተማማኝ ደረጃ እግር ለመትከል ተቋማት በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡

## 6.4. ክትትልና ግምገማ

የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅዱን በተሟላና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መከታተልና መገምገም በየጊዜው የሚከሰቱ ተግዳሮቶችን በፍጥነት ለመለየትና አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ከማስቻሉም በላይ በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን ይረዳል፡፡ በዚህ ረገድ እስካሁን በዞን ደረጃ ለተመዘገቡ ውጤቶች የክትትልና ግምገማ ስራ የራሱ አስተዋጽኦ ቢኖረውም በርካታ ድክመቶችም ነበሩት፡፡ ከድክመቶቹ መካከል የእቀድ ክትትልና ግምገማ ቅንጅት ደካማ መሆን፣ በተለያዩ ደረጃዎች የክትትልና ግምገማ አቅም ውስን መሆን፣ በክትትልና ግምገማ ዙሪያ የተዛባ አመለካከት መኖር፣ የክትትልና ግምገማ አሰራሩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አለመሆን፣ ከስኬት (outcome) ይልቅ ሂደትና ውጤት (process and output) ላይ ማተኮር እንድሁም በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልጽነትና ተጠያቂነት በሚፈለገው ደረጃ ላይ ያለመድረስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ የክትትልና ግምገማ ሥራው በሚከተለው መልኩ በተጠናከረ መልኩ ይካሄዳል፡፡

### 6.4.1. የመረጃ ስርዓት

በወሳኝ ኩነቶች ሁሉን አቀፍ አካታች ዲጂታል የሆነ ምዝገባ ስርዓትን ማጎልበት የሚያስችል ተቋማዊ አቅም በመገንባት ለፍትህ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲክስ አገልግሎት የሚውል አስተማማኝ መረጃዎችን ማመንጨት የሚለው አላማ ሲሆን ዋና ዋና ግቦችም ጥራቱን የጠበቀ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሽፋንን ማሳደግ ማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ ምዝገባን ማሳደግ እንድሁም የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የመረጃ ማስረጃ አቅርቦት ማሻሻያ የሚሉት በትኩረት የሚተገበሩ ይሆናሉ፡፡

በአጠቃላይ ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት የክትትልና ግምገማ ዋና ማስፈጸሚያ መሳሪያ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የመረጃ ስርዓት በሚከተሉት አግባብ ጥቅም ላይ ይቅላል፡፡

1. የመንግስት የተቀናጀ የመረጃ ስርዓት፡-

- ዲጂታል የፕሮጀክት የአፈጻጸም ሂደት መረጃ
- የዘርፎች የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት አፈጻጸም መረጃ

2. የዳሰሳ እና የሙሉ ቆጠራ የስታትስቲክስ መረጃ ስርዓት

- የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ መረጃ ስርዓት
- የፕላን ኮሚሽን ከዘርፈ መምሪያዎች እና ሌሎች አስፈጻሚ ተቋማት ጋር በመተባበር የዳሰሳ መረጃዎች፣ ሙሉ ቆጠራዎች፣እና የወሳኝ ኩነት መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማዘመን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አማካኝነት ተደረሽ ማድረግ
- በወሳኝ ኩነቶች እና የነዋሪነት መረጃዎች የቀበሌ-የወረዳ-ዞን-ክልል የተቀናጀ መረጃ ስርዓት ማስፈን በተለይም ቀበሌዎች ድጋፍ ተደርጎላቸው በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ታግዘው ነዋሪዎቻቸውን ከመሰረታዊ መረጃዎች ጋር መሰነድ.
- የስነ ህዝብ መረጃዎች በማደራጀትና በመተንተን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል፣
- የዜጎች መረጃ ከብሄራዊ (የዲጂታል) መታወቂያ (ፋይዳ) ጋር ማቀናጀት፡፡

3. ዘመናዊ የመረጃ ምንጮች (Big Data Gis መረጃዎች፣ ወዘተ) በስፋት ጥቅም ላይ እንድውሉ ማድረግ፤

## 6.4.2. ክትትልና ድጋፍ

የዕቅድ ዘመኑ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በጥብቅ ድስፕሉን የሚመራ ራሱን የቻለ በዞኑ አስተዳዳሪ ስር ሆኖ በሚደራጅ እና የእለት ከዕለት ተግባሩ የእቅዱን የተግባር አፈጻጸም እየገመገመ ሳይንሳዊ ትንታኔዎችን እያካተተ ለዞኑ ዋና አስተዳዳሪ (ምክትል አስተዳዳሪ) እያቀረበ እያስወሰነ እቅዱን በስኬት ላከናዉኑ አካላት የማበረታቻ ስርአት እንድኖር በማድረግ የሚበረታቱበት፣ ዕቅዱን በአግባቡ በማይፈጽሙ አካላት ላይ ደግሞ ተገቢዉ ድጋፍ እንድደረግላቸዉ፣ ተገቢዉ ድጋፍም ተደርጎላቸዉ ማስፈጸም የማይችለ አካላት ደግሞ በአቅማቸዉ ወደ ሚያከናውኑበት ቦታ ስምሪት እንድሰጥ ለአስተዳዳሪው (ም/አስተዳዳሪው) ምክረ ሀሳብ እያቀረበ እያስወሰነ የሚሄድ ተቋም የድጋፍ የክትትል እና የግምገማ ስርአቱን እንድመራ የሚደረግ ሲሆን የተለያዩ አካላትን የሚያካትትና በትኩረት በየደረጃው የሚተገበር የድጋፍ የክትትል እና ግምገማ ስርአት የሚያከናዉኑ አካላት በተጨማሪነት የሚሳተፈበት ይሆናል፡፡

**ዓመታዊና የሩብ ዓመታት የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፦** የልማት ዕቅድን በተሟላ ሁኔታ በመከታተል፣ በመገምገምና በመደገፍ ውጤታማነቱን ማረጋገጥ በሁሉም የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በባለቤትነት ተይዞ መፈጸም ያለበት ትልቅ ኃላፉነት ነው፡፡ በዚህም መሠረት የልማት ዕቅድን

የክትትልና ግምገማ ሜትሪክስ መሠረት ያደረገ፣ ቁልፍ የውጤት መስኮችን፣ ኢላማዎችንና ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾችን በግልጽ ለይቶ ያስቀመጠና በበጀት የተደገፈ ዓመታዊ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዕቅድ ማዘጋጀትና ይህንንም ተፈፃሚ ማድረግ ከእያንዳንዱ የመንግሥት አስፈፃሚ አካል የሚጠበቅ ይሆናል:: የክትትልና ግምገማው ሥራ በተለያዩ አካላት በተለያየ ደረጃ የሚከናወን ቢሆንም የዋና ዋና የኢኮኖሚና የዘርፍ መረጃዎችን በመጠቀም አጠቃላይ ዓመታዊና የሩብ ዓመታት የልማት ዕቅድ አፈጻጸም በፕላን ኮሚሽን እየተዘጋጀ ለዞን አስተባባሪ ኮሚቴ የሚቀርብ ይሆናል:: ከዚህ በተጨማሪም ተቋማት በተመረጡ ቁልፍ የአፈተጻጸም አመልካቾች (KPIs) እየተመዘኑ ደረጃ የሚሰጣቸው ይሆናል::

**በመስክ ጉብኝትና ምልከታ የታገዘ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፦** የመስክ ጉብኝት ክትትልና ግምገማ ማለት የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃን ለማረጋገጥ በተመረጡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዙሪያ የሚዘጋጅ ጉብኝት ሆኖ ዓላማው በየጊዛው ከሚዘጋጁ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች በተጨማሪ በመስክ ምልከታ የአፈጻጸም ልዩነቶችን በማረጋገጥና የአፈጻጸም ክፍተቶች ካለም የማስተካከያ እርምጃዎች በወቅቱ እንድወሰዱ ማስቻል ነው:: ይህም በዓመታዊ ዕቅድና የአፈጻጸም መርሃ ግብር በሚገባ በማካተት በኃላፊዎችና በከፍተኛ አመራሮች ደረጃም በተመረጡና ፋይዳቸው ከፍተኛ በሆኑ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ላይ የሚከናወን ይሆናል:: የመስክ ጉብኝቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ከማመንጨት በተጨማሪ በአንድ የመረጃ ምንጭ ወይም በሪፖርት ላይ ከመወሰን ይልቅ የመረጃ ምንጮችን ማስፋትና የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመስክ ከተገኘው መረጃ ጋር ለማመሳካር (tri angulation) ጠቃሚ በመሆኑ ነው::

**ዓመታዊ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሪፖርቱን በባለድርሻ አካላት ማስገምገም፦** የምክክር መድረኮችን በዞንና በወረዳ/ከተማ አስተዳደር ደረጃዎች በማዘጋጀት በዓመታዊ የልማት ዕቅደ ረቂቅ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ይካሄዳል:: ይህም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈንና ለማጠናከር እንድሁም በህብረተሰቡ ዘንድ የባለቤትነት ስሜት እንድፈጠር ከማድረግ አንጻር ጠቀሜታው የጎላ ነው:: ከምክክር መድረኮች የተገኙ አስተያየቶችን በማካተት የአፈጻጸም ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለባለድርሻ አካላት በተለያዩ ዘዴዎች ተደራሽ ይደረጋል:: ከዚህ በተጨማሪ በየደረጃው ላለ አስፈጻሚ አካላት በክትትልና ግምገማ አቅም የማጎልበትና ድጋፍ የመስጠት እንድሁም አሠራሮችን የመዘርጋት ተግባራት በተጠናከረ መልኩ የሚከናወኑ ይሆናል::

በአጠቃላይ የክትትል እና ድጋፍ ሥርዓቱ የፕሮጀክት ወጪዎች በአግባቡ መታቀዳቸውን እና መፈጸማቸውን፣ ወቅታዊ እና መደበኛ የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት መቅረቡን፣ በሚመለከታቸው ተቋማት እና ተጠቃሚዎች ጭመር መደበኛ ክትትል መደረጉን፣ ጥብቅ እና ዘመናዊ የንብረት ምዝገባ እና አያያዝ፣ አጠቃላይ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋቱን፣ የፋይናንስ

እና የፊዚካል ምርመራ በማድረግ ጥራት መጠበቁን፣ ፋይናንስ ለታለመለት ዓላማ መዋለን፣ እና ድህረ-ፕሮጀክት የመልካም ተጽዕኖ ጥናት መከናወኑን በሚመለከት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

## 6.5. የተግባቦት ስትራቴጅ

የአጭር፣ የመካከለኛም ሆነ የረጅም ዘመን የልማት ዕቅዶችን በስኬታማነት ለመፈፀም ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች መካከል አንዱ ዕቅዶች የሚፈፀሙበትን የትግበራ ስትራቴጂ መቅረጽና መተግበር መሆኑ እሙን ነው፡፡ ከነዚህ ስትራቴጂዎች ውስጥ የስልታዊ ተግባቦት ስትራቴጂ አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የተግባቦት ስትራቴጅ በሚከተለው መልኩ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የተግባቦት ስትራቴጅው የቁልፍ መልዕክቶች የትኩረት አቅጣጫ አንድነት እና ትብብር ላይ ማተኮር፣ የኢኮኖሚ ዕድሎችን አጉልቶ ማሳየት፣ ፅናት እና ተስፋን ማሳየት እንዲሁም ባህል እና እሴት ለሁለንተናዊ እድገት የሚሉት ሲሆኑ የተግባቦት ዘዴዎችም በሚከተለው መልክ ቀርበዋል፡፡

1. ለአሰልጣኞች
- እማራጭ አንድ፡- የገጽ ለገጽ መድረክ
- አማራጭ ሁለት፡- የነባራዊ ሁኔታ የአካል ጉብኝት
2. ለመንግስታዊ መዋቅሩ
- የአቀራረብ ስልቱ እንደየተቋማቱ ባህሪ የሚለያይ ሆኖ ሊዘጋጅ ቢችልም ከመድረክ ገለጻ እና ከአካላዊ ጉብኝት አይወጣም፡፡ የመድረክ ገለጻው በሰለጠነ ገለጻ አቅራቢ ቁልፍ መልእክት አድራሽነት የሚመራ ሆኖ ዕቅዱ ቁጭትን በሚፈጥሩ ተደማሪ ጥበባዊ የፈጠራ ዉጤቶች ሊታጀብ ይችላል፡፡ እነዚህ ጥበባዊ የፈጠራ ዉጤቶች ፎቶ ኤግዚቢሽን፣ አጫጭር ቪዲዮዎች፤ ሽለላና ፉከራ፤ በልሃ ልበልሃ! መዝሙር፣ ሙዚታ፣ ታሪክና ባህል ነክ ግጥሞች፤ ጭውውቶች! መነባንብ እና ሌሎችም ናቸው፡፡
3. ለአርሶ አደሮች
- አማራጭ እንድ፡- ራዲዮ
- አማራጭ ሁለት፡- የሞባይል ጥሪ ማእከል መፍጠር
- አማራጭ ሶስት፡- የገጽ ለገጽ ውይይት
4. ለተማረው የማህበረሰብ ክፍል
- አማራጭ አንድ፡- ዲጂታል የሚዲያ መዋቅር መትከል
- አማራጭ ሁለት፡- የቴሌቪዥን ቻናል
- አማራጭ ሶስት፡- ጋዜጦችና ሌሎች የህትመት ውጤቶች
- አማራጭ አራት አውደ ጥናቶችና ጉባኤዎች
5. ለከተማ ነዋሪዎች

- አማራጭ አንድ፡- የህዝብ የገጽ ለገጽ የጉብኝት መድረክ መፍጠር
- አማራጭ ሁለት፡- የባዛርና ኤግዚቢሽን መድረኮችን ማዘጋጀት
- አማራጭ ሶስት፡- የስፖርት ዉድድሮችና የሙዚቃ ድግስ መድረኮችን ማዘጋጀት
- አማራጭ አራት፡- ቋሚና ተንቀሳቃሽ መልእክቶችንና ማስታወቂያዎችን ማዘጋጀት
- አማራጭ አምስት፡- የኪነጥበብ ስራዎች የሚቀርቡበት መድረክ መፍጠር
- አማራጭ ስድስት፡- የሚዲያ አካላት ጉብኝት መድረክ መፍጠር /Media Tours/
- አማራጭ ሰባት፡- የልማት ማስጀመሪያና ምረቃ መድረኮችን መፍጠር /Media Launch/
- አማራጭ ስምንት፡- ስክሪን

6. ለባለ ሃብቶች

- አማራጭ አንድ፡- የገፅ ለገፅ ዉይይት መድረክ
- አማራጭ ሁለት፡- ጉብኝት
- አማራጭ ሶስት፡- መደበኛ ሚዲያ

7. ለመምህራንና ተማሪዎች

- አማራጭ እንድ፡- የገጽ ለገጽ ውይይት
- አማራጭ ሁለት፡- ክበባትን በት/ቤቶች መፍጠር
- አማራጭ ሶስት፡- የተማሪዎች ጥያቄና መልስ ውድድር በት/ቤቶች ማዘጋጀት
- አማራጭ አራት፡- የክልልህን እወቅ ጉብኝቶችን ማካሄድ

8. በክልሉ ለሚገኙ የሃይማኖት መሪዎችና አባቶች

- አማራጭ አንድ፡ የገፅ ለገፅ የዉይይት መድረክ
- አማራጭ ሁለት፡- የልማት ስራዎች ጉብኝት

9. ለሴቶች

- አማራጭ እንድ፡- የገፅ ለገፅ ውይይት
- አማራጭ ሁለት፡- መደበኛ ሚዲያ
- አማራጭ ሦስት፡- አካባዊ የመስክ ጉብኝት

10. ለወጣቶች

- አማራጭ አንድ፡- የገፅ ለገፅ መድረክ
- አማራጭ ሁለት፡- የኪነ ጥበብ እና ስፖርታዊ የውድድር መድረኮችን ማዘጋጀት
- አማራጭ ሶስት፡- ሚዲያ
- አማራጭ አራት፡- ልምድ ልውውጥ

11. ከክልሉ ውጭ ለሚኖሩ የክልሉ ተወላጆች

- የልማትና የመልካም አስተዳደር እቅዱን በዉል ተረድተዉ የአጋዥነት ሚናቸዉን ከፍ ማድረግ ይቻል ዘንድ እንደ አንድ የዕቅዱ አጋር አካል ሆነዉ ተቆጥረዉ በተግባቦት ስራዉ ተደራሽ የሚደረጉ የህብረተሰብ ክፍል ሆነዉ ተወስደዋል፡፡ በመሆኑም ተወላጆች በቁጥር በርክት ብለዉ የሚገኙባቸዉ ክልሎች/ከተሞች/አካባቢዎች እየተመረጡ የገጽ ለገጽ የዉይይትና ምክክር መድረኮች በክልል ደረጃ ይዘጋጃሉ፡፡

12.በውጪ ሀገራት ለሚኖሩ የክልሉ ተወላጆች

- አማራጭ አንድ፡- የገፅ ለገፅ ውይይት
- አማራጭ ሁለት፡- ማህበራዊ ሚዲያ
- አማራጭ ሶስት፡- አካላዊ ጉብኝት
- አማራጭ ሶስት፡- በልዩ ልዩ ጆርናሎች የምርምር ውጤቶችን ማሳተም (Journal Articles)
- አማራጭ አምስት፡- የሚዲያ ወኪሎች መመደብ (ኮርስፖንዳንት)

13.ለሚዲያ አካላት

- አማራጭ እንድ፡- የገፅ ለገፅ መድረክ
- አማራጭ ሁለት፡- የሚዲያ አካላት የጉብኝት መድረክ መimር /Media Tours/
- አማራጭ ሶስት፡- የሚዲያ ፎረም መመስረትና ነባሮችን መጠቀም

14.ለሌሎች

ለዚህ የተግባቦት እቅድ ሌሎች በሚል የሚገለጹት የሲቪክ ማህበራት፣ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ከክልሉ ዉጪ የሚኖሩ የአማራ ተወላጆች እና በቀዳሚ ታሳሚነት የተቀመጡ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ ሀገር በቀልም ይሁኑ ዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በክልሉ ሰላም እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የበኩላቸዉን ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል፡፡ በተለይም የክልሉ መንግስት በማይደርስባቸዉ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ተሳትፎ ጉልህ ነው፡፡ በተለይም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከዉጪ ሃገራት ጋር ያላቸዉ ግንኙነት ስር የሰደደ በመሆኑ በክልሉ አጠቃላይ ገጽታ ላይ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ ያላቸዉ ሚናም ከፍተኛ ነዉ፡፡ ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር የተጠና ተግባቦት ማድረግ ፋይዳዉ ላቅ ያለ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ እነዚህን ባለድርሻ አካላት ክልሉ በቀውስ ምክንያት የደረሰበትን ውድመት የሚያሳዩ ፎቶዎችና አጫጭር ዘጋቢ ፊልሞችን በማቅረብ የክልሉን እሁናዊ ገጽታ በማሳየት በቁጭት መነሳሳትን በሚፈጥርመልኩ የዕቅድ ሰነዱ ላይ በገጽ ለገጽ የተግባቦት ስልት የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ የክልሉን ባህልና እሴት በሚያሳዩ እንደ የእዝማሪ ጨዋታና ባህላዊ የሙዚቃ ስራዎች ሳቢና ስሜት ቀስቃሽ እንዲሆን በሚያስችል መልኩ መድረኮቹ ይዘጋጃሉ፡፡